www.ethiopianorthodox.org

# ሺህ ዓመትና ሐሳዊ መሲሕ

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።

ኢትዮ ጥቁር አባይ ማተሚያ ቤት(1997 ዓ.ም)

መምህር ስቡሕ አዳምጤ የሰዋሰወ ብርሃን ቅ/ጳውሎስ
ከ/መ/ት/ቤት የሐዲሳት ትርጓሜ መምህር

# መታሰቢያነቱ

ዋጋ ሳልከፍል ያላቸውን የዕውቀት ሀብት [illegible] መምህሮቼ ይሁን።

1ኛ. ቅኔ እስከነአገባቡ ግሥ እስከነርባ ቅምሩ ላስተማሩኝ በተጨማሪም ውዳሴ ማርያምና ቅዳሴ ማርያም አንድምታ ትርጓሜን ላስተማሩኝ በምሁርነታቸውና በብሕትውናቸው ታዋቂ ለሆኑት በደቡብ ጐንደር በደራ ወረዳ ደብረ ምሕረት ዛራ ቅዱስ ሚካኤል ለሚገኙት የቅኔና የመጽሐፍ መምህር ለሆኑት ለመልአከ ምሕረት ጥበቡ ታየ።

2ኛ. የሐዲሳት ትርጓሜን ላስተማሩኝ በሰሜን ጐንደር ዋና ከተማ በመንበረ መንግሥት መድኃኔዓለም የአራቱ ጉባኤ መጻሕፍት መምህር ለነበሩት ለአንጋፋው ሊቅ ለሊቀሊቃውንት መንክር መኮንን።

3ኛ. በዚሁ በመንበረ መንግሥት መድኃኔዓለም በሚገኘው የሊቃውንት ጉባኤ የአራቱን ጉባኤ መጻሕፍት ሲያስተምሩ በነበሩበት ጊዜ የሐዲሳት ትርጓሜንና ሃይማኖተ አበውን ላስተማሩኝ አሁን የሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከ/መ/ት/ቤት የበላይ ኃላፊና የሰሜን ጐንደር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ለሆኑት ለብፁዕ አቡነ እንድርያስ።

4ኛ. የብሉይ ኪዳን ትርጓሜን ላስተማሩኝ በሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤት የብሉይ ኪዳን ትርጓሜን በማስተማር ላይ ለሚገኙት የአራቱ ጉባኤ መጻሕፍት መምህር ለሆኑት ለታላቁ ሊቅ ለመልአከ ገነት ገብረ ሥላሴ አወቀ።

5ኛ. ከመምህሮቼ እንደ አንዱ ለማያቸው ከምግብ እስከ ልብስና እስከ መጽሐፍ ድረስ የሚፈለገውን አስተዋጽኦ ችለው በሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከ/መ/ት/ቤት የብሉይ ኪዳን ትርጓሜን ላስተማሩኝ አሁንም ምእመናንን በማስተባበር በዚሁ ቅዱስ ተግባር ለቤተ ክርስቲያናችን ተተኪ የሚሆኑ በርካታ ደቀመዛሙርትን በማስተማር ለሚገኙት ለአፈ ማርቆስ ተፈራ ይሁንልኝ።

# ምስጋና

ይህን መጽሐፍ ሳዘጋጅ ጥልቅ ሐሳባቸውን በመለገሥና አይዞህ በማለት የረዱኝ በሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤት የብሉያት አንድምታ ትርጓሜን በማስተማር ላይ የሚገኙት መምህር ገብረ ማርያም ጥበቡንና በዚሁ በተጠቀሰው ቦታ የሐዲሳት አንድምታ ትርጓሜን በማስተማር ላይ የሚገኙትን መምህር እሸቱ ዓለማየሁን ከልብ አመሰግናለሁ።

እንዲሁም ጥሩ የጽሑፍ ችሎታ ስላላቸው ጊዜያቸውን መሥዋዕት አድርገው በእጅ ጽሑፍ የረዱኝን አባ ገብረ ሕይወት ፍሥሐንና አባ ሥምረተ አብ እሸቱን ሳላመሰግን አላልፍም።

እንደሚታወቀው የሥነ ጽሑፍ ድካም ብዙ ነው። በእጅ ጽሑፍ በለቀማ ደከመን ሰለቸን ሳይሉ አብረውኝ ለተሰለፉ:

ለመምህር ጽጌ ፍቃዴ
ለመምህር በሙሉ አስፋው
ለመምህር ብርሃኑ ጫኔ
ለመምህር ሢራክ ንጉሤ
የምስጋና እጅ መንሻዬን አቀርባለሁ።

የገንዘብ አስተዋጽኦ በማድረግ ኮምፒዩተሩን ያጻፉልኝ ዮሐንስ ጻድቁ /ፈቃደ ሥላሴንና/ ቄስ ዘማርያም ሙጨን አመሰግናቸዋለሁ።

ከዚህ በላይ ለጠቀስኳቸው አባቶቼና ወንድሞቼ ሁሉ ለአራቱ የወንጌል ጸሐፍት ለማቴዎስ ለማርቆስ ለሉቃስ ለዮሐንስ የሰጣቸውን ጸጋ ይሰጥልኝ ዘንድ እግዚአብሔርን በጸሎት እጠይቃለሁ።

www.ethiopianorthodox.org

# ማውጫ

ገጽ


መግቢያ ........ 1


## ምዕራፍ አንድ


ሺ.ህ ዓመት ........ 3
መጽሐፍ ቅዱስን ያለትርጓሜ መረዳት አይቻልም ........ 6
ቁጥሮች በመጽሐፍ ቅዱስ ........ 9
ሺ.ህ ቁጥር በመጽሐፍ ቅዱስ ........ 12
ሺ.ህ በልማዳዊ አነጋገር ሲነገር ........ 14
ሺ.ህ ዐመት ዘመነ ሥጋዌ ነው ........ 15
ሰይጣን ለምን ታሰረ? ........ 16
ሰይጣን መቼ ታሰረ? ........ 24
ሰይጣንን እንዳሰረው የጌታ ምሳሌያዊ አነጋገር ........ 24
ሰይጣን የዚህ ዓለም ገዥ ነበር ........ 26
የዚህ ዓለም ገዢ ወደውጭ ይጣላል ........ 27
ሰይጣን ድል እንደተነሣ የራሱ ምስክርነት ........ 32
ሰይጣን ከገዢነት ወደተገዢነት ........ 32
ለጥቂት ጊዜ ይፈታ ዘንድ ይገባዋል ........ 34
ከክርስቶስ ጋር መንገሥ ........ 36
የፊተኛው ትንሣኤ ........ 38


## ምዕራፍ ሁለት


ሐሳዌ መሲሕ ........ 43
ሐሰተኞች ነቢያት ሐሰታዊ ትንቢትን ለመናገር የሚነሣሡባቸው ምክንያቶች ........ 45
የሐሳዌ መሲሕ የስሙ ትርጉም ........ 46
የእናቱ ስም ትርጉም ........ 47
ስለሐሳዌ መሲሕ መምጣት የቅዱስ ጳውሎስ ትንቢታዊ ቃል ........ 48
ሐሳዊ መሲሕና መጥፎ ተግባሩ ........ 52
ሐሳዌ መሲሕ በራእየ ዮሐንስ ........ 61
አውሬው ከባሕር ሲወጣ መታየቱ ........ 62
የአውሬው ሰባት ራሶች ........ 63
የአውሬው አሥር ቀንዶች ........ 72
አውሬው ምን ይመስላል? ........ 73
የሐሳዌ መሲሕ በአራዊት መመሰሉ ........ 75
ዘንዶው ማን ነው? ........ 76
የዘንዶው ውጊያ ከመላእክት ጋር ........ 77
የዘንዶው ሥልጣን ለአውሬው ........ 79
የአውሬው አድናቂዎች ........ 81
አውሬው ተሳዳቢ ነው ........ 84


## ምዕራፍ ሦስት


ሐሳዌ ኤልያስ ........ 86
የአውሬው ሁለት ቀንዶች ........ 87
የሐሰት ምስክር ለሐሰተኛ ........ 90
የአውሬው መቁሰልና መፈወስ ........ 92
የአውሬው ስብከት ለአውሬው ........ 94
አውሬው ምልክቶችን ያደርጋል ........ 96
አውሬው በምልክቶች ያስታል ........ 98
ምስል ማሠራቱ ........ 101
ምስል ማናገሩ ........ 102
ለስዕሉ በማይሰግዱት የሚወሰድ እርምጃ ........ 103
ክርስቶስ ወደምእመናን የቀረበበት መንገድ ........ 105
የሐሰተኛው ኤልያስ ዋጋ ምን ይሆን ........ 109


## ምዕራፍ አራት


ስድስት መቶ ስድሳ ስድስት ........ 113
መንፈሳዊ ጥበብ ምንድን ነው? ........ 115
መንፈሳዊ ጥበብ የተሰጣቸው ሰዎች ........ 115
የአውሬውን ቁጥር ትርጉም የሚያውቀው ማን ነው? ........ 118
ቁጥሩ የሰው ቁጥሩ ነውና ........ 119
መርምያዋየስ ........ 120
ፀራዊ ........ 123


## ምዕራፍ አምስት


ሁለቱ ወይራዎች ........ 127
ሄኖክና ኤልያስ ለምን አልሞቱም ........ 131
1ኛ. የሕይወትና የትንሣኤ ምልክቶች ሊሆኑ ........ 136
አዳም የሞትን ተግባራዊነት ያረጋገጠባቸው ነገሮች ........ 137
2ኛ. የእግዚአብሔርን ሕያውነት ሊገልጹ ........ 140
3ኛ. የእግዚአብሔርን አምላክነት ሊመሰክሩ ........ 142
ምስክር ወይም ሰማዕት ........ 143
የሄኖክና የኤልያስ ምስክርነት ........ 144
ሄኖክና ኤልያስ የሚያደርጉት ተአምር ........ 145
የሄኖክና የኤልያስ ተአምራት ማድረግ አስፈላጊነት ........ 150
የሄኖክና የኤልያስ ሞት ........ 151



www.ethiopianorthodox.org

# መግቢያ

ይህን መጽሐፍ ለመጻፍ የተነሣሣሁት ዳግም ምጽአትን በተመለከተ ስለሚከሰቱ ሁለት ነገሮች የተቻለኝን ያህል መፍትሔ ለመስጠት ነው።

አንደኛው በዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 20 ቁጥር 1 እስከ 10 የሚገኘው ሺህ ዓመት የሚለው ቃል ነው። ሁለተኛው ደግሞ ከዳግም ምጽአት አስቀድሞ የሚገለጠው ሐሳዌ መሲሕ /ሐሰተኛው ክርስቶስ/ ነው።

1ኛ. ሺህ ዓመት

በዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 20÷1-10 ያለውን ስናነብ ሰይጣን ሺህ ዓመት እንደታሠረ ሺሁ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ በእሥራቱ እንደሚቆይ ከዚያም በኋላ ለጥቂት ጊዜ እንደሚፈታ የሚገልጹ ቃላትን እናገኛለን። በተጨማሪም የእግዚአብሔርን ቃል በማስተማራቸውና ስለክርስቶስ በመመስከራቸው በሰማዕትነት የሞቱት ሰዎች ከክርስቶስ ጋር ሺህ ዓመት እንደሚነግሡ የፊተኛውን ትንሣኤ እንደሚነሡና የእግዚአብሔርና የክርስቶስ ካህናት እንደሚሆኑ ከላይ በተጠቀሰው ምዕራፍ የሚገኘው ንባብ ይጠቁማል።

ሆኖም ሺህ ዓመት ከየት እስከ የት እንደሆነ ግልጽ ሆኖ ባለመቀመጡ የተለያዩ መምህራን የተለያዩ አስተያየቶችን ይሰጣሉ። እኔም የሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንን ትርጓሜ መሠረት በማድረግ ሺህ ዓመት ከየት እስከ የት እንደሆነ ለመግለጽ ሞክሬአለሁ። ከክርስቶስ ጋር መንገሥ መቼ እንደሆነና የፊተኛው ትንሣኤ የተባለውም ምን ዓይነት ትንሣኤ እንደሆነ የቻልኩትን ሳላብራራ አላለፍኩም።

ሁለተኛ ሐሳዌ መሲሕ፣ ሐሳዌ መሲሕ /ሐሰተኛው ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ከመሆኑ አስቀድሞ የሚገለጥ የዳግም ምጽአት ምልክት ነው። ስለሐሳዌ መሲሕ መገለጥ እንድጽፍ ምክንያት የሆነኝ ነገር ቢኖር የሚከተለው ነው።

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀት የሌላቸው አታላዮች አወናባጆች ምጽአት በዚህ ሳምንት በዚህ ወር በዚህ ዓመት ይደረጋል፣ ቀርቧል ገንዘባችሁን ስጡን እንመጽውትላችሁ እያሉ የዋሃን ምእመናንን ሲያታልሉ ይታያሉ። ብዙ ምእመናንንም በየጊዜው በአታላዮች ስብከት ይሰናከናሉ።

ስለዚህ የሐሳዌ መሲሕ መንግሥት በምድር ላይ ሳይመሠረት ዳግም ምጽአት ወይም ኅልቀተ ዓለም እንደማይሆን ለምእመናን ማሳወቅ አስፈላጊ ሆኖ አገኘሁት። የሐሳዌ መሲሕም አመጣጥ እንዴት እንደሆነ የቻልኩትን ያህል ለመግለጽ ሞከርኩ። ይህን መጽሐፍ ያነበቡ ምእመናን ሰማዩ ተንዶ ሊጫንህ ነው ምድሩ ተከፍቶ ሊውጥህ ነው። በሚሉ በወዮልህ ሰባኪዎች ከመደናገር ሊድኑ ይችላሉ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።

ሐሳዌ መሲሕ ሳይመጣ ዳግም ምጽአት አይሆንም ሰማይና ምድርም አያልፉም አታደናግሩን ማለት ይችላሉ።





ይህ መጽሐፍ በአምስት ምዕራፎች የተከፈለ ሲሆን አምስት ዋና ዋና ርእሶችም አሉት።

1ኛ. ሺህ ዓመት
2ኛ. ሐሳዌ መሲሕ
3ኛ. ሐሳዌ ኤልያስ
4ኛ. ስድስት መቶ ስድሳ ስድስት
5ኛ. ሁለቱ ወይራዎች

አንባብያን ሆይ ሺህ ዓመት የሚለውን አንደኛውን ዓቢይ ርእስ ከማንበባችሁ በፊት በዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 20 ከቁጥር 1 እስከ 10 የሚገኘውን ቃል በሚገባ አንብባችሁ ከተሰጠው ማብራሪያ ጋር በማገናዘብ ለማለት የፈለኩትን እንድትረዱልኝ ስል አሳስባለሁ።

እንዲሁም ከሁለት እስከ አራት ያሉት ዓበይት ርእሶችን ከማንበባችሁ በፊት የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 13ትን በሙሉ በጥሩ ሁኔታ መላልሳችሁ እንድታነቡና ከእኔ አገላለጽ ጋር እያዋሀዳችሁ በማስተዋል ምሥጢሩን ትመረምሩ ዘንድ የአደራ መልእክቴን አስተላልፋለሁ። በአምስተኛው ርእስ ሁለቱ ወይራዎች የተባሉት ሄኖክና ኤልያስ መሆናቸው ተገልጿል። አሁንም በዚህ ርእስ ውስጥ የሚገኘውን ፍሬ ሐሳብ ለመጨበጥ በዮሐንስ ራእይ 11÷3-13 የሠፈረውን ቃል በማስተዋል ማንበብ ያስፈልጋል።

የመጽሐፉ ፍሬ ሐሳብ መጽሐፍ ቅዱስ ለሚያነቡ ሰዎች የተሰወረና የተደበቀ አይደለም። በእነዚህ ዓበይት ርእሶች የሚገኘውን ፍሬ ሐሳብ ለመረዳት በዮሐንስ ራእይ የሚገኙትን ከዚህ በፊት የተጠቀሱትን ሦስት ምዕራፎች ረጋ ብሎ ማንበብ ዋናው መፍትሔ ነው።

ሐሳዌ መሲሕ፣ ሐሳዌ ኤልያስ፣ ሐሳዌ ኤልሣዕ፣ ሐሳዌ አብድዩ ሁለቱ ወይራዎች ወይም መቅረዞች የተባሉት በትርጓሜ ትምህርት ቤት ላልቆያችሁት ሰዎች ግልጽ ላይሆኑላችሁ ይችላሉ። በየምዕራፋቸው ጥሩ ሆነው ተገልጸዋል። ልብ ብላችሁ አንብቡ። መንደርደሪያ እንዲሆናችሁ ከዚህም በመጠኑ ለመግለጽ እሞክራለሁ።

ሐሳዌ መሲሕ ማለት ሐሰተኛው ክርስቶስ ማለት ነው። ሐሳዌ ኤልያስ ማለት የሐሰተኛው ክርስቶስ ሰባኪ ወይም ነቢይ ሐሰተኛው ኤልያስ ነው። ሐሳዌ አብድዩና ሐሳዌ ኤልሣዕ የተባሉትም ሐሰተኛው አብድዩና ሐሰተኛው ኤልሣዕ ናቸው። እነዚህ ሁለቱ የሐሰተኛው ኤልያስ ደቀመዛሙርት ናቸው። ሁለቱ ወይራዎች ወይም መቅረዞች የተባሉትም በሐሳዌ መሲሕ ዘመን ወደዚህ ዓለም መጥተው ወንጌልን የሚሰብኩ የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክሮች ሄኖክና ኤልያስ ናቸው።

እንግዲህ በመግቢያው ላይ የተገለጸውን እንደምርኩዝ በመጠቀም የፍሬ ሐሳቡን አቀበት ለመውጣት አዳጋች እንደማይሆን እገምታለሁ።



www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ አንድ
# ሺህ ዓመት

ሺህ ዓመት የሚለው ንባብ በዮሐንስ ራእይ 20÷1-10 ላይ ይገኛል:: ይህ ሺህ ዓመት መነሻውና መድረሻው ከየት እስከ የት እንደሆነ ጎልቶና ግልጽ ሆኖ የተቀመጠበት ቦታ አይገኝም:: ትርጓሜ የሚያስፈልገው ንባብ ነው:: በዕውቀትና በአምላካዊ ጸጋ የበለጸጉ የሊቃውንትን ትርጓሜ የሚጠይቅ ንባብ ሆኖ እናገኘዋለን:: ይህ ንባብ ማንም ተነሥቶ በሰጠው አስተያየት ትክክለኛውንና ዓይነተኛውን ትርጓሜ ሊያገኝ አይችልም::

እንዲህ ያለውን ለመተርጐም ፍንጭ የማይሰጠውን ንባብ ሠውርና ድብቅ የሆነውን ምሥጢር ለመግለጽ እንደዮሴፍና እንደ ዳንኤል ሀብተ ትርጓሜ የተሰጣቸው መተርጉማን ያስፌልጋሉ:: ዳንኤላዊና ዮሴፋዊ ጸጋ ባይገኝ እንኳ አንዱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል ሌላውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል እንዳይቃወመው መንፈሳውያን መጻሕፍት እርስ በርሳቸው እንዳይጋጩ እንዳይለያዩ አድርገው አስማምተው የሚተረጉሙ ጥልቅ ዕውቀት ሰፊ ግንዛቤ ያላቸው መተርጉማን ሊተረጉሙ ይገባል:: ያለዚያ ግን ፊደልን ከፊደል አገጣጥሞ የማንበብና ቃላትን የማስዋብ ችሎታ ያላቸው ሁሉ የማመሥጠር ችሎታው ሳይኖር እንተረጉማለን ካሉ መጻሕፍትን ዱላ ያማዝዟቸዋል፣ ግንኙነታቸውን ያሻክሩታል፣ ተቀባይነታቸውንም ያደበዝዙታል::

## ስለሺህ ዓመት የተሰጡ የተሳሳቱ አስተያየቶች

ሺህ ዓመት የሚለውን ንባብ /ቃል/ ለመተርጐም በክርስትናው እምነት ውስጥ ያሉ ብዙ ግለሰቦችና ቡድኖች ትርጓሜው ወደማይገኝባቸው አቅጣጫዎች ሲመለከቱና አድራሻ በሌላቸው መንገዶች ሲሯሯጡ ይታያሉ:: አንዳንዶቹ ሺህ ዓመት ክርስቶስ ዳግመኛ ከመጣ በኋላ የክርስቶስ አማኞች፣ የክርስቶስ ተከታዮች ከክርስቶስ ጋር ነግሠው የሚኖሩበት ዘመን ነው





ሲሉ ይሰማሉ:: የተለያዩ ሰዎች የሰጧቸው የተለያዩ አስተያየቶች የሚከተሉት ናቸው:

- ትውልዱ በተምህርት እየተሻሻለ እየበለጸገና እያደገ ሲሄድ የአኗኗር ሥርዓቱ ሲለወጥ ከሕገወጥነት ወደ ሕጋዊነት ሲያዘነብል የሺህ ዓመት መንግሥት ይመጣል የሚሉ አሉ::
- ሌሎች ቡድኖች ደግሞ ወንጌል ቀስ በቀስ ዓለምን ያጥለቀልቃታል ከአሁኑ ዘመን በበለጠ የወንጌል ቃል ሰውን ይለውጣል:: የሰዎች መለወጥም የሰላም የበረከት ዘመን የሚሆን ሺህ ዓመትን ያመጣል ይላሉ::
- ከሁለቱ ቡድኖች የተለዩ ሌሎች ደግሞ ክርስቶስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ የዳዊትን መንግሥት የመመሥረት ዓላማ ነበረው:: ነገር ግን የአይሁድ ሕዝብ ንስሐ ስላልገቡ ጊዜውን ወደ ዳግም ምጽአት አስተላለፈው:: እስከዚያም ከአይሁድም ከአሕዛብም የምትሰበሰበውን ቤተ ክርስቲያን መሠረተ ነገር ግን ሰዎችን በብዛት ለመመለስ ወንጌል በቂ አይሆንም:: በመጨረሻ ክርስቶስ በአየር ይመጣል የሞቱትንም ቅዱሳን ያስነሣል:: በሕይወት ካሉት ምእመናን ጋር ነጥቆ ወደበጉ ሠርግ ግብዣ ይወስዳቸዋል:: በምድርም ላይ የመከራ ዘመን ይሆናል::

በዚህም ዘመን እስራኤል ወደጌታ ተመልሳ ወደ ሀገሯ ወደ ቅድስት ምድር ትገባለች:: በመከ ራው ዘመን ፍጻሜ ላይ ክርስቶስ ወደ መሬት ይመለስና በአሕዛብ ላይ ይፈርዳል:: በጎችን ከፍየሎች ይለያል:: ሰይጣን ለሺህ ዓመት ይታሰራል:: በመከራ ዘመን ያመኑት የሞቱት ቅዱሳን ይነሳሉ:: ከዚያም የሺሁ ዓመት መንግሥት ይመሰረታል:: እርሱም የአይሁድ መንግሥት ይሆናል:: በዓለም ዙሪያም ይስፋፋል:: ክርስቶስና ቅዱሳኑ በኢየሩሳሌም ይነግሣሉ:: ከሺህ ዓመት መንግሥት በኋላ ከሰይጣንና ከተከታዮቹ ጋር የመጨረሻው ጦርነት ይደረጋል:: ከዚያም በኋላ ሰይጣን ወደ ጥልቁ ይወረወራል:: ከዚያም በኋላ የማያምኑት ከሙታን ይነሣሉ:: የመጨረሻው ፍርድም ይከተላል ይላሉ::

ከአንድ እስከ ሦስት የተጠቀሱት ቡድኖች በሺህ ዓመት ላይ የሰጡት አስተያየት የሺህ ዓመትን ትርጓሜ ካለመዳሰሱም



www.ethiopianorthodox.org

በላይ የመጻሕፍትን ምሥጢር የሚበታትን ነፋስ ነው ማለት ይቻላል:: አንደኛው ቡድን በሰው ሥጋዊ ዕውቀት ኃይል ሰይጣን የሚታሰርበት የክርስቶስ የሺህ ዓመት መንግሥት ይመጣል ነው የሚለው:: ወንጌል ግን ሰይጣን በጾምና በጸሎት ከሰው እንደሚርቅና እንደሚወጣ ማር. 9÷14-29 ይነግረናል እንጅ በፍልስፍና፣ በሥጋዊ ጥበብ፣ ጥልቅ በሆነ ምርምር እንደሚታሰር አይጠቁምም::

ሁለተኛው ቡድን በወንጌል ስብከት የዓለም መጥለቅለቅ በክርስቲያኖች የቁጥር መበርከት ሰይጣን የሚታሰርበት የክርስ ቶስ የሺህ ዓመት መንግሥት ይመጣል ነው የሚለው:: ይህን ሐሳብ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል ያፈርሰዋል:: ምክንያቱም ወንጌል ዓለምን የሚያጥለቀልቀው ለአሕዛብ ምስክር ሊሆንባቸው ነው እንጅ የሺህ ዓመት መንግሥትን ሊያመጣ አይደለም:: የክርስ ቶስን ነገር አልሰማንም የሚሉ የአዳም ልጆች እንዳይኖሩ በመጨረሻው ዘመን የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ እንደሚሰበክ ማቴ. 24÷14 ላይ ተገልጿል:: ከሺህ ዓመት ጋር ግን ግንኙነት የለውም:: የአማኞች እምነት ጥንካሬ እንጅ የአ ማኞች ብዛት ሰይጣንንም ሊያስር አይችልም ኢየሱስ ክርስቶስም ሰይጣንን እንዳሰረው ይናገራል:: ሰይጣን ያልታሰረ ሆኖ ገና ለወደፊት የሚታሰር አይደለም የክርስቶስም መንግሥት በዚህ ዓለም አትመሠረትም::

ሦስተኛው ቡድን ኃጥአንና ጻድቃን በትንሣኤ እንደሚ ለያዩና የሺህ ዓመት መንግሥት የእስራኤል ብቻ እንደሚሆን ይተነብያል:: ጻድቃን አስቀድመው ተነሥተው ከክርስቶስ ጋር ሺህ ዓመት እንደሚነግሡ ደፍሮ ይናገራል:: ሆኖም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ አያገኝም:: ጻድቃንና ኃጥአን በትንሣኤ እንደ ሚለያዩ የሚጠቁም ሃይማኖታዊ ጽሑፍ አልተጻፈም:: የጻድቃ ንና የኃጥአን ትንሣኤ አንድ ጊዜ እንደሆነ ግን የሚከተሉት ጥቅሶች ያስረዳሉ:: «በምድርም ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉቱ ብዙ ዎች ይነቃሉ እኩሌቶቹ ወደ ዘላለም ሕይወት እኩሌቶቹም ወደ ዘላለም እፍረትና ጉስቁልና...» ዳን. 12÷2 «ጻድቃንም ዐመፀኞችም ከሙታን ይነሡ ዘንድ እንዳላቸው ተስፋ በእግዚአ ብሔር አለኝ» ሐዋ. ሥራ 24÷15 «በመቃብር ያሉቱ ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል:: መልካምም ያደረጉ





ለሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉና በዚህ አታድንቁ» ዮሐ. 5÷28-29

ስለዚህ ኃጥአንና ጻድቃን የሚነሡት አንድ ጊዜ ነው:: የሦስቱም ቡድኖች ሐሳብ የቅዱሳት መጻሕፍትን ትምህርት ለመናድ የተወረወረ ፈንጅ ይመስላል:: እነዚህ ሰዎች እንደ ሐምሌ ውኃ ሙላት የጎርፍ ብዛት ያገኘውን የዕንጨትና የሣር ዘር ተሸክሞ እንደሚጓዝ ይህን ልተወው ይህን ልሸከመው ብሎ እንደማይመርጥ በመንገድ ያገኘውን ሁሉ እንደሚነዳ በአጋጣሚ ያገኙትንና ድንገት የመጣላቸውን ሐሳብ በንባቡ /በቃሉ/ ላይ ጭነውበታል:: ሰዎቹ በጉባኤ ቤት ያልዋሉ ምሥጢር ያላደላ ደሉ የጉባኤ ቤት ጠረጴዛ ያልገጫቸው የመምህራን አንደበት ያልገረፋቸው ቅምጥሎች አፈ-ጮሌዎች ሳይሆኑ አይቀሩም::

## መጽሐፍ ቅዱስን ያለትርጓሜ መረዳት አይቻልም

ከተርጓምያን ሊቃውንት የአተረጓጐምን ስልት ሳይቀ ስሙ መጽሐፍ ቅዱስን ለመተርጐም መሞከር «ሳም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ» እንደሚባለው ይሆናል:: የተሳሳተ ትርጉም የሚ መጣውም ከዚህ የተነሣ ነው:: ያለ መሪ ወደሩቅ ቦታ የሚሄዱ ማየት የተሳናቸው ሰዎች እሾህ ላይና ደንጊያ ላይ መውደቃ ቸው አይቀሬ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስንም ያለተርጓሚ ያለ መምህር ያነበቡት ሁሉ እንደየፍላጐታቸው፣ እንደየስሜታቸው፣ እንደየአመለካከታቸውና እንደየግንዛቤአቸው እንደመሰላቸው ከተረጐሙት መሠረታዊ የትርጓሜው ትምህርት ሣይኖራቸው ከመሬት ተነሥተው ከአብራሩትና ከገለጹት በንባብ ዳጥ ተንሸ ራተው ወደ ስሕተት ጉድጓድ መግባታቸው አይቀርም::

የእያንዳንዱ ሰው ግንዛቤ የተለያየ ነው:: እንደመልኩ፣ እንደቁመቱ፣ እንደቅርፁ፣ እንደጠባዩና እንደድምፁ ሐሳቡና አስተያየቱም ይለያያል:: መጽሐፍ ቅዱስን እያንዳንዱ ሰው እንደአመለካከቱ ከገለፀው አንዲት ሃይማኖት የሚለው የጳውሎ ስም አነጋገር ይዛባል:: ያለትርጓሜም የመጽሐፍ ቅዱስን ሐሳብ ለመጨበጥ መከጀል ጤፍን ሳይፈጭ ሳይቦካ ሳይጋገር ለምግብ ነት እንደማቅረብ ይቆጠራል::



www.ethiopianorthodox.org

የጌታ ደቀመዛሙርትም የጌታን አነጋገር እንደመሰላቸው ለመፍታት ሲሞክሩ ይሳሳቱ ነበር:: «ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን እርሾ ተጠንቀቁና ተጠበቁ» ባላቸው ጊዜ በቀጥታ የፈሪሳውያንን እንጀራ መብላት እንደሌለባቸው ያስጠነቀቃቸው መስሎአቸው ነበር:: ጌታ ባለማስተዋላቸው ሲገሥጻቸውና ስለ እንጀራ እንዳልነገራቸው ሲገልጽላቸው ነው ወደ ዐይነተኛው ትርጉም የቀረቡት:: ማቴ. 16÷5-12 ከትንሣኤ በኋላ ጋብቻ ያለ መስሎአቸው ከትንሣኤ በኋላ ስለአለው ጋብቻ ጥያቄ ያቀረቡ ሰዱቃውያንንም «መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ትስታላችሁ» ብሎ ጌታ ገሠጻቸው:: ከትንሣኤ በኋላም ማግባት መጋባት እንደሌለ ገለጸላቸው:: ማቴ.22÷23-33 ጌታ በመስቀል ላይ «ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ» ሲል የሰሙ አይሁድም ኤሎሄ ማለት ኤልያስ ማለት መስሎአቸው ይህስ ኤልያስን ይጠራል በማለት የተሳሳተ ትርጉም ሲሰጡ እንመለከታለን:: ማቴ. 27÷46-47 ለምሳሌ ያህል እነዚህ ተጠቀሱ እንጂ በመሰለኝ ትርጉም የመጽሐፍ ቅዱስን ፍሬ ሐሳብ አቅጣጫ ወደጐን ትተው ሪሳቸው በጠረጉት መንገድ የሚጓዙ ብዙ ናቸው::

የመጽሐፍ ቅዱስ ምሥጢር እንደድንችና እንደካሮት ተቆፍሮ የሚወጣ እንጂ እንደበቆሎ ፍሬ ለመንገደኛው ሁሉ የሚታይ አይደለም:: ስለዚህ በጥልቀት የሚቆፍር ጠንካራ የአእምሮ ጡንቻ ያለው ቆፋሪ ያስፈልጋል:: የተወሰኑት የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት ብዙ ምሥጢርን አምቀው የያዙ ስለሆኑ በቀጥታ አይፈቱም ውስጠ-ትርጉም አላቸው ማለት ነው:: በተለይም በምሳሌያዊ አነጋገር የተገለጹ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላትና ራእይ ነክ ወይም ትንቢት ነክ የሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባባት የተሸከሙት ምሥጢር በቀላሉ አይገኝም:: እንደ ወራጅ ወንዝ ውኃ ወይም እንደ ዓባይ ውኃ ሁሉም የሚቀዳው አይደለም:: ዓይነተኛ ትርጉሙ ለመተርጉማን ሣይገኝ ሣይገለጥ ጊዜ ብቻ የሚተረጉመው የሚገልጠው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃልም አይጠፋም::

ሺህ ዓመት የሚለው ንባብም የራእይ ውጤት በመሆኑ ውስጠ ትርጉም ያለው ንባብ ነው:: ሺህ ዓመት ከየት እስከየት እንደሆነ ሲገልጹ ያየናቸው ሰዎች ግን ውስጠ-ትርጉሙን





አልነኩትም:: በቀጥታ ሺህ ዓመት ትርፍም ሕጸጽም ሳይኖረው ሺህ ዓመት ነው የሚል ሐሳብ ወይም ግምት ነው ያላቸው:: «ከክርስቶስም ጋር ሺህ ዓመት ኖሩና ነገሡ» የሚለውንም በቀጥታ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ የሺህ ዓመት መንግሥትን እንደሚመሠርትና ጻድቃን ከእርሱ ጋር እንደሚነግሡ ያስባሉ:: «በፊተኛው ትንሣኤ ዕድል ያለው ብፁዕና ቅዱስ ነው» የሚለውንም በቀጥታ ጻድቃን አስቀድመው እንደሚነሡ ያምናሉ::

እነዚህ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ እንደሚያስፈልገው አልተገነዘቡም:: እንኳን መጽሐፍ ቅዱስ ከወንድሞቻችንና ከእኅቶቻችን ጋር ስንወያይ አንዳንድ ጊዜ ለማለት የፈለጉት አይገባንም ምን ለማለት ፈልገህ ነው? ምን ለማለት ፈልገሽ ነው? እንላለን:: እስኪተረጉሙልን ድረስ በመጓጓት:: ታዲያ በሰው ፈቃድ ያልመጣውን የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል ከትርጓሜ አዋቂዎች ልንረዳ አይገባንምን? እንኳን እኛ የቅጅ ቅጅ የደረሰን ጌታ በመካከላቸው ተገኝቶ ያስተማራቸው ሐዋርያትም የጌታ ትምህርት ሲከብዳቸው ተርጉምልን የማለት ጥያቄ ያቀርቡ ነበር:: ጌታም ይተረጉምላቸው ነበር:: ማቴ. 13÷36-43፤ 15÷15-20

መጽሐፈ ኢሳይያስን ሲያነብ የነበረው ኢትዮጵያዊው ጃንደረባም ፊልጶስ «የምታነበውን ታስተውለዋለህን» ብሎ በጠየቀው ጊዜ የሚመራኝ ሳይኖር ይህ እንዴት ይቻለኛል የሚል መልስ ነው የሰጠው:: የሚተረጉምልኝ ሳይኖር እንዴት ላውቀው እችላለሁ ማለቱ ነው:: ከዚህም በኋላ እንዲተረጉምለት ፊልጶስን ጠየቀው:: ፊልጶስም ተረጎመለት:: ሐዋ. 8÷26-40 ሔኖክም የሚያየው ራእይ እንደሰማይ የመጠቀ እንደውቅያኖስ የጠለቀ እንደነፋስ የረቀቀ ምሥጢሩ የተደበቀ ቢሆንበት እንዲተረጉምለት መልአኩን ጠየቀው:: መልአኩም ለሔኖክ አእምሮ የራቀውን በማቅረብ የረቀቀውን በማጉላት ተረጎመለት:: ሔኖ. 14÷1-11፤ 12÷8-9::

ዳንኤልም የሚያስደነግጥ እጅግ ግሩም የሆነ ራእይን አይቶ ፍቺውን ለማወቅ ተቸግሮ ሳለ ፍቺውን ይነግረው ዘንድ ከመላእክት አንዱን ጠየቀው:: የተጠየቀውም መልአክ የራእዩን ገጽታዎች በትርጓሜ ገላልጦ ለዳንኤል አሳየው:: ዳን. 7÷1-28



www.ethiopianorthodox.org

ዮሐንስ ወንጌላዊም የሚያስደንቅና የሚያስገርም ራእይን አይቶ በራእዩ ግሩምነት በምሥጢሩ ሥውረንት ወይም ጥልቅነት ተደንቆና ተገርሞ ሳለ ምሥጢሩን የማወቅ ፍላጐት በዮሐንስ አእምሮ እንዳለ የተገነዘበው መልአክ ንባቡን ፈታትቶ ምሥጢሩን ገላልጦ ተርጉሞለታል፡፡ ራእ. 17÷1-18 ከዚህ በላይ የተጠቀሱትና ሌሎች ያልተጠቀሱት ነቢያትና ሐዋርያት ያዩትን ራእይ የተማሩትን ትምህርት ደህና አድረገው ሊረዱ የቻሉት በትርጓሜ ነው፡፡

ነቢያት ስለአዩት ራእይ ሐዋርያት ስለተማሩት ትምህርት ግምታዊ ትርጉም ሲሰጡ አናይም፡፡ ትርጓሜ በሰዎች የተፈጠረ አዲስ ግኝት የመማሪያ ዘዴ ሳይሆን ከጥንት ጀምሮ ሲያያዝ የመጣ ነው፡፡ የመጀመሪያ ተርጓሚዎች እግዚአብሔርና መላእክቱ ናቸው፡፡ ከዚህ በላይ እንደተገለጸው መላእክት ለሔኖክ፣ ለዳንኤል ለዮሐንስ ሲተረጉሙላቸው አይተናል፡፡ ጌታ ለሐዋርያት ሐዋርያትም ለተከታዮቻቸው በመተርጐም አሁን እስከአለው ትውልድ ደርሷል፡፡ ወደፊትም እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ የትርጓሜ ቅብብሎሽ ይቀጥላል፡፡ የቅዱሳት መጻሕፍት ንባብ /ቃል/ የሚተረጐመው የአበውን ትርጓሜ መሠረት በማድረግ ምሥጢር እንዳይዛባ በመፍራት፣ በመንቀጥቀጥ ነው እንጂ በድፍረት አገኝ አጣውን በመዘላበድ አይደለም፡፡ ወይም የፈጠራ ችሎታን ማንጸባረቂያ መድረክ አይደለም፡፡

## ቁጥሮች በመጽሐፍ ቅዱስ

በዮሐንስ ራእይ 20÷1-10 ሺህ ዓመት የሚለው ንባብ /ቃል/ ከሐዋርያት ጀምረው የትርጓሜን ትምህርት በመማርና በስተማር ሲያስተላልፉ ከቆዩት አበው በተማሩ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን እንደሚከተለው ይተረጎማል፡፡ ሺህ ዓመት ዘመነ ሥጋዌ /ጌታ ሰው የሆነበት ዘመን/ ዘመነ ክርስትና፣ ዓመተ ምሕረት /የይቅርታ ዘመን/ ነው፡፡ ምክንያቱም መጽሐፍ ብዙ ጊዜ ስለቁጥር ሲናገር ቁጥሮችን ሲያስቀምጥ የጐደለውን መልቶ ያነሰውን አብዝቶ የተረፈውንም አጉድሎ፣ ቀንሶ፣





አጥፎ፣ ከፍሎና ጠቅልሎ ስለሚናገር ነው፡፡ ለአብነት ያህልም የሚከተሉትን የመጻሕፍት ማስረጃዎች እንመልከት፡፡

1ኛ. እስጢፋኖስ እስራኤል በግብፅ 400 ዓመት ባሪያዎች እንደሚሆኑ በዘፍ. 15÷13 ላይ የተጻፈውን በመጥቀስ 400 ዓመት ለግብፃውያን እንደተገዙ ይናገራል፡፡ ሐዋ. 7÷6 በዘፍጥረትም በዋርያት ሥራም እስራኤል 400 ዓመት በግብፅ ባሪያዎች መሆናቸው እንደተገለጸ ልብ እንበል፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች በላከው መልእክቱ ምዕ. 3÷15-18 ያለውን ስናነብ ደግሞ የተስፋው ቃል ለአብርሃም እንደተነገረ እያብራራ እየገለጸ መጥቶ ቁጥር 16 ላይ «ይህንንም እላለሁ ከአራት መቶ ሠላሳ /430/ ዓመት በኋላ የተሰጠው ሕግ...» ይላል፡፡ አብርሃም የተስፋውን ቃል ከሰማበት ጀምሮ እስራኤል ከግብፅ እስከወጡበት ወይም ኦሪት እስከ ተሰጠችበት ድረስ ያለው ዘመን 430 /አራት መቶ ሠላሳ/ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ ይህንንም የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት አብርሃም ተስፋውን ከሰማ ጀምሮ እስራኤል ወደ ግብፅ እስኪ ወርዱ 215 /ሁለት መቶ አሥራ አምስት/ ዓመት እስራኤል ወደ ግብፅ ከወረዱ ጀምሮ ከግብፅ እስኪወጡ ድረስ 215 /ሁለት መቶ አሥራ አምስት/ ዓመት መሆኑን በትክክል ይገልጻሉ፡፡ ገላ.3÷17 የትርጓሜ መጽሐፍ ይመልከቱ፡፡ እስራኤል በግብፅ በባርነት የኖሩት 215 /ሁለት መቶ አሥራ አምስት/ ዓመት ሲሆን በዘፍጥረትና በሐዋርያት ሥራ 400 /አራት መቶ/ ዓመት መባሉ ወደ ግብፅ ከመውረዳቸው በፊት በከነዓን የቆዩት 215 /ሁለት መቶ አሥራ አምስት ዓመት/ ተጨምሮ ተቆጥሮ ነው፡፡

2ኛ. ነቢዩ ዳዊት በመዝሙሩ እንዲህ ይላል «ስለጽድቅህ ፍርድ 7 /ሰባት/ ጊዜ በቀን አመሰግንሃለሁ» መዝ. 118÷164 የእግዚአብሔርን ምሥጋና በ7 /ሰባት/ ጊዜ ብቻ መወሰኑ ሳይሆን በቀን ብዙ ጊዜ የሚያመሰግነው መሆኑን ፍጹም በሆነ በ7 /ሰባት/ ቁጥር መግለጹ ነው፡፡

3ኛ. በገላትያ መልእክት ምዕ. 5÷19-23 አሥራ አምስት የሥጋ ሥራና ዘጠኝ የመንፈስ ፍሬ ተገልጠዋል፡፡ እነዚህም አሥራ አምስቱ ፈቃዳተ ሥጋ ዘጠኙ ፈቃዳተ ነፍስ በመባል



www.ethiopianorthodox.org

ይታወቃሉ:: ይሁን እንጂ የሥጋ ፈቃዶች አሥራ አምስት ብቻ የነፍስም ፈቃዶች ዘጠኝ ብቻ ሆነው ሳይሆን መሰሎቻቸውን ሁሉ በእነዚህ ለመግለጽ ነው::

4ኛ. ዳግመኛም ነቢዩ ዳዊት ስለሰው ዕድሜ ሲናገር እንዲህ ብሏል «የዘመኖቻችንም ዕድሜ ሰባ /70/ ዓመት ነው ቢበረታም 80 /ሰማንያ/ ዓመት ነው ቢበዛ ግን ድካምና መከራ ነው» መዝ. 89÷10 ነቢዩ እንዲህ ሲል በ50 ዓመታቸው የሚደክሙ እንዳሉና እስከ መቶ ዓመት ድረስ ያለ መድከም የሚሠሩ እንደሚኖሩ ተዘንግቶት አይደለም:: አማካይ የሆነውን ቁጥር ተናገረ እንጅ::

5ኛ. እስራኤል ሆይ ስማ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው:: አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ፣ በፍጹምም ኃይልህ ውደድ:: ዘዳ. 6÷4 እስራኤል በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠሩ ሕዝቦች ሲሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ግን እንደ አንድ ሰው በመቁጠር ለአንድ ሰው በሚነገርበት ዘይቤ የአነጋገር ስልት እስራኤል ሆይ ስማ በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም ኃይልህ ውደድ ሲል እንመለከታለን:: ብዙዎችን ወደ አንድ በመጠቅለል አንድ አካል አስመስሎአቸዋል::

6ኛ. መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምሳሌ ሲያስተምር በመልካም መሬት ላይ የወደቀው ዘር አንዱ መቶ አንዱ ስድሳ አንዱ ሠላሳ እንደሚያፈራ ተናግሯል:: ማቴ. 13÷8 በመሬት ላይ የወደቀው ዘር ግን በዚህ አይወሰንም:: ለምሳሌ የበቆሎ ፍሬን ብንወስድ አንዱ ዘር ከሺህ በላይ የሆኑ ፍሬዎችን ይሰጣል:: ዳጉሳንም ጤፍንም ሌሎችንም የዘር ዓይነቶች ብናይ አብዛኞዎቹ ከሺህ በላይ ያፈራሉ:: የዘሮች ባሕርይ ለጌታ ተሰውሮት አይደለም:: ጌታ ሊገልፅ የፈለገው ደረጃቸውን ነው እንጂ የቁጥራቸውን መጠን ስላልሆነ ነው:: ዘሮች ዝቅተኛ መካከለኛ ከፍተኛ የፍሬ ብዛትን የሚሰጡ መሆናቸውን ለማንጸባረቅ ነው:: የዘሮች ምሳሌ የያዘው ምሥጢርም የወንጌል ልጆች ጻድቃን የሚያገኙትን የጽድቅ ደረጃ የሚያመለክት ነው::

7ኛ. ቅዱስ ኤፍሬም በማክሰኞ ውዳሴ ማርያም ድርሰቱ ተጸውረ በከርሥ ተሰዓተ አውራኀ፡ ዘጠኝ ወር በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ማኅፀን ተወሰነ ይላል:: መድኃኒ





ታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደማንኛውም ሕፃን ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በእመቤታችን ማኅፀን ቆይቶ የተወለደ ሲሆን ቅዱስ ኤፍሬም ዘጠኝ ወር ማለቱ አምስቱን ቀን አጥፎ፣ ጠቅልሎ ዘጠኝ በሚለው ንባብ አካቶ መቁጠሩ ነው::

8ኛ. ቅዱስ ያሬድም «ረገዝዎ ገቦሁ በኩናት»፣ ጐኑን በጦር ወጉት ይላል:: የጌታን ጐን በጦር የወጋው ከጭፍሮች አንዱ መሆኑን ዮሐንስ እንደሚከተለው ጽፏል:: «ነገር ግን ከጭፍሮቹ አንዱ ጐኑን በጦር ወጋው ወዲያውም ደምና ውኃ ወጣ» ዮሐ. 19÷34 ዮሐንስ የጌታን ጎን የወጋው አንድ ሰው መሆኑን ሲገልጽ ያሬድ ደግሞ ለብዙ ሰዎች በሚነገርበት ዘይቤ የአነጋገር ስልት ይገልጻል::

ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው መጽሐፍ ብዙውን ወደ አንድ በመሰብሰብ በመጠቅለል አንዱን ወደ ብዙ በመዘርዘር በማጉደልና በማትረፍ አስቀምጦ እናገኘዋለን:: ቁጥር በውሳኔም ያለውሳኔም ይነገራል:: በተለይም ሺህ ቁጥር ያልተወሰነ የሰው ብዛት የዘመን ርዝመት ነው:: ለዚህም የሚከተሉት ጥቅሶች ማስረጃ ይሆኑናል::

## ሺህ ቁጥር በመጽሐፍ ቅዱስ

ሺህ ቁጥር በመጽሐፍ ቅዱስ የቁጥርን መጠን በመግለጽ ብቻ አይወሰንም:: ሺህ ቁጥር ከሺህ በላይ ብዛት ላላቸው ነገሮች ሁሉ መገለጫ ገጽታ ነው:: ለዚህም የሚከተሉት ጥቅሶች ማስረጃ ይሆኑናል::

1ኛ. በዘዳግም 32÷30 ላይ ያለውን እንመልከት «እርሱ አምላካቸው ካልሸጣቸው እግዚአብሔር አሳልፎ ካልሰጣቸው አንድ ሰው እንዴት ሺህን ያሳድድ ነበር? ሁለቱስ እንዴት አሥሩን ሺህ ያሸሹ ነበር» በዚህ ንባብ አንድ ሰው ሺሁን አሥሩን ሺህ እንደሚያሳድዱና እንደሚያሸሹ ሁለቱ ደግሞ አሥሩን ሺህ እንደሚያሳድዱና እንደሚያሸሹ እንደሚያሸንፉም ተነግሯል:: ይህ ሺህ ቁጥር የሚገልጽልን ብዛትን ነው:: የቁጥርን መጠን አይደለም የቁጥርን መጠን ቢሆን ኖሮ አንድ ሰው አንድን ሺህ እንደሚያሳድድ ከገለጸ ሁለቱ ደግሞ በአንጻሩ ሁለቱን ሺህ እንደሚያሳድዱ መግለጽ



www.ethiopianorthodox.org

ነበረበት። ሁለቱም አሥሩን ሺህ እንደሚያሸንፉ ከገለጸ አንዱ አምስቱን ሺህ እንደሚያሸንፍ መግለጽ ነበረበት። የአንዱን ሰው ኃይል አንድን ሺህ በማሸነፍ ወስኖ የሁለቱን ሰዎች ኃይል አሥሩን ሺህ ወደ ማሸነፍ ማሳደግ አልነበረበትም። ወይም የሁለቱን ሰዎች ኃይል አሥሩን ሺህ ወደማሸነፍ ካሳደገ የአንዱን ሰው ኃይል አንድ ሺህ ሰዎችን ብቻ በማሸነፍ መወሰን አልነበረበትም። ነገር ግን ለመግለጽ የተፈለገው የቁጥርን ቅደም ተከተል፣ መስተካከል፣ የቁጥርን ልክ፣ መጠን፣ መስፈርትና የቁጥሮቹን አንፃራዊ አቀማመጥ አይደለም። እንዲገለጽ የተፈለገው አንዱ ብዙዎችን የብዙ ብዙዎችን የሚያሳድድ፣ የሚያሸሽና የሚያሸንፍ መሆኑን ነው።

2ኛ. በሁለተኛ ነገሥት ምዕ. 11÷12 የሚገኘውን ንባብ እንመልከት። «የንጉሡንም ልጅ አውጥቶ ዘውዱን ጫነበት ምሥክሩንም ሰጠው። ቀብተውም ንጉሥ አደረጉትና ንጉሡ ሺህ ዓመት ይንገሥ እያሉ እጃቸውን አጨበጨቡ» ይላል። እስራኤል ኢዮአስን ሺህ ዓመት ይንገሥ ያሉት ነቢዩ ዳዊት የሰው ዕድሜ በሰባና በሰማንያ ዓመት እንደተወሰነ ከተናገረ በኋላ መሆኑ ግልጽ ነው። እሥራኤል ነቢዩ ዳዊት የተናገረውን ዘንግተው፣ ረስተው ነውን? በእውነት ለኢዮአስ የሺህ ዓመት መንግሥት እየተመኙለት ነውን? አይደለም። እንኳን ኢዮአስ የሰው ዕድሜ እንደረጅም ዛፍ ከመቆረጡ በፊት የነበረ አባታችን አዳምም ሺህ ዓመት አልኖረም። ኢዮአስም ቢሆን ሺህ ዓመት ይቅርና ሁለት መቶ ዓመት እንዳይነግሥ ያውቃሉ። ነገር ግን ሺህ የሚለው ቁጥር ብዛትን ስለሚያመለክት ብዙ ዓመት ይንገሥ ማለታቸው ነው። ብዙ ዓመት ቢነግሥ እንደሚፈቅዱ ምኞታቸውንና ፈቃዳቸውን መግለጻቸው ነው። ከሺህ በታችም ይሁን ከሺህ በላይ ሺህ የብዙ ነገር መገለጫ መሆኑን ልብ ይሏል።

3ኛ. በመዝሙረ ዳዊት 89÷4 ላይ ያለውን እንመልከት። «ሺህ ዓመት በፊት እንደአለፈች እንደትናንት ቀን እንደሌሊትም ትጋት ነውና ዘመኖች የተናቁ ይሆናሉ» ይላል። ይህም ሺህ ዓመት የሚያመለክተው በሰው ዘንድ ብዙ የሆነው ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥቂት መሆኑን ነው። ከልዑልነቱ ከገናናነቱ የተነሣ ለሰው አእምሮ ብዙ መስሎ የሚታየው ነገር





ሁሉ ለእርሱ ጥቂት ነው። ቢሆንም የእግዚአብሔርን ልዑልነት ሺህን ዓመት እንደትናንት ቀን በመቁጠር ብቻ አንወስነውም። ልዑልነቱ በሰው አእምሮ በዚህ ልክ ነው ተብሎ አይወሰንም። ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስኪያልፍ ድረስ ያለው ዘመን በእግዚአብሔር ዘንድ አንድ ሰዓት ላይመላ ይችላል። ነቢዩ ዳዊት ሺህ ዓመት በፊትህ እንዳለፈች እንደትናንት ቀን ነው ሲል የእግዚአብሔርን ልዑልነት ሺህን ዓመት እንደትናንት ቀን በመቁጠር ለመወሰን ፈልጎ ሳይሆን ሺህን ከሺህ በላይ ለሆነ ነገር ሁሉ የብዛት መገለጫ በማድረግ ስለእግዚአብሔር ልዑልነትና ገናናነት በውስጡ ያለውን ሐሳብ ለማውጣት ስለፈለገ ነው።

4ኛ. በሁለተኛ የጴጥሮስ መልእክት 3÷8 ላይ ያለውን እንመልከት። «እናንተ ግን ወዳጆች ሆይ በጌታ ዘንድ አንድ ቀን አንድ ሺህ ዓመት ሺህ ዓመትም እንደ አንድ ቀን እንደሆነ ይህን አንድ ነገር አትርሱ» አሁንም ሺህ ዓመት የቁጥርን መጠን አይገልጽም። ንባቡ የሚገልጸው በሰው ዘንድ ጥቂቱ በእግዚአብሔር ዘንድ ብዙ በሰው ዘንድ ብዙው በእግዚአብሔር ዘንድ ጥቂት መሆኑን ነው። በሰው ዘንድ የተናቀው፣ የተነቀፈው፣ የተቃለለውና የተጠላው በእግዚአብሔር ዘንድ የከበረ፣ የላቀ ከፍ ያለና እጅግ የተወደደ መሆኑን በሰውም ዘንድ የከበረው፣ የታፈረው፣ ከፍ ያለው፣ የተሞገሰው፣ የተወደደው በእግዚአብሔር ዘንድ የተናቀ፣ የተነቀፈ፣ የተዋረደ፣ ኢምንት የሆነ፣ የተጠላ መሆኑን ነው። ለምሳሌ ብር፣ ወርቅ፣ እንቍ ሰዎች ከፍተኛ ቦታ የሚሰጧቸው የክብር ቁንጮዎች ሲሆኑ በእግዚአብሔር ዐይኖች ግን ከጠጠርና ከአሸዋ ከዛፍ ቅጠሎች ተለይተው አይታዩም።

## ሺህ በልማዳዊ አነጋገር ሲነገር

ሺህ ቁጥር ብዛትን ለመግለጽ በልማዳዊ አነጋገር በሙገሳና በነቀፋ ይነገራል።

በሙገሳ ሲነገር:- አንድን ሰው ዘመዳም ነው /ዘመደብዙ ነው/ ለማለት እገሌ የሺህ ወገን ነው ይባላል። አባት ሴት ልጁን



www.ethiopianorthodox.org

ሲመርቅ ሺህ ሁኝ፣ ሺህ ያርግሽ ይላል:: ልጆችሽ ይብዙልሽ ለማለት ነው:: የብቸኝነትን ስሜት ለማራቅ:- የሺህ ሞት ሠርግ ነው ይባላል::

**የሰው ስም:-** ብዙ ሰው እንደሚፈራው የሚተነበይለት ወንድ ልጅ ሺህ ፈራው፣ ሺህ ባባው ይባላል:: ጀግንነትን ለመግለጽ አንድ ለእናቱ ሺህ ለጠላቱ ይባላል:: በብዙ ሰዎች ተወዳጅነትን እንደምታገኝ የሚተነበይላት ሴት ልጅ የሺህወርቅ፣ የሺህሐረግ ትባላለች:: ከሴቶች በላይ እንደምትሆን የሚተነበይላት ደግሞ የሺህእመቤት ትባላለች:: ሌላው ክረምት እንደገባ በምድር ላይ የሚርመሰመሰው ከረምት አግቢ በመባል የሚታወቀው የነፍሳት ወገን ብዙ እግሮች ስለአሉት ሺህ እግር ይባላል::

**በነቀፋ ሲነገር:-** ከራስ ፀጉሩ ሺህ ተባይ ይገኛል፣ ስለውሽታም ሰው በቀን ሺህ ጊዜ ይዋሻል ይባላል:: እነዚህ ሁሉ ሺህን የተመረኮዙ አባባሎች በቁጥር ያልተወሰነ ብዛትን የሚገልጹና የሚያንጸባርቁ ናቸው:: ሺህ የሚለው ንባብ /ቃል/ ብዙ ነው ለተባለ ነገር ሁሉ መጠቆሚያ መሣሪያ ነው::

## ሺህ ዓመት ዘመነ ሥጋዌ ነው

የሺህ ዓመት ትርጉም ብዙ ጊዜ የዘመንን ርዝመት፣ የሰውን ብዛት፣ ይገልጻል እንጂ በሺህ ቁጥር የተወሰነ ነገርን ብቻ እንደማይገልጽ ከተረዳን በዮሐንስ ራእይ 20÷1-10 የተቀመጠው ሺህ የሚለው ንባብ የዘመንን ብዛት የሚገልጽ መሆኑን ልናስተውል ይገባናል::

በዚህ ምዕራፍ ሺህ ዓመት በመባል የተገለጸው ከሺህ በላይ የሆነ ዘመነ ሥጋዌ፣ ዘመነ ክርስቶስ፣ ዘመነ ክርስትና በመባል የሚታወቀው እግዚአብሔር ራሱን በአርዓያ ብእሲ /በሰው አምሳል/ ለሰዎች የገለጠበት፣ ሰው የሆነበት፣ ክርስቶስ የተባለበት፣ የኃጢአትን ሥር የነቀለበት፣ የጽድቅን ችግኝ የተ ከለበት፣ አጋንንትን ያሰረበትና በሲኦል ታስረው የነበሩ ነፍሳ ትን የፈታበት ዘመን ነው::





የዚህም ዘመን መነሻውና መድረሻው እንደሚከተለው ነው:: አካላዊ ቃል በእመቤታችን ማሕጸን ከአደረበት ሰዓትና ደቂቃ ጀምሮ ሐሳዌ መሲሕ እስከሚጸነስበት ሰዓትና ደቂቃ ድረስ ያለው ዘመን ዘመነ ሥጋዌ ሺህ ዓመት በመባል ተገል ጿል:: በሺህ ዓመት ተውጦና ተጠቅልሎ የተጠራው ዘመነ ሥጋዌ መነሻው የእውነተኛው ክርስቶስ መጸነስና መወለድ ሲሆን መድረሻው ደግሞ የሐሳዌ መሲሕ መጸነስና መወለድ ይሆናል:: ከዚህ በፊት እንደተገለጸው የትርጓሜ ስልት ወይም ልምድ ባላቸው በቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት አተረጓጐም ሺህ ዓመት ቃል በቃል አይወሰድም:: ምክንያቱም አንደኛ ቃል በቃል ቢወሰድ የመጻሕፍትን ምሥጢር ስለሚያዛባ ሁለተኛ በመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ በልማዳዊ አነጋገር ሺህ የብዛት መገ ለጫ ሆኖ ስለሚገኝ ሺህ ዓመት ዘመነ ሥጋዌ ተብሎ ይተረጐ ማል:: ራእይ 20÷1-10 ያለው ንባብ ሰይጣን ሺህ ዓመት እንደ ታሰረ ከዚያም በኋላ ለጥቂት ጊዜ እንደሚፈታ ይገልጻል:: እንደሚከተለውም ይቀርባል::

«ወአኃዞ ለዝክቱ አርዌ ዘውእቱ ቀዳማዊ ወውእቱ ጋኔን ሰይጣን ወአሰሮ ዐሠረተ ምዕተ ዓመተ ወአውደቆ ውስተ ማዕምቅ ወአፀወ ላዕሌሁ በማኅተም ከመ ኢያስሕት አሕዛበ እስከ ይትፌጸም አሠርቱ ምእት ዓመት ወእምድኅረ ዝንቱ ሀለዎ ይትፈታሕ ኅዳጠ መዋዕለ»

የመጽሐፍ ቅዱሱ ትርጉም «የቀደመውንም እባብ ዘንዶ ውን እርሱም ዲያቢሎስና ሰይጣን የተባለውን ያዘው ሺህ ዓመ ትም አስረው ወደጥልቅም ጣለው:: አሕዛብንም ወደፊት እንዳ ያስት ሺህ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ በእርሱ ላይ ዘግቶ ማኅተም አደረገበት:: ከዚያም በኋላ ለጥቂት ጊዜ ይፈታ ዘንድ ይገባ ዋል::» ቁጥር ሁለትና በዚህ ንባብ ላይ ሰይጣን ሺህ ዓመት እንደታሰረ ተገልጿል:: ይህን ማንም አይክደውም:: እያወዛገበ ያለው ግን ሺህ ዓመት ከየት እስከ የት የሚለው ጉዳይ ነው::

## ሰይጣን ለምን ታሰረ?

1ኛ. **ሌባ ስለሆነ:-** መታሰር ማለት እንቅስቃሴን ማቆም፣ በአሳ ሪው ቁጥጥር ሥር መዋል፣ ነፃነትን ማጣት፣ በአንድ ቦታ



www.ethiopianorthodox.org

መወሰን፣ ከማንኛውም የእንቅስቃሴ ድርጊት መከልከል፣ የፈለጉትን ማድረግ አለመቻል ሲሆን ከመታሰር መያዝ ይቀድማል:: ከመያዝም መታሰር ይከተላል:: የሕዝብን ንብረት ሲዘርፍ፣ ሕዝብን ሲያተራምስ ሲቀማና የሕዝብን ሰላም ሲያናጋ የነበረው የስፈር አምላክ የሚባለው ዐመፀኛ ሌባ በፖሊስ ተይዞ በታሰረ ጊዜ ያ ሁሉ የዓመፅ እንቅስቃሴ እንደሙታን ትንፋሽ በቅጽበት ይጠፋል:: ወንበዴው የነበረበት አካባቢ ሰዎች ከአገኙት ዕረፍት የተነሳ ገነት የገቡ ይመስላቸዋል:: ዕረፍትንም ከመናፈቃቸው አንጻር የወርን ዕረፍት እንደ ዓመት ይቆጥሩታል::

የሰይጣንም መታሰር እንደሌባው እንደወንበዴው ነው:: ሌባ፣ ወንጀለኛ የሚባለው ወይም ሌባ የሚለውን ስያሜ የሚሸከመው የእርሱ ያልሆነውን ስለሚወስድ ነው:: ዲያብሎስም የእግዚአብሔር የእጅ ሥራዎች የሆኑትን የሰው ዘሮች ወደ አምልኮ-ጣዖት ወደ ገቢረኃጢአት በመንዳት በነፍስና በሥጋ ላይ ሌባ፣ ወንበዴ፣ ቀማኛ ሆኖ ሲኖር የነፍስና የሥጋ ፈጣሪ ወይም ባለቤት ኢየሱስ ክርስቶስ ሌባውን ዲያብሎስን ይዞ አስረውና እንቅስቃሴውን ገታው::

በዐመፀኛው ዲያብሎስ ተይዞ መታሰር፣ ሥጋና ነፍስ ያኗቸው የአዳም ዘሮች ተደንቆ የማይሰለች ዘላለማዊ ሰላም አግኝተዋል:: ሌባ የሰረቀውን ከብት የሰማይ ገጽታ በማይታይበት፣ ከአራዊት ድምፅ በቀር የሰው ድምፅ በማይሰማበት፣ በቀንም በሌሊትም ጨለማ በነገሠበትና ዓለመአራዊት በሚባለው ጫካ እንደሚያስቀምጠው ሁሉ ዲያብሎስም ከሥርቆት ባልደረቦቹ ከሐሰት ነቢያቱ ጋር ከሃይማኖት ከጽድቅ ማደሪያቸው እየነጠቀ የወሰዳቸውን የአዳም ልጆች ሥጋቸውን በመቃብር ነፍሳቸውን ብርሃን በማይፈራረቅበት፣ ጨለማ በሞላበት በሲኦል ሲያከማቻቸው ኑሯል::

ንብረቱ በሌባ የተሰረቀበት ባለንብረት ንብረቱን እየፈለገ የሚጠረጥራቸውን ሰዎች ቤት ወይም አካባቢ ፍተሻ ባደረገ ጊዜ ንብረቱ የተገኘበት ሰው ሌባ ተብሎ እጅ ከፍንጅ ተይዞ ይህን ያየህ ተቀጣ ለማለት የሠረቀውን ንብረት ተሸክሞ በሬ አርዶ በልቶ ከሆነ ቆዳውን ተሸክሞ በግ ወይም ፍየል አርዶ በልቶ ከሆነ የበጉን የፍየሉን ቆዳ ለብሶ በፖሊስ ታጅቦ





እየተገረፈ ወደ እስር ቤት ይሄዳል:: የጠፋው እንስሳም ሆነ ቁሳዊ ንብረት ከእጁ ስለተገኘ ምስክር አይፈለግለትም::

ወልደ እግዚአብሔርም በመቶ በጐች ከተመሰሉት ፍጥረቶቹ በአንድ በግ የተመሰለው አዳም በጠፋ ጊዜ በዘጠና ዘጠኝ በጐች የተመሰሉ መላእክትን ትቶ አንዱን አዳምን ሲፈልግ የተጠርጣሪ የዲያብሎስንም ቤት ሲፈትሽ የጠፋው በግ አዳም በዲያብሎስ ግቢ በሲኦል ስለተገኘ የዲያብሎስ ዕድል መታሰር ሆነ:: ወልደ-እግዚአብሔር ራሱ ባለንብረት ራሱ ንብረት ፈላጊ፣ ራሱ ፍትሕ ሰጭ፣ በያኒ ፈራጅ፣ ራሱ አሳሪ ሆኖ በማያንቀሳቅስ በረቂቅ ሰንሰለት ዲያብሎስን ቀፈደደው:: ዲያብሎስ ለምን ታሰረ? ለሚለው ጥያቄ የሚሰጠው መልስ እጅ ከፍንጅ የተያዘ ሌባ ስለሆነ የሚል ነው::

2ኛ. **ነፍሰ-ገዳይ ስለሆነ**:- ሰይጣን ነፍሰ-ገዳይ ለመሆኑና ሐሰተኛ ለመሆኑ በአንደበቱ ሐሰት የማይገኝበት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ሲል መስክሮበታል:: «እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ-ገዳይ ነበር:: እውነትም በእርሱ ስለሌለ በእውነት አልቆመም» ዮሐ. 8÷44 ሰይጣን ሁለት ጊዜ ነፍስ ያስገድላል

ሀ. **በክፉ ሰዎች አድሮ**:- ሰይጣን በክፉ ሰዎች አድሮ በሰይፍ በጐራዴ በጦር በሌላም መሣሪያ ነፍስ ከሥጋ እንድትለይ ያደርጋል:: ሰይጣን ስለነፍስ ግድያ የብዙ ዘመን ልምድን ያካበተ የነፍሰ-ገዳዮች ሁሉ መምህር ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ የሰይጣንን ነፍሰ-ገዳይነት ሲገልጽ ከጥንት ከመጀመሪያ በዚህ እኩይ ተግባር የተካነ በነፍሰ-ገዳይነት የሚቀድመው የሌለ ተወዳዳሪ የማይገኝለት ብቸኛ ጨካኝ ፍጡር መሆኑን ገልጿል:: አዳምና ሔዋን ከተፈጠሩ ነፍስና ሥጋ ከተዋሐዱ ጀምሮ የሰይጣን እንቅስቃሴ በነፍስ ግድያ መስክ ላይ የሚተገበር ነው::

በእባብ አድሮ በአዳምና በሔዋን ሞተ ሥጋን ሞተ ነፍስን ያመጣ ሰይጣን ነው:: በቃኤል አድሮ ልቡን በቅንዓት መልቶ ንጹሑን የእግዚአብሔርን በግ አቤልን ያስገደለ ሰይጣን ነው:: በመምለኬ ጣኦት በምናሴ አድሮ የሕገ እግዚአብሔር ጠባቂና አስጠባቂ የሆነውን ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስን በኩላብ አሰቅሎ በመጋዝ አስተርትሮ ያስገደለ ሰይጣን ነው::



www.ethiopianorthodox.org

በእስራኤል አድሮ ዓይነ-ልቡናቸውን አሳውሮ አጨልሞ ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ የተቀደሰውን ኤርምያስን በደንጊያ አስቀጥቅጦ ያስገደለ ሰይጣን ነው:: በሄሮድስ አድሮ የኢየሱስ ክርስቶስን መንገድ ጠራጊ መጥምቀ መለኮት ዮሐንስን ያስገደለ ሰይጣን ነው::

በአጠቃላይ ከጥንት ጀምሮ ክፉ ሰዎችን በመሣሪያነት ተጠቅሞ መንፈሳውያን ሰዎችን የሚያስገድል ብቸኛ ነፍሰ-ገዳይ ሰይጣን ነው:: መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰይጣን ከመጀመሪያ ነፍሰ-ገዳይ ነበር ሲል ነፍሰ-ገዳይነቱን ገለጸ እንጂ የመግደያ መሣሪያውንና የአገዳደል ስልቱን አልገለጸም:: ሰይጣን ነፍስ ሲገድል ከብረት የተሠራ ሰይፍ ጐራዴ፣ ጦር ሌላም መሣሪያ ይዞ አይታይም::

ሰይጣን ራሱ ረቂቅ ነው:: መሣሪያውም ረቂቅ ነው:: የሰይጣን መሣሪያ ሰዎችን ማነሳሳት ነው:: የሰዎችን አእምሮ አጨልሞ በጐ አመለካከታቸውን ከውስጣቸው ማጥፋት ሰብአዊ ርኅራኄያቸውን ነቃቅሎ መጣል የዘወትር ተግባሩ ነው:: ነፍስ መግደል ኃጢአት እንዳልሆነ አድርጐ ማሳየትና ገዳዩ ሰውን ስለገደለ በዕረፍት እንደሚኖር የሚያገኘውም ልዩ ነገር እንዳለ አድርጐ ማስጐምጀት የሰይጣን የመግደያ መሣሪያው ነው::

እንዲህ ስለሆነ ነው ሰዎች ሰውን እስኪገድሉ ድረስ የሚቸኩሉና ከገደሉ በኋላ የሚጨነቁ:: ከመግደላቸው በፊት በራሳቸውና በቤተሰባቸው ላይ የሚደርሰው ችግር አይታያቸውም ሰይጣን አእምሮአቸውን ወደ አንድ አቅጣጫ ብቻ ይወረውረዋል:: ሊያፈሰው የፈለገውን ደም እስኪያፈስ ድረስ ሰይጣን ነፍሰ-ገዳዩን ያስቸኩለዋል:: ነፍስ መግደል የወንድነት፣ የጉብዝና መመዘኛ እንደሆነ አድርጐ በልቡናው ይስልበታል::

ሰይጣን ይህን መጥፎ ድርጊት ካስፈጸመ በኋላ ድርጊት ፈጻሚው ሰው ነፍሰ-ገዳይ ይባላል:: የነፍስ ግድያን ድርጊት ፈጻሚው ሰው ሲታሰር ድርጊት አስፈጻሚው ሰይጣን አይታሰርም:: ነፍሰ-ገዳዩን ሰው ሲጨነቅና ሲያዝን ሰይጣን ይደሰታል:: የነፍሰ-ገዳይ ቤተሰቦች የሚውሉበት የሚያድሩበት ሲያጡ ሲንከራተቱ ሰይጣን አይንከራተትም:: ይልቁንም የተገዳይ ወገን እንዲበቀላቸው ያሉበትን ቦታ ይጠቁማል::





የግድያውን ተግባር በማከናወን አንደኛውና ዋነኛው ሰይጣን ሆኖ ሳለ ነፍሰ-ገዳይ ተብሎ የሚታሰረውና የበቀል እርምጃ የሚወሰድበት ሰው ነው:: ሰይጣን ነፍስ ገደለ ተብሎ ተከሶ አያውቅም:: የሰይጣን መጥፎ ተግባሩ እንጂ አካሉ አይታይም:: በግዙፋን ሰዎች ዓይን ስለማይታይ በሰዎች አንደበትም ሰይጣን ነፍሰ ገዳይ ነው ተብሎ ተነግሮ አያውቅም የተደበቀውንና የተሰወረውን ገልጦ የሚያይ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የገዳይንም የተገዳይንም ነፍስ ገዳይ ሰይጣን እንደሆነ ለብዙ ዘመናት ያልታወቀ ስውር ተንኰሉን ገለጠበት:: ረቂቁን ነፍሰ ገዳይ ሰይጣንን በረቂቅ ሰንሰለት ያሰረውም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው::

**ለ. ኃጢአት አሠርቶ:-** ሰይጣን ሰዎችን ኃጢአት አሠርቶ ነፍስ በኃጢአት መርከስ ምክንያት ከቅዱስ ፈጣሪዋ ከእግዚአብሔር እንድትለይ ያደርጋል:: የነፍስ ሞቷ ከእግዚአብሔር መለየቷ ነውና:: ሰው በኃጢአት ሲሰናከል ሞተ ይባላል:: «በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ» ኤፌ. 2÷1::

ተቆርጦ ከግንዱ የተለየ ቅርንጫፍ ከመውደቅና ከመድረቅ ያለፈ ዕድል እንደማይኖረው ከእግዚአብሔር የተለየች ነፍስም ወደ ሲኦል ከመውደቅና ሕይወት አልባ ከመሆን ሌላ ዕድል አይኖራትም:: ዲያብሎስ አምስት ሺህ ከአምስት መቶ ዘመን በተለያየ መንገድ ሰዎችን ከእግዚአብሔር በመለየት ሲገድላቸው ኖሯል::

ዋነኛው የነፍስ መግደያ መሣሪያው አምልኮ ጣዖት ነው:: ሰዎች ለጣዖታት ሲሰግዱ ዲያብሎስ በጣዖታቱ ላይ አድሮ የስግደቱ ተቀባይ ሆኖ ይመካ ነበር:: ሰው ሁሉ ሌባ እንደ ሰረቀው እንስሳ የጌታው የእግዚአብሔር መሆኑ ቀርቶ የሌባው የዲያብሎስ አገልጋይ ሆኖ ይንበረከክለት እንደነበር እንዲህ ተብሎ ተጽፏል:: «ነገር ግን በዚያን ጊዜ እግዚአብሔርን ሳታውቁ በባሕርያቸው አማልክት ለማይሆኑ ባሪያዎች ሆናችሁ ተገዛችሁ» ገላ. 4÷8፤

«ነገር ግን አሕዛብ የሚሠዉት ለአጋንንት እንዲሆን እንጂ ለእግዚአብሔር እንዳይሠው እላለሁ» 1ኛቆሮ. 10÷20:: በኤልያስ ጊዜ የነበሩ ጣዖት አምላኪዎች የጣዖቱ ነቢያትና ካህናት ሰውነታቸውን በስለት በጦር እየወጉና እየቆራረጡ



www.ethiopianorthodox.org

ደማቸውን ይሰውለት እንደነበር 1ኛነገ. 18÷25-29 ተጽፏል:: እግዚአብሔር የመረጣቸው፣ ባሕረ ኤርትራን ከፍሎ ያሻገራቸው፣ ታቦተ-ሕጉን የሰጣቸው እስራኤልም በዚሁ ሰይጣንን የማምለክ በሽታ ተለክፈው በከተማቸው ቁጥር ጣዖታትን አቁመው እንደነበር የሚከተለው ንባብ /ቃል/ ያመለክታል:: «ይሁዳ ሆይ አማልክትህ እንደከተሞችህ ቁጥር እንዲሁ ናቸው» ኤር. 11÷13::

ዲያብሎስ ያንን የተመኘውን አምላክነት ማግኘት ባይቻለውም ማስተዋል የጐደላቸውን ሰዎች ለእርሱ እንዲንበረከ በማድረግ ከሕይወታቸው ከእግዚአብሔር ይለያቸው ነበር:: የሚሸጥን እንስሳ ጨው እያላሱ እያታለሉ ከመንጋው ለይተው ወደ ገበያ እንደሚወስዱት ሁሉ ዲያብሎስም ፍቅረ ጣዖትን እንደጨው አድርጐ በማቅረብ የአዳምን ልጆች ከመንጋቸው ከማኅበረ መላእክት ከመንጋው ባለቤት ከእግዚአብሔር ለይቶ ወደ ቅጽረ ግቢው ወደ ሲኦል ሲነዳቸው ነው የኖረው::

የአዳም ልጅ ተብሎ የሲኦልን ቁልቁለት ያልወረደ እንዳልነበረ መጻሕፍት ይመሰክራሉ:: «ሕያው ሆኖ የሚኖር ሞትንስ የማያይ ማን ነው? ነፍሱንስ ከሲኦል እጅ የሚያድን ማን ነው?» መዝ. 88÷48፤ «ባለጠጋው ደግሞ ሞተና ተቀበረ በሲኦልም በሥቃይ ሳለ አሻቅቦ አብርሃምን በሩቅ አየ» ሉቃ. 16÷22:: ባለጠጋው ወደ ሲኦል መውረዱን ልብ ይሏል:: «እስመኩሉ ዘሞተ ይወርድ ነፍሱ ውስተ ሲኦል፤ የሞተው ሰው ሁሉ ነፍሱ ወደ ሲኦል ይወርድ ነበርና» መቅ.ወን.፤ «አሜሃ በውእቱ መዋዕል ኮና ነፍሳት ሶበ ይወጽአ እምሥጋ ሰብእ ይወርዳ መትሕተ ምድር ወይትፌነዋ ውስተ ገሃነም እስከ ይመልአ አብያተ ሞት፤ ያን ጊዜ በዚያ ወራት ነፍሳት ከሥጋቸው በተለዩ ጊዜ ከምድር በታች ወደ ሲኦል ይወርዱ ነበር የሞት ቤቶችም እስኪመሉ ድረስ ወደ ገሀነም ይሄዱ ነበር» ቄር. ሃይ. አበ. ምዕ. 80 ገጽ 335::

ሲኦልም ጨለማና እሳት የመላባት ቦታ ናት:: «እሳት በቁጣዬ ትነድዳለችና እስከ ሲኦል ድረስ ታቃጥላለች» ዘዳ. 32÷22:: ስለጨለማዋ ጽንዓትም የሚከተለው ቃል ይገልጻል:: «ኢይሬእዩነ ወኢንሬእዮሙ አላ ይመስለነ ለባሕቲትነ ዘሀሎነ





ህየ እንዘምስሌነ ብዙኀ ጉባኤ እስመ ጽልመት ኢየሐድገነ ንትረአይ በበይናቲነ፤ እነርሱ አያዩንም እኛም አናያቸውም ከእኛ ጋር ብዙ ሰዎች እያሉ ብቻችንን ያለን ይመስለናል እንጂ እርስ በርሳችን እንተያይ ዘንድ ጨለማው አይለቀንምና» ዮሐ. አፈ. ተግሳጽ 1 ገጽ 9::

በዚህ ንባብ እንደተመለከትነው ነፍሳት መከራ በሚቀበሉበት ቦታ እርስ በርሳቸው እንደማይተያዩ እንረዳለን:: ከዓለመ ሥጋ መከራ ይልቅ የዓለመ ነፍስ መከራ እንደሚጸና ዮሐንስ አፈወርቅ በተጠቀሰው ተግሣጹ እንዲህ ይላል:- በዚህ ዓለም እሳት ባለበት አካባቢ ጨለማ የለም:: የእሳቱ ብርሃን ጨለማውን ይገፈዋል:: ብርሃን የሌለው እሳት የለምና:: በዓለመ ነፍስ ግን በጨለማ መካከል እሳት በእሳት መካከል ጨለማ አለ:: ሁለት ተቃራኒ ነገሮች ተስማምተው ነፍሳት የሚቀበሉትን ሥቃይ ያጠናክራሉ ማለት ነው::

ወደዚህ ጽኑዕ ሥቃይ የተወረወሩ ነፍሳት የሞት ሞት ሞተዋል:: ከአንድ ጊዜ በላይ ብዙ ጊዜ ተገድለዋል ማለት ይቻላል:: በዚህ የጨለማ ባሕር ውስጥ ሰምጠው እንዲቀሩ ያደረጋቸው ያው ክፉ ጠላት ዲያብሎስ መሆኑ ግልጽ ነው:: ታዲያ ዲያብሎስ ነፍሰ ገዳይ ያልተባለ ማን ይባል? ሰውን ሁለት ጊዜ የሚገድል ለነፍስ ግድያ ቆርጦ የተነሣ ዲያብሎስ ነው:: በኢየሱስ ክርስቶስ አንደበት ነፍሰ ገዳይ ተብሏል:: ነፍሰ ገዳይ ለጊዜው የሰዎችን ሕይወት ቢቀጥፍም የእርሱም ሕይወት የሚቀጥፍበት ጊዜ ይመጣል:: ሁል ጊዜ ተደላድሎ ተቀማጥሎ አይኖርም:: አንድ ቀን ይያዛል:: ከተያዘም በእስራት አልያም በሞት ይቀጣል:: ዲያብሎስም ተይዞ ሺህ ዓመት ወይም ዘመነ ሥጋዌን በሙሉ መታሰሩ ነፍሰ ገዳይ እንደመሆኑ ለነፍሰ ገዳይ የሚገባውን ቅጣት መቀጣቱ ነው:: ሰይጣን ለምን ታሰረ ለሚለው ጥያቄ የሚሰጠው ተጨማሪ መልስ ነፍሰ ገዳይ ስለሆነ የሚል ነው::

3ኛ. **ክፉ ጠላት ስለሆነ:-** ወንጀል ሌብነት ወይም ነፍስ ግድያ ብቻ አይደለም:: የተለያዩ ወንጀሎች አሉ:: በቅናት በምቀኝነት የወንጀል ተግባርን የሚፈጽሙ ሰዎች አሉ:: የሰዎችን ንብረት ለማውደም የሰዎችን ዕድል ለመዝጋት የሰዎችን ሰላም



www.ethiopianorthodox.org

ለማናጋት ጠላትነት፣ ታጥቀው የሚነሱ የተንኮል አርበኞች ሞልተዋል። ብዙ ጊዜ ደሃው በባለጠጋው ላይ ኢምሁሩ በምሁሩ ላይ በሽተኛው በጤነኛው ላይ፣ ሥጋዊው በመንፈሳዊው ላይ ሲዘምት ይታያል።

ባለጽግነት ወደነርሱ የተዛወረ ይመስል በባለጸጋው ንብረት መውደም በደስታ የሚፈነጥዙ ድሆች ብዙ ናቸው። ለበሽታቸው ፈውስ እንዳገኙ ሁሉ በጤነኞች መታመም የሚፅናኑ ሕሙማንም አይታጡም። በጓደኞቻቸው የትምህርት መውደቅ እነርሱ ያለፉ ያህል የጉብዝና ስሜት የሚሰማቸው የአእምሮ ዘገምተኞች ስፍር ቁጥር የላቸውም።

የምቀኝነት መንፈስ የተጠናወታቸው ሰዎች በተሰለፉበት የሥራ መስክ እንደወንድሞቻቸው ለመሆን ከመጣር ይልቅ የወንድሞቻቸውን ውድቀት ሲመኙ ነው የሚውሉት። ከመጥፎ ምኞታቸውም አልፈው በጠላትነት ሲነሱ በንብረት ላይና በሰው ሕይወት ላይ ወንጀል ሲፈጽሙ ይገኛሉ። ሆኖም እነዚህ ወንጀለኞች ከተያዙ እንደወንጀላቸው ክብደት በብዙ ዓመት እሥራት መቀጣታቸው አይቀሬ ነው።

ሰይጣንም በንጹሕ ስንዴ መካከል እንክርዳድን የሚዘራ ማቴ. 13÷25-39 በምዕመናን ልቡና የተዘራውን የወንጌል ቃል የሚነጥቅ የሚያወድም ማቴ. 13÷19 ምቀኛ፣ ተንኮለኛ፣ ቀናተኛ ክፉ ጠላት ነው። ከአዳምና ከሔዋን ጀምሮ እስከ ክርስቶስ ድረስ በሰው ልጆች ላይ የፈጸመው ወንጀል ሰማይና ምድር ብራና /ወረቀት/ ቢሆኑ ደቂቀ አዳም በሙሉ ጸሐፍት ጋዜጠኞች ቢሆኑ ተጽፎ አያልቅም።

እንደሌሎቹ ክቡራን መላእክት በተፈጥሮ የተሰጠውን ክብር በትዕቢቱና በትምክህቱ አውልቆ ጥሎ ከክብር የተራቆተ የክብር ደሃ በመሆኑ «ነጋዴ ጓደኛው ስለቀረ ነው እንጂ እርሱ ስለከሰረ ወይም ስለተወረሰ አያዝንም» እንዲባል የአዳም ልጆች የእግዚአብሔርን ክብር እንዳይወርሱ ከእግዚአብሔር ጋር የሚያገናኛቸውን የቅድስና ድልድይ ለመናድ መደሻውን ይዞ የተሰለፈ ክፉ ጠላት ነው። ስለሆነም እውነተኛው ዳኛ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሠራውን ወንጀል ተመልክቶ ለብዙ ዓመታት እንዲታሰር ፈረደበት።





## ሰይጣን መቼ ታሰረ?

ሰይጣን መቼ ታሰረ ለሚለው ጥያቄ የሚሰጠው መልስ ተቀዋግቶ በተሸነፈ ጊዜ የሚል ነው። አንድ ሀገረ ገዢ ከሌላ ሀገረ ገዢ ጋር ተዋግቶ ከተሸነፈ ከነሠራዊቱ ተማርኮ ይታሰራል። መሣሪያውንም ይገፈፋል። የሚራራለትም የለም። አሸናፊው ሀገረ - ገዥም የተሸናፊውን ሠራዊትና ሀብት ንብረት መማረክ፣ መውረስ የሚችለው ያሸነፈውን የሀገር መሪ በቁጥጥሩ ሥር ካዋለ በኋላ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስም ዲያብሎስ አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን የወረረውን ዓለም ነፃ ለማውጣት በዲያብሎስ የተማረኩ ፍጥረቶቹን ለመመለስ ወይም መልሶ ለመማረክ የመጀመሪያ እርምጃው ሰይጣንን ማሰር ነበር። በሦስቱ የጦር እቃዎች ማለትም በትዕግሥት፣ በትሕትናና በጸሊዓ ንዋይ /ገንዘብን በመጥላት/ ከመታውና ድል ካደረገው በኋላ መሣሪያውን ገፎ ጥሎ በረቂቅ ሰንሰለት አስሮታል።

## «ሰይጣንን እንዳሰረው የጌታ ምሳሌያዊ አነጋገር»

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አጋንንትን ከሰዎች እያስወጣ ወደ ውጭ በጣለችው ጊዜ በችሎታውና በኃያልነቱ በመደነቅ ፈንታ በተቃራኒው የምቀኝነትና የቅንዓት አረቄ ያሰከራቸው አይሁድ ከአጋንንት ጋር ተስማምቶ ተግባብቶ ተወያይቶ በአጋንንት አለቃ አጋንንትን ያስወጣቸዋል በማለት ተአምራቱ ተቀባይነት እንዳይኖረው ለማድረግ ሞክረው ነበር። «ፈሪሳውያን ግን ሰምተው ይህ በብዔል ዜቡል /በአጋንንት አለቃ/ ካልሆነ በቀር አጋንንትን አያወጣም አሉ» ማቴ. 12÷24

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም የፈሪሳውያን አነጋገር ከመርዛማ የቅንዓትና የምቀኝነት ምንጭ የተቀዳ መሆኑን አውቆ ገንም እንዳይጐነጨው ጤናማ አለመሆኑን ከመግለጽ ጋር አጋንንት አንዱ ሌላውን በማውጣት እርስ በርሳቸው የሚጣሉና የሚለያዩ ከሆነ በጎብረት የሚሠሩት የማሳት ተግባራቸውን ማከናወን እንደማይችሉ ይጠቁማል። ማቴ. 12÷25-28 ሆኖም ለፈሪሳውያን የሰጠው መልስ በዚህ አልተገታም።



www.ethiopianorthodox.org

አጋንንትን በኃይለ መንፈስ ቅዱስ እንደሚያወጣቸውና ከአጋንንት ጋር ኅብረት እንደሌለው ሐሰት በማይነገርበት አንደበቱ ይገልጣል:: አጋንንትን የሚያወጣበትንና ወደ ውጭ የሚጥልበትን መንፈስ ቅዱስን የአጋንንት አለቃ በማለታቸው ኃጢአታቸው እንደማይሰረይላቸው ነግሮአቸዋል::

ኢየሱስ ክርስቶስ ከአጋንንት ጋር ስምምነት ቢኖረውኖሮ አጋንንት ልታጠፋን መጣህ? ባላሉትም ነበር:: የፍርሃትና የድንጋጤ ቃላትን ነው ሲወረውሩ የተደመጡት:: ኢየሱስ ክርስቶስ አጋንንትን ሊያጠፋ እንደመጣ ለፈሪሳውያን ባይገባቸውም ለአጋንንት ገብቶአቸዋል:: ፈሪሳውያን ኢየሱስ ክርስቶስን የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ብለው የተናገሩበት ቦታ የለም:: ይልቁንም የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ቢላቸው እንደሐሰተኛ ቆጥረው ድንጋይ አነሡበት አጋንንት ግን የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ሆይ ልታጠፋን መጣህን? ማቴ. 8÷29 ብለው የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን መስክረዋል:: ለፈሪሳውያን እንደመሰላቸው ወዳጆችን ረዳታችን ተባባሪያችን ወይም የሥራ ባልደረባችን አላሉም:: ጠላታቸው አንደሆነ እንጅ ወዳጃቸው እንደሆነ አልመሰከሩም::

ኢየሱስ ክርስቶስም አለቃቸው ዲያብሎስን ካሰረ በኋላ ሠራዊቱን እንደሚያስወጣ በሚከተለው አነጋገሩ አስታውቋል:: «ወይስ ሰው አስቀድሞ ኃይለኛውን ሳያስር ወደ ኃይለኛው ቤት ገብቶ ዕቃውን ሊነጥቀው እንዴት ይችላል? ከዚያም ወዲያ ቤቱን ይበዘብዛል:: ከእኔ ጋር ያልሆነ ይቃወመኛል ከእኔ ጋርም የማይከማች ይበትናል» ማቴ. 12÷29-30 በዚህ ምዕራፍና ቁጥር ላይ የሚገኘው ኃይለ ቃል አጋንንትን በአጋንንት አለቃ ያወጣል የሚሉ የፈሪሳውያንን አንደበት የሚዘጋ ኃይለ ቃል ነው:: የአንድን ኃይለኛ ሰው ቤት ለመዝረፍ ወይም ዕቃውን ለመንጠቅ ኃይለኛውን ሰው ማሰር ግድ ይሆናል:: ያለዚያ ግን ዕቃውን ለመንጠቅ አይቻልም:: ወደ ቤቱ ለመግባትም አይሞከርም::

ስለሆነም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ምሳሌያዊ አነጋገር የዲያብሎስን መታሰር በትክክል ያስረዳናል:: በኃይለኛ የተመሰለው የዚህ ዓለም ገዥ የነበረው የአዳምን ልጆች እንደወፍ ጫጩት እያነቀ 3ኛመቃ. 1÷3 ወደ ሲኦል





የሚወረውራቸው በእግዚአብሔር ላይ መፈንቅለ መንግሥት ያካሄደው ዲያብሎስ ነው:: ኃይለኛውንም የሚያ/ር ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን ዕቃ የተባሉትም የዲያብሎስ ሠራዊት አጋንንት ናቸው:: የኃይለኛውን ሶቃ መንጠቅ የሚቻለው ኃይለኛው ከታሰረ በኋላ እንደሚሆን ሁሉ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በሦስት ፈተናዎች ተፈትኖ በትዕግሥት በትሕትና በጸሊዓ ንዋይ ድል አድርጎ በረቂቅ ሰንሰለት ፈታኙንና ኃይለኛውን ዲያብሎስን ካሰረው በኋላ በዕቃ የተመሰሉ ሠራዊተ ዲያብሎስን አጋንንትን ከሰዎች ማስወጣት ጀመረ:: አለቃ የሌለው ሕዝብ አውራ የሌለው ንብ ኃይል አንድነት እንደማይኖረው አጋንንትም አለቃቸው ዲያብሎስ ከተሸነፈና ከታሰረ በኋላ ኃይል አላገኙም::

ከአጋንንት አለቃ ጋር በመስማማት አጋንንትን ያወጣል የሚሉ ፈሪሳውያን አንድ ያላስተዋሉት ነገር አለ:: በስምምነት ዕቃውን የሚያስነጥቅና የሚያዘርፍ ማነው? በስምምነት ሠራዊቱን የሚያስማ( ካ ንጉሥ ኢይኖርም:: ዲያብሎስም በዚህ ዓለም ነግሦ የዚህ ዓለም ገዢ ሆኖ ነበር:: እንዲህ ከሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዲያብሎስ ያሰማራቸውን ሠራዊተ ዲያብሎስ አጋንንትን ከማደሪያቸ( ከሰው ልቡና ሲያስወጣ ሲያሳድድ እንዴት ዲያብሎስ ተባባሪ ይሆናል? ሠራዊቱ እንዲበተኑ ይፈቅዳልን? ወይስ አጋንንት የዲያብሎስ ሠራዊት መሆናቸው ይዘነጋልን? አጋንንት የዲያብሎስ ሠራዊት መሆናቸው ከታመነበት ደግሞ ዲያብሎስ የገ ሠራዊቱን ለመበተን ከክርስቶስ ጋር ይተባበራል ብሎ ማሰብ ላስተዋዮች ማኅበር ይጨምራል::

## ሰይጣን የዚህ ዓለም ገዢ ነበር

የ'ለም ፈጣሪ አስገኝና ገዢ እግዚአብሔር ሆኖ ሳለ ዓለሙን በአምልኮ ጣዖትና በተለያየ የኃጢአት ዓይነት የተቆጣጠረው ሰይጣን የዓለም ገዢ ተብሏል:: ሰይጣን የዓለም ገዢ መሆኑ፣ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ሲል ገልጿል «ከእንግዲህ ወዲህ ከእናንተ ጋር ብዙ አልናገርም የዚህ ዓለም ገዢ ይመጣልና በእኔ ላይም አንዳች የለውም» ዮሐ. 14÷30



www.ethiopianorthodox.org

በዚህ ንባብ እንደምንረዳው ከፍተኛ ኃጢአትን የማሸተት ችሎታ ያለው ዲያብሎስ ጥቂት የኃጢአት ፍርፋሪ አገኛለሁ ብሎ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ማዕድ ሳይልከፈከፍ አልቀረም:: ሆኖም ኢየሱስ ክርስቶስ ንጹሐ ባሕርይ በመሆኑ ዲያብሎስ ሊስተናገድ አልቻለም:: «ተልባ መስሎሽ ሰናፍጭ ትቀምሺ» እንዲሉ ሌሎችን የአዳም ልጆች በኃጢአት ዝንባሌ ወጥመድ እየነቀ ወደ ሲኦል መወርወር የለመደው ሰይጣን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ በቀረበ ጊዜ በመስቀል በትር ራሱን ተመትቶ ተመልሷል:: በእያንዳንዱ ሰው ጭንቅላት ላይ ዙፋኑን ዘርግቶ ነግሦ ለሚኖር ዲያብሎስ የኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል አንሽራታች ሆነበት::

አንዱን ሽባ አንዱን ጉባጣ ሌላውን ድዳ ሌላውንም ደንቆሮ በማድረግ በሰው ሕይወት ሲጫወቱ የነበሩ የዲያብሎስ ሠራዊት አጋንንትን ኢየሱስ ክርስቶስ በተአምራት እያስወጣ ሰደዳቸው:: ሠራዊቱ ከተማረኩ የዓለም ገዢውም ያለው ዕድል መማረክ ወይም ግዛቱን መልቀቅ ነውና ዲያብሎስ ያለውድ በግድ ከዓለም ገዢነቱ ተወገደ:: በዲያብሎስ ሳያስበው በጠራ ሰማይ ላይ በረዶ የወረደበት ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ልጅ በጉበኝነት ሰው በሆነበት በመዋዕለ ስብከቱ ነው::

## የዚህ ዓለም ገዢ ወደ ውጭ ይጣላል

ዲያብሎስ ወደ ውጭ እንዲጣል ቁርጥ ውሳኔ ያስተላለፈው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: የሰዎችን ኃጢአት እንደ በር በመጠቀም ወደ ዓለም ገብቶ በዓለም ውስጥ የነበረው ዲያብሎስ ወደ ውጭ እንደሚጣል በሚከተለው ንባብ ያስረዳናል «አሁን የዚህ ዓለም ፍርድ ደርሷል:: አሁን የዚህ ዓለም ገዥ ወደ ውጭ ይጣላል:: እኔም ከምድር ከፍ ከፍ ያልሁ እንደሆን ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ» ዮሐ. 12÷31-32 የዚህ ዓለም ገዥ ወደ ውጭ ይጣላል ሲባል ዲያብሎስ ከየት ወደየት ይወጣል የሚለው ጥያቄ መነሳቱ አያጠራጥርም ሆኖም መልሱ እንደሚከተለው ይቀርባል::





ዓለም ተብሎ በጅምላ የሚጠራው በዓለም ውስጥ የሚኖረው ሰው መሆኑ ግልጽ ነው:: ስለሆነም ዲያብሎስ የሚወጣው ከሰዎች ልቡና ነው:: መቼም ሳይገባ ይወጣል አይባልምና ዲያብሎስ ወደሰዎች ልቡና እንደሚገባ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ሲል ይገልጻል «ጴጥሮስም ሐናንያ ሆይ መንፈስ ቅዱስን ታታልልና ከመሬቱ ሽያጭ ታስቀር ዘንድ ሰይጣን በልብህ ስለምን ሞላ» ሐዋ. 5÷3፤ «ቁራሽም አጥቅሶ ለአስቆሮቱ ለስምዖን ልጅ ለይሁዳ ሰጠው ቁራሽም ከተቀበለ በኋላ ያን ጊዜ ሰይጣን ገባበት::» ዮሐ. 13÷26-27

ሰይጣን በሰዎች ልቡና ካደረ በኋላ ፈረሱ ያደረጋቸዋል:: ወደ ወደደው ቦታም ይነዳቸዋል:: እግዚአብሔርንና ቅዱሳን መላእክትን ሌሎችንም የእግዚአብሔርን ወዳጆች ለመሳደብ አፋቸውን እንዲከፍቱ በማድረግ በአምልኮ ጣዖት ገመድ ከግንድ ጋር ያስራቸዋል:: ሰይጣን የገባባቸው ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ዘወር ማለት አይችሉም:: አምላካችንም የሚሉት የዲያብሎስ ማደሪያ የሆነውን ጣዖቱን ነው:: ሰይጣን የገባባቸው ሰዎች ጣዖትን ማምለክ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ወንጀሎችንም ይፈጽማሉ:: ከእግዚአብሔር ጋር የሚያለያዩ ከባድ ከባድ ኃጢአቶችን ይሠራሉ:: ሹፌር መኪናውን ወደፈለገው አቅጣጫ እንደሚያሽከረክር ዲያብሎስም ወደ ፈለገው የኃጢአት ከተማ ይወስዳቸዋል:: እንደመኪና ሾፌር በመስታወት አይታይም እንጂ የኃጢአተኞች ሁሉ ሹፌር ዲያብሎስ ነው::

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም እስኪገለጥ ድረስ ዲያብሎስ የዓለም ገዥ ነበር:: ብዙ ሠራዊትም ነበሩት:: የሕገ መንግሥቱ ረቂቆች ሰውን ለማሳት የሚቀርቡ ፈተናዎች ናቸው:: ሠራዊቱ እነዚህን ሕጎች ለማስጠበቅ በሚያደርጉት ዘመቻ ዓለምን ተቆጣጥረውት ነበር:: መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ የዚህ ዓለም ገዥ ዲያብሎስ በሦስት ፈተናዎች ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ውጊያውን ቀጠለ:: ውጊያዎች ከተካሄዱ በኋላ ጦር ሜዳው ላይ እንዳለ ጌታ ሂድ አንተ ሰይጣን ባለው ጊዜ ሰይጣን እንደጢስ ተኖ እንደትቢያ በኖ እንደጠፋ የሚከተለው ንባብ ያመለክታል::

«ዲያብሎስም ፈተናውን ሁሉ ከጨረሰ በኋላ እስከጊዜው ከእርሱ ተለየ» ሉቃ. 4÷13 ከዚህ በኋላ ዲያብሎስ በፍርሃት



www.ethiopianorthodox.org

ላይ ፍርሃት እየጨመረ ሄደ ኃይሉ ደከመ:: ተዋግቶ ተሸነፈ:: መሸሽ ጀመረ:: «የሽሮ ድንፋታ ውኃ እስኪገባበት ድረስ ነው» እንደሚባለው ዓለምን ሁሉ ሲያስጨንቅ ሲ[illegible] የነበረው ዲያብሎስ ጭስ የተጨሰበት ንብ መሰለ::

የአዳምን ልጆች ግራ ሲያጋባና የሚጨብጡትን ሲያሳጣ የነበረው የዲያብሎስ አጭበርባሪነት በኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ አከተመ:: የዲያብሎስ ዋና ተግባሩ የአዳምን ልጆች ማሳደድ ነበር:: የኢየሱስ ክርስቶስ ዋና ተግባር ደግሞ ዲያብሎስን ከነሠራዊቱ ማሳደድ ሆነ::

በኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ የተጨነቁት የዲያብሎስ ሠራዊት እንዲህ ይላሉ:: «እነሆም ኢየሱስ ሆይ የእግዚአብሔር ልጅ ከአንተ ጋር ምን አለን ጊዜው ሳይደርስ ልታሰቃየን ወደዚህ መጣህን» ማቴ. 8÷29፣ ማር. 5÷6-12 አጋንንት ጊዜው ሳይደርስ ልታሰቃየን መጣህ? ማለታቸው ጌታ በተሰቀለ ጊዜ ከዚህ የበለጠ ሥቃይ ስለሚቀበሉ ነው:: ታዲያ አጋንንት ጨኸታቸውን ያሰሙት መቼ ነው? ከማደሪያቸው ከሰው ልቡና የተባረሩት መቼ ነው? ወደ ውጭ የተጣሉት መቼ ነው? የዚህ ዓለም ገዥ ወደ ውጭ ይጣላል ተብሎ ፅኑዕ አዋጅ በታወጀበት የሰው ልጅ ነፃነት ብልጭ ባለበት በኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ አይደለምን?

የሰው ውድቀት በዲያብሎስ የስብከት ዘመን እንደነበረ የዲያብሎስም ውድቀት በክርስቶስ የስብከት ዘመን ነው:: የዲያብሎስ ስብከት የሰው ልጅ ወደውጭ ወደገሀነም ይጣላል የሚል ነበር:: የስብከት ድምፁን እንዲህ በማለት አሰምቷል:: «ከእኔ ጋር ወደ ገሀነም ሊሄዱ ጐጣ ጉጥ ወደሆነ ጐዳናም እመልሳቸው ዘንድ ምክንያት እሆናለሁና...» መቃ. ሳልስ 1÷5 በአንጻሩ በክርስቶስ ስብከት የዚህ ዓለም ገዥ ዲያብሎስ ወደ ውጭ ይጣላል የሚል ቃለ ብስራት /የምሥራች ቃል/ ተሰማ ተደመጠ::

ስለዚህ ዲያብሎስ ወደ ውጭ የተጣለው በዘመነ ሥጋዌ፣ ክርስቶስ ሰው በሆነበት ዘመን መሆኑ የተረጋገጠ ነው:: አስቀድሞ ኃይለኛውን ሳያስር ወደ ኃይለኛው ቤት ገብቶ ዕቃውን ሊነጥቀው እንዴት ይችላል:: ማቴ. 12÷29 የሚለው ንባብ ጌታ ሰው ሆኖ ወንጌልን በሰበከበት ዘመን ዲያብሎስ የታሰረ





መሆኑን ያረጋግጣል:: በዘመነ ሥጋዌ፣ ጌታ ሰው በሆነበት ዘመን ዲያብሎስ እነደታሰረ ራሱ ባለቤቱ ክርስቶስ ከመሰከረ ገና እንዳልታሰረ አድርጐ ለወደፊት ይታሰራል ማለት የክርስቶስን ቃል ማስተባበል ይሆናል::

ኢየሱስ ክርስቶስ በምሳሌያዊ አነጋገሩ ሰይጣንን እንዳሰረው ተናገረ እንጅ ገና ሳስረው ነው አላለም:: «አሁን የዚህ ዓለም ፍርድ ደርሷል አሁን የዚህ ዓለም ገዥ ወደ ውጭ ይጣላል» አለ እንጂ ነገ ከነገ ወዲያ ይጣላል አላለም:: ዮሐ. 12÷31 ዳግመኛም እንዲህ ይላል:: «ስለፍርድም የዚህ ዓለም ገዥ ስለተፈረደበት ነው» ዮሐ. 16÷11 ሊፈረድበት ቀን ተቀጥሯል አላለም:: ስለተፈረደበት ነው ያለውን ልብ ይሏል:: ተፈርዶበታል ታስሮአል ወደ ውጭ ተጥሏል::

ኢየሱስ ክርስቶስ ሰይጣንን አሰርኩት ወደ ውጭ ጣልኩት ካለ በኋላ ፈታሁት አነሳሁት አላለም:: መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰይጣን እንደተፈረደበት እንደታሰረ ወደ ውጭ እንደተጣለ የምሥራች በተባለችው በሕገ ወንጌል እያበሠረን በዮሐንስ ራእይ 20÷2-3 ላይ «የቀደመውንም እባብ ዘንዶውን እርሱም ዲያብሎስና ሰይጣን የተባለውን ያዘው ሺህ ዓመትም አሰረው ወደ ጥልቅም ጣለው:: አሕዛብንም ወደፊት እንዳያስት ሺህ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ በእርሱ ላይ ዘግቶ ማኅተም አደረገበት» የሚለውን ንባብ ሰይጣን እስከአሁን እንዳልታሰረና ገና ለወደፊት ሺህ ዓመት እንደሚታሰር አድርጐ መተርጐም ወንጌላዊ ዮሐንስ የወንጌል ተቃራኒ የሆነ ራእይ አይቷል ማለት ይሆናል::

ቅዱሳን መጻእያትን ወደፊት የሚሆኑ ነገሮችን ሲናገሩ መንፈስ ቅዱስ ተናገሩ ያላቸውን ብቻ ሳይቀንሱ ሳይጨምሩ ይናገራሉ እንጂ ከራሳቸው አንቅተው አይናገሩም:: የመንፈስ ቅዱስ ቃል በማናቸውም ጊዜ ቢነገር ከወንጌል ጋር አይቃረንም አይጣላም የሚያጣሉት ሰዎች ናቸው:: ከአመለካከት ከአተረጓጐም ችግር ካልሆነ በቀር ዮሐንስስ ሺህ ዓመት ያለው ዘመነ ሥጋዌ የክርስትና ዘመን ነው:: ጌታ በወንጌል ኃይለኛውን ዲያብሎስን ካሰረ በኋላ ሠራዊቱን እንደበተነ የገለጸውን ዮሐንስ በራእዩ ደገመው:: ሰይጣን የታሰረበትንና የወደቀበትን ዘመነ ሥጋዌንም ሺህ ዓመት በማለት ጠቀለለው::



www.ethiopianorthodox.org

ዮሐንስ ሃላፊያትንም መጻእያትንም አይቷል:: ያለፉ ድርጊቶችን በመተረክና ገና ለወደፊት የሚደረጉ የሚሆኑ ነገሮችን በመተንበይ ብዙ የተሰወሩ ምሥጢሮች፣ [illegible]ጣል:: ስለ ሰይጣንም መታሰር የጻፈው ኃይለቃል የሆነ የተደረገና ለሦሰመናን የተበሠረ የታሪክ ይዘት ያለው ኃይለ ቃል ነው:: የጠላትን ውድቀት ደጋግሞ መናገር የሚነግርላቸው ምእመናንን ከማስደሰቱም በላይ ለመንፈሳዊው ተግባር የተነሳሽነት ስሜትን የሚያጭር በመሆኑ በወንጌል ከተገለጸው አብልጦ አጉልቶ እንዲታይ አድርጎ አስቀመጠው እንጂ የወንጌል ተቃራኒ የሆነ መልእክት ማስተላለፉ አይደለም::

የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 20 ከምዕራፍ 12 ጋር በምሥጢር ይስማማል:: በምዕራፍ 12 ላይ ያለው ንባብ እንደሚከተለው ይቀርባል:: «ዓለሙንም ሁሉ የሚያስተው ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ ወደ ምድር ተጣለ መላእክቱም ከርሱ ጋር ተጣሉ ታላቅም ድምፅ በሰማይ ሰማሁ እንዲህ ሲል አሁን የአምላካችን ማዳንና ኃይል መንግሥትም የክርስቶስም ሥልጣን ሆነ:: ቀንና ሌሊትም በአምላካችን ፊት የሚከሳቸው የወንድሞቻችን ከሳሽ ተጥሎአልና እነርሱም ከበጉ ደም የተነሣ ከምሥክራቸውም ቃል የተነሣ ድል ነሱት::» ራእይ 12÷9-11 ከዚህ በላይ የተቀመጠው ንባብ ሰይጣን በዕለተ ፍጥረት መውደቁንና በዕለተ ዐርብ መውደቁን ያመለክታል:: በዕለተ ፍጥረት የማይገባውን ሥልጣነ እግዚአብሔርን ለመጨበጥ እጁን በሰነዘረ ጊዜ ክብሩን ብርሃኑን ተገፎ በጨለማ ተጠቅልሎ ወደ አንጦርጦስ ወርዷል:: በዕለተ ዐርብ በክርስቶስ መስቀል ተመትቶ ከሥልጣኑ ተሽሮ ወደውጭ ተጥሏል::

ከሳሹ በተጣለ ጊዜ የአምላካችን ማዳንና ኃይል ሆነ ይላል የአምላካችን ማዳንና ኃይል የሆነ መቼ ነው? አምላክ ሰው በሆነ ጊዜ አይደለምን? መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእመቤታችን በድንግል ማኅፀን ካደረበት ቀን ጀምሮ እስከ ዐረገበት ቀን ድረስ ያለው ዘመን ሁሉ የማዳን ዘመን ይባላል:: በተለይም በመስቀል ተሰቅሎ ህማማችንንም ተሸክሞ ደሙን አፍሶ 5500 ዘመን በህማመ ነፍስ ሲሰቃዩ የነበሩ ነፍሳትን ከሕመማቸው የፈወሰበት ዕለት ዕለተ ዐርብ የማዳን ቀን





ትባላለች:: ታዲያ ሰይጣን የተጣለው የአምላካችን ማዳንና ኃይል በሆነ ጊዜ አይደለምን?

## ሰይጣን ድል እንደተነሣ የራሱ ምስክርነት

በመስቀል ድል እንደተነሣ ራሱ ዲያብሎስ መስክሮአል:: ትምህርተ ኅቡዓት በተባለው በቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፍ የሚቀጥለው ንባብ ይገኛል:: «መኑ ዝንቱ ዘነኪር እምሕግየ መኑ ዝንቱ ዘእምዚአየ ይጼውው መኑ ዝንቱ ዘበኃይለ ነደ እሳት ምስለ ሞት ይትበአስ መኑ ዝንቱ ዘሞዖ ለጽልመት፤ ከኔ ሕግ ልዩ የሚሆን ማን ነው? ከእኔ ወገን ነፍሳትን ማርኮ የሚወስድ ማነው? ነደ እሳት በሚሆን ኃይል ከኔ ከሞት ጋር የሚሰላለፍ የሚዋጋ ይህ ማነው? ጨለማውን ድል የነሳው ያሸነፈው ማንነው?» በማለት የጥያቄ ቃላትን ካዥጐደጐደ በኋላ ለጥያቄው ራሱ መልስ ይሰጣል «ዝንቱ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ፤ ይህን ሁሉ ያደረገ የተሰቀለው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው» ይላል::

አንባቢ ሆይ ሞት ጨለማ የተባለ ራሱ ዲያብሎስ መሆኑን ልብ በል:: እንግዲህ ሰይጣን የተሸነፈው የደከመው የተጨነቀው በዕለተ ዐርብ ከሆነና ምእመናንም ከበጉ ደም የተነሳ ድል እንደነሱት ራሱ ዮሐንስ በራእዩ ምዕራፍ 12 ላይ ከገለጠ በምዕራፍ 20 ላይ ሺህ ዓመት አስረው ያለው ዘመነ ሥጋዌ ዘመነ ክርስትና መሆኑ ግልጽ ነው::

## «ሰይጣን ከገዥነት ወደ ተገዥነት»

ሰይጣን 5500 ዘመን የዚህ ዓለም ገዥ ሆኖ በሰው ልጅ ላይ ሠልጥኖ በነፍስና በሥጋ ላይ ቤተ መንግሥቱን ገንብቶ ረቂቃንና ግዙፋን አጋንንትን በሠራዊትነት አጠናክሮ ከኖረ በኋላ በኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ከገዥነት ወደ ተገዥነት ወርዷል:: በሙስና የተዘፈቀ ባለሥልጣን ከገዥነት ተወግዶ ተገዥ መሆኑ ግድ ነው:: በኃጢአት ዙፋን ላይ ነግሦ የነበረው ዲያብሎስም የሙ ስና ተግባሩን ሲያካሂድ ቆይቶ በክርስቶስ ገምጋሚነት ከሥልጣኑ ወርዷል::



www.ethiopianorthodox.org

ሲገዛው ለነበረው ለሰው ልጅ ከነሠራዊቱ ተገዥ ሆኗል:: ኢየሱስ ክርስቶስ በሦስት ፈተናዎች ተፈትኖ ድል ካደረገው በኋላ የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮችም ሰይጣንን ቀጥቅጠው መግዛት ችለዋል::ለሰብአ (፸) አርድእት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አጋንንት ተገዝተውላቸዋል:: «ሰብዓውም በደስታ ተመልሰው ጌታ ሆይ አጋንንትስ እንኳ በስምህ ተገዝተውልናል አሉት:: እንዲህም አላቸው ሰይጣንን እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ እነሆም እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ የሚጐዳችሁም ምንም የለም» ሉቃ. 10÷17 በዚህ ንባብ አጋንንት ለሰብዓ አርድእት እንደተገዙላቸው እንመለከታለን:: ሐዋርያው ጳውሎስ «የሚገዙም ምንም እንደሌላቸው ይሁኑ» ብሎ የተናገረው አስቀድሞ በአጋንንት ላይ የተፈጸመ ቃል ኖሯል ማለት ይቻላል:: 1ኛቆሮ. 7÷30

የአዳምን ልጆች ወደፈለጉት አቅጣጫ ሲነዱአቸው የነበሩት የዲያብሎስ ሠራዊት አጋንንት እንደተማረከ ወታደር እጃቸውን ለሐዋርያት ሰጡ:: የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሲጠራ መብረቅ የወረደ ያህል የድንጋጤ ማዕበል ይነዳቸው ጀመር:: ላመኑበት ሕይወት የሚሆነው የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ለአጋንንት የሞት ሞት ሆነባቸው:: ሰይጣንን እንደመብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ የሚለው የኢየሱስ ክርስቶስ አነጋገርም የሰይጣንን መውደቅ የቦታ መልቀቅ ያመለከታል:: መብረቅ ከወደቀ በኋላ ኃይል እንደሌለው ሁሉ ሰይጣንም በኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ኃይሉን ሥልጣኑን ተገፏል:: የክርስቶስ መገለጥ ብቻ ሳይሆን ሞቱም ሰይጣንን የሚደመስስ ከባድ መዣሪያ ነበር «ከመ በሞቱ ይስዓሮ ለመልአከሞት ዘውእቱ ሰይጣን፤ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር ይኸውም ዲያብሎስ ነው...» ዕብ. 2÷14-15 ተብሎ እንደተጻፈ በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት የሰይጣን መርዛማ ሥልጣን ተሽሯል::

መርዝ የሌለው እባብ ቢኖር ማን ይፈራው ነበር? ዓለሙን ሁሉ ጤና ያሳጣው የሰይጣንም መርዝ በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ተሽሯልና ሰይጣንን የሚፈራው የለም:: ስለዚህ ሰብዓ አርድእት ሐዋርያት ሰይጣንን በማዕድ ጊዜ ወደ ቤት እንደገባ ልክስክስ ውሻ ሂድ ውጣ እያሉ ከገባበት የሰዎች ልቡና እያስ





ወጡ መስደድ ችለዋል:: እንዲህም ስለሆነ ሰይጣን የታሰረው የወደቀው ወደ ውጭ የተጣለው፣ ተተኩሶ ኢላማውን እንደሳተ ጥይት የሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ነው:: ከቤተልሔም እስከ ቀራንዮ ያለው የክርስቶስ መንገድ ሰይጣንን የሚጥል መሰናክል ነበር::

## «ለጥቂት ጊዜ ይፈታ ዘንድ ይገባዋል»

ሰይጣን ሺህ ዓመት ማለትም ዘመነ ሥጋዌን በሙሉ ታስሮ ከቆየ በኋላ ይፈታል:: የሚፈታውም በመጨረሻው ዘመን ሐሳዌ መሲሕ ሐሰተኛው ክርስቶስ በሚነግሥበት ጊዜ /ዘመን/ ነው:: የክህደትና የማሳት ሥራውን ሁሉ ከሐሰተኛው ክርስቶስ ጋር በመተባበር ይሠራል ከእሥራቱ ይፈታልና:: በዓለም ላይ ሰላምን ያጠፋል:: በዚሁ ምዕራፍ ማለትም በራእይ 20÷7-10 ያለውን ንባብ እንመልከት «ሺሁም ዓመት ሲፈጸም ሰይጣን ከእሥራቱ ይፈታል በአራቱም በምድር ማዕዘን ያሉትን አሕዛብ ጎግንና ማጎግን እንዲያስታቸው ለሰልፍም እንዲያስከትታቸው ይወጣል፤ ቁጥራቸውም እንደባሕር አሸዋ የሚያህል ነው»

ጎግ ማለት ሠራዊት፣ መንጋ፣ በዝቶ የሚሄድ፣ የሚንጋጋ ማለት ነው:: ሁለተኛም ጎግ ብዙ ማጎግ የብዙ ብዙ ማለት ነው:: ጎግ ማጎግ የያፌት ልጆች መሆናቸው በዘፍጥረት 10÷2 ላይ የተገለጸ ሲሆን በእስራኤል ላይ በጠላትነት የሚነሱ ጨካኞች አሕዛብ መሆናቸው ደግሞ በሕዝቅኤል 39÷2 ላይ ተገልጿል:: ጠባያቸውና ጭካኔአቸው እንደአራዊት ስለሆነ ስማቸው ማስፈራሪያ ሆኖ ቀርቷል:: ዛሬም ቢሆን በክፉ ጊዜና በክፉ ሰው ላይ ይነገራል:: ኃያላን ስለሆኑ በጦርነት የሚቋቋማቸው የለም:: በምድር ላይ የሰውን ዘር እንዳያጠፉ እግዚአብሔር በአንድ ቦታ እንዲወሰኑ አድርጓቸዋል::

ምድቅኤል ቅርፍትኤል የሚባሉ ሁለት ተራሮች ነበሩ:: እስክንድር መቄዶናዊ እነዚያን ተራሮች በጸሎት አቃርቦ ዘግቶባቸዋል:: እንዳይከፍቱትም የመልአክ ዘበኛ ቆሞባቸዋል:: በሕዝቅኤል በምዕራፍ 38 ና 39 ላይ እንደተገለጸው በፍጻሜ ዘመን ወደ ምድረ እስራኤል ገብተው ይዋጋሉ:: እግዚአብሔርም በመቅሰፍት ያጠፋቸዋል::



www.ethiopianorthodox.org

ከእስራት የሚፈታው ሰይጣን ቁጥራቸው እንደባሕር አሸዋ ብዙ የሚሆን ጎግማጎግ የሚባሉትን አሕዛብን ይሰበስባቸዋል:: ከሐሳዌ መሲሕ ሠራዊት ጋር እንዲተላለቁ ያደረጋል:: እርስ በርሳቸው እንዲነካከሱ፣ እንዲበላሉ፣ እንዲተራረዱና እንዲገዳደሉ ያነሳሳቸዋል:: መቼም ሰይጣን የአዳም ልጆች በሕይወት ሲኖሩ የሚያዝን የሚተክዝ ሲቅበዘበዙና ሲጠፉ የሚደሰት የሚፈነጥዝ ርጉም ፍጡር መሆኑ አይዘነጋም:: ስለሆነም ለሰልፈኞች /ለተዋጊዎች/ ሰይፍ እንጂ ጋሻ አያቀብልም::

ሐሳዌ መሲሕና ሠራዊቱ ወዳጆቹ ቢሆኑም የሚጋብዛቸው የሰይፍ ስለትን ነው:: ማንም ቢሆን ለወዳጁ ግብዣ ማድረግ የሚችለው ከጓዳው ያለውን ከእጁ ያገኘውን ነው:: በዲያብሎስም ጓዳ መልተው የሚገኙት የሚከተሉት ናቸው:: የሥጋ ሞት፣ የነፍስ ሞት ሰላም ማጣት፣ ጥላቻ፣ እልቂት፣ መቅሰፍት፣ ውድቀት፣ ሐዘን፣ ለቅሶ፣ ከፈጣሪ መለየት፣ በገሀነመ እሳት መጋየት፣ በጨለማ መዋጥ፣ በመከራ መቅለጥ:: ሰይጣን እነዚህንና የመሳሰሉትን አዘጋጅቶ ወዳጁን አፍህን ክፈት ላጉርስህ ይለዋል:: ሰይጣን ከእስራቱ የሚፈታው ለጥቂት ጊዜ ነው:: የሐሳዌ መሲሕ መንግሥት ተጀምሮ እስኪፈጸም ድረስ ነው:: የሐሳዌ መሲሕም የመንግሥት ዘመን ሦስት ዓመት ከመንፈቅ /አርባ ሁለት ወር/ ነው:: ራእ. 13÷5

## «ከክርስቶስ ጋር መንገሥ»

«ዙፋኖችንም አየሁ በእነርሱም ላይ ለተቀመጡት ዳኝነት ተሰጣቸው ስለ ኢየሱስም ምስክርና ስለእግዚአብሔር ቃል ራሶቻቸው የተቆረጡባቸውን ሰዎች ነፍሳት ለአውሬውና ለምስሉም ያልሰገዱትን ምልክቱንም በግንባራቸው በእጃቸውም ላይ ያልተቀበሉትን አየሁ፤ ከክርስቶስም ጋር ሺህ ዓመት ኖሩና ነገሡ» ራእ. 20÷4-5::

መንገሥ ማለት መሰልጠን፣ ጌታ መሆን፣ የሕዝብ አለቃ ቀንድ መሆን፣ መክበር ማለት ነው:: «ኢትህፍርዎሙኬ ለአለ ይቀትሉክሙ ሥጋክሙ ወለነፍስክሙሰ ኢይክሉ ቀቲሎታ፤ ሥጋተሁን የሚገድሉአችሁን አትፍሩአቸው ነፍሳችሁን ግን





መግደል አይቻላቸውም» ማቴ. 10÷28 ተብሎ የተነገረውን የወንጌል ቃል መሠረት በማድረግ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምነው በሰይፍ የተሰየፉ፣ በእሳት የተቃጠሉ፣ ደማቸውን ያፈሰሱ አጥንታቸውን የከሰከሱ ሰማዕታት የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክሮች ከክርስቶስ ጋር ይነግሣሉ::

ከክርስቶስ ጋር ይነግሣሉ ማለት የክርስቶስ ማደሪያዎች ይሆናሉ:: የክብሩ ወራሾች ይሆናሉ በነፍስ ሕያዋን ሆነው ሰማያዊ ጸጋን ይጐናጸፋሉ:: ክርስቶስ በሞቱ ሰይጣንን ድል እንደነሣው ሥጋን የሚገዛ ፈቃደ ሥጋን እና የጨለማ ገዦች አጋንንትን ድል ያደርጋሉ ማለት ነው:: የጸጋ አምላክነት ተሰጥቷቸው ከሞቱ በኋላ እንኳ አምላካዊ ኃይልን ያደርጋሉ:: ለአውሬው ምስል ያልሰገዱት የኢየሱስ ምስክሮች ከክርስቶስ ጋር የሚነግሡት በመንፈስ እንጂ በሥጋ አይደለም:: ከክርስቶስ ጋር መንገሥ ማለት ከጐኑ በፈሰሰው ውኃ ተጠምቆ በሥጋውና በደሙ አንድነትን ኅብረትን መሥርቶ የባሕርይ ሕይወቱን በጸጋ ወርሶ ከእርሱ ጋር መኖር ማለት ነው:: ስመክርስትና ሀብተ ወልድና ያላቸው ክርስቲያኖች ሁሉ የክርስቶስ አካላት ሕዋሳት ስለሆኑ ከክርስቶስ ጋር የጸጋ ተዋህዶ ተዋህደው ይኖራሉ እንጂ ከክርስቶስ የተገነጠሉ አይደሉም::

ስለሆነም ክርስቲያኖች በክርስቶስ ስም ከተጠሩበት ጊዜ ጀምሮ ከክርስቶስ ጋር ነግሠው ነው የሚኖሩት:: ከክርስቶስ ጋር የመንገሥ ምሥጢሩ እንዲህ ሆኖ ሳለ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ በዚህች ምድር ላይ ምድራዊ መንግሥት እንደሚመሠርትና ከክርስቶስ ጋር ነግሠው የቤተ መንግሥቱ አማካሪዎች ሆነው ከክርስቶስ በታች ያለውን የሥልጣን ደረጃ ተረክበው ሲያቀጥላቸው የኖረውን የሥልጣን ጥማት ማርካት እንደሚችሉ የሚያልሙ ሰዎች አሉ::

በዚሁ በራእየ ዮሐንስ 20÷3 ላይ ያለውንና በቁጥር 6 ላይ «የእግዚአብሔርና የክርስቶስ ካህናት ይሆናሉ ከእርሱም ጋር ይህን ሺህ ዓመት ይነግሣሉ» የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥሬ ቃል እንዳለ በመውሰድ ያለትርጓሜ በንባብ ማዕበል ተነድተው ከማይወጡበት የስሕተት ባሕር ውስጥ ሰምጠው የቀሩ አሉ::



www.ethiopianorthodox.org

ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የሚመጣው በዚህ ዓለም ሊነግሥ ሳይሆን ይህን ዓለም ሊያሳልፍ ነው፡፡ ይህ ዓለም እንኳን ክርስቶስ ሊነግሥበት የሰዎች መንግሥትና ሥልጣንም የሚያከትም በትና ወደ አለመኖር የሚለወጥበት ዓለም ነው፡፡ ክርስቶስ የሰዎችን ምድራዊ መንግሥት ሊሽርና ሊያሳልፍ እንጂ እርሱ ተረክቦ በተሻለ ሁኔታ ሊሠራበት አይመጣም፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስም የሚከተለውን መልእክት አስተላልፏል «በኋላም መንግሥቱን ለእግዚአብሔር ለአባቱ አሳልፎ በሰጠ ጊዜ አለቅነትንም ሁሉና ሥልጣንን ሁሉ ኃይልንም በሻረ ጊዜ ፍጻሜ ይሆናል» 1ኛቆሮ. 15÷24 ክርስቶስ ከመጣ በኋላ በምድር ላይ መንገሥም ማንገሥም የለም፡፡ የክርስቶስም መንግሥት በዚህ ዓለም አይደለም፡፡ ዘለዓለማዊ መንግሥት በዚህ ዓለም አይመሠረትም፡፡ ለኃላፊው ዓለም ኃላፊ የሆነው የሰዎች መንግሥት ነው የሚገባው፡፡ ጌታ በዚህ ዓለም እንደማይነግሥ እንዲህ ሲል ይገልጻል፡፡ «መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም» ዮሐ. 18÷36፡፡

ድውያንን ሲፈውስ አጋንንትን ሲያስወጣ ሙታንን ሲያስነሣ አይተው የተደነቁና ያበረከተውን ሕብስት በልተው የጠገቡ 5000 ሕዝቦችም ለማንገሥ ሙከራ ቢያደርጉ ወደ ተራራ ነው የሸሸው፡፡ በወንጌል እንዲህ ተብሎ እንደተጻፈ «በዚህም ምክንያት ኢየሱስ ያነግሡት ዘንድ ሲመጡ ሊነጥቁት እንዳላቸው አውቆ ደግሞ ወደተራራ ብቻውን ፈቀቅ አለ» ዮሐ. 6÷15 እነዚህ ሰዎች ክርስቶስን ለማንገሥ የሞከሩት የተደረገላቸው የእንጀራ በረከት በበለጠ ሁኔታ እንዲቀጥል ስለፈለጉ ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰማያዊ እንጀራን ሊመግባቸው መጥቶ ሳለ የምድራዊው እንጀራ ጣዕም ትዝታ ስለማረካቸው በዚህች ምድር ነግሦ በምድራዊው እንጀራ ሆዳቸውን ይመላ ዘንድ እናንግሥህ አሉት፡፡

ሆኖም ኢየሱስ ክርስቶስ በሰዎች ልቡና ጽድቅን ሊመላ እንጂ እንጀራን ሊመላ ስላልመጣ ሐሳባቸውን አልተቀበለውም፡፡ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያትም መካከል ዮሐንስና ወንድሙ ያዕቆብ ክርስቶስ በዚህ ዓለም የሚነግሥ መስሎአቸው በቀኙና በግራው ያስቀምጣቸው ዘንድ የልመና ጥያቄ አቅርበው እንደነበር የሚከተለው የወንጌል ቃል ያስረዳናል «እነርሱም በክብርህ ጊዜ





አንዳችን በቀኝህ አንዳችንም በግራህ መቀመጥን ስጠን አሉት» ማር.10÷37 ፍሬ ሐሳቡን ለመገንዘብ ከቁጥር 35-45 ያንብቡ፡፡ ፍቅረ መንግሥትን በልባቸው ጸንሰው ያቀረቡትን ዮሐንስንና ያዕቆብን ሲገስጻቸው እንጂ ሲያመሰግናቸው አልተሰማም፡፡ ኃላፊውንና ምድራዊውን መንግሥት መመኘታቸው በኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ አላዋቂነት ነበር፡፡

ስለሆነም በዮሐንስና በያዕቆብ ልብ ውስጥ ተጸንሶ የነበረውን ፍቅረ መንግሥት በበትረ መዓት መትቶ እንዲጨነግፍ አድርጎታል፡፡ ከክርስቶስ ጋር በዚህ ዓለም መንገሥ የፈለጉት ዮሐንስና ያዕቆብ የምትለምኑትን አታውቁም ተብለዋል፡፡ ዛሬም ከክርስቶስ ጋር በዚህ ዓለም መንገሥ የሚፈልጉ ሰዎች የሚፈልጉትን የማያውቁ ሰዎች መሆናቸው ግልጽ ነው፡፡ ክርስቶስ ወደ ምድር የመጣው የሰው ልጅ በምድር ላይ እንዳይቀር ነው፡፡ እርሱ ከምድራዊ መንግሥት የበለጠ ሰማያዊ መንግሥት ሊያወርሰን ተዘጋጅቶ እያለ እንደፍልፈል በመሬት ውስጥ መንገሥን መፈለግ የለብንም፡፡

## «የፊተኛው ትንሣኤ»

«የቀሩቱ ሙታን ግን ይህ ሺህ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ በሕይወት አልኖሩም ይህ የፊተኛው ትንሣኤ ነው» ራእይ 20÷5 የዚህ ንባብ ትርጉም ያልገባቸው ሰዎች የጻድቃንና የኃጥአንን ትንሣኤ እንደሚለያይ አድርገው ያስባሉ፡፡ ጻድቃን ቀድመው ተነስተው በዚህ ዓለም ከክርስቶስ ጋር ሺህ ዓመት እንደሚነግሡና ኃጢአተኞች ግን ያን ሺህ ዓመት በመቃብር ውስጥ እንደሚያሳልፉ ሺሁ ዓመት እስኪፈጸምም ድረስ እንደማይነሡ አድርገው የመሰላቸውን ያትታሉ፡፡

የአመለካከታቸውና የግንዛቤአቸው ውጤት የጻድቃንና የኃጥዓንን የትንሣኤያቸውን አንድነት ገመድ የሚበጥስ ስለት ነው፡፡ ትንሣኤን የጻድቃን የግል ሽልማታቸው አድርገው ያስባሉ፡፡ እንዲህ ዓይነት ግንዛቤ ያላቸው ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ያለትርጓሜ እንረዳለን የሚሉ ናቸው፡፡ እያንዳንዱን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል መሆኑን እንጂ ምን ለማለት



www.ethiopianorthodox.org

እንደተፈለገ አያስተውሉትም:: «የቀሩቱ ሙታን ግን ይህ ሺህ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ በሕይወት አልኖሩም ይህ የፊተኛው ትንሣኤ ነው» የሚለውን ንባብ ቃል በቃል ስለወሰዱት ንባቡም ሰፊ ወደሆነ የስሕተት ከተማ ወስዷቸዋል::

ጻድቃን ከኃጢአተኞች ቀድመው ይነሣሉ የሚለውን ሐሳብ ለመደገፍ ምርኩዝ የሚሆን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ አይገኝም:: ጻድቃን ከተነሡ በኋላ ኃጢአተኞች ሺህ ዓመት ቆይተው ትንሣኤ ሥጋ ይነሣሉ የሚል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጽሑፍ አልተጻፈም:: በማቴ. 25÷31-33 የተጻፈው ጻድቃንና ኃጥአን በአንድ ቀን እንደሚነሡ ያመላክታል:: እንዲህም ይላል «አሕዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ እረኛም በጐችን ከፍየሎች እንደሚለይ እርስ በርሳቸው ይለያቸዋል:: በጐችን በቀኙ ፍየሎችንም በግራው ያቆማቸዋል» በበጐች የተመሰሉት ጻድቃንና በፍየሎች የተመሰሉት ኃጥአን በክርስቶስ ቀኝና ግራ መቆም የሚችሉት ትንሣኤያቸው አንድ ቀን/ጊዜ/ ቢሆን ነው:: የሺህ ዓመት ልዩነት ካለማ እንዴት በቀኝና በግራው ያቆማቸዋል ይባላል? ወይስ ጻድቃን ቀድመው ተነሥተው በክርስቶስ ቀኝ ሺህ ዓመት ቆመው ኃጥአን እስኪነሡ ድረስ ይጠብቃሉ ሊባል ይሆን?

እረኛ በጐችን ከፍየሎች እንደሚለይ እርስ በእርሳቸው ይለያቸዋል ይላል:: እረኛ በጐችን ከፍየሎች መለየት የሚችለው በጐች ከፍየሎች ጋር በአንድ ቦታ ተቀላቅለው ተደባልቀው ሲገኙ ነው:: ቦታውን በጐች ብቻ ከያዙት ግን ለያቸው የሚለው ኃይለ ቃል አይነገርም:: በጐችና ፍየሎች በአንድ ቦታ ተሰማርተው ካሉ ግን በጐችን ከፍየሎች ለይቶ ፍየሎችንም ከበጐች ለይቶ ወደየማደሪያቸው ይወስዳቸዋል::

በጐችን ከፍየሎች በሚለይ እረኛ አንጻር የተገለጸው ጌታም ጻድቃንን ከኃጥአን ለይቶ በቀኙ ኃጥአንን ከጻድቃን ለይቶ በግራው የሚያቆማቸው ጻድቃንና ኃጥአን በአንድ ቀን በአንድ ሰዓት በአንድ ቅጽበት ስለሚነሡ ነው:: ጻድቃን ከኃጥአን ሺህ ዓመት ቀድመው ይነሣሉ ከተባለ ግን እርስ በርሳቸው ይለያቸዋል የሚለው የወንጌል ቃል ትርጓሜ ያጣል::

መጽሐፍ ቅዱስ የሚተረጎመው ወንጌሉን ከራእዩ ራእዩንም ከወንጌሉ ጋር በማስማማት በማዋሐድና በማጣጣም እንዳይለያይ በመጠንቀቅ ነው:: መጻሐፍት የተለያዩ አይደሉም::





እንኳን ሐዲሳት እርስ በርሳቸው ሐዲሳትና ብሉያትም አይለያዩም አንድ ክርስቶስን ነው የሚሰብኩት:: የሰዎች ግንዛቤ ግን ልዩ ልዩ ስለሆነ ልዩ ልዩ ትርጉም እየሰጠ ይበታትናቸዋል:: የሙታንንም ትንሣኤ የሚለያዩ ሰዎች የፊተኛው ትንሣኤ በሚለው ንባብ ተታልለው በተለያዩ መላምቶችና ግምቶች የመጽሐፍ ቅዱስን ምሥጢር ሲጋርዱት እናያለን::

በቃሉ የተሰናከሉ ሰዎች ትንሣኤ ሲባል ከመቃብር መውጣት ብቻ መስሎአቸው ይደናገራሉ:: ትንሣኤ ማለት መነሣት ቢሆንም የመነሣት ብዙ ትርጉሞች አሉት:: ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች እንመልከት፤

1ኛ. ከሙታን መነሣት ማቴ. 28÷7፤ 22÷23

2ኛ. ዓይንን ወደላይ ማንሣት ዮሐ. 11÷41

3ኛ. በጠላትነት መነሣት ወይም ማስነሣት ፊሳ. 13÷17

4ኛ. መንገድ ለመሄድ መነሣት ዮናስ 1÷3

5ኛ. ለመርዳት ወይም ለማዳን መነሣት መዝ. 43÷26

6ኛ. በእምነት ከክርስቶስ ጋር መነሣት ቆላ. 3÷1

ለአብነት ያህል እነዚህ ቢጠቀሱም ሌሎች ያልተጠቀሱ የትንሣኤ ትርጉሞች ይኖራሉ:: ስለዚህ መነሣት ወይም ማስነሣት የሚል ንባብ ስናገኝ ስለሙታን መነሣት ብቻ የተነገረ ሊመስለን አይገባም:: ትንሣኤ ብዙ ትርጉሞች እንዳሉት ከተረዳን የፊተኛው ትንሣኤ የተባለው ትንሣኤሙታን /የሙታን መነሣት/ ወይም ከመቃብር ውስጥ መውጣት እንዳልሆነ እናስተውል:: ፊተኛው ትንሣኤ ከመቃብር ውስጥ መውጣትን ፈጽሞ አያመለክትም:: የፊተኛው ትንሣኤ የተባለው ትንሣኤ ልቡና ነው::

ትንሣኤ ልቡናም ማለት ለእምነት የልብ መነሣት የሐሳብ መነሣሣት፣ ከደነደነ ልብ አልጋ /መኝታ/ መነሣት ማለት ነው:: ወይም ከክርስቶስ ጋር በእምነት መነሣት ማለት ነው:: ይህም ክርስቶስን በእምነት ለመቀበል የተደረገ የውስጥ ተነሣሽነት ነው:: ከተያዙበት የክህደትና የኃጢአት እንቅልፍ መንቃት ማለት ነው:: «ከእንቅልፍ የምትነሡበት ሰዓት አሁን እንደደረሰ ዘመኑን ዕወቁ» ሮሜ.13÷11፣ 1ኛተሰ.5÷6 ምንጊዜም የትንሣኤ ትርጉም ሕይወት ነው:: ሞትን ድል ማድረግ ነው::



www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህ በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው ከድንቁርና ወደ ዕውቀት ከጨለማ ወደ ብርሃን ከሞት ወደ ሕይወት የተሸጋገሩት ሁሉ ከተወረወሩበት የስሕተት ገደል በኢየሱስ ክርስቶስ መሰላልነት ወጥተው ወደ ሕይወት አፋፍ ብቅ ስላሉ ፊተኛውን ትንሣኤ ተነሡ ይባላል:: «የቀሩቱ ሙታን ግን ይህ ሺህ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ በሕይወት አልኖሩም» ይላል:: የቀሩቱ ሙታን የተባሉትም በክህደት የቀሩ ሙታነ ልቡና ናቸው እንጂ ሙታነ ሥጋ አይደሉም:: ሙታነ ልቡናም ማለት ክርስቶስን ለመቀበል የውስጥ ተነሳሽነት የሌላቸው ነፍስ እንደተለየችው በድን ለእምነት የማይንቀሳቀሱ ንስሐ ለመግባት ከኃጢአት እንቅልፍ የማይነቁ ማለት ነው::

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ከማመን የዘገዩትን የወንጌሉን ቃል ያልተቀበሉትን ሙታን ብሏቸዋል:: «ከደቀመ ዛሙርቱም ሌላው ጌታ ሆይ አስቀድሜ ልሂድና አባቴን እቀ ብር ዘንድ ፍቀድልኝ አለው:: ኢየሱስ ተከተለኝ ሙታናቸውንም እንዲቀብሩ ሙታንን ተዋቸው አለው» ማቴ. 8÷21-22፤ ሉቃ. 9÷59-60 ጌታ የደቀመዝሙሩን ዘመዶች ሙታን ያላቸው በሥጋ ስለሞቱ አይደለም:: በሥጋ ሙተው ቢሆንማ ኖሮ ለእነ ማርታ እንደአደረገ አብሮ ሄዶ ያስተዛዝነው ነበር:: ወይም ሙታኑን እንደአልዓዛር ያስነሳቸው ነበር:: «ሙታናቸውን እንዲቀብሩ ሙታንን ተዋቸው» የሚለው ቃልም ሙታነ ሥጋ አለመሆናቸውን ያስረዳል:: ምክንያቱም ሙታነ ሥጋ ሙታነ ሥጋን አጥበው ገንዘው መቃብር ቆፍረው ሊቀብሯቸው አይች ሉም:: ስለዚህ የደቀመዝሙሩ ዘመዶች ሙታነ ልቡና /ሙ[illegible] ሕሊና ናቸው/ ወንጌል እየተሰበከ ተአምር እየተደረገ ወደ እምነት የማይሳቡ የደነዘዙ ስለሆኑ ሙታነ ሕሊና ተብለዋል::

በዚሁ ምዕራፍ ማለትም በራእይ 20÷6 ላይ «በፊተኛው ትንሣኤ ዕድል ያለው ብፁዕና ቅዱስ ነው:: ሁለተኛው ሞት በእነርሱ ላይ ሥልጣን የለውም:: ዳሩ ግን የእግዚአብሔርና የክርስቶስ ካህናት ይሆናሉ» ይላል:: ሁለተኛው ሞት ሥልጣን የማይኖረው በእነማን ላይ እንደሆነ ልብ እንበል:: አንደኛው ሞት የሥጋ ከነፍስ መለየት ስለሆነ ጻድቁም ኃጢአተኛውም ይሞታል:: ሁለተኛው ሞት ግን የኃጢአተኞች የከሃዲዎች የግል ሀብታቸው ነው::





በኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑ ከኃጢአት የተለዩ ንስሃ የገቡ ከጐኑ በፈሰሰው ውኃ ታጥበው የነጹና በደሙ የተቀደሱ ምእ መናን ለሁለተኛው ሞት አይገዙም:: ከሁለተኛው ሞት ማምለጥ የሚችሉት በሃይማኖትና በጽድቅ ሜዳ ላይ ወደፊት የሮጡ ብቻ ናቸው::

የፊተኛው ትንሣኤ ዕድል የሌላቸውን ማለትም ያላመኑ ትንና ንስሀ ያልገቡትን ግን ሁለተኛው ሞት ከተሰወሩበት ጓዳ ገብቶ እንደወፍ ጫጩት እያነጠቀ ይወስዳቸዋል:: «ዳሩ ግን የሚፈሩና የማያምኑ የርኩሳንም፣ የነፍስ ገዳዮችም፣ የሴሰኞዎችም፣ የአስማተኛዎችም፣ ጣዖትንም የሚያመልኩ፣ የሐሰተኛዎችም ሁሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ነው:: ይኸ ውም ሁለተኛ ሞት ነው» ራእይ 21÷8

አንባቢ ሆይ በሁለተኛው ሞት ሥልጣን የ[illegible]ረገጡ እነ ማን እንደሆኑ ተረዳህን? እምነትም ጽድቅም የሌላቸው ጥልቅ በሆነ የኃጢአት ጉድጓድ ተዳፍነው የተገኙት ናቸው:: የፊተኛው ትንሣኤ ዕድል ተሳታፊዎች በሆኑት ምእመናን ላይ ግን ሁለተ ኛው ሞት ሥልጣን የለውም ተብሏል:: ይህ ፊተኛ ትንሣኤ የተባለው ታዲያ ምን ይመስልሃል? መንግሥተ ሰማያት ቀርባ ለችና እመኑ ንስሃ ግቡ:: ማቴ. 4÷17 ተብሎ በተሰበከው መሠ ረት በእምነትና በንስሃ ከወደቁበት የኃጢአት መሬት መነሣት አይደለምን?



www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ ሁለት

## ሐሳዌ መሲሕ

## የሐሳዌ መሲሕ ሐረገ ትውልድና ነቢያተ ሐሰት

ሐሳዊ መሲሕ ከዚህ በፊት የነበረ በታሪክ የሚወሳ ወይም አሁን በዚህ ዘመን ያለ ሳይሆን ገና ወደፊት ይመጣል ተብሎ የሚጠበቅ ክርስቶስ ሳይሆን በክርስቶስ ስም የሚመጣ ሐሰተኛ ክርስቶስ ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በትንቢ ታዊ ታሪክ እንዳስቀመጡት ሐሳዌ መሲሕ በእናቱ ከነገደ ዳን የሚወለድ ሲሆን በአባቱ ከነገደ ኤሳው ይወለዳል፡፡ የእናቱ ነገድ መነሻ የሆነው ዳን ከአሥራ ሁለቱ የያዕቆብ ልጆች አንዱ መሆኑ በዘፍ. 30÷6 ላይ ተጠቅሷል፡፡

የአባቱ ነገድ መነሻ የሆነው ኤሳውም የይስሃቅ ልጅ የያዕቆብ ወንድም መሆኑ በዘፍ. 25÷19-30 ተገልጿል፡፡ በሐረገ ትውልድ ከነገደ ዳን የሆነችውን ከዳን ወገን ሥር የበቀለችውን የሐሳዌ መሲሕን እናት ነቢያተ-ሐሰት /የሐሰት ነቢያት/ በድን ግልና ጸንሰሽ በድንግልና ትወልጃለሽ በማለት የሐሰት ቀሚስ እንደሚያለብሷት መምህራነ ቤተ ክርስቲያን ይናገራሉ፡፡

ነቢያተ - ሐሰትም ማለት ሐሰትን የሚተነብዩ መንፈስ ርኩስ አድሮባቸው ሳለ መንፈስ ቅዱስ አድሮብናል በማለት መንፈስ ርኩስ ያስገሳቸውን ክፉ ነገር የመንፈስ ቅዱስ የሚያስ መስሉ የዲያብሎስ መንግሥት ሰባኪዎች ናቸው፡፡ ነቢያተ-ሐሰት የነቢያተ-ጽድቅ ተቃራኒዎች ተቃዋሚዎች ስለሆኑ ከዚህም ( ፊ ት በዘመነ ነቢያተ-ጽድቅ /በእውነተኞች ነቢያት ዘመን/ የነቢያ ነት ብቃት ሳይኖራቸው ነገሥታቱን ጥግ በማድረግ ከነቢያት ጋር ሲወዳደሩና የነቢያትን እውነት ሲቃወሙ እንደነበሩ በመጻሕፍተ-ነቢያት ተገልጿል፡፡

አሜስያስ የተባለው ነቢየ-ሐሰት ነቢየ ጽድቅ አሞጽን እንደተቃወመው፡፡ አሞ. 7÷10-13 ኤርምያስ እስ ·ኤል ሕገ እግዚአብሔርን ባይጠብቁና ከኃጢአታቸው ባይመለሱ ወደባቢ ሎን እንደሚማረኩ በሚተነብይበት ጊዜ ነቢያተ-ሐሰት ሰላም ሰላም መማረክ የለም በማለት ከኃጢአተኞች ነገሥታት ጉን





ቆመው ኃጢአተኞችን እያበረታቱ ኤርምያስን እንደተቃወሙት፡፡ ኤር 23÷9-32

ከገዛ ልባቸው ተነሥተው የራሳቸውን ሐሳብ የሚናገሩትን ሐሰተኞች ነቢያትን እግዚአብሔር በሕዝቅኤል አድሮ ሰነፎች ነቢያት በማለት እንደወቀሳቸው፡፡ ሕዝ. 13÷2-15 ተጽፎ እናገኛለን፡፡

ሐሰተኛው መንፈስ ራሱ በነቢያት ሁሉ አፍ ሐሰተኛ መንፈስ እሆናለሁ ብሎ እንደመሰከረ 1ነገ. 22÷19-23

ሐሰተኞች ነቢያት በዘመነ ብሉይ የእስራኤልን ነገሥታት ለማስደሰት ጥሩ ሕልም ዓለምን መልካም ራእይ አየን ከማለት ጋር ለነገሥታቱ እንደሚስማማቸው እድሜያቸው እንደሚረዝምና ጠላቶቻቸውን ድል እንደሚነሡ ይተነብዩላቸው ነበር፡፡ ነገሥታቱን ክፉ ነገር እንደማይገጥማቸው ጣዖት በማምለካቸውና በሌላውም ኃጢአታቸው እግዚአብሔር ተለይቷቸው ሳለ አብሮአቸው እንደአለ እንደሚረዳቸውም በመተንበይ የሐሰት ተስፋን የተመሉ ትንቢቶችን በማንጋጋት ያታልሏቸው ነበር፡፡ ነገሥታቱ ንስሐ እንዳይገቡ፣ ጣዖታቸውን እንዳይተው፣ ከኃጢአታቸው እንዳይመለሱ፣ የእግዚአብሔር የይቅርታ በር እንዳይከፈትላቸው ማድረጋቸውን በተጠቀሱት ጥቀሶች ተመልክተናል፡፡

ክፉ መንፈስ እስከአሁን ያየናቸውን ሐሰተኞች ነቢያትን እንደወለደ መውለዱን በነሱ የደመደመና የመከነ አይደለም፡፡ በዘመነ ሐዲስም ብዙ ዲቃሎችን እንደሚደቅል ዲቃሎችም እንደዶሮ ጫጩት እንደሚፈለፈሉ በሚከተሉት ጥቅሶች ተገልጿል፡፡ ማቴ. 7÷15-19፣ 2ኛጴጥ. 2÷1፣ 1ኛዮሐ. 4÷1፣ ማቴ. 24÷24 በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አንደበትና በሐዋርያቱ አንደበት የተነገረው ትንቢታዊ ቃል ሳይፈጸም አይቀርምና ሐሰተኞች ነቢያት እንደክረምት አግቢ ምድርን ይወሯታል፡፡ ዛሬም ቢሆን በውዳሴ ከንቱ ተጠልፈው ራእይ አየን ሕልም ዓለምን እንዲህ እንዲህ ይሆናል የሚሉ ባለሕልሞች አይጠፉም፡፡



www.ethiopianorthodox.org

# ሐሰተኞች ነቢያት ሐሰታዊ ትንቢትን ለመናገር የሚነሣሡባቸው ምክንያቶች

1ኛ. በኅብረተሰቡ ዘንድ ትንቢት ተናጋሪዎች ናቸው፣ እግዚአብሔር የመረጣቸው፣ የወደዳቸው፣ ምሥጢሩን የገለጸላቸው፣ ደጋግ አባቶች ናቸው ተብለው መደነቅን መከበርን የሚወዱ የውዳሴ ከንቱ ሱስ ያሰከራቸው ግብዞች ስለሆኑ፤

2ኛ. እውነተኞች ነቢያት በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ወደፊት የሚገለጠውን መልካም ነገር ወይም ክፉ ነገር ሲናገሩ ሰምተው ማን ከማን አንሶ ማን ከማን ሰንፎ በማለት መጥፎ እልህ ልባቸውን ስለሚያጠፋቸው፣ ራሳቸውን ከፍ የማድረግ የትዕቢት ስሜት ውስጣቸውን ስለሚያቃጥላቸው፣ ከቅዱሳን ነቢያት ጋር የመወዳደር የመፎካከር እነርሱንም የመምሰል ግፊት ውስጣቸውን ፈንቅሎ ስለሚያወጣባቸው ኤር. 20÷1-6፤

3ኛ. በጊዜያቸው ያለውን የሀገር መሪ ደስ ለማሰኘት ለሀገር መሪው ጥሩ ጥሩ ትንቢቶችን በመተንበይ ተቃዋሚ እንደማይነሣበትና እርሱ ካለፈ በኋላ ልጆቹ የልጅ ልጆቹ እንደሚገዙ ተስፋን በማጐናጸፍ መወደድን መከበርን ለማትረፍ፤ አሞ. 7÷10-13

4ኛ. ክፉ መንፈስ ሐሰተኞች ነቢያት የሐሰት ምርት ማምረቻ ፋብሪካ ስለሚያደርጋቸው የክፉ መንፈስ ዕቃዎች እንደመሆናቸው የክፉውን መንፈስ ሐሳብ ስለሚሸከሙ ነው:: የአንድ ነጋዴ አህያ ነጋዴው የጫናትን ሸቀጣ ሸቀጥ ተሸክማ በነጋዴው እየተነዳች ከታሰበበተ ቦታ እንደምታደርስ ሁሉ ሐሰተኞች ነቢያትም የራሳቸውን ሳይሆን ዲያብሎስ የጫናቸውን የሐሰት ወሬ ተሸክመው በዲያብሎስ እየተነዱ ወደ ሕዝብ ጆሮ ስለሚያደርሱ፤ 1ኛነገ. 22÷19-25::

የዲያብሎስ አህዮች ሐሰተኞች ነቢያት የከበዳቸውን ጭነት ወይም ሸክም በሐሳዌ መሲሕ እናት ላይ ሳይጥሉት እንደማይቀሩ ይነገራል:: ከነገደ ዳን /ከዳን ወገን/ የተወለደች ያች ርግምት ሴት ነቢያተ ሐሰት የቀባጠሩትን በመቀበል ከሙታን መቃብር ቆማ ስትጸልይ ከነገደ ኤሳው /ከኤሳው ወገን/ የተወለደ አንድ ዓይና ጐልማሳ /ጐረምሳ/ ፀዋሬ አበሳ





ከክብር ያሳንሳታል፣ ይደርስባታል ሐሳዌ መሲሕ ይጸነሳል:: ያች የሰይጣን ገረድ ሐሳዌ መሲሕን ጸንሳ ስትወልድ በድንግልና ጸንሼ በድንግልና ወለድኩት በማለት አስቀድማ በሐሰተኞች ነቢያት እጅ ጐርሳ የዋጠችውን የሰይጣን ሐሳብ በአንደበቷ ትተፋዋለች:: ትርጓሜ ራእይ 13÷1

ከአንድ ዓይናው ጐልማሳ /ጐረምሳ/ ጋር ያሳለፈችው ጊዜ እየመጣ ከፊቷ ድቅን ቢልም አላውቅሁም ብላ ትክደዋለች:: ሕልም ለማስመሰልም ትሞክራለች:: የመራራ ዛፍ ፍሬ መራራ መሆኑ አይቀሬ ነውና ሐሳዌ መሲሕም ተወልዶ ካደገ በኋላ የእናቱን ሐሰት በትውፊት ተቀብሎ በድንግልና ተጸንሼ በድንግልና የተወለድኩ አምላክ ነኝ ይላል:: «ከእሾህ ወይንን ከኩርንችትም በለስን መልቀም» እንደማይቻል ማቴ. 7÷16 በሐሳዌ መሲሕም አንደበት እውነት ሊነገር አይችልም::

«የሐሰት አባት» የተባለው ዲያብሎስ በነቢያቱ አንደበትና በዚያች ርግምት ሴት አንደበት የዘራውን ሐሰት ከሐሳዌ መሲሕ አንደበት ያጭዳል:: ከእስራቱ የሚፈታበት ዘመን ስለሚሆን ከመታሠሩ በፊት ይሠራው የነበረውን ሥራ ለመሥራት በትጋት ይንቀሳቀሳል:: ሥራውም በአዳምና በሔዋን የጀመረው አምላክ የመሆን ምኞትን በሰዎች ልቡና መዝራት ሲሆን ክርስቶስ ካሰረው ወዲህ ተቋርጦ ይኖር ነበር:: በሐሳዌ መሲሕ ዘመን ከእስራቱ ተፈቶ ያቋረጠውን ሥራ ይጀምራል::

## የሐሳዌ መሲሕ የስሙ ትርጉም

ሐሳዌ መሲሕ የሚለው ቃል የሁለት የተለያዩ የግዕዝ ቃላት ጥምር ነው:: አንደኛው የግዕዝ ቃል ሐሳዊ ሁለተኛውም መሲሕ በመባል ይታወቃሉ::

1ኛ. ሐሳዊ:- ሐሳዊ ሐሰወ - ዋሸ ከሚለው የግዕዝ ግሥ የወጣ /የተገኘ/ ለውሸታም ሰው የሚቀጸል ወይም የውሸታም ሰው መጠሪያ ቃል ነው:: ትርጉሙም ሐሳዊ ማለት የሚዋሽ፣ ዋሾ፣ ውሸተኛ፣ ሐሰተኛ፣ ከሐዲ፣ ሸፋጭ፣ ነገር ለዋዋጭ፣ አሉ የሚልና የሚያብል ማለት ነው::



www.ethiopianorthodox.org

2ኛ. መሲሕ:- መሲሕ መሰሐ - ቀባ ከሚለው የግዕዝ ግሥ የተገኘ /የወጣ/ ሲሆን መሲሕ ማለት የተቀባ፣ ቅቡዕ፣ የተሾመ ወይም የነገሠ ማለት ነው:: መሲሕም የተባለ ክርስቶስ ነው:: ቅድመ ዓለም ንጉሥ ቢሆንም በሰውነቱ ተቀባ፣ ከበረ፣ ተሾመ፣ ነገሠ ይባላል::

የእያንዳንዳቸውን የሐሳዊንና የመሲሕን ትርጉም ከብዙ በጥቂቱ ከገለጽን በተገናኝ ሐሳዌ-መሲሕ ወደሚለው ትርጉም እንምጣ:: ሐሳዌ መሲሕ ማለት ክርስቶስን የሚያብል፣ የሚዋሽ፣ በክርስቶስ ላይ ሐሰትን የሚናገር፣ የመሲሕ ክርስቶስን ስም በሐሰት የወረሰ ማለት ነው:: ሳይናበብ ሐሳዊ መሲሕ ካለም ሐሰተኛው መሲሕ፣ ሐሰተኛው ክርስቶስ ተብሎ ይተረጐማል::

## የእናቱ ስም ትርጉም

ክርስቶስን ሳይሆን በሐሰት ክርስቶስን ለመሆን የከጀለው ያ ርጉም ፍጡር ሐሳዌ መሲሕ ከተባለ በስሕተት በዝሙት ከአንድ ዓይና ጐልማሳ /ጐረምሳ/ ደቅላ በድንግልና ጸንሼ በድንግልና ወለድኩህ የምትለው ርግምት እናቱም የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን ታሪክ ለመውረስ ስለተነሣች ሐሳዊተ-ድንግል ማርያም ትባላለች::

ሲተረጐምም:- ድንግል ማርያምን የዋሸች፣ በድንግል ማርያም ላይ በሐሰት የተነሣች፣ ብቸኛ የሆነውን የድንግል ማርያምን ቅጽል ስም ለመጋራት የከጀለች ወይም የሞከረች፣ የድንግል ማርያምን ስም ለመውረስ ሐሰትን ታጥቃ የተነሣች ማለት ነው:: ሳይናበብ ሐሳዊት ማርያም ካለም ሐሰተኛይቱ ማርያም ማለት ነው::

በድንግልና ተጸንሶ በድንግልና የተወለደ ከክርስቶስ በፊት አልነበረም:: ከክርስቶስ በኋላም ድንቅ በሆነ በዚህ ተግባር ያለፈ የለም:: ለወደፊትም አይኖርም:: ክርስቶስ አምላክ መሆኑንና ከፍጡራን የተለየ መሆኑን የገለጸበት ድንቅ ሥራ ነው::

በድንግልና ጸንሳ በድንግልና የወለደች ሴትም ከእመቤታችን ከድንግል ማርያም በፊት አልነበረችም:: ከድንግል





ማርያም በኋላም የድንግል ማርያምን ታሪክ የደገመች ሴት የለችም:: ወይም አልተነሣችም:: ለወደፊትም አትኖርም:: በኀቱም ድንግል ጸንሶ በኀቱም ድንግልና መውለድ ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም ብቻ የተሰጠ ልዩ ጸጋ ነው:: «ቡርክት አንቲ እምአንስት፤ ከሴቶች ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ» የተባለችበት ልዩ ድንቅ ነገር ነው:: ከሴቶች ተለይተሽ ሲል እመቤታችን ልዩ የሆነችው በጊዜዋ ከነበሩ ሴቶች ብቻ አይደለም:: ከእርሷ በፊት ከነበሩት በእርሷ ጊዜም ከነበሩት ከእርሷም በኋላ ከሚኖሩት ከሔዋን ጀምሮ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከሚነሡት ሴቶች ሁሉ የተለየች ናት እንጂ::

ክርስቶስ አንድ ብቸኛ አምላክ በመሆኑ ሌላ ሁለተኛ ክርስቶስም ባለመኖሩ እኔ ክርስቶስ ነኝ የሚል ሁሉ የክርስቶስ ተቀናቃኝ፣ ተቃዋሚ ጠላት እንደሆነ ሁሉ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም እናትነት ከድንግልና ድንግልና ከእናትነት ሁለት ተቃራኒ ነገሮችን አስማምታ አስተባብራ ይዛ የተገኘች ብቸኛ ድንግል ወእም ስለሆነች በድንግልና ጸንሼ በድንግልና ወለድሁ የምትል ሴት ሁሉ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ተቀናቃኝ፣ ተቃዋሚት፣ ተቃራኒት ወይም ክፉ ጠላት መሆንዋ ነው::

## ስለሐሳዌ መሲሕ መምጣት የቅዱስ ጳውሎስ ትንቢታዊ ቃል

ሐዋርያው ጳውሎስ የራቀውን አቅርቦ የረቀቀውን አጉልቶ የተሰወረውን ገላልጦ በሚያሳይ ከመንፈስ ቅዱስ በተሰጠው መጻእያትን የማወቅ ጸጋ የሐሳዌ መሲሕን መምጣት ተመልክቶ የተሰሎንቄን ሰዎች ያስጠነቅቃል:: ለቅዱሳን ከተሰጡ ጸጋዎች አንዱ ለወደፊት የሚከሰቱ ነገሮችን እንደሚከሰቱ አውቆ መናገር ነው:: ቅዱስ ጳውሎስም ይህ ጸጋ በስፋት የተለገሠው ሐዋርያ እንደመሆኑ ሐሳዌ መሲሕ ወደዓለም ሲመጣ ከነንዙ ተመለከተው::

ሆኖም ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ምስጢር ለራሱ አውቆ ሰውሮ ደብቆ ቢያስቀረው መክሊትን መቅበር ነውና መክሊትን



www.ethiopianorthodox.org

መቅበርም አንተ ሰነፍ ባሪያ አሰኝቶ የሚያስወቅስ ስለሆነ ከማስወቀስም አልፎ የሚያስቀጣ በመሆኑ ለተሰሎንቄ ሰዎች ሊገልጠው ወደደ:: መገለጥ የሚገባው ምሥጢር ነው:: መነገር የሚገባው ትንቢት ነው::

ምክንያቱም ይህ ምሥጢር ባይገለጥ ትንቢቱም ባይነገር ሐሳዌ መሲሕ ክርስቶስ ነኝ ብሎ የሐሰት መርዝን የተመላ ጽዋውን ለአይሁድ በአደላቸው ጊዜ ምእመናን ተቀብለው ተጐንጭተውት ዘላለማዊውን ሞት በሞቱ ነበርና:: መርዝ፥መርዝ መሆኑ ከታወቀ የሚቀምሰው የለም:: ቅዱስ ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች መርዝነቱን ገለጠ:: «ነገር ግን ወንድሞች ሆይ ስለ ጌታችን ስለኢየሱስ ክርስቶስ መምጣትና ወደእርሱ ስለመሰብሰባችን በመንፈስ ወይም በቃል ወይም ከእኛ እንደሚመጣ በመልእክት የጌታ ቀን ደርሶአል ብላችሁ ከአእምሮአችሁ ቶሎ እንዳትናወጡ እንዳትደነግጡም እንለምናችኋለን» 2ኛተሰ. 2÷1-3

ሐዋርያው የዳግም ምጽአትን ነገር የትንሣኤ ሙታንን ነገር ሲያስተምር የሐዋርያውን ትምህርት በደንብ ያልተረዱ የተሰሎንቄ ሰዎች እነሱ ባሉበት ዘመን ዳግም ምጽአት የሚደረግ መስሎአቸው ይደነግጡና ይጨነቁ ነበር:: መቸም ሰው ሆኖ ስለዳግም ምጽአት ሲነገር የማይደነግጥ የማይርበተበት የለም:: ምክንያቱም በዳግም ምጽአት ብዙ ሰውን የሚያስጨንቁ ነገሮች ስለሚከሰቱ ነው:: የሚከሰቱትም ነገሮች:-

1ኛ. የሰማይና የምድር ንጉሥ በሆነው በማያዳላውና እውነት በሚፈርደው በክርስቶስ ፊት መቆም:: ማቴ. 25÷32
2ኛ. እያንዳንዱ ሰው የሠራው ሥራ መልካምም ሆነ መጥፎ በፈጣሪ ፊት መገለጥ ማቴ. 25÷12፣ ራእይ 20÷12
3ኛ. እጅንና እግርን ታስሮ ለቅሶና ጥርስ ማፏጨት ወዳለበት ጨለማ መጣል ማቴ. 22÷13
4ኛ. የሕይወት ባለቤት ከሆነው ከፈጣሪ ተለይቶ ወደ ገሃነም መውረድና ወደ እሳት ባሕር መጣል ራእይ 20÷15 ከዚህም ጋር በዓለም ላይ ያለ ሰው ኅልፈተ ዓለም ኅልቀተ ዓለም ደረሰ ቀረበ ሲባል ከገደል አፋፍ የቆመ ያህል ይደነግጣል:: የሚይዘውን ያጣል::





ዛሬም አንዳንድ አባቶችና እናቶች ትንቢት እንናገራለን እያሉ ሕዝብን የሚያሸብሩ ወሮበላዎች በሚናገሩት ነገር ሲደነግጡ ይታያሉ:: ምጽአት በዚህ ሳምንት በዚህ ወር ይደረጋል:: ከንንብረትህ/ሽ/ ከነገንዘብህ/ሽ/ ለጥፋት ቀርበሃል/ሻል/ ሲሉአቸው ከፍርሐታቸውና ከድንጋጤያቸው የተነሣ ገንዘባቸውን ለአታላዮች ሰጥተው ምጽአት በተነገራቸው ሳምንትና ወር ሳይደረግ ቀርቶ ከነቤተሰቦቻቸው ከማይወጡበት የችግር አዘቅት ውስጥ የወደቁ አባቶችና እናቶች አይጠፉም::

ብዙ ጊዜ በአታላዮች የስብከት ንፋስ የሚገለባበጡት ሰዎች በእምነት በንጽሕና በቅድስና የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያዎች ወይም ቤቶች ሆነው ሳሉ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ እውቀት ላይ ያልተመሠረቱ ምእመናን ናቸው:: የእግዚአብሔርን ቃል:- ሰዎች በልባቸው ፈጥረው ከሚቀባጥሩት የአሉባልታ ወሬ ለይተው የማያውቁ ሰዎች የዚህ ችግር ሰለባዎች ይሆናሉ:: የተሰሎንቄ ሰዎችም ኅልቀተ ዓለም /የዓለም ፍጻሜ/ ይደርስብናል በማለት ይፈሩና ይጨነቁ የነበሩ በወንጌል የተጻፉትን የዳግም ምጽአትን ምልክቶች ባለማወቃቸው እንደሆነ የቅዱስ ጳውሎስ ቃል ያስረዳናል:: «ማንም በማናቸውም መንገድ እንዳያስታችሁ ክሕደቱ አስቀድሞ ሳይመጣና የዓመፅ ሰው እርሱም የጥፋት ልጅ ሳይገለጥ አይደርስምና...» 2ኛተሰ. 2÷3 ሐሳዌ መሲሕ የሚፈጽማቸው የክሕደትና የተንኮል ድርጊቶች ሳይፈጸሙ ጌታ በወንጌል የተናገራቸው ምልክቶች በቅደም ተከተል ሳይደረጉ ኅልቀተ ዓለም አይሆንም በማለት ሐዋርያው የተሰሎንቄን ሰዎች አረጋግቷቸዋል::

ሐሳዌ መሲሕ ሳይመጣ ምልክቶች ሳይደረጉ ዳግም ምጽአት ይሆናል ማለት ነቢዩ ኢሳይያስ ሐሰት በአንደበቱ አልተገኘበትም ብሎ የመሰከረለት የእውነትና የጽድቅ ባለቤት ክርስቶስን ሐሰተኛ ማድረግ ነው:: ድፍረትም ነው:: ክርስቶስ የተናገረው ቃል አያልፍም አይሻርም እርማትም አያስፈልገውም:: እንደዘመኑ ፖለቲካ ለማስመሰል የተነገረ ቃል አይደለም:: እንኳን የጌታ ቃል የሐዋርያው ቃል በእውነት ላይ የተመሠረተ ነው:: ሐዋርያውም ሐሳዌ መሲሕ ሳይመጣ ጌታ ዳግመኛ እንደማይመጣ የተናገረው ቃል ሐሰት ያልተቀላቀለበት እውነት ነው:: ተናጋሪው ጳውሎስ ቢሆንም አናጋሪው



www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው:: አሉባልታ አይደለም:: ቡና ለመጠጣት የተሰበሰቡ ሰዎች በሹክሹክታ የሚነጋገሩት ሐሜትም አይደለም ወይም ሰዎች የጠሉትን ሰው እንደሚያክፋፉት ጠንካራ ጐኑን ሰውረው ደካማ ጐኑን ብቻ አጉልተው እንደሚናገሩበትና ስሙን እንደሚያጠፉት የሐሳዌ መሲሕን ስም ለማጥፋት ፈልጐ የተናገረው አይደለም:: ሐሳዌ መሲሕ በሚያስቀምጠው የመሰናከያ ደንጊያ ምእመናን እንዳይሰናከሉ እያስጠነቀቀ ነው እንጂ::

ስለዚህ አንባብያን ሆይ ዳግም ምጽአት እንደደረሰ አድርገው የአሉባልታ ወሬ በሚነዙ ቢጽ ሐሳውያን ልትሸበሩ አይገባም:: መጻሕፍትን መርምሩ:: መምህራንን ጠይቁ ከዚህ በፊት ምጽአት እንደደረሰ እንደቀረበ አድርገው የሐሰት ትንቢት ሲናገሩ ነበር:: ለምን ምጽአት አልተደረገም ሰማይና ምድር ለምን አሳለፉም:: እነሆ ሰማይና ምድር ባሉበት ጸንተው ሐሰታቸውን ገለጡባቸው::

ዳግም ምጽአት ሲባል በሰዎች ሕሊና የሚታሰበው እንደ መቅሠፍት ነገር፣ እንደድንገተኛ አደጋ፣ የጭካኔ ተግባር እንደሚፈጸምበት ክፉ ቀን ተደርጐ ነው:: በእርግጥ ያ ቀን የፍርድ ቀን በመሆኑ ሊያስደነግጥና ሊያስፈራ ይችላል::

ነገር ግን መፍራት ያለብን ዳግም ምጽአትን አይደለም:: ዳግም ምጽአት ማለት የክርስቶስ ሁለተኛ መምጣት ማለት ነው:: ይልቁንስ መፍራት የሚገባን በክርስቶስ ፊት የሚያስወቅሱ የወንጀል ዓይነቶችን መፈጸምን ነው:: ንስሐ ከገባንና ከኃጢአታችን ከተለየን ዳግም ምጽአትን እንናፍቀዋለን እንጂ አንፈራውም:: ያ ቀን ለጻድቃን ዋጋቸው ለኃጥአን ፍዳቸው የሚከፈልበት ቀን ነውና::

ከመብራታችን ጋር ዘይታችንን ይዘንና የሠርጉን ልብስ ለብሰን ከተገኘን ማለትም ከሃይማኖታችን ጋር መልካም ሥነ ምግባርን ይዘን ከተገኘን ከሙሽራው ጋር ወደሠርጉ ቤት የምንገባበት ቀን ነው:: ማቴ. 25÷1-13 ሞትን ድል አድርገን በማይፈርስ በማይበሰብስ በሐዲስ ሥጋ የምንነሣበት ቀን ነው:: በዓይን ያልታየውን በጆሮ ያልተሰማውን በልብ ያልታሰበውን እግዚአብሔር ለወዳጆቹ ያዘጋጀው ክብረ መንግሥተ ሰማያትን





የምንወርስበት ቀን ነው:: ስለዚህ ዳግም ምጽአትን ልንናፍቀው ይገባናል::

ዳግመኛም ብዙ ጊዜ እንደተገለጸው ሐሳዌ መሲሕ አስቀድሞ ሳይመጣ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ የማይመጣ መሆኑን ልናስተውል ይገባናል:: በውኑ ደመና ሳይታይ ዝናብ ይዘንባልን? ዝናብ መጣ የምንለው ደመናውን አይተን አይደለምን? የዝናብ ምልክቱ የደመናው መታየት እንደሆነ ሁሉ የዳግም ምጽአት ወይም የኅልቀተ ዓለም ምልክቱ የሐሳዌ መሲሕ በዓለም ላይ መገለጥ ነው::

## ሐሳዌ መሲሕና መጥፎ ተግባሩ

### 1ኛ. ሐሳዌ መሲሕ ከሐዲ ነው

የሐሳዌ መሲሕን ከሐዲነት ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ በማለት ይገልጠዋል:: «ክሕደቱ አስቀድሞ ሳይመጣ...» ይላል:: ዳግም ምጽአት አይደረግም ማለቱ ነው::

ክሕደት ማለት መክዳት፣ እምነትን ውልን መሐላን ማፍረስ፣ መሸፈጥ፣ ቃልን መለወጥ፣ መዋሸት፣ ማበል፣ መወንጀል ማለት ነው::

ክሕደት ፍጡራን ከፈጣሪያቸው የሚለዩበትና እንዳይነሡ ሆነው የሚወድቁበት ጥልቀት ያለው ገደል ነው:: ወደ ክሕደት ገደል ገብተው ገጸ-ፈጣሪያቸውን ቀና ብለው ማየት የተሳናቸው ፍጡራን ብዙ ናቸው:: ለወደፊትም በጣም ረዥም ጥልቀት ወዳለው የክሕደት ገደል የሚገባው ከፍጡራን ወገን የሚሆነው ሐሳዌ መሲሕ ነው:: ሐሳዌ መሲሕ ፈጣሪውን ብቻ ሳይሆን ራሱንም ይክዳል:: ያለውን አዳማዊ ባሕርዩን ክዶ የሌለውን እግዚአብሔራዊ ባሕርይ እንዳለው አድርጐ ያምናል:: ፍጡር ሆኖ ፍጡርነትን መካድ ራስን መካድ ነውና ራሱን ይክዳል ቢባል ከእውነት የራቀ ሐሰት አይሆንም:: ራሱን ብቻም ሳይሆን አባቱንም ይክዳል:: አዳማዊ ባሕርይ ካለው አባት በዘር በሩካቤ ተወልዶ ሳለ በድንግልና ተጸንሼ በድንግልና ተወለድሁ ይላልና የአባቱን ሕልውና ከአእምሮው ይሰርዛል:: ሐሳዌ መሲሕ



www.ethiopianorthodox.org

ፈጣሪውንም አባቱንም ራሱንም አላውቃችሁም የሚል የከሐዲዎች ሁሉ እንግዳ የተለየ መልክ ያለው ከሐዲ ነው::

ክሕደት በትንሽ ነገር ነው የሚጀመረው:: ክሕደት ከሰዎች ልቡና ሲወለድ ሕፃን ሆኖ ነው የሚወለደው:: እያደገና እየጐለበተ ሲሔድ ግን እግዚአብሔር ነኝ ከማለት የሚያደርስ ሆኖ ይገዝፋል:: እግዚአብሔር ነኝ ማለት የክሕደት የመጨረሻው የዕድገት ደረጃ ነው:: በዓለም ላይ ብዙ ከሐዲዎች ቢኖሩም ከሐሳዌ መሲሕ ጋር የሚወዳደር ከሐዲ አይኖርም:: ሐሳዌ መሲሕ የክሕደት ደረጃውን ከዲያብሎስ የክሕደት ደረጃ ስለሚያደርሰውና ስለሚያሳድገው ማንም አይደርስበትም:: እግዚአብሔር ነኝ ከማለት በላይ ለክሕደት ቁንጮ የለውምና::

ሐሳዌ መሲሕ እግዚአብሔር ነኝ ብሎ በእግዚአብሔር ስም እንደሚመጣ ሐዋርያው እንዲህ ሲል ይገልጻል:: «እኔ እግዚአብሔር ነኝ ብሎ አዋጅ እየነገረ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እስኪቀመጥ ድረስ አምላክ ከተባለው ሁሉ ሰዎችም ከሚያመልኩት ሁሉ በላይ ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደረገው ተቃዋሚ እርሱ ነው» 2ኛተሰ. 1÷4::

ሐዋርያው ጳውሎስ የሐሳዌ መሲሕ ክሕደት ሳይገለጥ ኅልቀተ ዓለም፤ የዓለም ፍጻሜ አይሆንም ነው የሚለው:: የሐሳዌ መሲሕ ክሕደት በሥርቆት እንደጸነሰች ሴት በድብቅ የሚያዝ ሳይሆን ይፋ የሚወጣ ነው:: በሐሰት ነቢያቱና በምትሐት ታምራቱ ገዝፎ እንደ ትልቅ ተራራ ጽንፍ እስከ ጽንፍ የሚታይ ነው የሚሆነው:: የሐሳዌ መሲሕ ክሕደት በተወሰኑ ሀገሮች ብቻ የሚገለጥ ሳይሆን ዓለምን በሙሉ የሚወር ክፉ ባሕረስ እንደሚሆን በትንቢት ተናግሯል:: የተወሰኑ ሰዎች እንደምሥጢር የሚይዙትና በሹክሹክታ የሚነጋገሩት ቁጥብ ነገር ስለማይሆን ሁሉ ይሰማዋል:: ሁሉ ያውቀዋል:: ስለዚህ የሐሳዌ መሲሕ ክሕደት ሳይገለጽ ክርስቶስ ዳግመኛ አይመጣም::

## 2ኛ. የዓመፅ ሰው ነው

ሐሳዌ መሲሕ የዓመፅ ሰው መሆኑን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በግልጽ ይናገራል:: 2ተሰ. 2÷3 ከ1-12 ይመልከቱ:: ዓመፅ ማለት መሸፈት፣ መበደል፣ ክፉ መሆን፣ ግፍ መሥራት፣





መሥረቅ፣ መቀማት ማለት ነው:: ለንጉሠ ሰማይ ወምድር
ለእግዚአብሔር አንገዛም የሚሉ ፍጡራን ሁሉ አማፅያን
ይባላሉ:: «ሁሉ ዓመፁ በአንድነትም ረከሱ» መዝ. 13÷3
«እውነትን በዓመፃ የሚከለክሉ ሰዎች በኃጢ አተኛነታቸውና
በዓመፃቸው ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ከሰማይ ይገለ
ጣልና...» ሮሜ. 1÷18 ነቢዩ ዳዊትም እግዚአብሔር ዓመፅን
የማይወድ መሆኑን እንዲህ ብሎ ገልጿል:: «ጽድቅን ወደድህ
ዓመፃንም ጠላህ» መዝ. 44÷7 ዳግመኛም ራሱ ዳዊት ለእግዚአ
ብሔር ሕግ መገዛት ደስ የሚያሰኘው መሆኑንና ሕገ ወጦችን
ወይም ዓመፀኞችን ግን የሚጠላ መሆኑን እንዲህ ሲል ይናገ
ራል:: «ዓማፅያነ ጸላዕኩ ወሕገከሰ አፍቀርኩ፤ ዓመፀኞችን ጠላሁ
ሕግህን ግን ወደድሁ» መዝ. 118÷113::

ከዚህ በፊት እንደተገለጸው የዓመፅ ትርጉሙ ሕገ ወጥ
ነት ወይም እምቢተኛነት ነው:: ስለሆነም ሕገ ወጥና እምቢተኛ
የሆነ ሰው ዓማፂ፤ ዓመፀኛ ይባላል:: ለሕግ የማይገዛ፣ ከሕግ
በታች የማይውል፣ ሕግን የሚተላለፍና የሚራመድ ሰው፣
ዓመፀኛ የሚለውን ቅጽል ስም ይቀበላል:: በአንድ ሀገር ውስጥ
ለሚኖረው የሀገር መሪና ለአወጣው ሕግ አልገዛም በማለት
አፈንግጦ ራሱ ኮብልሎ ሌሎችንም የሚያስኮበልል ከከተማ
ወጥቶ በዱር በገደል በዋሻ የሚኖር ሰው አመፀኛ ይባላል::
በገዢው ላይ ያመፀ ገዢውን የናቀ የገዢው ጠላት ነው:: ዓመ
ፀኛው የገዢውን ሥልጣን ለመረከብ ኃይሉን አጠናክሮ የሚታ
ገል የገዢው ተቀናቃኝ ነው የሚሆነው::

ሐሳዌ መሲሕም ፍጡር እንደመሆኑ የሰማይና የምድር
ገዢ ለሆነው ለእግዚአብሔር የአምልኮትና የስግደት ግብር
እየገበረ መኖር ሲገባው ከእግዚአብሔር የአምልኮት ከተማ
አፈንግጦ ወጥቶ ሌሎችንም ፍጡራን ከዚሁ ከተማ በማስኮብለል
የራሱን የአምልኮት ከተማ ስለሚቆረቁር የዓመፅ ሰው ዓመፀኛ
ነው:: አይሳካለትም እንጂ እንደ ዲያብሎስ የእግዚአብሔርን
መንግሥት ለመፈንቀልና እጅ ለማድረግ የቻለውን ያህል
ይታገላልና የእግዚአብሔር ጠላት ነው::



www.ethiopianorthodox.org

## 3ኛ. የጥፋት ልጅ ነው

ሐሳዌ መሲሕ የጥፋት ልጅ መሆኑን ቅዱስ ጳውሎስ ሳይጠቁም አላለፈም «የጥፋት ልጅ ሳይገለጥ አይደርስምና...» 2ተሰ.2÷3 የጥፋት ልጅ ሐሳዌ መሲሕ ሳይገለጥ ዳግም ምጽአት አይሆንም ማለቱ ነው:: ጥፋት ማለት መታጣት፣ ዕልም ድርግም ማለት፣ መበላሸት፣ ከንቱ መሆን፣ መሸሽ፣ መኮብለል፣ መውደም፣ መፈታት ማለት ነው::

ጥፋት ብዙ ጊዜ ለዘለዓለም ከእግዚአብሔር የመራቅና ከጸጋውም የመውጣትን ሁኔታ ያመለክታል:: «በአንድም ነገር እንኳ በተቃዋሚዎች አትደንግጡ ይህም ለእነርሱ የጥፋት ለእናንተ ግን የመዳን ምልክት ነው» ፊል. 1÷28 «ዳሩ ግን ባለጠጐች ሊሆኑ የሚፈልጉ በጥፋትና በመፍረስ ሰዎችን በሚያሰጥምና በሚያሰንፍ በሚጐዳም በብዙ ምኞትና በፈተና በወጥመድም ይወድቃሉ» 1ጢሞ. 6÷9::

ከወንጌል አደባባይ የታጡ በዲያበሎስ ቤት የሚቀላውጡ ከቤተ ክርስቲያን የኮበለሉ በጠንቋዮች ቤት የሞሉ ከእውነት የሸሹና የራቁ በሐሰት ዋሻ የተደበቁ ከሃይማኖት የራቁ በክሕደት የወደቁ ሁሉ የጥፋት ልጆች ይባላሉ:: ጌታውን መምህሩን ለ30 ብር የሸጠ በዲያብሎስ ሰይፍ ሕይወት ገመዱ የተቆረጠ በፍቅረ ንዋይ የተቃጠለ ከወንድሞቹ የተገነጠለ ይሁዳም የጥፋት ልጅ ተብሏል:: «ከእነርሱ ጋር በዓለም ሳለሁ የሰጠኸኝን በስምህ እኔ እጠብቃቸው ነበር ጠበቅኋቸውም:: መጽሐፉም እንዲፈጸም ከጥፋት ልጅ በቀር ከእነርሱ ማንም አልጠፋም» ዮሐ. 17÷12::

የጥፋት ልጅ የሚለው ቃል ሐሳዌ መሲሕ አጥፊና ጠፊ መሆኑን ያመለክታል::

ሀ/ <u>አጥፊነቱ</u>:- ሐሳዌ መሲሕ ፍጡርነቱንና የሰይጣን ፈረስ መሆኑን ስግደትም ለፈጣሪ እንጂ ለፍጡር የማይገባ መሆኑን ተገንዝበው የማይንበረከኩለትን የአምልኮት ግብርም የማይገብሩለትን ይልቁንም ስቶ የሚያስት ክዶ የሚያስክድ ሐሰተኛው ክርስቶስ መሆኑን የሚገልጡበትን ምእመናን ነፍሳቸውን ማጥፋት ባይቻለውም በሥጋቸው ያጠፋቸዋል:: ምንም በሥልጣን





የሚቆይባቸው ዓመታት ሦስት ዓመት ከመንፈ፦ ቢሆኑም የሚሠራው የጭካኔና የአረማዊነት ሥራ ብዙ ነው:: ቅዱሳንን የሚዋጋ ከቅዱሳን ጋር ኅብረት የሌለው ዘንዶ የተባለው ሰይጣን ኃይሉንና ሥልጣኑን የሚሰጠው አውሬ ስለሚሆን ከቅዱሳን ጋር ይዋጋል:: «ቅዱሳንንም ይዋጋ ዘንድ ድልም ያደርጋቸው ዘንድ ተሰጠው:: በነገድና በወገንም በቋንቋም በሕዝብም ሁሉ ላይ ሥልጣን ተሰጠው» ራእይ 13÷7::

ሐሳዌ መሲሕ አምላክነቴን ተቀበሉ በማለት የስሕተት ስብከቱን ሲያጧጡፍ ስሕተቱን የሚገልጹበትና የሚቃወሙት ቅዱሳን ናቸው:: ቅዱሳን አምላክ አለመሆኑንና ስሑት ፍጥረት መሆኑን ይገልጹበታል:: አይፈሩትም ቅዱሳንን የከሐዲዎች ሰይፍና ጦር ያነደዱትም እሳት አያስፈራቸውም:: መቼም ሌባ ሌብነቱን የገለጡበትንና ያጋለጡትን ሰዎች የቻለውን ያህል መበቀሉ አይቀሬ ነውና ሌባው ሐሳዌ መሲሕ ቅዱሳንን ይጣላቸዋል:: በሥጋዊ ኃይሉ ያሸንፋቸዋል:: ድልም ያደርጋቸዋል:: የሐሳዌ መሲሕ ኣጥፊነት የቅዱሳን ምእመናንን ሥጋዊ ሕይወት በማውደም ይገለጻል::

በሰይፍ በመቁረጥ በእንጨት ላይ በመስቀልና በእሳት በማቃጠል በሥጋዊ ሕይወት ላይ የሚወሰደው እርምጃ የከሐዲዎች ድል መገለጫ ሲሆን የቅዱሳን ድል ግን የሚገለጸው መከራውን ጨክነው በመቀበላቸው ሥጋቸውን የሚገድሏቸውን ባለመፍራታቸውና በሰማዕትነት በመሞታቸው ነው:: ምክንያቱም ቅዱሳን በሥጋ ቢሞቱ በነፍስ ሕያዋን ናቸው:: በዚህ ዓለም ሲታሰ· በወዲያኛው ዓለም አሉ:: ከሐሳዌ መሲሕ ፊት ሲጠፉ በክርነቶስ ፊት ይገኛሉ:: በዚህ ዓለም ሲጠወልጉ በወዲያኛው ዓለ ° ይለመልማሉ:: ሲሸነፉ ያሸንፋሉ:: መሪያቸውና ፈጣሪያቸ· ክርስቶስ ሰይጣንን ድል ያደረገው እጆቹንና እግሮቹን ተቸ/ክሮ በመስቀል ላይ በሆነው በሞቱ ስለሆነ ቅዱሳንም በሞታቸ ድል ያደርጋሉ::

ለ/ <u>ጠ ነቱ</u>:- ሐሳዌ መሲሕ ሦስት ዓመት ከመንፈቅ እንደ ሦስት ወር ክረምት መብረቅ የብዙ ምእመናን መቅሠፍት ሆኖ ከቆየ በኋላ እርሱም ይቀሠፋል «በዚያም ጊዜ ኢየሱስ በአፉ መንፈስ የሚያጠፋው ሲመጣም በመገለጡ የሚሽረው ዐመፀኛ



www.ethiopianorthodox.org

ይገለጣል» 2ተሰ.1÷8 ዓመፀኛው ሐሳዌ መሲሕ በመንፈስ ቅዱስ የመቅሠፍት ብትር የሚመታ መሆኑን ነው ሐዋርያው የሚገልጽልን የሐሰት ዕድሜ አጭር ነውና የሐሳዌ መሲሕ የሐሰት አምላክነት በሦስት ዓመት ከመንፈቅ ያከትማል::

የሐሰት ሕልውና እውነት እስኪገለጥ ድረስ ነው:: ጤዛ ወይም ውርጭ ፀሐይ እስኪወጣ ድረስና የፀሐይ ሙቀት እስኪ ገርፈው ድረስ በሣሮችና በቅጠሎች ላይ ነግሦ እንዲቆይ ሐሰትም እውነት እስኪወጣ ድረስ በሰዎች ላይ ነግሦ ይቆያል::

የዓለም ፀሐይ እውነተኛው ክርስቶስም ከመዓት ጨረሩ ጋር ብልጭ ባለጊዜ ለሦስት ዓመት ከመንፈቅ ያህል በምእመናን ላይ አሰቃቂ ጤዛ ወይም ውርጭ ሆኖ የሚቆየው ሐሰተኛው ክርስቶስ ሕልውናውን ያጣል:: ሐዋርያው ጳውሎስ የሐሳዌ መሲሕን መገለጽ ብቻ ሳይሆን ጥፋቱንም ተናግሮአል:: የኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ ሕይወቱ መንፈስ ቅዱስ የሚያጠፋው መሆኑን ጠቁሟል:: 2ተሰ. 2÷8

ሐሳዌ መሲሕ ከነተከታዮቹ ነው የሚጠፋው:: የአምልኮት መባ የሚያቀርቡለትን ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚሉትንና የሚምበረከኩለትን ከእግዚአብሔር የታዘዘ መቅሠፍት ያጠፋቸዋል «ለአውሬውና ለምስሉ የሚሰግድ በግንባሩም ወይም በእጁ ምልክቱን የሚቀበል ማንም ቢኖር እርሱ ደግሞ በቁጣው ጽዋ ሳይቀላቀል ከተዘጋጀው ከእግዚአብሔር ቁጣ ወይን ጠጅ ይጠጣል:: በቅዱሳንም መላእክትና በበጉ ፊት በእሳትና በዲን ይሰቃያል /ይሳቀያል/ የስቃያቸውም ጢስ ለዘለዓለም እስከዘለ ዓለም ድረስ ይወጣል:: ለአውሬውና ለምስሉም የሚሰግዱ የስሙንም ምልክት የሚቀበል ሁሉ ቀንና ሌሊት ዕረፍት የላቸውም» ራእይ 14÷9-11

## 4ኛ. ተቃዋሚ ነው

ሐሳዌ መሲሕ ተቃዋሚ መሆኑን ቅዱስ ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች ይገልጻል:: 2ተሰ. 2÷4 ተቃዋሚ ማለት ተሟጋች፣ ተቀናቃኝ፣ ተከራካሪ፣ ተወዳዳሪ፣ ተፎካካሪ፣ ወደረኛ፣ ከሳሽ፣ ባላጋራ፣ ጠላት ማለት ነው:: የክርስቶስ ሥልጣንና





የክርስቶስ ስም የእኔ ነው በማለት ከክርስቶስ ጋር የሚከራከረውና የሚፎካከረው ሐሳዌ መሲሕ ተቃዋሚ ተብሏል:: ምንም ባይሳካለት የክርስቶስ መንግሥት ተቀናቃኝ ነው:: በደጋፊዎቹ ፊት ውድድሩን ያካሂዳል:: ውድድር ማለት የማሸነፍ ሕልምን በሚያልሙ በሁለት ተወዳዳሪዎች መካከል የሚካሄድ የአሸንፋለሁ ባይነት ተግባር ነው:: አንድ ተወዳዳሪ ውድድሩን የሚያካሂደው በማናቸውም የችሎታ መገለጫ በሆነ ነገር እኩያው ከሆነው ከጓደኛው ጋር ነው::

የሐሳዌ መሲሕ ውድድር ግን ከዚህ የተለየ ነው:: የሐሳዌ መሲሕ ውድድር «ያላቻ ጋብቻ» እንደሚባለው ነው:: ዳግመኛም እንዲህ ይባላል:: «የፍየል ወጠጤ ልቡ ያበጠበት እንዋጋ ብሎ ለነብር ላከበት ሌላም አይጥ ለሞቷ የድመት አፍንጫ ታሸታለች» ይባላል:: የሐሳዌ መሲሕ ተቃውሞም እነዚህ አባባሎች የሚያስፈልጉት ሆኖ እናገኘዋለን:: ምክንያቱም ሐሳዌ መሲሕ ከእግዚአብሔር ጋር መወዳደር እግዚአብሔርን መቃወም ስለማይችል ነው::

ውድድር ከእኩያ ጋር ከሆነ የእግዚአብሔር እኩያ /ጓደኛ/ ማን ነው? መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በማናቸውም ነገር ብቸኛ መሆኑን ይገልጻል:: «እንደ እግዚአብሔር ቅዱስ የለምና እንደአምላካችንም ጻድቅ የለምና ከአንተ በቀር ቅዱስ የለም» 1መጽ.ሳሙ.2÷2 «እግዚአብሔርን በሰማይ የሚተካከለው ማነው? ከአማልክትስ ልጆች እግዚአብሔርን ማን ይመስለዋል» መዝ. 88÷6 የጌታን ልብ ያወቀው ማን ነው ወይስ አማካሪው ማን ነበር ወይስ ብድራቱን ይመልስ ዘንድ ለእርሱ አስቀድሞ የሰጠው ማን ነው? ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱም ነውና» ሮሜ.11÷34-35 «በምድርም የሚኖሩ ሁሉ እንደምናምን ይቆጠራሉ:: በሰማይም ሠራዊት በምድርም ላይ በሚኖሩ መካከል እንደፈቃዱ ያደርጋል» ዳን. 4÷35

ታዲያ ሐሳዌ መሲሕማ በምድር የሚኖር እንደመሆኑ ምናምን ከተባሉት አንዱ አይደለምን? የውድድር ሕልሙም ፍች የሌለው ቅዠት ነው:: ስለዚህ እግዚአብሔር ተወዳዳሪ የሌለው ብቸኛ የሰማይና የምድር ንጉሥ ነው:: መንግሥቱንም ከእርሱ በፊት ከነበረ ንጉሥ አልወረሰውም:: ለወደፊትም



www.ethiopianorthodox.org

የእርሱን መንግሥት የሚወርስ ንጉሥ የለም። ቅድመ ዓለም በማዕከለ ዓለም ድኅረ ዓለም ንጉሥ ነውና።

አምባ ገነኑ ንጉሥ ናቡከደነጾር እንኳ ለሰባት ዓመት ያህል ሰብአዊ ባሕርዩን ተገፎ ከተቀጣ በኋላ እንዲህ ሲል ምስክርነቱን ሰጥቷል «ግዛቱ የዘለዓለም ግዛት ነውና መንግሥቱም ለልጅ ልጅ ነውና» ዳን. 4÷34 ሐሳዌ መሲሕ ግን በሐሰት ጨለማ የሚድበሰበስ ዕውረ ልብ ስለሆነ የክርስቶስ ዘለዓለማዊ መንግሥት አይታየውም እራሱን ዘለዓለማዊ ንጉሥ አድርጎ የመኖር ምኞች ዓይነ ልቡናውን ይጋርደዋል።

## በተአምራት ይመጣል

ሐሳዌ መሲሕ በተአምራት /በምልክቶች/ እንደሚመጣ ሐዋርያው ያስጠነቅቃል 2ተሰ. 2÷10 ተአምራት ማለት ድንቆች ምልክቶች ልዩ ጉድ ብርቅ የሆኑ ነገሮች በሰው የሥራ ችሎታ ያልተለመዱ ሥራዎች ናቸው። ሐሳዌ መሲሕ ከፍጡራን በላይ የሆነ ፈጣሪን መስሎ ለመታየትና የሕዝብን ልብ ፀሐይ ሳይገባ ለመሥረቅ የምትሐት ተአምራቱን እያዥጐደጐደ ይመጣል። ከእምነት ማዶ ያሉትን ሰዎች ወደ እምነት ለማሻገር ምልክት ወይም ተአምር ዋና ድልድይ ነው። ከአንድ ሺህ የጦር ሠራዊት ይልቅ ትንሽ ምልክት ሰዎችን ይማርካል። ማግኔት ብረት ነክ ነገሮችን እንደሚስብ ሁሉ ድንቅ ነገርም ሰዎችን ከእያሉበት ይሰበስባል ተአምራትን /ድንቅ ነገሮችን/ ማድረግ የሚችለው እግዚአብሔር ሲሆን ሰይጣንም የማስመሰል ምልክቶችን በማሳየት የምእመናንን ልቡና ያደናግራል።

ሰይጣን ብርቅና ድንቅ የሆኑ ነገሮችን ከማሳየት ወደኋላ እንደማይል በሚከተሉት ቃላት ምስክርነቱን ሰጥቷል «ማደሪያዬንም ላደረግኋቸው ሰዎች ምልክትን አሳያቸዋለሁ በከዋክብት አካሄድም ቢሆን በደመና መውጣትም በእሳት ማናፋትም ቢሆን በአውሬዎችና በወፎችም ጩኸት ቢሆን እነርሱ ማደሪያዎቼ ናቸውና በዚህ ሁሉ በልቡናቸው ምልክቶችን አሳድርባቸውአለሁ» ሣልስ መቃ. 1÷12 የሰይጣን ሥራዎች የሐሰት ሥራዎች ስለሆኑ የማስመሰል ሥራዎች ናቸው። ሰይጣን:- ብዙ ልምድ





እንዳካበተ ደራሲ ዕለት ዕለት የሚፈጥራቸው ብዙ የማታለያ ዘዴዎች አሉት። ሰይጣን ተለዋዋጭና ተገለባባጭ ነው። ሰዎች እሱን የማመን ደረጃቸውን እንዲያሳድጉ የሚያደርግበትን ዘዴ ከዕለት ዕለት በማሻሻል ላይ ይገኛል። ዲያብሎስ ለራሱ ሥራ የራሱ ሳይንቲስት ነው።

ብዙ ምልክቶች የሚመረቱባቸው የዲያብሎስ ፋብሪካዎች የጠንቋዮችና የመተተኞች ቤቶች ናቸው። በእነዚህ ፋብሪካዎች የሚመረተውን ምርት ለመግዛት ሰዎች ያላቸውን ሁሉ ይሸጣሉ። ዲያብሎስ ከሰዎች የሚፈልገው የአምልኮት መባ ነውና በየጠንቋይ ቤቶች መሥዋዕት እንዲቀርብለት ያደርጋል። ቀይ በግ፣ ነጭ በግ፣ ቀይ ዶሮ፣ ነጭ ዶሮ ወዘተ። የዲያብሎስ ካህን ጠንቋዩ እንደአዘዘ ይሠዋሉ። መሥዋዕት በሚሠዋበት ቦታም ዲያብሎስ ጉድ ጉድ የሚያሰኙ አንድ አንድ ምልክቶችን ብልጭ ያደርጋል። የዲያብሎስ አሠራር ይህን ይመስላል።

የሐሳዌ መሲሕም አመጣጥ ወይም የሥራው ዓይነት እንደዲያብሎስ አሠራር መሆኑን ሐዋርያው ጳውሎስ ይነግረናል «የእርሱ መምጣት በተአምራት ሁሉና በምልክቶች የሐሰተኞች ድንቆችም በዐመፅም መታለል ሁሉ እንደ ሰይጣን አሠራር ነው» 2ተሰ. 2÷10 የሐሳዌ መሲሕ አመጣጥ እንደ ሰይጣን አሠራር ነው ማለት ምልክቶችን ብርቅና ድንቅ የሆኑ ነገሮችን እያደረገ ያስታል ማለት ነው። «ይነግሣል ብለው ያልጠረጠሩት ሐሳዌ መሲሕ ይነግሣል ከሰማየ ሰማያት ወረድሁ ከድንግል ማርያም ተወለድሁ ሲል ሁሉ ቃሉን ያሰማልና በየሀገሩ ሽብር ይሆናል እሳትም ከሰማይ ተጠቅሎ ይወረዳል የምድረ በዳ አውሬዎችም ቦታቸውን ትተው ወደከተማው ይገባሉ ከሴቶችም ሽብቶ ጥርስ አውጥቶ ይወለዳል» እዝ. ሱቱ. 3÷6-8

ከሰማይ እሳት ይወርዳል ማለት ሐሳዌ መሲሕ ከሰማይ እሳትን ያወረደ እያስመሰለ ሰብአ ሰዶምን ሰብአ ገሞራን እንዲህ አድርጌ ያጠፋኋቸው እኔ ነኝ አሁንም ለእኔ የማይሰግደውን እኔን የማያመልከውን እንዲህ አድርጌ አጠፋዋለሁ በማለት የምትሐት ተአምራት ያሳያል ማለት ነው። አውሬዎች ወደ ከተማው ይገባሉ ማለትም «ዘመድ ከዘመዱ አህያ ከአመዱ» እንዲሉ ጣዖት አምላኪዎች ኃጢአተኞች ሁሉ ሐሳዌ መሲሕ ወደአለበት ከተማ ይሰበሰባሉ ማለት ነው። ዘመኑ የሐሳዌ



www.ethiopianorthodox.org

መሲሕ ዘመን መሆኑንና ዳግም ምጽአት እየቀረበ መሆኑን የሚያስረዱ ብዙ ምልክቶች ይደረጋሉ። ሐሳዌ መሲሕ መንገዶ ቹን በተአምራት መካከል እንደሚያደርግ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጠቁሞአል «ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉና ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ።» ማቴ.24÷24፣ ማር.13÷22

# ሐሳዌ መሲሕ በራእየ ዮሐንስ

## ሐሳዌ መሲሕ ለምን አውሬ ተባለ?

ወንጌላዊ ዮሐንስ የሐሳዌ መሲሕ መምጣት ተገልጾለት ገጽታውን ከነጸባዩ ገልጾታል። ውጫዊ መልኩንና ውስጣዊ መልኩን የአመጣጡን ምልክት የሥራውን ይዘት ከዘንዶው ጋር ያለውን ዝምድና ከሥሩ ከመሠረቱ ከመነሻው እስከ መድረሻው ምን እንደሚመስል አሳውቋል። የሐሳዌ መሲሕን ጉድ የገለጸው ራእይ በተባለው መጽሐፉ ሲሆን በተለይም በምዕራፍ 13÷1-18 ያለውን ስናነብ አጸያፊ የሆነ የሐሳዌ መሲሕን መልክ አጉልቶ ያሳየናል። በዚሁ ምዕራፍ ቁጥር አንድ ላይ የሚከተለውን ንባብ እናገኛለን።

«አንድም አውሬ ከባሕር ሲወጣ አየሁ» ወንጌላዊ ዮሐንስ አውሬ በማለት የገለጸው ሐሳዌ መሲሕ ነው። ለምን አውሬ አለው የሚለው ጥያቄ በአንባብያን ልቡና ስለሚመላለስ መልሱ ከዚህ ይቀጥላል። መጀመሪያ አውሬ የሚለው ንባብ ቃል ፥ ን ትርጉም እንዳለው እናያለን። አውሬ ማለት ቁጡ፣ ቁጠኛ፣ ጠ ባየ ክፉ፣ ደም ልሶ ሥጋ /ብርንዶ/ ጉርሶ አጥንት ከስክሶ የሚ ኖር የሚያድንና የሚታደን በረኸኛ የሰውና የእንስሳ ደመኛ ማለት ነው።

አውሬ የተለያየ ስም የተለያየ ዓይነት የተለያየ ነገድ አለው። አውሬ ሲባል በተንኮለኛነቱና በአስፈሪነቱ ቢታወቅም ከአውሬ የሚበልጥ እጅግ የሚያስፈራ አውሬ አለ። ከአውሬ የሚከፋ አውሬ አለ። አውሬዎች /አራዊት/ በተንኮላቸውና በአስፈሪነታቸው ይበላለጣሉ። አንበሳ፣ ነብር፣ ድብ /ጅብ/





በመባል የሚታወቁት አራዊት /አውሬዎች/ እጅግ ግሩማን፣ የሚያስፈሩ የሚያስደነግጡ አውሬዎች ናቸው። ሐሳዌ መሲሕም እጅግ አስደንጋጭና ጨካኝ ፍጡር ስለሚሆን በእነዚህ በተጠ ቀሱት ግሩማን አውሬዎች መልክ ተገልጿል።

ሰው በክፉ ጠባዩ፣ በክፉ ሥራው፣ በክፉ አመለካከቱ ከሰው አውሬ ይባላል። ሐሳዌ መሲሕም ምንም ነገዱ ትውልዱ ከሰው ወገን ቢሆን ቁመናው አካሉ ውጫዊ ገጽታው ሰዎችን ቢመስል ክፉ ጠባዩ ከአውሬ ጋር ስለሚመሳሰል አውሬ ተብሏል። እግዚ አብሔር ለዮሐንስ የሐሳዌ መሲሕን መልክ በአርአያ አውሬ /በአውሬ ምስያ/ ገልጾታል። አውሬ ያገኘውን ተንቀሳቃሽ ሁሉ በጥርሱ ከመንከስ በጥፍሩ ከመቧጨር ወደኋላ እንደማይል ሁሉ ሐሳዌ መሲሕም ለክርስቲያኖች አውሬ በመሆን በኢየሱስ ክርስ ቶስ ስም ሲጠራ ያገኘውን ሁሉ በጦሩ ከመው.ነት በሰይፉ ከማረድ ወደኋላ ስለማይል አውሬ ተብሏል።

አውሬ ደም ልሶ ብርንዶ ጉርሶ አጥንት ከስክሶ እንደ ሚኖር በጭካኔው አንጻርም ርኅራኄ እንደሌለው ሐሳዌ መሲ ሕም የክርስቲያኖችን ደም ያፈሳል። አጥንታቸውን ይከስክሳል ሥጋቸውን ለመቃብር ያጉርሳል። ይህን ክፉ ተግባር ሲፈጽም ሰብአዊ ርኅራኄ ውስጡን አይከራከረውም ርኅራኄ እንደማይጠ በቅበት እንደ በረኸኛው አውሬ ይሆናል። ይህን ክፉ ተግባሩን በራእይ የተመለከተው ዮሐንስ አውሬ የሚል ቅጽል ስም ሰጥቶታል።

## አውሬው ከባሕር ሲወጣ መታየቱ

ባሕር ሰፊ ዓለም ነው፤ በውስጡም ብዙ ጉድ ይገኛል። በባሕር ውስጥ የሚገኙ ፍጥረቶችን ሰው ሊያውቃቸውም ሊቆ ጥራቸውም አይችልም። ብዙዎቹም ከመታየት የዘለሉ ናቸው። የአራዊት /የአውሬዎች/ መዲናቸው በደን የተሸፈነ መሬት ወይም የብስ ብቻ አይደለም። ባሕርም የአውሬዎች መዲና ናት። ባሕር ያለመደቻቸው አውሬዎች ብዙዎች ናቸው። አውሬ የተባለው ሐሳዌ መሲሕም ከባሕር ሲወጣ መታየቱ ስፍር ቁጥር የሌለው ወንጀልን ስለሚፈጽም ነው። የሚፈጽማቸው ስሕተቶችም



www.ethiopianorthodox.org

ዛሬ ከመታየት ማዶ ስለሆኑ ነው:: ሁለተኛም ከባሕር ሲወጣ መታየቱ ሐሳዌ መሲሕ በሰፌ ከተማ ላይ መንገሡን ያመለክታል:: ባሕር የተባለች ሐሳዌ መሲሕ የሚነግሥባት ከተማ ናት:: ባሕር መባሏም በባሕር ውስጥ ብዙ በኅብረተሰቡ ዘንድ የሚታወቁና የማይታወቁ አራዊት /አውሬዎች እንደሚኖሩ ሁሉ አውሬ የተባለው ሐሳዌ መሲሕም ብዙ ከሚሆኑ የክሕደት ተባባሪዎቹና ሠራዊቱ ጋር በከተማ ነግሦ ስለሚኖር ነው:: ባሕር በነፋስ በማዕበል ሞገድ የሚነዋወጥ የሚታወክ እንደመሆኑም የሐሳዌ መሲሕ ከተማ ብዛታቸው እንደ ሰማይ ኮከብ እንደ ባሕር አሸዋ በሆነ ጎግ ማጎግ በሚባሉ ተቃዋሚዎች ትጥለቀለቃለች ትታወካለች ማለት ነው::

ይህችም ከተማ ሐሳዌ መሲሕ የሚነግሥባት ኢየሩሳሌም ናት:: ሰላሟን ኢየሱስ ክርስቶስን አልተቀበለችምና ለምን ጊዜውም ሰላም አታገኝም «ሰላምሽ ከዓይንሽ ተሰውሯል ጠላቶችሽ ቅጥር ይቀጥሩብሻል ይከብቡሻል» ሉቃ. 19÷41-44 በማለት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረው ትንቢታዊ ቃል መፈጸሙን በዘመነ ጥጦስ ጀምሮ በዘመነ ሐሳዌ መሲሕ ይጨርሳል::

## የአውሬው ሰባት ራሶች

ዮሐንስ ያየው አውሬ አሥር ቀንዶችና ሰባት ራሶች አሉት አሥር ቀንዶች ሰባት ራሶች በምዕራፍ 17÷9-14 ነገሥታት ተብለው ተተርጉመዋል:: የቤተክርስቲያናችን ሊቃውንት አበውም የሚከተለውን ትርጉም ሰጥተዋል:: ሰባት ራሶች በመባል የተገለጹት ሰባቱ ነገሥታት እግዚአብሔርን የማያውቁ በኃይላቸውና በሥልጣናቸው የሚመኩ አንዳንዶችም ራሳቸውን እግዚአብሔር ለማድረግ ሞክረው ያልተሳካላቸው ከሐዲዎች ናቸው ይላሉ:: ከሰባቱ ነገሥታት አምስቱ ወድቀዋል ይላል:: የወደቁት አምስቱ ራእዩ ከመታየቱ በፊት የነበሩት በጭካኔ በክሕደትና በአረማዊነት የታወቁት እነፈርዖንን እነናቡከደነፆርን እነሰናክሬምን የመሳሰሉ ክፉዎች ነገሥታት ናቸው:: «አንዱም አለ» የተባለውም ዮሐንስ ራእዩን ባየበት ጊዜ የነበረ የአረማውያን ንጉሥ /መሪ/ ነው:: «የቀረውም ገና አልመጣም» የተባለው





ደግሞ ገና ወደፊት የሚመጣ ሐሳዌ መሲሕ ነው በማለት አመሥጥረው ተርጉመዋል::

ሌላው የሰባቱ ራሶች ትርጓሜ እንደሚከተለው ነው:: ሰባት ራሶች የተባሉ ሰባት አርእስተ ኃጣውእ /የኃጢአት ዋናዎች/ ወይም ታላላቅ ኃጢአቶች ናቸው:: አውሬው ሰባት ራሶች አሉት ማለት እነዚህ ዋና ዋና ኃጢአቶች በአውሬው በሐሳዌ መሲሕ ጊዜ ይሠራሉ ራሱ ሐሳዌ መሲሕና ተከታዮቹ መሰሎቹም ይሠሯቸዋል ማለት ነው::

ሰባቱ አርእስተ ኃጣውእ

1ኛ. ኃጢአተ አዳም
2ኛ. ቅትለተ አቤል
3ኛ. ጥቅመ ሰናዖር
4ኛ. ኃጢአተ ሰዶም
5ኛ. ኃጢአተ እስራኤል
6ኛ. ቅትለተ ዘካርያስ
7ኛ. ሞተ ወልደ እግዚአብሔር ናቸው::

እነዚህም ሲዘረዘሩና ሲተነተኑ:-

1ኛ ኃጢአተ አዳም /የአዳም ኃጢአት/

የአዳም ኃጢአት አምላክነትን መመኘት ለፈጣሪ አለመታዘዝ ነው:: ዘፍ. 3÷4-8 እግዚአብሔር አምላክ አዳምን በምድር ላይ ካሉ ፍጥረታት ሁሉ አልቆና አብልጦ አክብሮ የፍጥረታት ሁሉ ገዥ አድርጐ ከፈጠረው በኋላ አዳም ፍጡር መሆኑና እግዚአብሔር ፈጣሪ መሆኑ ይታወቅ ዘንድ በገነት ካሉት ዛፎች መካከል አንዱን ዕፀ በለስን እንዳይበሉ አዳምንና ሚስቱን አጥብቆ አዘዛቸው::

የተንኰል አባት ዲያብሎስ ሁለቱን ፍጡራን ከፈጣሪያቸው ከእግዚአብሐር ጋር ለማጣላት ስለፈለገ አትብሉ የተባሉትን ዕፀ በለስ ቢበሉ እንደ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር እንደሚያውቁና የእግዚአብሔርን ቦታ መያዝ እንደሚችሉ ጠቁሞ አስጐመጃቸው:: የዲያብሎስ ሐሰት እውነት መስላ የታየቻቸው አዳምና ሔዋን ይህን ከፍተኛ ቦታ ለማግኘት ጓጉተው የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በስተጀርባቸው አስቀምጠው የዲያብሎስን ምክር ለማየት ሆር አሉ::

የእግዚአብሔርን አምላክነት ለመጨበጥ መጀመሪያ እጇን ወደ ዕፀ በለሱ መዘርጋት ወይም መላክ እንዳለባት ከሰይጣን ምክር የተቸረችውና የተለገሠችው ሔዋን በዘረጋችው



www.ethiopianorthodox.org

እጇ ያን ዕፀ በለስ አምጥታ በላች:: ለአዳምም አበላችው:: እግዚአብሔርም እንደተናገረ ሁለቱ ሞቱ የአዳምና የሔዋን አምላክነትን መሻት /መፈለግ/ ታላቅ ኃጢአት በደል ሆኖ ተቆጠረባቸው::

የአዳም ኃጢአት በሐሳዊ መሲሕ ዘመን ይሠራል ማለት የአዳምን ዘር ሁሉ ሲያደማ የኖረው አምላክነትን በመፈለግ ምክንያት በዓለም ላይ የበቀለውን የኃጢአት እሾህ ወልደ እግዚአብሔር ሰው ሆኖ ሥጋ ለብሶ በመስቀሉና በሞቱ ነቅሎ ከጣለው በኋላ ዳግመኛ በሐሳዊ መሲሕ ጓሮ ይበቅላል ማለት ነው:: አዳምና ሔዋን እግዚአብሔር መሆንን ተመኙ እንጂ እግ ዚአብሔር ነን አላሉም:: ሐሳዊ መሲሕ ግን እኔ እግዚአብሔር ነኝ እመኑብኝ ይላልና በአዳምና በሔዋን ማሳ ከበቀለው ይልቅ በሐሳዊ መሲሕ ማሳ የሚበቅለው የኃጢአት እሾህ እጅግ የበለጠ ስለሚሆን በቅጠሉና በልምላሜው ምድርን ያለብሳታል::

2ኛ. ቅትለተ አቤል /የአቤል መገደል/

አቤል ቅንና የዋህ እግዚአብሔርን የሚፈራ ጻድቅ መሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጿል:: አቤልና ወንድሙ ቃኤል ለእግዚ አብሔር መሥዋዕትን ባቀረቡ ጊዜ እግዚአብሔር የአቤልን መሥዋዕት ወደደ:: የአቤል መሥዋዕት በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደው አቤል ጻድቅና አማኝ በመሆኑ እንደሆነ መጽሐፍ ቅድስ ይናገራል:: ዕብ. 11÷4 ጠማማ ልቡናን ተንኰልን በውስጡ ይዞ መሥዋዕትን በማቅረቡ እግዚአብሔር መሥዋዕቱን ያልተቀበለለት ቃኤል ግን ልቡናውን ማቅናትና ተንኰሉን ወርውሮ መጣል ሲገባው በቅናት ተነሣስቶ ወደ ወንድሙ ወደ አቤል ድንጋይ መወርወርን መረጠ:: የአቤልን ንጹሕ ደም አፈ ሰሰ:: ዘፍ. 4÷4-8 አቤል ሳይበድል የተበደለ ሳይገድል የተገደለ ያለኃጢአት የሞተ ጻድቅ ሰው ነው::

ቅትለተ አቤል /የአቤል መገደል/ ከሰባቱ የሐሳዊ መሲሕ ኃጢአቶች አንዱ ይሆናል ማለት አቤል ለሁለተኛ ጊዜ ይገደላል ማለት ሳይሆን በአቤል ላይ የተፈጸመው ግፍ በሐሳዊ መሲሕ ጊዜ በሚኖሩ ምእመናን ላይ ይፈጸማል ማለት ነው:: ቃኤል የሰይጣን ማደሪያ በመሆኑ ጻድቅና ታማኝ እግዚአብሔርን የሚፈራ ወንድሙን አቤልን በቅናት እንደገደለው ሁሉ ሐሳዊ





መሲሕም ቃኤልን ሆኖ የእግዚአብሔርን ስም የሚጠሩትን የእግዚአብሔርን ወዳጆች ይገድላቸዋል:: የምእመናንን ንጹሕ ደም ያፈሳል:: የአቤል ወንድሞች የንጹሐን ጻድቃን መገደል ለሐሳዊ መሲሕ ትልቅ ኃጢአት ሆኖ ይቆጠርበታል::

3ኛ. ጥቅመ ሰናዖር /የሰናዖር ግንብ/

ሦስተኛ ኃጢአት ተብሎ የተቆጠረው ጥቅመ ሰናዖር ነው:: ጥቅመ ሰናዖር ሲባል በሰናዖር ሜዳ ላይ የተሠራው ግንቡ ሳይሆን ግንቡን የገነቡት የሰዎች ሕገ ወጥነት ነው:: ኃጢአት የተባለው የሰዎች ሕገ ወጥነት ነው:: ከጥፋት ውኃ በኋላ ሰዎች ተሰባስበው ስማቸውን ለማስጠራት ትልቅ ግንብ መሥራትን ጀመሩ በትዕቢትና በትምክህት ተሞልተው ሰማይ ጠቀስ ገንብ ለመሥራት ስለጀመሩና እግዚአብሔርንም ስለአልፈሩት እግዚአ ብሔር አንዱ የአንዱን ቋንቋ እንዳይሰማው ቋንቋቸውን በመደ ባለቅ አምላካዊ ኃይሉን በዐመፀኞች ሰዎች ላይ ገለጠ:: በምድር ላይም በተናቸው የተሰበሰቡበት ቦታም ባቢሎን ተባለ::ትርጉሙም መበተን /ዝርወት/ ድብልቅልቅ ማለት ነው:: ዘፍ. 11÷1-9

በመጽሐፍ ቅዱስ ከሚተረከው ታሪክ ሌላ መምህራን አጣፍጠው አቀነባብረው በጉባኤ ቤት /በትምህርት ቤት/ የሚ ተርኩት ለደቀመዛሙርትም የሚያስተምሩት ታሪክ እንደሚከ ተለው ይቀርባል:: ከማይ አይኅ በኋላ የተወለዱ ልጆች አባቶቻ ችን በጥፋት ውሃ ያለቁ ግንብ ባይሠሩ ነው ማየ አይኅ /የጥፋት ውኃ/ በወረደ ጊዜ የምንጠጋበት ትልቅ ግንብ እንሥራ ብለው መከሩ:: ሰይጣንም ይህን ሐሳባቸውን ምክንያት አድርጎ ከፈጣሪያቸው የሚያለያይ ምክር ለገሣቸው:: ራሱ ወደ ሰማይ የሚደርስ ግንብ ሠርተን ከሰማይ ሆኖ የጥፋት ውኃ እያወረደ አባቶቻችንን ያጠፋቸውን ባለቤቱን ወግተን እንግደለው ብለው እንዲመክሩ አደረጋቸው:: የሰይጣንን ምክር ተቀብለው ከምሥ ራቅ ተነሥተው ወደምዕራብ በሔዱ ጊዜ ሰናዖር የሚባል ሰፊ ሜዳ አገኙ:: ግንቡን የሚያሠሩ 72 አለቆች /የሕንፃ ኮሚቴ/ መርጠው ሹመው መሥራት ጀመሩ:: የግንቡ ቁመት 5433 ክንድ ከሁለት ስንዝር /2716 ሜትር/ የሚሆን ነበር:: ይህንም ለመሥራት አርባ ሦስት ዓመት ወስዶባቸዋል::



www.ethiopianorthodox.org

ከዚህ በኋላ እግዚአብሔርን ለመውጋት ፍላፃቸውን ወደላይ መወርወር ጀመሩ:: በአየር ያሉ አጋንንት ደም የተቀባ እያስመሰሉ መለሱላቸው:: እነርሱም አሁን ባለቤቱን ወጋነው አሁን አጋፋሪውን ወጋነው አሁን ቢትወደዱን ወጋነው እያሉ ከሰማያዊ ንጉሥ ጋር በአደረጉት ጦርነት ድልን እንደአገኙ አድርገው ተመኩ:: ትዕግሥተኛው አምላክ እግዚአብሔርም ከትዕቢት ወደትሕትና የማይመለሱ ስለሆኑ ፍጡርነታቸውንና ደካማነታቸውን የእርሱንም ፈጣሪነትና ኃያልነት ለማሳወቅ አንዱን ቋንቋቸውን በ72ቱ አለቆች ልክ ከሰባ ሁለት ከፋፈለባቸው ደባለቀባቸው::

ከዚህ በኋላ እርስ በእርሳቸው ተለያይተው ትተውት ሄደዋል:: የሠሩትንም ግንብ ነፋስ ገለባብጦ ጥሎታል:: በሰናዖር ሜዳ የተሰበሰቡ ሰዎች በጥበባቸው ከእግዚአብሔር ቁጣ ለመዳንና እግዚአብሔርንም ለመውጋት የተነሱ የልብ እውሮች ናቸው:: ሐሳዌ መሲሕም ይሕን ታሪክ በመድገም የእግዚአብሔርን ቦታ ለመያዝ ራሱን እግዚአብሔር አድርጎ ከእግዚአብሔር ጋርና ከቅዱሳኑ ጋር ይዋጋል:: እንዲህ ስለሚሆን በሰናዖር ሜዳ የተሠራው ኃጢአት በሐሳዌ መሲሕ ዘመን ይሠራል ማለት ነው::

## 4ኛ. ኃጢአተ ሰዶም /የሰዶም ኃጢአት/

ሰዶም በዝሙት ኃጢአት የታወቀች ሀገር ናት:: በተለይም ወንድ ከወንድ ሴት ከሴት ጋር በሚፈጽሙት የዝሙት ዓይነት ትታወቃለች:: ዘፍ. 19÷5-29 ሰዶምና ገሞራ በሚባሉት ከተሞች የሚኖሩ ሰዎች እግዚአብሔርን የማይፈሩና የማያመልኩ ኃጢአት ሠረተው የማይሰለቹ ነበሩ:: በተለይም ከተሞቻቸው በሚታወቁበት በሚጠሩበት ወንድ ከወንድ ሴት ከሴት ጋር በሚፈጽሙት የዝሙት ዓይነት የረከሱ ሰዎች ነበሩ:: ኃጢአትን መደመር እንጅ መቀነስ የማያውቁ የሰዶምና የገሞራን ሰዎች እግዚአብሔር ሊያጠፋቸው ወሰነ:: በከተማቸው መካከል የነበረ መጥፎ ልምዳቸውን ይተዉ ዘንድ ይመክራቸውና ያስተምራቸው የነበረ ኃጢአታቸውን ያልተሳተፈ ርኩሰታቸውን የተጸየፈ ሎጥን ከምትጠፋው ከተማ ያወጡት ዘንድ





ሁለት መላእክትን ልኮ ከአስወጣው በኋላ ሰዶምንና ገሞራን በእሳትና በዲን አጠፋቸው::

ጥፋታቸውም በየጊዜው ለሚነሣው ትውልድ ትምህርት ሰጭ ሆኖ ይኖራል:: በሰዶምና በገሞራ ላይ የእሳት ዝናብ እንዲዘንብ ያስደረገ ይህ ኃጢአት በሐሳዌ መሲሕ ዘመን ከሐሳዌ መሲሕ ጋር በሕዝቡ ላይ አድሮ ይነግሣል:: ሰዎች የዚህ ኃጢአት ሰለባ የሚሆኑት እግዚአብሔርን መፍራትና ማምለክ ሲተዉ ለጣዖታት ሲሰግዱ ነው:: ሮሜ. 1÷22-27 በሐሳዌ መሲሕ ዘመን የሚኖሩ ሰዎችም እግዚአብሔርን ረስተው ዘንግተው አምልኮተ እግዚአብሔርን በአምልኮተ ሐሳዌ መሲሕ ስለሚለውጡ ለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ሊንበረከኩ የተፈጠሩ ሲሆኑ ለጣዖታዊ ሐሳዌ መሲሕ ስለሚንበረከኩ የዚህ አስነዋሪ ኃጢአት ምርኮኞች ይሆናሉ::

## 5ኛ. ኃጢአተ እሥራኤል /የእሥራኤል ኃጢአት/

እሥራኤል የሠሩት የኃጢአት ዓይነት ብዙ ቢሆንም አሁን ሊጠቀስ የተፈለገው ለጣዖት መንበርከካቸው ብቻ ነው:: እሥራኤል የእግዚአብሔር ወዳጆች የአብርሃም ልጆች በመሆናቸው እግዚአብሔር የወደዳቸው የመረጣቸውና ያከበራቸው ወገኖች ነበሩ:: ተስፋ የተሰጣቸው፣ ሱባዔ የተቆጠረላቸው፣ ትንቢት የተነገረላቸው፣ አበው በረከታቸውን የለገሷቸው፣ የበረከት ልጆች ነበሩ:: እግዚአብሔር ከበላቸውና ከዋጣቸው ዘንዶ ከፈርዖን ሆድ መንጥቆ ያወጣቸው፣ ፈርዖን ያስማራቸው የግብዕ አራዊትም /አውሬዎችም/ እንዳይነጥቋቸው፣ በደመና አጥር አጥሮ የጠበቃቸው፣ ባሕረ ኤርትራን ከፍሎ ያሻገራቸው፣ እንደጓሮ ተክል የተንከባከባቸው ምርጥ ዘሮች ነበሩ:: ለወላጆቹ አንድ የሆነ ልጅ ወይም የመጀመሪያ ልጅ የጠየቀው ሁሉ እንደሚሟላለት እግዚአብሔርም ወልድየ ዘበኩርየ /የበኩር ልጆቼ/ ዘጸ. 4÷22:: ያላቸው እሥራኤልን አንድ ልጅ ብቻ እንዳላቸው ወላጆች የሚንከባከብ እንደመሆኑ ብዙ ተአምር ብዙ ምልክት ብዙ ድንቅ ነገር አድርጎላቸው ነበር:: እሥራኤል ግን ይህን ሁሉ እንክብካቤ ረስተው ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይኑሩህ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝና የሚለውን አምላካዊ ቃል አቃለው ሙሴ ወደ ሲና ተራራ



www.ethiopianorthodox.org

ወጥቶ ቢዘገይ በአሮን እጅ የጥጃ ምስል አሠሩ:: አታምልኩት የተባሉትን አመለኩ፣ አትስገዱለት ለተባሉት የወርቅ ስብስብ ወድቀው ስገዱለት፤ መሥዋዕት ሠውለት ዘጸ. 32÷1-35:: «የበሬን ምስጋና ፈረስ ወሰደበት» እንዲባል ከግብፅ ያወጣቸው እግዚአብሔር ሆኖ ሳለ አሮን ያቆመላቸውን ምስል ከግብፅ ያወጣን አምላክ ነው ብለው አመሰገኑት::

ፍጡር ከሚሠራቸው ኃጢአቶች ሁሉ የሚበልጠውና ታላቁ ኃጢአት ፈጣሪውን መተው ነውና የእግዚአብሔር ቁጣ በእሥራኤል ላይ ነደደ:: ይህ ታላቅ ኃጢአት እሥራኤልና እግዚአብሔር የተሳሰሩበትን የፍቅር ገመድ በጠሰ:: ከዚህም የበለጠ ትልቅ ኃጢአት የለም::

ይህ ትልቅ የኃጢአት ግንድ በክርስቶስ ሞት በሐዋርያት ስብከት ቢቆራረጥም በሐሳዌ መሲሕ ዘመን ተመልሶ ያለመል ማል:: ሐሳዌ መሲሕ ውሃ እያጠጣ ያሳድገዋል:: ብዙ የዲያብ ሎስ ጫጩቶች በቅርንጫፉ ላይ ይቀመጣሉ:: በአጭሩ የእሥራ ኤል ኃጢአት በሐሳዌ መሲሕ ዘመን ይደገማል:: አምልኮተ ጣዖት ይስፋፋል ማለት ነው::

6ኛ. ቅትለተ ዘካርያስ /የዘካርያስ መገደል/

የካህኑ የዮዳሄ ልጅ ዘካርያስ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የተላለፉትንና ሕጉን የማይጠብቁትን ሰዎች ገሠጻቸው:: እግዚ አብሔርን ስለተዋችሁት እግዚአብሔርም ትቷችኋል:: በማለት መንፈስ ቅዱስ የገለጸለትን ትንቢት ተናገረ:: የእግዚአብሔርን መንገድ ለቀው ሌላ መንገድ ይጠርጉ የነበሩት ንጉሡ ኢዮአስና መሰሎቹ ግን ደንግጠው ንስሐ መግባት ወደ እግዚአብሐርም መመለስ ሲገባቸው የእግዚአብሔርን መልእክት የተሸከመ ዘካ ርያስን ለመግደል ተማማሉ:: በንጉሡ በኢዮአስ ትእዛዝ በእግ ዚአብሔር ቤት አደባባይ ውስጥ በድንጋይ ወግረው ገደሉት:: 2ዜና. 24÷20-22::

ሁለተኛም የበራክዩ ልጅ ዘካርያስ በዚህ ዓይነት አሟ ሟት ሞቷል:: ይኸውም ዘካርያስ የመጥምቁ ዮሐንስ አባት ሕገ እግዚአብሔርን ጠብቆ የሚኖር ጻድቅ ካህን ነበር:: ሄሮድስ የክርስቶስን መወለድ ከሰባ ሰገል ከሰማ በኋላ ክርስቶስ የአይሁድ ንጉሥ በመባሉ መንግሥቴን ይወስዳል የሚል ሥጋት ስላደረ





በት ክርስቶስን ለመግደል አቀደ:: ንጉሥ የተባለው ክርስቶስ ግን የት ላይ እንዳለና የትኛው እንደሆነ ማወቅ አልተቻለውም:: ስለሆነም ከብዙ ሕፃናት መካከል አንዱ ክርስቶስ ሳይሆን አይቀርም በማለት በቤተልሔም ዙሪያ ያሉትን ከሁለት ዓመት በታች የሆኑትንና በሁለት ዓመት ውስጥ የእድሜ ክልል የሚገኙትን ሕፃናት ማስገደል እንደአማራጭ አድራጐ ወሰደ::

የካህኑ የዘካርያስ ልጅ ዮሐንስም በዚህ የእድሜ ክልል ውስጥ ነበር:: ይልቁንም ዮሐንስ ከሌሎቹ ሕፃናት በተለየ ሁኔታ ክርስቶስ ይሆናል ተብሎ የሚገመትበት ታሪክ ነበረው:: መልአኩ ቀዱሰ ገብርኤል ዮሐንስ እንደሚወለድ ለዘካርያሰ የነገረውን ትንቢታዊ ቃል ዘካርያሰ ባለማመኑ ዮሐንስ ተጸንሶ እስኪወለድ ድረስ የዘካርያስ አንደበት ተዘግቶ ዲዳ ሆኗል:: ዮሐንስ ከተወለደ በኋላ ግን የዘካርያስ አንደበት ተከፍቷል መናገርም ችሏል:: ለዮሐንስ ይህ ድንቅ ነገር ተደርጐለታል:: ሉቃ. 1÷20-22፤ 1÷63

የዮሐንስን ታሪክ የሚያውቁ ሰዎች በተጸነሰ ጊዜና በተወለደ ጊዜ እንዲህ ያለ ተአምር ያደረገ የዘካርያስ ልጅ አለ:: እርሱ አንተ የምትፈልገው ክርስቶስ ሊሆን ይችላል ብለው ክርስቶስን ለሚፈልግ ሄሮድስ ነገሩት:: ሄሮድስም ብዙ ጭፍሮችን ወደዘካርያስ ቤት ሰደደ:: ነገር ግን መልአከ እግዚ አብሔር ዮሐንስንና ኤልሳቤጥን ነጥቆ ወደ በረሀ ስለወሰዳቸው ከሄሮድስ የተላኩት ጭፍሮች ዮሐንስን አላገኙም:: በዮሐንስ አለመገኘት የተናደደው ሄሮድስ ዘካርያስን እንዲገድሉት ጭፍ ሮችን አዘዘ:: ካህኑ ዘካርያስ በቤተመቅደስ አገልግሎት ላይ እንዳለ በመሠዊያውና በቤተ መቅደሱ መካከል ገደሉት:: ስንክሳር መስከረም 8 ቀን ይመልከቱ::

በሐሳዌ መሲሕ ዘመን ቅትለተ ዘካርያስ /የዘካርያስ መገደል/ ይደገማል ሲባል እኒህ ሁለቱ ዘካርያሶች ለሁለተኛ ጊዜ ይገደላሉ ማለት አይደለም:: ሁለቱ ዘካርያሶች እግዚአብ ሔርን በማገልገልና ቃሉን በመሸከም እንደተገደሉ ሁሉ እግዚ አብሔርን የሚያገለግሉ ካህናት በሐሳዌ መሲሕ ዘመን ይገደላሉ ማለት ነው እንጂ በቤተ መቅደስ የሚያገለግሉ፣ የሚቀድሱ የሚያወድሱ፣ የክርስቶስን ስም የለበሱ፣ ለስብከተ ወንጌል የሚ ፋጠኑ በሐሳዌ መሲሕ የማያምኑ ካህናት በእግዚአብሔር ቤት



www.ethiopianorthodox.org

መቅደስ አካባቢ በሰማዕትነት ይሞታሉ:: ኢዮአስና ሄሮድስ በጠረጉት የዓመፅ መንገድ ሐሳዌ መሲሕም ያልፍበታል:: በሐሳዌ መሲሕ ጊዜ የማይሠራ የኃጢአት ዓይነት አይኖርምና ከሚፈጽማቸው ታላላቅ ኃጢአቶች አንዱ የንጹሐን ሰዎችን ደም ማፍሰስ ይሆናል::

7ኛ. ሞተ ወልደእግዚአብሔር /የወልደእግዚአብሔር ሞት/

ነቢዩ ኢሳይያስ «በአፉም ተንኮል አልተገኘበትም ነበር ከዓመፀኞችም ጋር ተቆጥሮአል» ኢሳ. 53÷1-12 ብሎ የመሰከረለት ወልደ እግዚአብሔር፣ ፈሪሳዊ ኒቆዲሞስ «ሕጋችን አስቀድሞ ከእርሱ ሳይሰማ ምንስ እንዳደረገ ሳያውቅ በሰው ይፈርዳልን?» ዮሐ.7÷51 ብሎ አእምሯቸውን ከአጡ ከወንድሞቹ ከፈሪሳውያን ጋር የተከራከረለት ወልደ እግዚአብሔር፣ እውር ሆኖ የተወለደውና ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ ዓይኑን ያበራለት ሰው ኃጢአተኛ ስላለመሆኑና ወልደ እግዚአብሔር ስለመሆኑ በጠላቶቹ በአይሁድ ፊት የመሰከረለት ወልደ እግዚአብሔር፣ ሮማዊ ጲላጦስ እኔስ አንዲት በደልስ እንኳ አላገኘሁበትም ዮሐ. 19÷4-6 ብሎ የመሰከረለት ወልደ እግዚአብሔር፣ እግዚአብሔር አብ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው ብሎ በዮርዳኖስ የመሰከረለት ወልደ እግዚአብሔር፣ ዮሐንስ መጥምቅ ጫማውን ልሸከም አይገባኝም ከእኔ በኋላ የሚመጣው ከእኔ ይበረታል ማቴ. 3÷11 ብሎ የመሰከረለት ወልደ እግዚአብሔር፣ ምንም ስለንጹሕነቱና ስለጻድቅነቱ የሚመሰክሩለት ምስክሮች በሰማይም በምድርም ቢበዙ ያለኃጢአት ያለበደል ሞተ::

ያለ ኃጢአት በመሞቱ የኛ የኃጢአት ሸክም ቢቀልም የሞት ፍርድ በፈረዱበት በአይሁድ ላይ ግን ሊሸከሙት የማይችሉት የኃጢአት ክምር ተከምሮባቸዋል:: ኃጢአታችን አርጅቶ የአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሽማግሌ ሆኖ በሞተበት ቀን በዕለተ ዓርብ የአይሁድ ኃጢአት ተወልዶ ተተካ:: አይሁድ የእግዚአብሔርን በግ በ30 ብር ገዝተው ሥጋውን ባለመብላታቸው ኪሳራን ሳይከናነቡ አልቀሩም:: ከአዳምና ከልጆቹ ቤት ወጥቶ ወደውጭ የፈሰሰውን የኃጢአት አተላ የዲያብሎስ አህዮች ቀያፋና ሐና ሲሽቀዳደሙበት ታይተዋል:: በአጭሩ





የውልደ እግዚአብሔር በግፍ መሞት በአይሁድ ላይ ትልቅ ኃጢአት ሆኖባቸዋል::

በሐሳዌ መሲሕ ዘመን ሞተ ወልደ እግዚአብሐር ይደረጋል ማለት ወልደ እግዚአብሔር ዳግመኛ ይሞታል ማለት አይደለም:: ዳግመኛ በጲላጦስ አደባባይ ለፍርድ አይቀርብም ስቀለው ስቀለው የሚል የአይሁድ ጩኸት ዳግመኛ አይሰማም:: ዳግመኛ በመስቀል ላይ በሁለቱ ወንበዴዎች አይታጀብም እንደ ብሉዩ ሊቀ ካህናት ራሱን እየደጋገመ አይሠዋም::

ነገር ግን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እውነት ስለተናገረ ድውይ ስለፈወሰ ሙት ስለአስነሣ አጋንንትን ስለአወጣ ኅብስት አበርክቶ ስለአበላ የተለያዩ ታምራትን ስለአደረገ ጥቅም ፈላጊዎች ወግ አጥባቂዎች ፈሪሳውያን ራሳቸው የተበተቡት ትብትባቸው እንዳይፈታና ጥቅማቸው እንዳይነካ በቅንዓት በምቀኝነት እንደገደሉት ሁሉ በሐሳዌ መሲሕ ጊዜም ስለእውነተኛው አምላክ እውነት የሚመሰክሩ ምእመናን ያለኃጢአት ያለበደል ይሞታሉ ማለት ነው:: ንጹሕ የአምላካቸው ደም በፈሰሰበት ቦታ ንጹሕ ደማቸው ይፈሳል:: በወልደ እግዚአብሔር ሞት አንጻር የምእመናን ሞት ይታያል:: አይሁድ በቀራንዮ በክርስቶስ ላይ የፈጸሙትን ወንጀል ሐሳዌ መሲሕ በክርስቶስ ተከታዮች ላይ ይፈጽመዋል:: በአጭሩ ሞተ ወልደ እግዚአብሔር በሐሳዌ መሲሕ ዘመን ይሆናል ማለት አይሁድ የወልደ እግዚአብሔርን ንጹሕ ደም በማፍሰስ ከፈጸሙት ወንጀል ጋር ተመሳሳይ የሆነ የምእመናንን ንጹሕ ደም የማፍሰስ ወንጀልን ሐሳዌ መሲሕ ይፈጽማል ማለት ነው::

## የአውሬው ዐሥር ቀንዶች

ዐሥር ቀንዶች የተባሉ ገና ወደፊት ከአውሬው ከሐሳዌ መሲሕ ጋር የሚነግሡ ዐሥር ነገሥታት ናቸው:: ከአውሬው ከሐሳዌ መሲሕ ጋር አንድ ሐሳብ አላቸው:: ሥልጣናቸውም በአውሬው በሐሳዌ መሲሕ የበላይነት የታቀፈ ነው:: ራእይ 17÷12-14 እነዚህ ዐሥሩ ነገሥታት የሐሳዌ መሲሕ አምላክነት ተቀባይነት እንዲኖረው በኃይልም በዘዴም የተቻላቸውን ያህል



www.ethiopianorthodox.org

ይታገሳሉ:: የእውነተኛውን ክርስቶስን ቦታ ለሐሰተኛው ክርስቶስ ለመስጠት ይሯሯጣሉ:: እንደቀበሌ አስተዳዳሪ በደጋፊዎች ብዛት በሰው አእምሮ ግምት የአምላክነት ሹመት የሚገኝ መስሎአቸው እጃቸውን ያነሱለታል:: ከሐሰተኛው ክርስቶስ ጋር በመቆም እውነተኛውን ክርስቶስን ይቃወሙታል::

## አውሬው ምን ይመስላል

«የአየሁትም አውሬ ነብር ይመስል ነበር:: እግሮቹም እንደድብ እግሮች አፉም እንደአንበሳ አፍ ነበሩ» ራእይ 13÷2 ዮሐንስ አውሬ የተባለው ሐሳዌ መሲሕን ሲያየው ተፈጥሮው ሰብአዊ ተፈጥሮ ቢሆንም የተስተካከለ የሰው ቁመና አልነበረውም:: አካሉ ቆቅሻም /ቋቁሻማ/ እከካም ነበር:: አንደኛው ዓይኑ የሞተ ወይም የጠፋ ሲሆን ሁለተኛው ዓይኑ ግን ደም የሠረበው ደም የሚመስል የሚጉረጠረጥ ፈጣጣ ነበር:: አፉም እንደአንበሳ አፍ ከመጠን በላይ የተቀደደ ከንፈሩ የተለጠጠ የተዘለጠ አውራ፣ ጣቱ ጠማማ ነበር፣ እግሩ ወለፎ ወይም ወልጋዳ ነበር፣ ውጭአዊ አካሉ እንዲህ የተበላሸ መሆኑ በውስጡ የተሰወረ የጠባዩን ብልሹነት ይገልጻል:: ውጫዊ መልኩና ውስጣዊ መልኩ ከአውሬዎች ጋር እንጅ ከሰዎች ጋር አይገጥምም::

### ነብር መምሰሉ

ነብር ይመስላል ማለትም ነብር ቁጡ፣ ቁጠኛ፣ ግልፍተኛ፣ ደፋር፣ የፍየል ጠቦት ጠላት «የፍየል ዓይን ወደቅጠል የነብር ዓይን ወደፍየል» እንዲባል የፍየል ጠቦቶችን ወይም ግልገሎችን እየአነቀ የሚያርድ ሰውን የማይፈራ ከመጠን በላይ የሚኮራ መሆኑ ይታወቃል:: ሐሳዌ መሲሕም ፍጡርነቱን አውቀው አምላክነቱን በማይቀበሉት ምእመናን ላይ ይቆጣል ይበሳጫል አውሬያዊ ባሕርዩን ይገልጥባቸዋል:: እንደፍየል ጠቦት እየአነቀ ያርዳቸዋል:: ታማሚ መዋቲ ፍጡር ሲሆን ]ድፍረት እግዚአብሔር ነኝ ይላል:: ዓይናቸውን ወደእግዚአብሔር በሚያነሱና ወደእግዚአብሔር በሚመለከቱ ሰዎች ላይ ደም





የሰረበው ዓይኑን ያነሳል የምእመናን ዓይን ወደ እግዚአብሔር ሲሆን ቁጣን የተመላ የሐሳዌ መሲሕ ዓይን ደግሞ ወደ ምእመናን ይሆናል:: ሐሳዌ መሲሕ በቁጠኛነቱና በግልፍተኛነቱ አጠቃላይ በተዘረዘሩት የተንኰል ገጽታዎቹ ነብርን ይመስላል:: ነብር የክፉ ጠባዩ መገለጫ ሆኗል::

## እግሮቹ እንደድብ እግሮች ናቸው

እግሮቹ እንደድብ እግሮች ነበሩ ማለትም ድብ ከጅብና ከአንበሳ ተደቅሎ የሚወለድ አድብቶ የሚይዝ የሚሸምቅና የሚነጥቅ ጥላው የሚያፈዝ ጥፍሩና ጠጉሩ ረጅም ጅራቱ አጭር የሆነ ኃይለኛ አውሬ ነው:: ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት ገጽ 335 የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ገጽ 223 ይመልከቱ::

የድብ መልክና ጠባይ እንዲህ ሲሆን ሐሳዌ መሲሕም ከነገደ ኢሳውና ከነገደ እስራኤል የተደቀለ አምላክነትን ለመያዝ የሚያደባ የሚሸምቅና ተአምራትን በምትሐት የሚነጥቅ ተንኰሉና ሐሰቱ ረጅም የመንግሥቱ ዘመን አጭር የሆነ ክፉ ፍጡር ነው። ስለዚህ እግሮቹ የድብ እግሮችን መስለው ለዮሐንስ ታይተዋል:: ዳግመኛም የድብ አባት የሆነው ጅብ ሆዳም አግበስባሽና አይመርጤ ነው:: በጅብ መልክ የተገለጠው ሐሳዌ መሲሕም ኃጢአት ሠርቶ በቃኝ የማይል ሆዳም የዐመፅና የተንኰል ዓይነቶችን የሚያግበሰብስ የሚናገረውንም የማይመርጥ የቀን ጅብ ነው::

## አፉ እንደ አንበሳ አፍ መሆኑ

አፉም እንደ አንበሳ አፍ ነበር ማለት አንበሳ በኃይሉና በጀግንነቱ በጥንካሬው የታወቀ ከዱር አውሬዎች ሁሉ በአሸናፊነቱ የበላይነትን የያዘ አውሬ ነው እንስሳትን የሚነጥቅ የሚያደ፦ ደማቸውን የሚያፈስ አጥንታቸውን የሚከሰክስ ሥጋቸውን የሚጐርስ ገናና ስም ያለው የዱር አውሬ ነው:: ሐሳዌ መሲሕም በጨካኝነቱ በመጥፎ ሥራውና በከሐዲነቱ አንደኛውን ደረጃ የያዘ ከከሐዲዎችና ከትዕቢተኞች ከዓመፀኞችም ሁሉ



www.ethiopianorthodox.org

የበለጠ ክፉ ስም ያለው የሰው አውሬ ነው። ገና ሳይወለድ ምድርን ሳይረግጥ ዓለምን የሚያስደነግጥና የሚያንቀጠቅጥ በምድር ላይ እነደተጠመደ ፈንጅ አንድ ቀን ይፈነዳል ተብሎ የሚጠበቅ ለሰው ልጆች ሁሉ ያልተተረጐመ ክፉ ሕልም ነው።

## ሐሳዌ መሲሕ በአራዊት መመሰሉ

አንበሳ ነብር ድብ የእግዚአብሔር የመዓቱ የቁጣው መገለጫዎች ናቸው። እግዚአብሔር ትዕቢተኞችንና ዓመፀኞችን አጠፋቸዋለሁ ሲል እንዲህ ይላል «እኔ እንደ አንበሳ ሆንሁባቸው እንደ ነብርም በመንገድ አጠገብ አደባቸዋለሁ ልጇ እንደ ተነጠቀባት ድብ እገጥማቸዋለሁ» ሆሴዕ 13÷6:8። እነዚህ የተጠቀሡት አውሬዎች ቁጡዎች ኃይለኞችና አስፈሪዎች በመሆናቸው የጥፋት የመቅሠፍት መገለጫ እየሆኑ ይቀርባሉ 2ነገ. 2÷24፣ ጥበ. 11÷18። ሐሳዌ መሲሕም በእነዚህ አውሬዎች መልክ መገለጡ የጨካኝነቱና የአስፈሪነቱ የአጥፊነቱም መጠን ይታወቅ ዘንድ ነው።

ለሐሳዌ መሲሕ ምሳሌ በመሆን የተጠቀሱት ነብር ድብ አንበሳ በዱር እንስሳነታቸው ጠቃሚ ነገር ወይም መልካም ነገርን በጐጂ ተግባራቸው ጐን ለጐን ይዘው ቢገኙ እንኳ በበጐው ነገር ሐሳዌ መሲሕ አይመሰልም። ከደረቀ ግንድ ልምላሜ ወይም ቅጠል እንደማይገኝ ሁሉ ከሐሳዌ መሲሕም መልካም ነገር አይገኝምና። ሐሳዌ መሲሕ በመባል የሚታወቀው ሐሰተኛው ክርስቶስ በክፉነቱ ተወዳዳሪ የሌለው ተንኮልን የተመላ ከመሆኑ የተነሣ የተንኮሉ ገጽታዎችን የሚገልጽ ክፉ ነገር ቢፈለግ ከአውሬ በቀር ሌላ አልተገኘም።

ክፋት ከሰብአዊ ባሕርይ የሚመነጭ ቢሆንም ደረጃ ደረጃ አለው። አንዱ ክፉ ሥራዎችን በመጠኑ ሲያመርታቸው ሌላው ደግሞ በብዛት ያመርታቸዋል። ስንፍ የተንኮል ገበሬ እንዳለ ሁሉ ትጉህ የተንኮል ገበሬም አለ። ተንኮልን እንደ ቁርስ፣ እንደምሳ፣ እንደእራት የሚቆጥሩ ሰዎች አሉ። የለሉ የጠጡ ያህል በክፉ ሥራቸው የሚረኩ ግብዞች ብዙዎች ናቸው። ተንኮል እንደ ጥሩ ወንድም የሚናፍቃቸው ሰዎች





ሕልማቸውንና ቅዠታቸውንም የሚፈቱት ሰውን በመበቀልና በማስለቀስ ነው።

ሐሰተኛው ክርስቶስም ተንኮልን በብዛት የሚያመርት ትጉህ የተንኮል ገበሬ እንደመሆኑ መጠን ክፉ የሚለው ቃል ብቻ የክፋቱና የተንኮሉ መሥፈሪያ መለኪያ ሊሆን አይችልም። እጅግ በጣም ክፉ የከፋ ክፉ እጅግ በጣም ዓመፀኛ የዐመፀኞች ዓመፀኛ ለመሆኑ መለኪያ መሥፈሪያ የሚሆን አውሬ የሚለው ቃል ሊሆን ይችላል። ስለሆነም ዮሐንስ ሐሰተኛውን ክርስቶስን የክፋቱ መገለጫ በሚሆን በአውሬ አምሳል /ምስያ/ ከባሕር ሲወጣ አይቶታል።

## ዘንዶው ማን ነው?

«ዘንዶውም ኃይሉንና ዙፋኑን ትልቅም ሥልጣን ሰጠው» ራእይ 13÷2። ከነብርና ከድብ ከአንበሳም ጋር ለሚመሳሰለው አውሬ /ለሐሰተኛው ክርስቶስ/ ኃይሉንና ዙፋኑን ትልቅም ሥልጣን የሰጠው ዘንዶ ማን ነው? ለሚለው ጥያቄ ዓለሙን ሁሉ ያሳተ ዲያብሎስ ነው ከማለት ውጭ ሌላ መልስ አይሰጠውም። ሰይጣን የተባለውን ዲያብሎስን ዘንዶ ብሎ የገለጸው መጽሐፍ ቅዱስ ነው። «ዓለሙንም ሁሉ የሚያስተው ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ» ራእይ 12÷9።

ዘንዶ ሰውንና እንስሳን የሚውጥ የሚሰለቅጥ በባሕርም በየብስም የሚኖር አውሬ ሲሆን እባብ ደግሞ ተናዳፊ መርዛማ ተንኮለኛ ርጉም አውሬ ነው። ዲያብሎስ የእባብና የዘንዶን ባሕርይ በውስጡ የተሸከመ ስለሆነ እባብና ዘንዶ ተብሏል። ዘንዶ ሰውንም ሆነ እንስሳን ካገኘው ይውጠዋል። በሆዱ ይሸከመዋል። የራሱ ያደርገዋል። የተዋጠው አካል ሕልውናውን ያጣል። ዲያብሎስም የሰውን ዘር ሲያስተው፣ ወደራሱ የክሕደትም ዓለም ውስጥ ሲያስገባው፣ በአምልኮ ጣዖት ጥርሱ ሲያደቀው፣ ሃይማኖታዊ ሕልውናውን ሲያሳጣው፣ ወደራሱ የሥራ ቦታ ሲያሰማራው በባሕረ ኃጢአት ሲያስምጠው ዋጠው ይባላል። 1ጴጥ. 5÷8



www.ethiopianorthodox.org

እባብም ውጫዊ አካሉ የተዋበ ያማረ ለስላሳ ሲሆን
ስጣዊ አካሉ ግን መርዝን የተመላ ነው:: ምላሱ እንደእሾህ
ጉቶ የሚያደማ ነው:: መርዙን የሚሽር መድኃኒት ካልተገኘ
ተቀር በመርዙ የተወጋው ሰው አይድንም:: ከሕዋሳት አንዱን
ፍል እጅን ወይም እግርን ቢነድፍ መርዙ በመላው የሰውነት
ፍል የመሰራጨት ኃይል አለው:: በእባብ የተመሰለው ዲያብሎ
ም ወደሚያስታቸው ሰዎች ሲመጣ የብርሃን መልአክ መስሎ
ደእባብ አካል እንደበቱን አለስልሶ በለስላሳው አንደበቱ
ሸፈነ መርዛማ ሐሳብ አንግቦ ነው:: በአዳምና በሔዋን አካል
ላለፈው የዲያብሎስ መርዝ የአዳምና የሔዋን ዘሮችን በሙሉ
ገድል ኖረ:: የእባቡን መርዝ የሚሽር መድኃኔዓለም ክርስቶስ
ዚ መጣ ድረስ የሚድን አልነበረም:: በመርዛማ ምላሱ
ተወጋ ተወግቶ ያልቆሰለ አልነበረም:: እባብ በብዛት
ገኘው በቆላማ ቦታ ነበር:: ሰይጣን የተባለው እባብ ግን
ውንም ደጋውንም ወሮ በቆላ በደጋ የሚገኙትን የአዳም
ች ሁሉ አደማቸው::

ብዙ ጊዜ ስምና ግብር የ ያያዙ የተሳሰሩ የተዛመዱ
ው:: የዲያብሎስም ክፉ ግብሩ ከዘንዶና ከእባብ ክፉ ግብር
: ውህደት አንድነት ስለአለው ተፈጥሮው መልአክ ቢሆንም
ፈጥሮአዊ ባሕርዩ ጋር የሚስማማ ግብር የለውም:: ፈጣሪን
መስገን ማወደስ መቀደስ ክብሩን መውረስ ለፈጣሪ መገዛት
ን የመሰለውን ሁሉ መልአካዊ ተግባሩን ስለናቀው ስለለቀቀ
ኖ አውሬያዊ ግብርን ስለያዘ በክፉ ግብሩ ዘንዶ እባብ
ገኗል::

## የዘንዶው ውጊያ ከመላእክት ጋር

ዘንዶው ከሚካኤልና ከመላእክቱ ጋር ለመዋጋት ታጥቆ
ነሣ እልኸኛ ፍጡር ነው:: ሚካኤልንና መላእክቱን ለመው
ኃይሉን አጠናክሮ ተሰለፈ:: እግዚአብሔር ከመላእክት
አብልጦና አልቆ ቢፈጥረው ከፍጡራን በላይ መሆን አልበ
ብሎ ክብርን የማይጠግብ ስስታም ስለሆነ የፈጣሪን ክብር
ውረስ በፈጣሪ ቦታ ለመንገሥ ታጥቆ ተነሣ:: ለእርሱ





ድጋፍ በመስጠት ከእርሱ ጋር በመተባበራቸው ከነብራቸው የተራቆቱና ከቆሙበት ቦታ የወደቁ መላእክትም በውጊያው ጊዜ አብረውት ተሰልፈው ነበር::

ሆኖም የውጊያው ድል ለሚካአልና ለመላእክቱ ሆነ «በሰማይም ሠልፍ ሆነ ሚካኤልና መላእክቱ ዘንዶውን ተዋጉ:: ዘንዶውም ከመላእክቱ ጋር ተዋጋ:: አልቻላቸውምም:: ከዚያም ወዲያ በሰማይ ስፍራ አልተገኘላቸውም» ራእይ 12÷7-8 ዘንዶው ከማኅበረ መላእክት አፈንግጦ ከወጣ በኋላና ከማኅበረ አራዊት /ከአራዊት ማኅበር/ ገብቶ ከተቆጠረ በኋላ በመላእክት ላይ በጐ አመለካከት አልነበረውም::

መላእክት በአባታቸው በእግዚአብሔር ቤት ሆነው በእግዚአብሔር ቸርነት ታቅፈው ሲያያቸው የቅናት እሳት ውስጡን አቃጠለውና ዘመቻውን ጀመረ:: የዘመቻውም ውጤት ሲያርስ ከርሞ የአዘመራውን ፍሬ በረዶ እንዳረገፈበት ገበሬ ሆኖበት ከወገኖቹ ጋር ቦታውን ለቆ ተሰደደ «ከዚያም በኋላ በሰማይ ስፍራ አልተገኘ ቸውም» ራእይ 12÷8 ተብሎ እንደተጻፈ ድል የተነሣ ጦር ቦታው መልቀቅ ግድ ነውና ሠራዊቱን ይዞ ሸሸ::

በጉባኤ ቤት እንደሚተረከው በተፈጠረበት በዕለተ እሑድ የመላእክ ፈጣሪ እኔ ነኝ ብሎ ሐሰትን በወለደበት ቀን ከኢየሩሳሌ ሰማያዊት ወደ ኢዮር ወርዷል:: በዕለተ ረቡዕ የፀሐይን፣ የጨረቃንና የከዋክብትን መፈጠር አይተው መላእክት እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ አንተም ፍጡር ነህና አመስግን ቢ ት እኔስ ከማመስገን ነፃ ነኝ ይልቁንም እንደ እግዚአብሔር እናንት እኔን አመስግኑኝ በማለቱ ከኢዮር ወደ ዚህ ዓለም ርዷል:: ከዚህም በኋላ ከመላእክት ጋር ባደረገው ውጊያ በመ ነፉ በዕለተ ሐሙስ ከዚህ ዓለም ወደ ኤንጦርጦስ ወርዷል:: በትዕቢት ላይ ትዕቢት እየጨመረ በሄደ ቁጥር ቦታውን ለቅ ነበር::

የ ድሞ መልአክ ዘንዶው ውጊያውን በመላእክት ብቻ አላቆመ :: ከመላእክት ጋር ባደረገው ትግል የሽንፈት ካባን ቢከናነ ም በምኞት በቀረው የትግል ውጤት ተስፋ ልቆረጠ ም:: ዕለተ እሑድ ከተፈጠሩ ከመላእክት ጋር ታግዬ ከተሸነፍሁና ከወደቅሁ በዕለተ ዓርብ ከተፈጠረ ከአዳም ጋር መታገል አለብኝ ብሎ ወሰነ:: የውጊያ ስልቱንም ቀየረ ከሚካኤልና



www.ethiopianorthodox.org

ከመላእክቱ ጋር ሲዋጋ ከሠራዊቱ ጋር ፊት ለፊት በመሠለፍ ነበር:: ይህ ዓይነት የውጊያ ዘዴ ፍሬ አልባ መሆኑን ስለ ተገነዘበ አዳምን ፊት ለፊት አልተዋጋውም:: መጥቼብሃለሁ ታጠቅ አላለውም:: በእባብ ተሰውሮ ነው የሄደበት በሐሳብ የሚረዳው ጽኑዕ ወዳጅ መስሎ ነው የቀረበው::

ሰይጣን በእባብ አንደበት የተኮሰው ጥይት ግን አዳምንም ሆነ ሔዋንን አልሳተም:: አዳምንና ሔዋንን ጭንቅላት ጭንቅላታቸውን መትቶ ከቆሙበት ለእግዚአብሔር የመታዘዝ ስፍራ እየተወረወሩ እንዲወድቁ አደረጋቸው ሁለቱ ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ ልጆቻቸው ሁሉ በዚህ ጥይት ሲቆስሉና ሲሞቱ ኖሩ::

እባብና ዘንዶ የተባለ ሰይጣን የአዳምን ዘሮች ሲያቆስላቸውና ሲገድላቸው ከቆየ በኋላ ቁስላቸውን የሚፈውስና ደማቸውን የሚመልስ መድኃኔዓለም ክርስቶስ ወደቀራንዮ ወጣ:: ከጥንት ጀምሮ ነፍሰ ገዳይ የሆነውንና ዐመፀኛውን ዲያብሎስን በቀራንዮ በተተከለው መስቀሉ ግምባሩን ብሎ ከማቁሰሉም በላይ ዳግመኛ ሰውን እንዳያቆስልና እንዳይገድል ትጥቁን አስ ፈታው በአምላካዊ ሥልጣኑ አሰረው::

ይኸው ክፉ ጠላት በሐሳዌ መሲሕ ዘመን ከእስራቱ ተፈትቶ ትጥቁን አጠባብቆ ከሐሳዌ መሲሕ ጋር አንድ ወገን በመሆን ምእመናንን መውጋት ይጀምራል:: ቀድሞ በእባብ ተሰውሮ አዳምና ሔዋንን እንደወጋ ወደፊትም ነብርና ድብ አንበሳም በሚመስለው አውሬ በሐሳዌ መሲሕ ተሰውሮ ምእመ ናንን ይወጋል::

## የዘንዶው ሥልጣን ለአውሬው

«ዘንዶውም ኃይሉንና ዙፋኑን ትልቅም ሥልጣን ሰጠ ው» ራእይ 13÷2 ይህን ምዕራፍ ማለትም ራእይ 13ን ከቁጥር አንድ ጀምረን ስናነብ ሐሰተኛው ክርስቶስ አውሬ ተብሎ እንደ ተገለጸ እንረዳለን:: ኃይሉንና ዙፋኑን ትልቅም ሥልጣን በመስ ጠት የተገለጠው ዘንዶ ዲያብሎስ ሲሆን ይህን ሥጦታ በመቀበል የታወቀው አውሬ ሐሳዌ መሲሕ ወይም ሐሰተኛው ክርስቶስ ነው::





መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌልን በሚያስተምርበት ጊዜ ከአብ ጋር በሕልውና አንድ መሆኑን በአንድ ፈቃድ የሚሠራ መሆኑን ለመግለጽ «እውነት እውነት እላችኋለሁ አብ ሲያደርግ ያየውን ነው እንጅ ወልድ ከራሱ ሊያደርግ ምንም አይችልም» ዮሐ. 5÷19 ብሎ ነበር:: ዳግመኛም «ኩሉ ዘበ ለአቡየ ዚአየ ውእቱ፤ ለአብ ያለው ሁሉ የኔ ነው» ዮሐ. 16÷15 በማለት በሚያስተምረው ትምህርትና በሚያደርጋቸው ተአምራት ሁሉ አብ የማይለየው መሆኑን ገልጾ ነበር በትክክል መድኃኔዓለም ክርስቶስ ከባሕርይ አባቱ ከአብ ጋርና ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ይሠራ ነበር:: አሁንም ይሠራል::

የእውነተኛው ክርስቶስ ተቃራኒ ሐሰተኛው ክርስቶስም ከአባቱ ከዲያበሎስ ጋር የሚሠራ መሆኑ ይታወቅ ዘንድ ዘንዶ የተባለው ዲያብሎስ ኃይሉንና ዙፋኑን ትልቅም ሥልጣን ይሰጠ ዋል:: ክርስቶስ ነኝ ብሎአልና የሚሠራውን ሥራ ሁሉ ምንም የሐሰት ሥራ ቢሆን ከእውነተኛው ክርስቶስ ጋር ለማወዳደር ይሞክራል::

እውነተኛው ክርስቶስ ከአብ ተለይቶ በራሱ ምንም ሊያደርግ እንደማይችል ሐሰተኛው ክርስቶስም ከዲያብሎስ ተለይቶ ምንም ሊያደርግ አይችልም:: የእውነተኛው ክርስቶስ ትምህርት በአብ ፈቃድ እንደተመሠረተች የሐሰተኛው ክርስቶስ ትምህርትም በዲያብሎስ ፈቃድ ትመሠረታለች:: የእግዚአብ ሔር አብ ኃይል በእውነተኛው ክርስቶስ እንደተገለጠ የዲያብ ሎስ ኃይልም በሐሰተኛው ክርስቶስ ይገለጣል::

እግዚአብሔር አብ ለእውነተኛው ክርስቶስ ሥልጣኑን እንደሰጠው ዲያብሎስም ለሐሰተኛ ክርስቶስ ሥልጣኑን ይሰጠ ዋል:: ለአብ ያለው ሁሉ ለእውነተኛው ክርስቶስ እንደአለው ለዲያብሎስ ያለውም ለሐሰተኛው ክርስቶስ አለው:: እውነተኛው ክርስቶስ የእውነት ታምራትን እንደሚያደርግ ሐሰተኛው ክርስ ቶስም የምትሐት ተአምራትን ያደርጋል:: ያስመስላል:: ለእው ነተኛው ክርስቶስ ዮሐንስ መጥምቅ እንደመሰከረለት ለሐሰተ ኛው ክርስቶስም ሐሰተኛው ኤልያስ ይመሰክርለታል::

ለእውነተኛው ክርስቶስ ስሙን የሚሸከሙ ቅዱሳን ሐዋ ርያት እንዳሉት ለሐሰተኛው ክርስቶስም ስሙንና የስሙን ቁጥ ር በቀኝ እጃቸው በግንባራቸው የሚሸከሙ ተከታዮች አሉት::



www.ethiopianorthodox.org

እነዚህን በመሰሉ ነገሮች ከእውነተኛው ክርስቶስ ጋር ለመወዳደር ሐሰትን ተመርኩዞ ይነሣል:: ሐሰትን በእውነት ማዶ ያቆማታል:: እነዚህን የማስመሰል ተግባሮች ለማከናወን ከጐኑ ተሰልፎ አይዞህ የሚለው ያው የሐሰት አባት ዲያብሎስ ነው:: ሐሳዊ መሲሕ የሚሠራው ሥራ ሁሉ ከግብር አባቱ ከዲያብሎስ የተገኘ ነው::

ነገር ግን የዲያብሎስ አባትነት የሚያሳፍር በመሆኑ በግልጥ ዲያብሎስ አባቴ ነው አይልም:: በስርቆት የተደቀለ የዲቃላ ልጅ የአባቱን ስም እንደማያውቅ ቢያውቅም ስሙን ለመጥራት በስሙም ለመጠራት እንደሚያፍር ሐሰተኛው ክርስቶስም ዲያብሎስ በግብር ወልዶኛል ለማሳተም ልኮኛል ብሎ በግልጥ አይናገርም:: በአባቱ ስም ያፍራል:: ዲያብሎስም የኔ የዲያብሎስ የግብር ልጅ ነው ብሎ አይመሰክርለትም::

## የአውሬው አድናቂዎች

«ምድርም ሁሉ አውሬውን እየተከተለ ተደነቀ:: ለዘንዶውም ሰገዱለት:: ለአውሬው ሥልጣንን ሰጥቶታልና ለአውሬውም አውሬውን ማን ይመስለዋል:: እርሱንስ ሊዋጋ ማን ይችላል እያሉ ሰገዱለት::» ራእይ 13÷3-4:: በዚህ ንባብ አውሬ የተባለው በውጫዊ አካሉና በውስጣዊ አካሉ ከአውሬ ጋር አንድ ዓይነት ቁመና ያለው ሐሳዊ መሲሕ /ሐሰተኛው ክርስቶስ ሲሆን ዘንዶ የተባለውም ለአውሬው ለሐሳዊ መሲሕ ሥልጣንን የሰጠው ከማኅበረ መላእክት ከነገደ መላእክት ተለይቶ ከአራዊት ጋር ማኅበርን አንድነትን የመሠረተው ርጉሙ ፍጡር ዲያብሎስ ነው:: «ምድር ሁሉ አውሬውን እየተከተለ ተደነቀ» ማለትም ምድር በመባል የተገለጹት የሰው ዘሮች የሐሳዊ መሲሕ የሥራው አድናቂዎች ናቸው::

ሐሳዊ መሲሕ በዲያብሎስ ሐሰታዊ ጥበብ ታግዞ በሚያደርገው ምትሐታዊ ተአምር የሚማረኩ ሆደ ባሻዎች ተታላዮችና ፀረ ክርስቶሶች ክርስቶስ መሳዩን አውሬ ሐሳዊ መሲሕን ያደንቁታል:: የአውሬው አድናቂዎች ሐሰተኛውን ክርስቶስን በአድናቆታቸው ወደ አምላክነት ደረጃ ከአሸጋገሩት በኋላም





የስሕተት መርከባቸውን ከዚህ ላይ አያቆሟትም:: በሐሳዊ መሲሕ ላይ ለሚነግሠው ለዲያብሎስ የሚቀርብ የምስጋና፣ የስግደት፣ የአክብሮት ግብርን በዚችው መርከብ ጭነው ጉዞአቸውን ይቀጥላሉ:: የአንድ ኳስ ተጫዋች ቡድን ደጋፊዎች የሚደግፉት ቡድን ቢሸነፍ በሚደግፉት ቡድን መሸነፍ መናደዳቸውን መበሳጨታቸውን ትተው በአሸናፊው ቡድን ደስ እንደማይሰኙና ይልቁን የተሸነፈው ቡድን እንዲህ ባያደርግ አይሸነፍም ነበር እንዲህ እንዲህ ቢያደርግ ያሸንፍ ነበር በማለት ምክንያቶችን ከመደረደር ውጭ አሸናፊውን ቡድን እንደማያደንቁ ሁሉ የሐሳዊ መሲሕ አድናቂዎችም ሔኖክና ኤልያስ በሚያደርጉት ድንቅ ነገር አይደሰቱም::

ሔኖክና ኤልያስ በሚያደርጉት ተአምር ውሃውን ደም በማድረጋቸው ከሰማይ እሳት በማውረዳቸው ሐሳዊ መሲሕ ቢደነግጥም፣ በመቅሠፍቱ ቢመታም፣ ሌላውን ለማዳን የተነሣ የሐሰት አምላክ ሐሳዊ መሲሕ ራሱን ማዳን ቢሳነውም አድናቂዎቹ ወደ እውነተኛው አምላክ ፊታቸውን አያዞሩም የአውሬው አድናቂዎች ለእውነት እንዳይታዘዙ እንደ ገላትያ ሰዎች አዚም የሚያደርግባቸው ማን ይሆን?

የአውሬው አድናቂዎች በእግዚአብሔር በግ መሥዋዕትነት ያልተፈወሱ ናቸው:: «ከዓለምም ፍጥረት ጀምሮ በታረደው በግ ሕይወት መጽሐፍ ስሞቻቸው ያልተጻፉ በምድር የሚኖሩ ይሰግዱለታል» ራእይ 13÷8 የታረደው በግ ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን የሕይወት መነሻና መድረሻም እርሱ ነው:: የሰውን ማንነት ያለነጋሪ ጠንቅቆ በሚያውቅ በኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ዓለም ከመፈጠሩ በፊትም ሆነ ከተፈጠረ በኋላ የአውሬው አድናቂዎች ሕይወት የማይገባቸው የዲያ ብሎስ መንጋዎች መሆናቸው ይታወቃል::

«በታረደው በግ ሕይወት መጽሐፍ ስሞቻቸው ያልተጻፉ» ማለት ከኢየሱስ ክርስቶስ ጐን በፈሰሰው ውሃ ያልተጠመቁ፣ ደሙን ያልጨለጡ፣ ሥጋውን ያልጐረሱ፣ በክርስቶስ ስም ያልተጠሩ፣ ከሰማየ ሰማያት መውረዱን፣ ከድንግል ማርያም መወለዱን የካዱ፣ ለሰው ልጅ ነጻነት ሲል ከቤተልሔም እስከቀራንዮ በመከራ መንገድ መጓዙን ያልተመለከቱ፣ ቸርነቱን ተጠምተው በቸርነቱ ውሃ ጉሮሮአቸውን ያላለዘቡ፣ ለመንግሥተ



www.ethiopianorthodox.org

ሰማያት ያልታደሉ ርጉማን ናቸው:: እነዚህ ሁሉ የአውሬው አድናቂዎች ይሆናሉ::

በተለይም እግዚአብሔር አብ ወደልጁ ሠርግ ማለትም ወደኢየሱስ ክርስቶስ ሰው መሆን ወደወንጌል የጠራቸው ነገር ግን የሠርጉ እድምተኞች ለመሆን ፈቃደኞች ያልሆኑ አይሁድ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘለዓለማዊ ሕይወት የሚገኝበትን የወንጌል ቃል ቢነግራቸው ጆሮ ዳበ ልበስ ልብም ድንጋይ ሁን ብለው የሕይወትን ቃል ለመስማት ያልወደዱ አይሁድ፣ የኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርትና ተአምራት ባለመቀበላቸው «ብዙዎች ከምሥራቅና ከምዕራብ ይመጣሉ ከአብርሃምና ከይስሃቅ ከያዕቆብም ጋር በመንግሥተ ሰማያት ይቀመጣሉ የመንግሥት ልጆች ግን በውጭ ወደአለው ጨለማ ይጣላሉ» ማቴ.8÷11-12 ተብሎ የተነገረባቸው አይሁድ፣ ድኅነት ወደውስጣቸው እንዳይገባ ልባቸውን በምቀኝነትና በቅናት ቁልፎች አጥብቀው የቆለፉ አይሁድ፣ ለበሽተኞች መድኃኒት እንደሚያስፈልጋቸው ቢነገርም በሽተኞች ሆነው ሳሉ የዓለም መድኃኒት ክርስቶስን የማይፈልጉ አይሁድ የአውሬው የሐሳዌ መሲሕ የቅርብ ተጠሪዎች ይሆናሉ::

በክርስቶስ ዘመን የነበሩ ክርስቶስን ሰቅለው የገደሉ አይሁድ፣ በሐሳዌ መሲሕ ዘመን ባይኖሩም በሥጋም በግብርም የወለዷቸው የልጅ ልጆቻቸው ሐሳዌ መሲሕን አምላክ ነው ብለው ይቀበሉታል:: የአውሬው አድናቂዎች ሕዝበ አይሁድ፣ አውሬውን የሚያኽለውና የሚመስለው የሚያሸንፈውም እንደ ማይኖር አድርገው ከማገናዘብ በተራቆተና ዲያብሎሳዊ ነፋስ በመታው አእምሮአቸው ይገምታሉ:: ለአውሬው ማዋረድና ማክበር መግደልና ማዳን ከሁሉ መድረስና ሁሉን መመልከት ሁሉንም መቆጣጠር የሚችል እግዚአብሔራዊ ሥልጣን ያለው ይመስላቸዋል::

የአውሬው አድናቂዎች እግዚአብሔርን ስለሚረሱና ስለሚዘነጉ እግዚአብሔርንም ከማምለክ ቀንበር አፈንግጠው ስለሚወጡ እግዚአብሔር ይለያቸዋል:: ለክፉ መንፈስም አሳልፎ ይሰጣቸዋል:: በረድኤቱ አይጠብቃቸውም ማለት ነው:: «ስለዚህም ምክንያት በእውነት ያላመኑ ነገር ግን በዐመጽ ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ ፍርድን እንዲቀበሉ ሐሰትን ያምኑ ዘንድ





እግዚአብሔር የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል::» 2ተሰ. 2÷11-12 ምንጊዜም እግዚአብሔር ለሰው ልጆች መልካም ነገር ይሰጣል:: የእግዚአብሔርን ሥጦታ ለመቀበል የማይፈቅዱትን እጃቸውን የማይዘረጉትን ግን አያስገድዳቸውም:: በመብታቸው ላይ ተጽእኖ አያደርግም:: የእግዚአብሔርን መልካም ነገር የመጥሳትና ክፉውን የመምረጥ ነጻነት አላቸው:: ይህን ነጻነት እግዚአብሔር አይቀማቸውም:: በሐሰት በአመጽ ደስ ለሚሰኙት የሐሰትና የአመጽ ጌታ የሚሆን ሐሳዌ መሲሕን ይሰጣቸዋል::

የእውነተኛው ክርስቶስና የሐሰተኛው ክርስቶስ መሆን አይቻልም:: አንድ ባሪያ ለሁለት ጌቶች መገዛት እንደማይችል በወንጌል ተነግሯል:: ማቴ. 6÷24 ወደ ክርስቶስ እንዳይመለከቱ የእምቢተኝነት መጋረጃ የተጋረደባቸው ሁሉ ሐሳዌ መሲሕን ለመመልከት ያ መጋረጃ ይገለጥላቸዋል:: ብርሃኑን ጨለማ ጨለማውን ብርሃን አስመስሎ ማሳየት የዕለት ተግባር ያደረገው ሰይጣን የቀን ጨለማ ሐሳዌ መሲሕን ፀሐይ አስመስሎ ያሳያቸዋል::

## አውሬው ተሳዳቢ ነው

«ታላቅንም ነገርና ስድብን የሚናገርበት አፍ ተሰጠው በአርባ ሁለት ወርም እንዲሠራ ሥልጣን ተሰጠው» ራእይ 13÷5 አውሬው በአጋንንት ገበሬዎች ታርሶ የለሰለሰ የተለያዩ የተንኰልና የዐመጽ ዘሮችንም ለማብቀል የተዘጋጀ መሬት ነው:: ከኃጢአት ዘሮችም ሰውን በማርከስ የታወቀው በሰዎች ልብ ማኅፀን ተጸንሶ በአንደበት የሚወለደው ስድብ ነው::

የልብ ጥላቻ በአንደበት ሲገለጽ ስድብ ይባላል:: ስድብ የተሰደበውን ሰው ቆሻሻ የነካው ቁሳዊ ነገር አስመስሎ የሚያሳይ የግብዞች መስታወት ነው:: ስድብ የሰውን ውሳጣዊ አካሉን የሚወጋ ጦር ነው:: ስድብ የመግደል ትንሽ ወንድም ነው:: ሰዎች እርስ በእርሳቸው ሲጣሉ፣ የስድብ ጦርነት ይገጥማሉ:: ትንሹን ጦርነት ጀመሩ ማለት ነው:: በሰዎች አንደበት የሚተኮሱ ጥይቶች ቢኖሩ የስድብ ቃላት ናቸው:: እነዚህ ጥይቶች ባይገሉም እንኳ ያቆስላሉ::



www.ethiopianorthodox.org

ስድብ ሲባል የተለያየ ስድብ አለ። ቀላል ስድብ አለ ከባድ ስድብ አለ። ሰውንና ተግባሩን መስደብ ቀላል ስድብ ሲሆን እግዚአብሔርንና ተግባሩን መስደብ ግን እጅግ ከባድ ስድብ ነው። «በሰው ልጅ ላይ ቃል የሚናገር ሁሉ ይሠረይለታል። በመንፈስ ቅዱስ ላይ ግን የሚናገር ሁሉ በዚህ ዓለም ቢኾን ወይም በሚመጣው አይሠረይለትም» ማቴ. 12÷32

ሐሰተኛው ክርስቶስ ሦስት ዓመት ከመንፈቅ የምትሐት ተአምራት በማድረግ ራሱን የሐሰት እግዚአብሔር አድርጎ እውነተኛውን እግዚአብሔርን ይሳደባል። ሰማይንና ምድሩን ባሕሩንና የብሱን ምንጮችንና ወንዞችን በሰማይና በምድር የሚኖሩትን ተንቀሳቃሽና ኢተንቀሳቃሽ ፍጥረታትን ሁሉ የፈጠርኩ እኔ ነኝ ይላል። የእግዚአብሔርን ኃይልና ችሎታ ይክዳል።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ከቤተልሔም እስከቀራንዮ ድረስ ለሠላሳ ሦስት ዓመታት ያህል የደረጋቸውን ተአምራት የሠራቸውን ትሩፋት ያስተማራቸውን ትምህርቶች የስሕተት ድርጊቶች እንደሆኑ በመቁጠር አውሬው ለአድናቂዎቹ መልእክት ያስተላልፋል። የባሕርይ አምላክ ክርስቶስንም እሩቅ ብእሲ ወልደ ዮሴፍ፣ ፍጡር የዮሴፍ ልጅ ነው በማለት በክርስቶስ ላይ የስድብ በረዶን ያወርዳል «ታላቅ ንም ነገርና ስድብን የሚናገርበት አፍ ተሰጠው» የተባለ፣ ከዚህ የበለጠ ታላቅ ስድብ ስለሌለ ነው። ክርስቶስን ፍጡር ከማለት የበለጠ ታላቅ ስድብ የለም። የመጨረሻ መራራ መርገምን የተመላ አፍ ቢኖር ይህን ቃል የሚናገር አፍ ነው። «እግዚአ ብሔርንም ለመሳደብ ስሙንና ማደሪያውንም በሰማይም የሚያ ድሩትን ሊሳደብ አፉን ከፈተ» ራእይ 13÷6። የእግዚአብሔር ስም አምላክነትን የተጐናጸፈ ሲሆን የአውሬው /የሐሳዌ መሲሕ/ ሐሳብ ይህን መጐናጸፊያ ገፎ ራቁቱን ማቆም ነው።





# ምዕራፍ ሦስት

## ሐሳዌ ኤልያስ

## ከምድር የወጣው አውሬ ሐሳዌ ኤልያስ ነው

ሐሳዌ ኤልያስ ማለት በኤልያስ ላይ በሐሰት የተነሣ፣ ኤልያስን የሚያሳብል፣ ኤልያስ ሳይሆን ኤልያስ ነኝ የሚል ራሱን በራሱ ኤልያስ ብሎ የሰየመ፣ በኤልያስ ስም የሚመጣ ሐሰተኛው ኤልያስ ማለት ነው። «ሌላም አውሬ ከምድር ሲወጣ አየሁ። የበግ ቀንዶችን የሚመስሉ ሁለት ቀንዶችም ነበሩት። እንደዘንዶም ይናገር ነበር» ራእይ 13÷11

አውሬ የዓመፀኞች ሰዎች መጠሪያ የግብር ስም መሆኑን ከዚህ በፊት አይተናል። እግዚአብሔር የዓመፅ ጓዳ የተንኮል በረንዳ የሆኑትን ሰዎች ለዮሐንስ በአውሬ መልክእ አሳይቶታል። አሁንም ከላይ በተጠቀሰው ምዕራፍና ቁጥር «ሌላም አውሬ ከምድር ሲወጣ አየሁ» በማለት የገለጸው አውሬ ሐሳዌ ኤልያስ /ሐሰተኛው ኤልያስ/ ነው። እውነተኛው ኤልያስ ስለ እግዚአብሔር በእውነት የሚመሰክር እውነተኛ ነቢይ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል። ኤልያስ የእግዚአብሔር ቀን ዳግም ምጽአት ሳይደርስ አስቀድሞ ከእግዚአብሔር ተልኮ እንደሚመጣ ነቢዩ ሚልክያስ በዓይነ ትንቢት አይቶታል ሚልክ. 4÷5

ኤልያስ እግዚአብሔር በዳግም ምጽአት ከመገለጡ አስ ቀድሞ የሚገለጥ ነቢይ መሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ አንባቢዎች ዘንድ የታወቀ ነው። እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ያደረበትና መንፈስ ቅዱስ ያሳየውን የሚናገር ሰማይን እስከ መዝጋት ድረስ ልዩ ልዩ ተአምራትን ያደረገ በሕዝቡም በአሕዛቡም ዘንድ ታዋቂ ነቢይ መሆኑን ሁሉ ይረዳዋል። ስለሆነም ሐሰተ ኛው ኤልያስ እውቅና ባለው በእውነተኛው ኤልያስ ስም የስም ንግዱን ያጧጡፈዋል። ሐሰተኛው ኤልያስ ለሐሰተኛው ክርስቶስ የሐሰት ምስክር ለመሆን ራሱን በኤልያስ ስም ሰይሞ የማታለል ተግባሩን ለማከናወን ደፋ ቀና የሚል የሰይጣን መልእክተኛ ነው።

ይህ ሐሰተኛ ነቢይ ከሌሎቹ ነቢያት ለይቶ የኤልያስን ስም የሐሰቱና የዓመፁ ሽፋን ሊያደርገው የቻለው የእግዚአብ



www.ethiopianorthodox.org

ሔር ቀን ሳይደርስ አስቀድሞ እንደሚመጣ ትንቢት የተነገረለት ኤልያስ በመሆኑ ነው። ይህ ሐሰተኛ ነቢይ ሐሳዌ መሲሕን /ሐሰተኛው ክርስቶስን/ በእውነተኛው ክርስቶስ ስም ሸፍኖ ሰውሮና ደብቆ ለሕዝብ ለማቅረብ ከሰይጣን ተልኮ የሚመጣ የሰይጣን መልእክት ተሸካሚ ነው። ስለሆነም እንዲሁ ዝም ብሎ የኤልያስን ስም በሽፋንነት ሳይጠቀም የሐሰተኛው ክርስቶስን /የሐሳዌ መሲሕን/ ነገር ቢሰብክና ቢያስተምር እውነተኛው ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት ኤልያስ አስቀድሞ እንደሚመጣ ተነግሮአል። አንተ ማን ነህ? እንደሚባል ስለሚያውቅ የኤልያስን ስም ተከናንቦ ይመጣል።

## የአውሬው ሁለት ቀንዶች

«የበግ ቀንዶችም የሚመስሉ ሁለት ቀንዶች ነበሩት» ዮሐንስ ያየው አውሬ ሁለት ቀንዶች ያሉት አውሬ ነው። ይህ ባለሁለት ቀንድ አውሬ ሐሳዌ ኤልያስ ሲሆን ሁለት ቀንዶች የተባሉትም ሐሳዌ ኤልሣዕ እና ሐሳዌ አብድዩ ናቸው። ሐሳዌ ኤልሣዕ እና ሐሳዌ አብድዩ ማለትም ሐሰተኛው ኤልሣዕ እና ሐሰተኛው አብድዩ ማለት ነው። ኤልያስን ሳይሆን ኤልያስን ለመምሰል የሚጥረው ሐሰተኛው ነቢይ ለኤልያስ ሁለት ደቀ መዛሙርት እንደነበሩት ሁሉ ሁለት ደቀመዛሙርትን ያስከትላል። የኤልያስ ደቀመዛሙርት ኤልሣዕ እና አብድዩ ነበሩ።

ሀ. ኤልሣዕ፣ ኤልሣዕ የኤልያስ መንፈስ እጽፍ ድርብ ሆኖ ያደረበት የኤልያስ ደቀ መዝሙር ነው። ኤልሣዕ ነቢዩ ኤልያስ ከእግዚአብሔር በተገለጠለት መሠረት ከጠራው በኋላ ጨርቄን ማቄን ሳይል ቤቱንና ንብረቱን ሁሉን ትቶ ኤልያስን ተከትሎ ከኤልያስ ጋር በመንፈሳዊ አገልግሎት የኖረ መንፈሳዊ ደቀመዝሙር ነው። 1ነገ. 19÷16-21።

ኤልያስ በእሳት ሠረገላ ወደ ሰማይ ከተወሰደ በኋላ የኤልያስ መንፈስ በኤልሣዕ ላይ አድሮበት ኤልሣዕ ለረዥም ጊዜ በነቢይነት እግዚአብሔርን አገልግሏል። 2ነገ. 2÷1-14 ኤልሣዕ የኤልያስ ደቀመዝሙር በመሆኑና ከኤልያስ ዕርገት በኋላም





የኤልያስ መንፈስ ስለአደረበት ኤልያስ ያደረጋቸውን
ራት ደግሞ በማድረጉ በመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቅና ያለው
ነው። በእግዚአብሔር ፈቃድ ቢሆንም የጠራውና መንፈሳ
ያለማመደው ኤልያስ በመሆኑ የኤልያስ ደቀመዝሙር
እጅግ የጐላ ነው።

ስለሆነም ሐሰተኛው ነቢይ ኤልያስን ለመምሰል
ገጫ ቢሆነኝ ብሎ እንደእርሱ ያለውን ሐሰተኛ ሰው
ብሎ በመሰየም ደቀመዝሙር አድርጎ ያስከትለዋል።

ለ. አብድዩ:- አብድዩም የአክአብ የቤቱ አዛዥ ቢ
እግዚአብሔርን የሚፈራ የኤልያስን ቃል የሚያከብር ሕ
ዚአብሔርን የሚጠብቅ ከነአክአብ ጋር ሆኖ በነአክአብ
ያልሄደ ደግ ሰው ነበር። ይልቁንም ኤልዛቤል የእግዚአብ
ነቢያት በአስገደለች ጊዜ መቶውን ነቢያት ወስዶ በዋሻ
ሸሽጎ ሲመግብ የነበረ ኤልያስም ይወደው የበረና ወደ
የላከው ወደአክአብ መልእክትን በመሸከም ኤልያስን
ትሕትና ያለው ሰው ነው 1ነገ. 18÷1-16። በኋላም እንደ
ሣዕ ኤልያስን ተከትሎ ሄዶ የኤልያስ ደቀመዝሙር
ኤልያስን ለመከተል ምክንያት የሆነውን ነገር የሚከ
ታሪክ ይገልጸዋል።

በአካዝያስ ዘመነ መንግሥት የዝንብ መንጋ የሚያ
ሰዎች ነበሩ። አካዝያስ በታመመ ጊዜ የአቃሮንን አምላክ
ልዜቡልን ጠይቁ ብሎ ወደካህኑ ባየቱ መልእክተኞችን
የእግዚአብሔርም መልአክ ኤልያስን የሰማርያን ንጉሥ
ክተኞች ለመገናኘት ውጣና የአቃሮንን አምላክ ብዔልዜ
ትጠይቁ ዘንድ የምትሔዱት በእሥራኤል ዘንድ አምላክ
ነውን? ስለዚህም እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ትሞታለህ
ከወጣህበት አልጋ አትወርድም በላቸው አለው። ኤልያስም
መልአኩ እንደአዘዘው ነገራቸው። መልእክተኞችም ወደ
ያስ ተመልሰው ኤልያስ የነገራቸውን ሁሉ ለአካዝያስ ነገሩ
አካዝያስም ይህን ነገር የነገራቸው ሰው መልኩ
እንደሚመስል ጠየቀ። እነርሱም ሰውየው ጠጉራም ነው።
ቡም ጠፍር ታጥቆ ነበር አሉት። በእነዚህ ምልክቶች
መሆኑን ተረዳ። ከዚህ በኋላ ትሞታለህ እንጂ ከወጣ



www.ethiopianorthodox.org

አልጋ አትወርድም ያለው የኤልያስ ቃል ያበሳጨው አካዝያስ ኤልያስን ወደእርሱ ያመጡት ዘንድ የሃምሳ አለቃውን ከሃምሳ ሰዎች ጋር ሰደደ:: ኤልያስም ከሰማይ እሳት አውርዶ አቃጠላቸው:: አካዝያስም ሌላውን የሃምሳ አለቃ ከሃምሳ ሰዎች ጋር ላከበት:: ኤልያስም ለሁለተኛ ጊዜ የተላኩትን የሃምሳ አለቃውንና ሃምሳውን ሰዎች ከሰማይ እሳት አውርዶ አቃጠላቸው:: አልሞት ባይ ተጋዳይ የሆነው አካዝያስ ሦስተኛውን የሃምሳ አለቃ ከሃምሳ ሰዎች ጋር ሰደደ:: ሦስተኛው የሃምሳ አለቃ ግን አብድዩ ነበር:: አብድዩ እንደሁለቱ የሃምሳ አለቃዎች በትዕቢት ወደ ኤልያስ አልቀረበም:: በኤልያስ ፊት በጉልበቱ ተንበረከከና የእግዚአብሔር ሰው ሆይ ነፍሴና የእነዚህ የሃምሳው ባሪያዎችህ ነፍስ በፊትህ የከበረች ትሁን ብሎ በትሕትና ለመነው::

ኤልያስም በሁለቱ የሃምሳ አለቃዎችና በሰዎቻቸው ላይ ያወረደውን እሳት በአብድዩና በሰዎቹ ላይ አላወረደም:: መልአኩም ኤልያስን ከአብድዩ ጋር ይሔድ ዘንድ አዘዘው:: ኤልያስ ከአብድዩ ጋር ሄደ:: መጀመሪያ ለመልእክተኞች የነገራቸውን ቃል ለአካ ዝያስ ፊት ለፊት ነገረው:: ትሞታለህ እንጂ ከወጣህበት አልጋ አትወርድም አለው:: አካዝያስም ኤልያስ እንደተናገረ ሞተ:: 2ነገ. 1÷1-18 ከዚህ በኋላ አብድዩ ኤልያስን ተከትሎ ሄዷል:: በነቢይነት እግዚአብሔርን አገልግሏል:: ከአሥራ ሁለቱ ደቂቀ ነቢያት አንድ ተብሎ ተቆጥሮአል::

ራሱን በኤልያስ ስም ሰይሞ የሚመጣው ያ ሐሰተኛ ነቢይ የስሕተቱ ደጋፊ የሆነውን ደቀ መዝሙሩን በአብድዩ ስም ይሰይመዋል:: በአብድዩ ስም የተሰየመው የሐሰተኛው ኤልያስ ደቀመዝሙርም ሐሰተኛው አብድዩ በመባል ይታወቃል:: ኤልያስን ለመምሰል የሚፍጨረጨረውና የማስመሰያ ስልቶችን የሚጠቀመው ያ ሐሰተኛ ነቢይ ደቀመዛሙርቱን በኤልያስ ደቀመዛሙርት ስም ይሰይማቸዋል:: የእውነተኛው ኤልያስ ደቀመዛሙርት ኤልሣዕና አብድዩ እንደተባሉ ሁሉ የሐሰተኛው ኤልያስ ደቀ መዛሙርትም ሐሰተኛው ኤልሣዕ እና ሐሰተኛው አብድዩ ይባባላሉ::





# የሐሰት ምስክር ለሐሰተኛ

ለሐሰተኛ ሰው እውነተኛ ሰው ሊመሰክርለት አይችልም:
የሐሰተኛ ሰው ምስክር ሐሰተኛ ነው:: የእውነተኛ ሰው ምስ
ርም እውነተኛ ነው:: እውነተኛ ከሐሰተኛ ጋር ስምምነት የ
ውም:: ሐሰተኛ ሰው የሚያስበውንና የሚናገረውን እውነተ
ሰው አያስበውም:: አይናገረውምም:: ሁለቱ እርስ በእርሳቸው
አይፈላለጉም::

የሐሰተኛው ክርስቶስ ምስክር ሐሰተኛው ኤልያስ ነው:
የሐሰተኛው ኤልያስ ደመዛሙርትም ሐሰተኛው ኤልሣዕ እ
ሐሰተኛው አብድዩ ናቸው:: የእነዚህ ሁሉ እራስ የበላይ ጠባ
የሐሰት አባት የተባለው ዲያብሎስ ነው:: ለሐሰተኛው ክርስቶ
እውነተኛው ኤልያስ ምስክር ሊሆን አይችልም:: ምስክር ይሁ
ከተባለም በሐሰት መጋረጃ የተጠለለ ማንነቱን ይገልጥበታል:
በሰይጣን አማካሪነት የተቆለለ አምላክ ነኝ የማለት ቁልሉንም
እንደ እንቧይ ካብ ይንድበታል:: በእቅዱና በዓላማው ላይም
ድንገተኛ መቅሠፍት ይሆንበታል:: እንዲህ ስለሚሆን እራስ
ሐሰተኛው ክርስቶስ እውነተኛው ኤልያስን ለምስክርነት አይ
ውም /አይፈልገውም/::

ለሐሰተኛው ኤልያስም እውነተኛው ኤልሣዕ እና እው
ተኛው አብድዩ ደቀመዛሙርቱ ሊሆኑ አይችሉም:: ምክንያቱም
ከእሾህ ወይንን ከኩርንችትም በለስን መልቀም እንደማይቻል
ጌታ በወንጌል ተናግሯል:: ማቴ. 7÷16 ከፉ ዛፍም መልካም
ፍሬ ማፍራት እንደማይቻለው የተገለፀው ከሐዲ መምህር ሃይ
ማኖታዊ ደቀመዝሙርን ማፍራት የማይቻለው መሆኑን አመ
ሥጥሮ ለመንገር ነው::

እውነተኛው ክርስቶስም እነዚህን የሐሰት ቤተሰቦች
መመሥረት ወይም መምራት አይፈልግም:: እርሱ የእውነት
አምላክ ነው እንጂ የሐሰት አምላክ አይደለምና:: እርሱ ሐሰትን
ተተክላ ቢያገኛት ነቅሎ ይጥላታል እንጂ ውኃ አያጠጣትም::

«በፊተኛውም አውሬ ሥልጣን በእርሱ ፊት ሁሉን
ያደርጋል» ራእይ 13÷12 የፊተኛው አውሬ ሐሳዌ መሲሕ
ነው:: ሐሳዌ ኤልያስ /ሐሰተኛው ኤልያስ/ በፊተኛው አውሬ



www.ethiopianorthodox.org

በሐሳዌ መሲሕ ፊት ብዙ ምልክቶተን ያደርጋል:: ብዙ ምልክቶችን ማድረግ የሚችለው በሐሳዌ መሲሕ ስለአመነ እርሱንም ስለአመለከ እንደሆነና የምልክቶችም ክስተት በሐሳዌ መሲሕ ሥልጣን የሚተገበር መሆኑን በመግለጥ ብዙ አባላትን ወደ አምልኮተ ሐሳዌ መሲህ ይሰበስባል:: ከራስ ምስክርነት ይልቅ የሌላ ሰው ምስክርነት በተመልካቾችና በነገር ገምጋሚዎች ዘንድ እጅግ ተቀባይነት እንዳለው ያረጋገጠው ሐሰተኛው ክርስቶስ /ሐሳዌ መሲሕ/ እራሱ ለራሱ ምስክር ሆኖ ክርስቶስ ነኝ ተቀበሉኝ ቢል «ለራስ ሲቆርሱ አያሣንሱ» የማን እራስ ወዳድ ነህ እንደሚባል ስለሚያውቅ የሐሰቱ ተባባሪ የሚሆን ሌላ ምስክር መፈለግ ግድ ይሆንበታል:: ያው በእርሱ ላይ አድሮ አምላክ ነኝ እንዲል ይህን መጥፎ ሐሳብ በልቦናው አስረግዞ የሚያስወልደው የሐሰት አባት ዲያብሎስ ከተከታዮችህ አንዱን ምረጥና በኤልያስ ስም ሰይመው እኔ የምትህት ተአምራት የሚያደርግበትን ሥልጣን እሰጠዋለሁ በፊትህ ድንቅ ድንቅ ነገሮችን ያደርጋል ሲል ሹክ ይለዋል::

ሐሰተኛው ክርስቶስ ከአባላቱ አንዱን መርጦ ኤልያስ ብሎ ይሰይመዋል:: ዲያብሎስም በገባው ቃል ኪዳን መሠረት የመለዋወጥና የማስመሰል ኃይሉን ይሰጠዋል:: ከዚህ በኋላ ሐሰተኛው ክርስቶስ አድርግልኝ ያለውን የምልክት ዓይነት ሁሉ ሐሰተኛው ኤልያስ ያደርጋል::

ሐሰተኛው ኤልያስና ሐሰተኛው ክርስቶስ በመተባበር ሐሰትን እውነት ለማስመሰል ይታገሉላታል:: ሐሰተኛው ክርስቶስ በዝሙት ተወልዶ ሳለ እውነተኛውን ክርስቶስን ለመምሰል በሕቱም ድንግልና ተጸንሼ በሕቱም ድንግልና ተወልጄአለሁ ሲል ሐሰተኛው ኤልያስ ደግሞ ኤልሣዕና አብድዩ የሚባሉ ደቀመዛሙርት አሉኝ በማለት እውነተኛው ኤልያስን ለመምሰል ይፍጨረጨራል:: ይሁን እንጂ እውነት ግን ወደ እነርሱ አትጠጋም:: ሐሰተኛው ሰው ለአሉታዊ ዓላማው ብዙ ምስክሮችን ቢያገኝም እውነትን ግን ማግኘት አይችልም:: ምስክሮችም እንደእርሱ ሐሰተኞች ይባላሉ እንጂ የተሳሳተ ሐሳቡን ስለደገፉ እውነተኞች አይባሉም:: ይልቁንም በሰዎች ብዛት ቁጥር ስሕተት እየጐላች ትሄዳለች:: በደጋፊዎች ብዛት ሐሰት እውነት መሆን ብትችል ኖሮ የዲያብሎስ ፈጣሪነት እውነት በሆነች





ነበር:: ዲያብሎስ ፈጣሪ ነኝ ባለ ጊዜ አባባሉን የደገፉ መላእክት ብዙ ነበሩ:: ሆኖም የሐሰት አባላት ተብለው ከሐሰት አባት ከዲያብሎስ ጋር ወደ ምድር ተጣሉ እንጂ በእነርሱ ድጋፍ ዲያብሎስ አምላክ አልሆነም::

አንድ ሰው በሐሰተኞች ምስክርነት ቢሞት እንኳ ሐሰት በሰዎች ልቡና ውስጥ ተደብቃ ተሰውራ የምትገልጥበትን ጊዜ ትጠብቃለች እንጂ ተለውጣ እውነት አትሆንም:: ሰዎች በአንደበታቸው ሐሰትን እውነት ቢሉአትም ልባቸው ግን ያችው ሐሰት እንደሆነች ያውቃል:: ልባቸው የሚመለከተው ገፅታ ያው የሐሰት ገፅታ ነው::

ሐሰተኛው ክርስቶስም እራሱን ክርስቶስ አሰኝቶ ሲመጣ ክርስቶስ አለመሆኑን በትክክል ያውቃል:: ሰማይንና ምድርን በውስጣቸው የሚገኙትንም ፍጥረታት እንደፈጠረ ሲናገር ከእንስሳት ትንኝን ከዕፀዋት ችፍርግን ያልፈጠረ መሆኑን አይዘነጋውም:: ሆኖም ግን ከደረጃዎች ሁሉ በላይ የሆነውን የአምላክነትን ክብር የማግኘት ምኞት ልቡን የማረከው ሐሳዌ መሲሕ ፈጣሪ አለመሆኑን ክዶ ፈጣሪ መሆንን ለማመን ከገዛ ልቡ ጋር በቆራጥነት ይታገላል:: አምላክ እንደሆነ ልቡ ባያምንለትም ከፍተኛ ደረጃ ያለው የአምላክነት ክብር እንዳያመልጠው ከሐሰት ጋር ይቆራኛል:: የሐሰትን መልክ እውነት ለማስመሰል የማስመሰያ ቀለሞችን ይቀባባታል:: ከተከታዮቹ አንዱን ኤልያስ ብሎ መሠየም በምትሀት ፀሐይን የያዘ መስሎ መታየት እነዚህን የመሰሉ የማታለያ ቁሳቁሶችን ይሰበስባል::

## የአውሬው መቁሰልና መፈወስ

«ለሞቱ የሆነውም ቁስል ተፈወሰለት» ራእይ 13÷12 ለዚህ ንባብ መተርጉማን ተስማሚ የሆነ ትርጓሜ ሰጥተውታል:: ቁስሉ ተፈወሰለት የተባለው፣ በሐሳዌ መሲሕ አድሮ የሚመለከው የቀደመው አውሬ ዲያብሎስ ነው:: ቁስሉ መቼ እንደ ቆሰለና ቁስል የተባለው ምን እንደሆነ ደግሞም መቼ እንደ ተፈወሰ በትርጓሜ መገለፅ የሚገባው ጉዳይ ነው:: ከተፈወሰበት የቆሰለበትን ጊዜ ብንፈልግ መቅደም የሚገባው ነገር ሳይሆን አይቀርም::



www.ethiopianorthodox.org

ይህ ክፉ አውሬ የቆሰለበት መሣሪያ የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ሲሆን ቦታው ቀራንዮ እለቱም እለተ ዓርብ ነው። ይህም ንባብ በቆላ. 2÷14-15 ካለው ንባብ ጋር ይዛመዳል። በራእይ 20÷2 ካለው ንባብ ጋርም ይተባበራል። «የቀደመውን እባብ ዘንዶውን እርሱም ዲያብሎስና ሰይጣን የተባለውን ያዘው ሺህ ዓመትም አሰረው ወደ ጥልቅም ጣለው» ይህ ንባብ የዲያብሎስን መታሰር የሚያመለክት ሲሆን ጊዜውን አይጠቁምም። ይሁን እንጂ ዲያብሎስ የታሰረው፣ ወደውጪም የተጣለው ኃይሉን ያጣውና የደከመው በክርስቶስ መስቀል መሆኑ ግልጽ ነው። በመስቀል ተጠረቀ፣ ሺህ ዓመት ታሰረ፣ ወደ ውጪ ተጣለ፣ ቆሰለ የሚሉ ንባባት ወይም ቃላት ሁሉ አንድ ዓይነት ትርጉም የያዙ ሲሆኑ ትርጉማቸውም የሚገልጸው ዲያብሎስ በክርስቶስ መስቀል ድል የተነሣ መሆኑን ነው።

ይህ አውሬ የቆሰለበት ጊዜ የክርስቶስ ደም የፈሰሰበት ጊዜ መሆኑን ከተረዳን ከቁስሉ የተፈወሰበት ጊዜ መቼ ነው ወደሚለው ፍሬ ሐሳብ እንሔዳለን። በክርስቶስ መስቀል የቆሰለው ዲያብሎስ ይፈወሳል ሲባል ሕይወት ያገኛል ይቅርታ ይደረግለታል ማለት አይደለም። የማሳት ኃይሉ በክርስቶስ መስቀል ደክሞ ሲኖር በሐሳዌ መሲሕ ዘመን የተጠናከረ የማሳት ተግባሩን ያሳያል ማለት ነው። በራእይ 20÷2-3 ባለው ንባብ ላይ ሰይጣንን ያዘው፣ ሺህ ዓመትም አሰረው ካለ በኋላ ለጥቂት ጊዜ ይፈታ ዘንድ ይገባዋል ይላል። ይህም ጥቂት ጊዜ ሐሳዌ መሲሕ የሚነግሥበት ሰይጣን የሚሰለጥንበት ሦስት ዓመት ከመንፈቅ ነው።

ዲያብሎስ በክርስቶስ በመስቀል ላይ ሞት ከመታሰሩና ከመቁሰሉ በፊት ለእርሱ ያልተሳካለትን አምላክ የመሆን ምኞት በአዳምና በሔዋን ልቡና አስጸንሶ አስወልዷል። ሆኖም ከአዳምና ከሔዋን የተወለደው ምኞት የተባለው ሕፃን በተወለደ ጊዜ እንደ አርዌ ገሞራዊት ልጆች አባቱንና እናቱን ከገደለ በኋላ እርሱም በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክረስቶስ መስቀል የሞት ጽዋን ጠጥቷል።

ዲያብሎስ ይህን ዲቃላውን በክርስቶስ መስቀል ተቀሥፎበት ቢያጣውም በሐሳዌ መሲሕ ዘመን ሕያው ሆኖ ያገኘዋል። በአጭሩ በዲያብሎስ ቀስቃሽነት ተግባራዊ የሆነ የአዳምና





የሔዋን ኃጢአት በክርስቶስ ሞት ከተደመሰሰ በኋላ እንደገና በሐሳዌ መሲሕ ዘመን ተግባራዊ ይሆናል ማለት ነው። ዲያብሎስ ለሁለተኛ ጊዜ ሐሳዌ መሲሕን ይቀሰቅሳል። አምላክነትን በመመኘት የመጣው የአዳም ኃጢ አት መደምሰስ የዲያብሎስ መቁሰል ሲሆን ሐሳዌ መሲሕን የሐሰት አምላክ አድርጐ ማስነሳቱ ደግሞ የቁስሉ ፈውስ ተብሏል። ዲያብሎስ የሰዎች ኃጢ አት ሲደመሰስ የሚቆስል የሰዎች ኃጢአት ሲስፋፉ ከቁስሉ የሚፈወስ ተቃራኒ ፍጡር መሆኑን ንባቡ ይጠቁማል። የአዳምና የሔዋን የልጆቻቸውም ቁስል የተፈወሰው ዲያብሎስ የተከላት መላውን አካላቸውን ያደማቻቸው ያቺ የኃጢአት እሾህ በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ምሳር /መጥረቢያ/ ተቆርጣ በወደቀች ጊዜ ነው። ነገር ግን የኃጢአት መቆረጥ ለሰው ልጆች ፈውስ ሲሆን ለዲያብሎስ መድማትና መቁሰል ነበር። ኃጢአት ተነቅላ የወደቀችበት ቀን ለዲያቢሎስ የመከራና የኃዘን ቀን ነው። ቆሰለ የተባለውም በዚሁ ጊዜ ነው።

«ለሞቱ ከሆነው ቁስል ተፈወሰ» የሚባለውም የሰውን ዘር በሙሉ አቁስላ የነበረችውን አምላክ ልሁን የማለት ዓመፅ አሜኬላን በሐሳዌ መሲሕ ዳግሮ ዘርቶ ባበቀለ ጊዜ ነው። ዲያብሎስ በአዳምና በሔዋን ያደረገውን በሐሳዌ መሲሕ ሲደግም ማለትም አምላክነትን በመመኘት ቀለም በአዳምና በሔዋን በልብ ብራና ላይ የጻፈው መጽሐፈ ዕዳ በክርስቶስ ደም ታጥቦ ከተደመሰሰ በኋላ ለሁለተኛ ጊዜ በሐሳዌ መሲሕ የልብ ብራና ላይ ሲጽፈው ከእስራቱ ተፈትቷል፣ ከቁስሉም ተፈውሷል ማለት ነው። በቀራንዮ የሞተችው የአዳም ኃጢአት በሐሳዌ መሲሕ ሕይወት ስታገኝ የዲያብሎስ የቁስል ፈውስ ትባላለች። አውሬው ዲያብሎስ ለጥቂት ጊዜ ከእስራቱ ተፈታና ከቁስሉ ተፈወሰ ቢባልም እንደገና ታስሮ ወደ እሳት ባሕር ይጣላል። በማትድን ቁስልም ተይዞ ለዘለዓለም ሲቃጠል ይኖራል።

## የአውሬው ስብከት ለአውሬው

«ለፊተኛው አውሬ ምድርና በእርሱ የሚኖሩት እንዲሰግዱለት ያደርጋል» ራእይ 13÷12 ከአውሬ ጋር የሚውልና የሚያድር የአውሬ ጉረቤት በመልክም በግብርም አውሬን



www.ethiopianorthodox.org

የሚመስል ያው አውሬ ነው:: የበግ ቀንዶች የሚመስሉ ሁለት ቀንዶች ያሉት አውሬ ሐሰተኛው ኤልያስ መሆኑ ተገልጿል:: አውሬው ሐሳዌ ኤልያስ የፊተኛው አውሬ የሐሳዌ መሲሕ ሰባኪ ነው:: አውሬነቱን ደብቆ አውሬዎች ከሚኖሩበት ዋሻ አውጥቶ በመንበረ ጸባዖት እንዳለ አድርጐ በሐሰታዊ ስብከት መስታወት እንዲታይ የሚያደርገው ሐሳዌ ኤልያስ ነው:: የጨፈገገ ውስጣዊ ገጽታውን የአጥቢያ ኮከብ አስመስሎ ለሕዝብ የሚያቀርበው ሐሰተኛው ኤልያስ እንደሚሆን ዮሐንስ ይገልጻል::

ሐሰተኛው ኤልያስ የሐሰተኛው ክርስቶስ ሰባኪ እንደ መሆኑ አምላክነቱን አስፍቶ፣ አምልቶ አጉልቶ በመግለጽ በምድር ላይ የሚኖሩት ሁሉ ለሐሳዌ መሲሕ እንዲሰግዱለትና የክብር ምስጋና እንዲያቀርቡለት ያደርጋል:: ሐሰተኛው ኤልያስ እርሱ ኤልያስ ተብሎ የተሰየመ ሌላ ሰው እንጂ ኤልያስ አለመሆኑን ስለሚያውቅ ክርስቶስነቱን የሚሰብክለት ሐሳዌ መሲሕም ክርስቶስ እንዳልሆነ ሳያውቅ አይቀርም:: በጊዜያዊ ጥቅም ተስቦ የዲያብሎስም አሽከርካሪነት ተጨምሮበት ያልሆነውን ሆነ ያላደረገውን አደረገ በማለት አመላክነት የሌለውን እንዳለው አድርጐ ቢቀባጥርም አንዳንድ ጊዜ የገዛ ሕሊናው ሳይወቅሰው እንደማይቀር ይታሰባል::

በየትኛው ነቢይ ቃል ክርስቶስነቱን ያረጋግጣል:: የትኛውንስ ሱባዔ ቆጥሮ ልቡናውን ያስረዳዋል? እውነተኛውን ክርስቶስን እንዳይቀበሉ የአይሁድን ልቡና የዘጋ ያ ርኩስ መንፈስ ዲያብሎስ አንደበቱንም ልቡንም ተቆጣጥሮ የሐሳዌ መሲሕን አምላክነት የሚሰብክ ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ ወደልቡ መለስ ብሎ ከራሱ ጋር መከራከሩ የማይቀር ጉዳይ ነው:: በአጋንንት አእምሮውን ያጣ ሰው አልፎ አልፎ ፍሬ ነገር ጣል ያደርግ የለ? ዛር ተቆራኝቶ የሚያስጓራው ሰውም በሚያጓራበት ጊዜ የሚናገረውን ባያውቅም እንኳ መናፍስቱ ለቀቅ ሲያደርጉት በሌላ ኃይል ቁጥጥር ውስጥ እንደነበረና እንደቆየ ይገነዘባል:: ለመናፍስቱ መሥዋዕት የሚሆኑ ነገሮችን ሲገዛ እግዚአብሔር የማይወድለት መሆኑን እግዚአብሔር በሰጠው አእምሮ ያውቃል:: የሚያስፈርድበትም ይኸው እያወቀ ለመናፍስት መገዛቱ ነው::





ሐሳዌ ኤልያስም /ሐሰተኛው ኤልያስ/ እግዚአብሔር ሰብአዊ አእምሮ ሰጥቶ የፈጠረው ፍጡር እንደመሆኑ እርሱ ኤልያስ እንዳልሆነ ኤልያስ ከመባሉ በፊት ሌላ ስም እንደበረው ኤልሣዕ አብድዩ ብሎ የሰየማቸው ደቀመዛሙርትም በእውነት ኤልሣዕ እና አብድዩ እንዳልሆኑ ክርስቶስነቱን የሚሰብክለትያ ርጉም ፍጡርም ክርስቶስ እንዳልሆነ እግዚአብሔር በሰጠው ሰብአዊ አእምሮ በትክክል ያውቃል:: ከአውሬው ጋር ተይዞ በዲን ወደሚቃጠል የእሳት ባሕር እንዲጣል የሚያደርገውም ይኸው እያወቀ የሚፈጽመው ስሕተት ነው:: ራእይ 19÷20

## አውሬው ምልክቶችን ያደርጋል

«እሳትንም እንኳ ከሰማይ ወደምድር በሰው ፊት እስኪያወርድ ድረስ ታላላቆች ምልክቶችን ያደርጋል» ራእይ 13÷13 ሐሰተኛው ኤልያስ እውነተኛውን ኤልያስን ለመምሰል ብዙ ማስመሰያ ነገሮችን ይጠቀማል:: ይህ ሐሰተኛ ነቢይ ኤልያስ ነኝ ብሎአልና ይህን አባባል በሰዎች አእምሮ ለመቅረጽ ኤልያስ ያደረጋቸውን ተአምራት ሊያደርግ ይፍጨረጨራል:: በመጽሐፍ ቅዱስ ከተጻፉት ኤልያስ ካደረጋቸው ምልክቶች ጋር የሚመሳሰሉ ምልክቶችን በምትሐት /በማስመሰል/ ያደርጋል:: ነገሮችን የመለዋወጥና የማስመሰል ችሎታን ያው ያደረበት ርኩስ መንፈስ ይለግሰዋል:: ርኩስ መንፈስ ዲያብሎስ ከእስራቱ በተፈታበት በሐሳዌ መሲሕ ዘመን ይቅርና ዛሬ እንኳን በክርስቶስ ደም መፍሰስ ሰንሰለት በታሰረበት ዘመን ለመተተኞች /ለጠንቋዮች/ የማስመሰልና የመለዋወጥ ኃይልን ሲያለብሳቸው ይታያል::

መተተኞች ወይም ጠንቋዮች በመሰበወርቅ መና /እንጀራ/ ከሰማይ እናወርዳለን የሚሉበት ጥበብ፣ ባሕሩን ሜዳ ሜዳውን ባሕር እናደርጋለን የሚሉበት ጥበብ፣ በደመና ተጭነን ከቦታ ወደቦታ እንዘዋወራለን የሚሉበት ጥበብ፣ በጠላታችን ላይ የደንጊያ በረዶ ከሰማይ እናዘንብበታለን የሚሉበት ጥበብ በወዳጅነት በስምምነት ከሰይጣን የቀበሉት ቢሆንም ጥንተ ህብትነቱ የሰይጣን ህብት ነው::



www.ethiopianorthodox.org

ሰይጣን የመለዋወጥ ችሎታ እንዳለው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ሲል ይገልፃል:: «ሰይጣን ራሱ የብርሃን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና» 2ቆሮ. 11÷14 ሰይጣን ይህን መስሎ የመታየት ሀብቱን ለወዳጆቹ እንደየፍላጐታቸው ያሸክማቸዋል:: ለሐሰተኛው ነቢይም ይህን ስጦታ የፈለገውን ያህል አትረፍርፎ ይሰጠዋል:: ሐሰተኛው ነቢይ ወዳጁ ከመሆን አልፎ የሥራ ባልደረባው ነውና:: ሐሰተኛው ነቢይ ፍላጐትህ ምንድን ነው ተብሎ በሰይጣን ለሚጠየቀው ጥያቄ ኤልያስን መምሰል ነው ብሎ ይመልሳል::

የመምሰልን ተግባር በጥሩ ሁናቴ ለማከናወን ብቁ የሆነ ችሎታ ያለው ሰይጣን ኤልያስን ለመምሰል ኤልያስ ካደረጋቸው ምልክቶች /ድንቅ ነገሮች/ ጋር የሚመሳሰሉ ምልክቶችንና ድንቅ ነገሮችን ማድረግ ነዋ ይለዋል:: ይህን ምክር ተቀብሎ ሥራውን ይጀምራል::

ሐሰተኛው ኤልያስ እውነተኛው ኤልያስ ያደረጋቸውን ምልክቶች ሲመረምር ከሰማይ እሳት አውርዶ በጠላቶቹ ላይ እንዳዘነበ ይታወሰዋል 2ነገ. 1÷10-11 የኤልያስን ስም ከነታሪኩ ከነተአምራቱ ካልነጠቀ እንዲሁ በስሙ ብቻ ኤልያስ ተብሎ ቢጠራ በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነቱ እንደሚቀዘቅዝ የተረዳው ሐሰተኛው ነቢይ ሞቅ ደመቅ ያለ የሕዝብ ድጋፍን ለማግኘት በሚሰበስባቸው ሕዝቦች ፊት በሰይጣን ምትሐታዊ ኃይል ታግዞ ከሰማይ እሳት ያወርዳል::

በዚህም ምትሐታዊ ተአምር የተደናገጠ የሕዝብ ልቡና በመጽሐፈ ነገሥት የተጻፈውን የኤልያስን ታሪክ በማስታወስ ይህስ ከሰማይ እሳት አውርዶ ሁለቱን የሃምሳ አለቃዎች ከነ ሰዎቻቸው /ከነሠራዊታቸው/ እንዳቃጠላቸው የተጻፈለት በትክክል ኤልያስ ነው ብሎ እንዲያምን ያደርጋል::

ምንጊዜም ቢሆን የሰውን ልቡና አዲስ ነገር ይስበዋል:: እንግዳ ነገር ይማርከዋል:: አንድ የታክሲ ሹፌር የሚያሽከረክራትን ታክሲ አስፓልቱን አስለቅቆ በአየር ላይ ሲያበራት ቢታይ መንገደኛው ሁሉ መንገዱን ትቶ እርሱን ነበር የሚመለከተው:: አውሮኘላን ሲበር ግን ቀና ብሎ የሚያየው የለም:: የአውሮኘላን በአየር ላይ መብረር የተለመደ ጉዳይ ነዋ:: ታክሲ ግን በአስፓልት ላይ መሽከርከር እንጅ እንደአሞራ በአየር ላይ





የመክነፏ ጉዳይ አልተለመደም:: የዚያች ታክሲ ሹፌር ታክሲን በአየር ላይ በማብረር ብቸኛ ከሆነ እግዚአብሔር ነኝ ብሎ ደፍሮ ቢናገር እንኳ ለማምለክ የሚከጅሉ አይጠፉም::

በምሳሌው እንደተመለከትነው ከሰማይ እሳትን ማውረድ በኅብረተሰቡ ያልተለመደ ድንቅ ነገር ነው:: በሰብአዊ ጥበብ ተደርጐ የማይታወቅ በአምላካዊ ጥበብ ኃይል ብቻ የሚተገበር እንደሆነ ይታመናል:: ስለሆነም ብዙ ሰዎች ይህ ሐሰተኛ ነቢይ ከእግዚአብሔር የተላከው ኤልያስ መስሎአቸው ይሰናከሉበታል:: በተለይም መድኃኒታቸው ክርስቶስን ሰቅለው የገደሉ የአይሁድ የልጅ ልጆቻቸው በዚህ የመሰናከያ ደንጊያ ላይ ወድቀው ይሰበራሉ::

## አውሬው በምልክቶች ያስታል

«በአውሬውም ፊት ያደርግ ዘንድ ከተሰጡት ምልክቶች የተነሣ በምድር የሚኖሩትን ያስታል» ራእይ 13÷14 አውሬ የሚለው ንባብ ሐሰተኛው ክርስቶስንና የሐሰት አባት ዲያብሎስን ያስተረጉማል:: የአውሬ ተመሳሳይ ተግባር ያላቸው ሁለቱን ስሑታን ፍጡራን በትርጓሜ የያዘ ንባብ ነው:: እንዲህ ከሆነ ሐሰተኛው ኤልያስ ምልክቶችን የሚያደርገው በየትኛው አውሬ ፊት ነው? የሚለው ጥያቄ መልስ የሚያስፈልገው ጥያቄ ነው::

አንደኛው አውሬ ማለትም ሐሰተኛው ክርስቶስ ከአራቱ ባሕርያት የተፈጠረ የእለተ ዓርብ ፍጡር ሰው እንደመሆኑ በግዘፈ አካል በሕዝብ ፊት የሚገለጥ እንደማናቸውም ሰው በዐይነ ሥጋ የሚታዩ ሕዋሳት ያሉት ግዙፍ ፍጡር ነው:: ሁለተኛው አውሬ ዲያብሎስ ግን ተፈጥሮው መልአካዊ እንጂ ሰብአዊ ባለመሆኑ በዐይነ ሥጋ የሚታይ ግዙፍ አካል የለውም:: ረቂቅ መንፈስ ስለሆነ ለማሳት በሰወች መካከል ሲገኝም ተግባሩ እንጂ አካሉ አይገለጥም:: ስለሆነም ሐሰተኛው ኤልያስ ምልክቶችን የሚያደርገው በግዘፈ አካል በሚገለጠው አውሬ በሐሰተኛው ክርስቶስ ፊት ሲሆን ረቂቁ አውሬ ዲያብሎስም በሐሰተኛው ክርስቶስ ላይ በማደር በመንፈስ ይገኛል::



www.ethiopianorthodox.org

ሰዎች ሐሰተኛው ነቢይ በሚያደርጋቸው ምልክቶች ተስበው ክርስቶስ ተብሎ ለተሰየመው አውሬ የሚያቀርቡትን ስግደት በግዙፉ አውሬ ላይ ያደረው ረቂቁ አውሬ ዲያብሎስ ይቀበለዋል:: ሁለቱ አውሬዎች ግዙፉ አውሬ ሐሳዌ መሲሕና ረቂቁ አውሬ ዲያብሎስ በአንድ ቦታ ላይ ይገኛሉ:: ሐሰተኛው ነቢይ ምልክቶችን የሚያደርገው በሁለቱ አውሬዎች ፊት ነው:: ተገልጦ በዐይነ ሥጋ የሚታይ ግዙፉ አውሬ ሐሳዌ መሲሕ ብቻ ቢሆንም በዐይን የማይታይ ነገር ግን ከግዙፉ አውሬ የማይለይ ረቂቁ አውሬ አብሮ አለ:: በሐሰተኛው ነቢይ ከተሰበኩት ተሰ ብከውም ከአመኑት ሰዎች የሚቀርበውም የስግደት የምስጋና የአክብሮትና የአምልኮት ግብርን በይገባኛል ባይነት ለመቀበል እጆቹን ይዘረጋል:: በጥንተ ፍጥረት ተመኝቶት የነበረውን አምላክነት ያገኘሁት መስሎት በመጐምጀት ሐሰተኛው ነቢይ ያሳታቸው ሰዎች እንዲንበረከኩለት ያደርጋል::

አምልኮትና ስግደት ምስጋናም ሰማይንና ምድርን የብ ሱንና ባሕሩን መላእክትንና ደቂቀ አዳምን እንስሳትንና አራዊ ትን አፀዋትንና አዕባንን /ደንጊያዎችን/ በአጠቃላይ ተንቀሳቃ ሽንና ኢተንቀሳቃሽ የሆኑ ፍጥረታትን ለፈጠረ ሁሉን ማድረግ ለሚቻለው ብቸኛ ለሆነው አምላክ የሚቀርቡ ሲሆን በሐሰተኛው ነቢይ ስብከት የተሳሳቱ ሰዎች ለአውሬው ለሐሳዌ መሲሕ ያቀርቡለታል:: እነዚህ ሰዎች ወደ እውነት የሚያደርሰውን መንገድ ትተው እሾህና እንቅፋት በሞላበት ዋሻ እየወደቁና እየተነሱ እየደሙና እየቆሰሉ እንዲጓዙ ሐሰተኛው ነቢይ የሚ መራቸው ሰዎች ናቸው:: እንግዳ በሆኑ ነገሮች ተደናግጠው በምልክቶች ተማርከው የስሕተት ሰለባዎች የሚሆኑ ሰዎች ናቸው::

ከነጋዴዎች መካከል እራስ ወዳድነት ያሸነፋቸውና ለሌ ላው ሰው ሕይወት የማይጨነቁ ነጋዴዎች፣ መዳቡን ወርቅ ነው ብለው ድንችና ሙዝን ከቅቤ ጋር ቀላቅለው፣ የሸክላውን ዱቄት ከበርበሬ ጋር ጥቁር አሸዋን ከኑግ ጋር በመቀላቀል ወዘተ... ተመሳሳይ ነገሮችን ሁሉ በማሰባሰብ የየዋሁን ሕዝብ ልቡና እንደሚያታልሉ ሁሉ ሐሰተኛው ነቢይም ርጉሙን ፍጡር ፈጣሪ ነው ብሎ ሐሰተኛውን እውነተኛ ኃጢአተኛውን ጻድቅ አስመ





ስሎ የተለያዩ ምልክቶችን ለማስመሰል ተግባሩ ማበረታቻ በማድረግ ብዙ ሰዎችን ወደ ስሕተት ገደል ገፍቶ ይጥላቸዋል::

መቼም መዳብ መሆኑን እያወቀ በወርቅ ዋጋ መዳብን የሚገዛ ሙዝና ድንች የተቀላቀለበትን ቅቤና አሸዋ የተቀላቀለ በትን ኑግ እያወቀ በዚያው በኑጉና በቅቤው ዋጋ የሚገዛ ሰው አይኖርም:: ይልቁንም ይህ ዘዴ የገባው ሰው አታላዩን ነጋዴ በወንጀል ከሶ ያሳስረዋል:: ይህን ተንኮሉን ለደንበኞቹ ግልጽ አድርጐ የሚቀርብ ነጋዴም አይኖርም:: ሐሰተኛው ነቢይ እን ደዚህ ባለ ስግብግብ ነጋዴ ቢመስል ዓይነተኛ ምሳሌ ሳይሆን አይቀርም:: ሐሰተኛው ነቢይ የራሱን ስሕተትና አምላክ እንደ ሆነ የሚናገርለትን ሰው ስሕተት ገልጾ ቢናገር ተንበርክኮ የሚ ሰግድ ይቅርና ትምህርቱን የሚሰማ አይገኝም ነበር:: በተለይም የሚሰግዱለት ሰዎች ሐሳዌ መሲሕ የሰይጣን ማደሪያ መሆኑን ቢረዱ ኖሮ እያማተቡ እሩጫቸውን በተያያዙት ነበር:: ከብዙ ወተት ጋር ጥቂት መርዝ ተጨምሮ የተሰጣቸው ሰዎች የወተ ቱን መልክ በማየት እና ጣዕሙን በማጣጣም ሳያውቁት የጨለ ጡት መርዝ ወደ ሆዳቸው ከገባ በኋላ መርዝነቱን አስታውቆ እንደሚገድላቸው በሐሰተኛው ነቢይ ምልክቶች ተታለው ለሐ ሳዌ መሲሕ የሚሰግዱ ሰዎችም ለፍጡር በመስገዳቸው ተፈርዶ ባቸው ከሰገዱለት ፍጡር ጋር ወደ ገሃነም ይወርዳሉ::

ስሕተት ስሕተት መሆኗን ሳያውቁ በሐሰተኛው ነቢይ ስብከት ተታለው ለሐሰተኛው ክረስቶስ የሰገዱትና ያመለኩት ሰዎች ለምን ወደ ገሀነም ይወርዳሉ? ለምንስ ይፈረድባቸዋል? ተብሎ ይጠየቅ ይሆናል:: መልስ - እነዚህ ሰዎች ከእውነተኛው አምላክ ሕግ አፈንግጠው የወጡ ሰዎች ናቸው:: መልካሚቱንና ወደ ሕይወት የምትወስደውን መንገድ አምልኮተ እግዚአብ ሔርን ትተው ራሳቸው በጠረጉት መንገድ የሚጓዙ ሰዎች ናቸው:: ሰዎች እግዚአብሔርን ሲተው እግዚአብሔርም ይተዋ ቸዋል:: «እንደ ልባቸው ሥራ ተውኋቸው በልባቸውም አሳብ ሔዱ:: ሕዝቤስ ሰምቶኝ ቢሆን እስራኤልም በመንገዴ ሄደው ቢሆን ጠላቶቻቸውን ፈጥኜ ባጠፋሁላቸው ነበር» መዝ.80÷12-16 በእነዚህ ሰዎች ላይ አታላዩንና ዐመፀኛውን መምህር ሐሳዌ ኤልያስን የሚያመጣባቸው የመጀመሪያው እምቢተኛነታቸው



www.ethiopianorthodox.org

ነው። ምንጊዜም ቢሆን የመጀመሪያው ኃጢአት ለሁለተኛው ኃጢአት መንገድ ነው የሚሆነው።

## ምስል ማሠራቱ

«የሰይፍም ቁስል ለነበረውና በሕይወት ለኖረው ለአውሬው ምስልን እንዲያደርጉ በምድር የሚኖሩትን ይናገራል» ራእይ 13÷14 ከዚህ በፊት እንዳየነው አውሬ የሚለው ንባብ ዲያብሎስንም ሐሳዌ መሲሕንም ያስተረጉማል። ይህ አውሬ የሰይፍ ቁስል እንደነበረውና ከቁስሉ ተፈውሶ በሕይወት እንደ ሚኖር ባለራእዩ ዮሐንስ ደጋግሞ ገልጾታል። አውሬ የሚለው ንባብ ዲያብሎስ ተብሎ ሲተረጐም የዲያብሎስ ቁስል ምን እንደነበረ፣ መቼ እንደቆሰለና መቼ እንደሚፈወስ ከዚህ በፊት አይተናል። ሁለተኛ የቁስሉን ምንነትና ፈውስ የተባለውን ለማብራራት መሞከር የቃላት ድግግሞሽን መከመር ስለሚሆን በዚህ እንተወዋለን።

ሐሰተኛው ነቢይ በሥራ አስፈጻሚነት ከሚያከናውናቸው የሥራ ዘርፎች አንዱ ለአውሬው ለሐሳዌ መሲሕ ምስል ማሠራት ነው። ረቂቁ አውሬ ዲያብሎስ ከግዙፉ አውሬ ከሐሳዌ መሲሕ ስለማይለይ የሚሳለው ሥዕል የሚመስለው ምስል በግዙፉ አውሬ በሐሳዌ መሲሕ መልክእ ይሆናል። ተፈጥሮው ሰው ሲሆን ግብሩ ከአውሬ እንጂ ከሰው የማይስማማ በመሆኑ በባለራእዩ በዮሐንስ ሰያሚነት አውሬ ተብሎ የተሰየመው ሐሳዌ መሲሕ ከደቂቀ አዳም የክብር ደረጃ ባለመድረሱ ደረጃው በአራዊት ደረጃ ልክ ሆኖ ሳለ በሐሰተኛው ነቢይ አንደበት ግን አምላክ እንደሆነ ይነገርለታል።

ሐሰተኛው ነቢይ ምስል የመመሰልና ቅርጽ የመቅረጽ ችሎታ ያላቸው ጠበብቶችን በማሰባሰብ አምላክነቱን የሚመሰክርለትን የሐሳዌ መሲሕን ምስል አሠርቶ ያቆማል። የሐሳዌ መሲሕ ምስል እንዴት ሆኖ መሠራት እንዳለበት መመሪያ የሚሰጥና የሚከታተል ያው ሐሰተኛው ነቢይ ነው።

ምስል ማለት ዋናውን ባለቤቱን የሚመስል የሚመሰልለትን የባለቤቱን መልክእ የሚገልጽ ባለቤቱን ተክቶ የሚቆምና





የሚታይ ማለት ነው። የሐሳዌ መሲሕ ምስል በትክክል ይሠራ ከተባለ ባለራእዩ ዮሐንስ እንዳየው አሥር ቀንዶችና ሰባት ራሶች ያሉት አውሬ ሆኖ መቀረጽ ነበረበት። በራሶቹም ላይ የስድብ ስም ሊኖርበት ይገባ ነበር። ገጽታው ነብር የሚመስልና እንደጅብ እግሮች ያልተስተካከሉ እግሮች ያሉት እንደ አንበሳ አፍ ከመጠን በላይ ሰፊ የሆነ አፍ ያለው ደም የምትመስል አንዲት ዓይን ብቻ ያለችው አውሬ አይሉት ሰው ሰው አይሉት አውሬ ጉዳጉድ ነገር ሆኖ መሠራት ነበረበት።

ነገር ግን ሐሰተኛው ነቢይ እንዲህ አድርጐ አያሠራውም። ይህን ያህል ጉድ የተሸከመ ምስል አሠርቶ የአምላካችን መልክ ይህን ይመስላል ብሎ አያስተዋውቀውም። «አባቴ ታናሽ ነው ሃይማኖቴ ግብዝ ነው የሚል የለም» ይባል የለ? መቼም አምላክነቱን እየሰበከ ከአውሬ ጋር ያለውን ዝምድና አይገልጽበትም። «ባለቤቱ ያቃለለውን አሞሌ ባለእዳ አይቀበለውም» እንዲሉ። ጅብ የሚመስል አምላክ ተቀበሉ ቢል ማን ያዳምጠዋል፤ ጥሩ የሆነ ምስል እንደሚያሠራለት ይገመታል። አውሬነቱን ከገለጸማ ነቢዩም ነቢየ ሐሰት መባሉ ቀርቶ ነቢየ ጽድቅ በተባለ ነበር። አውሬነቱን ቢገልጽስ የሰገዱለትን ሰዎችም አሳሳተ ባልተባለም ነበር። እንደ እባብ መርዙን በውስጥ ቀብሮ ውጫዊ አካሉን አለስልሶ ያሳስታቸዋል እንጂ። በምልክቶች ውዥምብር እያናወጠ የሚያርፉበትን ቦታ በማሳጣት እርሱ ወደፈለገው አቅጣጫ የሚነዳቸውን ሰዎች በክሕደት ጉድጓድ ውስጥ ይቀብራቸዋል እንጂ።

## ምስል ማናገሩ

«የአውሬው ምስል ሊናገር እንኳ ለአውሬውም ምስል የማይሰግዱለትን ሁሉ ሊያስገድላቸው ለአውሬው ምስል ትንፋሽ እንዲሰጠው ተሰጠው» ራእይ 13÷15 ይህ ንባብ በጠበብቶች ጥበብ የተሠራውን የሐሳዌ መሲሕን ምስል ወይም ስዕል የማናገር ችሎታ ለሐሰተኛው ነቢይ እንደሚሰጠው ይገልጻል። የሐሳዌ መሲሕን ስዕል ወይም ምስል ማናገር ሐሰተኛው ነቢይ ከሚያደርጋቸው ምልክቶች አንዱ ነው። ምስልን ወይም ስዕልን



www.ethiopianorthodox.org

የማናገር ችሎታ ለሐሰተኛው ነቢይ ማን ሰጠው ተብሎ ቢጠየቅ ከሰማይ እሳት የማውረድ ችሎታንስ ማን ሰጠው የሚለው ጥያቄ ይከተለዋል::

ሆኖም በጥያቄ ላይ ጥያቄ ተጨመረ እንጂ የመጀመሪያው ጥያቄ መልስ አላገኘም:: ለሁለቱም ጥያቄዎች መልስ ሊሆናቸው የሚችል ኃይለ ቃል ቢኖር ምልክቶችን የማድረግ ችሎታ ያለው ረቂቁ መንፈስ ዲያብሎስ ነዋ የሚለው ኃይለ ቃል ይሆናል:: ነገሮችን በማስመሰል የብዙ ሺህ ዓመታት የሥራ ልምድ ያለው ዲያብሎስ ሐሰተኛው ነቢይ በአሳለው የሐሳዊ መሲሕ ስዕል ጠጋ ብሎ የተፈለገውን ነገር መናገርና ስዕሉ የተናገረ ማስመሰል እንደማያቅተው ለአንባብያን ግልፅ ነው:: ሐሰተኛው ነቢይ ከሐሰት አባት ከዲያብሎስ ጋር አብሮ ስለሚሠራ የሐሳዊ መሲሕን ምስል ወይም ስዕል ትንፋሽ የሚተነፍስ ዓይኑ የሚቁለጨለጭ ሲጠይቁት መልስ የሚሰጥ ሕይወት ያለው ነገር ያስመስለዋል::

## ለስዕሉ በማይሰግዱት የሚወሰድ እርምጃ

ሐሰተኛው ነቢይ በሰይጣናዊ ምትሐት የሐሳዊ መሲሕን ስዕል ከአናገረ በኋላ በምድር የሚኖሩት ሁሉ ለዚህ ስዕል እንዲሰግዱለት ጽኑእ አዋጅ ያውጃል:: የስዕሉ መናገር የአምላካዊ ኃይል መገለጫ መስሎ የታያቸው፣ የእግዚአብሔር ማኅተም በግንባራቸው የሌላቸው፣ የያዙትን ለመልቀቅና ያልያዙትን ለመቀበል ፈጣኖች የማያገናዝቡ፣ በምልክቶች የሚታለሉ መሠረተ እምነት የሌላቸው ሰዎች ለሐሳዊ መሲሕ ስዕል ይሰግዳሉ::

በአንጻሩ ደግሞ ሰይጣን የተለያዩ ምልክቶችን ማድረግ እንደሚችል እውነት የሚመስሉ የማሳሳቻ ዘዴዎችን እንደሚጠቀም የተረዱ፣ በእውነተኛው ክርስቶስ ስም ሐሰተኛው ክርስቶስ እንደሚመጣና የእርሱን ነገር የሚሰብክ በእውነተኛው ኤልያስ ስም ሐሰተኛ ኤልያስ እንደሚያስነሳ ከቅዱሳት መጻሕፍትና ከመምህራን ያገኙትን እውቀት በአግባቡ የሚተረጉሙ ሰዎች ለሐሰተኛው ክርስቶስ ስዕል አይንበረከኩም:: ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ ሲመጣ ሕዝብ በመሰብሰብና ተአምራት በማድረግ





እንደማይመጣ በወንጌል የተነገረውን ያልዘነጉና በምልክቶች የማይታለሉ በሰዎች ላይ የሃይማኖት ድርቅን የሚፈጥር ዲያብሎሳዊ ነፋስ በነፈሰ ጊዜ ሊገለባብጣቸው ሲሞክር አምልኮተ እግዚአብሔርን ሙጭጭ አድርገው የያዙ ምእመናን ለዚያ ርኩስ ስዕል አይሰግዱም:: የስዕሉ መናገርም አያስደንቃቸውም:: የሐሰተኛው ኤልያስና የሐሰተኛው ክርስቶስ ጉራም አያስደነግጣቸውም::

ሐሰተኛው ነቢይ ለሐሳዊ መሲሕ ስዕል አንሰግድም በሚሉት ምእመናን ላይ የተለያዩ የቅጣት እርምጃዎችን ይወስዳል:: በእስራት፣ በግርፋት በሌሎችም እነዚህን በመሰሉ በሚያስጨንቁ ሥቃዮችና መከራዎች ውስጥ እንዲገቡ በማድረግ ወደአምልኮተ ሐሳዊ መሲሕ ለማምጣት ይሞክራል:: ምእመናን ግን «ሥጋችሁን የሚገድሏችሁን አትፍሩአቸው ነፍሳችሁን ግን መግደል አይቻላቸውም» የሚለውን የጌታቸውን የኢየሱስ ክርስቶስን ቃል መሠረት በማድረግ በሐሰተኛው ክርስቶስ እጅ የሚቀዳውን የመከራ ጽዋ በድፍረት ይጎነጩታል እንጂ ለስዕሉና ለምስሉ አይንበረከኩም::

የሐሳዊ መሲሕን አምላክነትና የእርሱን ምትሐታዊ ምልክት በማቃለላቸው የተናደደው ሐሳዊ ኤልያስ በሐሳዊ መሲሕ ቤተ መንግሥት ውስጥ በሚገኘው የጦር ኃይል ምእመናንን ያስገድላቸዋል በሰይፍ ያስቀላቸዋል፣ ያሳርዳቸዋል::

ሐሳዊ መሲሕ ኃላፊ ጠፊ ፍጡር መሆኑን ሐሳዊ ኤልያስም ሆነ ራሱ ሐሳዊ መሲሕ ሳይረዱት አይቀሩም:: የዘለዓለማዊነት ተስፋ ቢኖረው ኖሮ ያላመኑበትን ሰዎች ኋላ በገሃነመ እሳት ዘለዓለማዊ ቅጣት እቀጣቸዋለሁ ባለ ነበር:: ወይም በእኔ ካላመናችሁ ዘለዓለማዊ ሕይወት የላችሁም በማለት የቀቢጸ ተስፋ /ተስፋ የማስቆረጥ ድምፅን አሰምቶ በተዋቸው ነበር:: ወይም ልትድኑ ትወዳላችሁን? በማለት ፈቃደኞችን ብቻ በተቀበለ ነበር:: ወይም ለእኔ መንግሥት የተመረጡ ጥቂቶች ናቸው በማለት በተወሰኑ አማኞች በረካ ነበር:: ወይም ሰዎች በትምህርቱ ተመስጠው በተአምራቱ ተስበው በአምላክነቱ እስኪያምኑ ድረስ በታገሳቸው ነበር::

ነገር ግን ያለው እንቅስቃሴ ሁሉ በሞት እንደሚገታና ከሞተም በኋላ በጠላቶቹ ላይ መፍረድ ይቅርና ሕልውናውን



www.ethiopianorthodox.org

ማግኘት እንደማይቻለው ስለሚያውቅ አምላክ ነኝ ማለቱም ሰዎችን ለማታለል እንጂ ስንኳን የባሕርይ አምላክነት «አንስ እቤ አማልክት አንትሙ፤ እኔ አማልክት ብያችኋለሁ» እንደ ተባሉ እንደቅዱሳን የጸጋ አምላክነት የሌለው ከጸጋ እግዚአብ ሔር የተራቆተ ፍጹም ድሀ መሆኑን ስለሚረዳ ለጊዜው በሠራዊቱ እጅ ባገኘው ሰይፍና ጦር ምእመናንን ይበቀላል።

ይህ ፍሬ ሐሳብ በአጭር ዓረፍተ ነገር ሲገለጽ:- ሐሳዌ መሲሕን አምላክ አይደለህም መባሉ የሚያበሳጨው አምላክ አለመሆኑን ስለሚረዳ ነው። አንድ አስተዳደር የማይችልን ሰው በሥልጣን ላይ እያለ አስተዳደር አትችልም ቢሉት በጣም ይናደዳል። ቁስሉ ተነክቶበታልና ይጠዘጥዘዋል። የሚያስተዳድ ራቸው ሰዎችም ይህን ቢሰሙ የሚገባውን ስድብ አገኘ የማለት ምስክርነታቸውን ለመስጠት ራሳቸውን ይነቀንቃሉ። ችሎታ ያለው ሰው የዚህን ዓይነት ስድብ ቢሰደብ ግን ተሳዳቢውን መገምገም እንደማይችል እንዳላዋቂ በመቁጠር ይንቀዋል እንጂ በስድቡ አይናደድም። ስድቡን የሰሙ ሰዎችም ይህ ዓይነቱ አነጋገር ከጥላቻ የመነጨ እንደሆነ ይገነዘባሉ እንጂ ራሳቸውን አይነቀንቁበትም። የሐሳዌ መሲሕ ርኩስ ተግባር የመጀመሪያ ውን ሰው ምሳሌ የያዘ ሲሆን የእውነተኛው ክርስቶስ ቅዱስ ተግባር ደግሞ የሁለተኛውን ሰው ምሳሌ የያዘ ይሆናል።

## ክርስቶስ ወደ ምእመናን የቀረበበት መንገድ

ክርስቶስ ወደ ምእመናን የቀረበበት መንገድ ሐሳዌ መሲሕ ከሚቀርብበት መንገድ እጅግ የተለየ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በጦርና በሰይፍ የታጀበ ወንጌልን አልሰበከም። የተአ ምራቱ ኃይልም በሠራዊት ኃይል አልታገዘም። ያላመኑበትንም በመጨረሻው ዘመን ፍርድ እንደሚጠብቃቸውና ዘለዓለማዊ ሕይወት እንደማይኖራቸው አስጠነቀቃቸው እንጂ የአምላክነቱን ኃይል ሊገልጥባቸው አልፈለገም። በተአምራቱ ከደዌ ሥጋ በትምህርቱ ከደዌ ነፍስ ያዳናቸውን ሰዎችም ልትድኑ ትወዳላ ችሁን? ብሎ በመጠየቅ አስወድዶ አስፈቅዶ አዳናቸው እንጂ አላስገደዳቸውም። የተጠማ ቢኖር ወደእኔ ይምጣ የሕይወትንም





ውሃ ይጠጣ አለ እንጂ የሕይወት ውኃን የተጠሙትን እንደ መንፌቅ ሕፃን ያለውድ በግድ አልጋታቸውም።

ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ እርሱ የሚመጡትን ሰዎች ከል ባቸው ጋር እንጂ በእግራቸው ብቻ እንዲመጡ አልፈለገም። ሳያምኑበት ጊዜያዊ ጥቅም ፈልገው ወደ እርሱ የመጡትን ሰዎች ራሱን ጉድጓድ ካላቸው ቀበሮችና መጠለያ ካላቸው ወፎች በማሳነስ እነርሱን መቀበል እንደማይፈልግ ነግሮ አሰና ብቷቸዋል። ኢየሱስ ክርስቶስ ነጻነቱን በሰይጣን የተገፈፈውንና የተራቆተውን የአዳም ዘር ሁሉ የቀደመ ልብሱን /ልጅነትን/ በማልበስና በሞቱ የተገኘ የጺጋውን ካባ በመደረብ ወደ ክብረ መንበሩ ለመመለስ መጣ እንጂ አምላካዊ ግብሩን ገልጦ ከሰዎች ክብርን ለመቀበል አልመጣም።

ስለሆነም በግድ እመኑብኝ አላለም። አምላክነቱን ባልተ ቀበሉት ሰዎች አልተበሳጨም። ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ ቢያ ምኑ በአምላክነት ክብሩ ላይ የሰናፍጭ ቅንጣት ታህል ክብር አይጨምሩም። ባያምኑም ከአምላካዊ ክብሩ ይችኑ ቅንጣት ታህል አይቀንሱም። የሰዎች ማመንና አለማመን የራሳቸውን ክብር በማሳደግና በማሳነስ ላይ ብቻ የተመሠረቱ ናቸው። እው ነተኛው ክርስቶስ ሰዎችን ለመቅጣት አይቸኩልም የሰደቡትንም ቢሆን፣ ደንጊያ የወረወሩበትንም ቢሆን፣ ከሰው በጲላጦስ አደባ ባይ ያቆሙትንም ቢሆን፣ በሐሰት የመሰከሩበትንም ቢሆን፣ የሰቀሉትንም ቢሆን፣ እንደተበቀሉኝ ልበቀላቸው አላለም። 1ጴጥ. 2÷23 ሥልጣኑ ዘለዓለማዊ ስለሆነ የሥልጣኔ ዘመን ሳያልፍ እርምጃ ልውሰድባቸው አይልም። ነገሮችን የሚያገናዝ ቡበት ዕድሜ በእውነት መንገድ ላይ ተጉዘው ወደእምነት የሚደርሱበት ዕድሜ ንስሐ የሚገቡበትና የሚመለሱበት ዕድሜ ይሰጣቸዋል እንጂ ፈጥኖ አይፈርድባቸውም። የክርስቶስ መገለጥ ይህን ሲመስል ሐሳዌ መሲሕ ግን ትንሽ ያላት እንቅልፍ የላት እንዲሉ ባለችው ትንሽ ኃይል እርምጃ ለመውሰድ የሚቸኩል በመሆኑ ፍጡርነቱን በተግባሩ ያንጸባርቃል።

«ታናናሾችና ታላላቆችም ባለጠጋዎችና ድሆችም ጌታ ዎችና ባሪያዎችም ሁሉ በቀኝ እጃቸው ወይም በግምባራቸው ምልክትን እንዲቀበሉ ያደረጋል» ራእይ 13÷16 የሐሳዌ ኤል ያስ /የሐሰተኛው ኤልያስ/ የሥራ ድርሻው ሐሳዌ መሲሕን



www.ethiopianorthodox.org

/ሐሰተኛው ክርስቶስን/ በአምላክነት ደረጃ ለሕዝብ ማስተዋወቅና ስዕሉን ማሳል ምስሉን ማስመሰል ላስመሰለው ምስልና ላሳለው ስዕል ሰዎች እንዲሰግዱለት መልእክት ማስተላለፍ ነው:: በተጨማሪም በሐሳዌ መሲሕ ግዛት ውስጥ የሚኖሩትን ሰዎች ከሽማግሌዎች እስከ ልጆች ከባለጸጋዎች እስከ ድሆች ድረስ የሐሳዌ መሲሕን የስሙን ምልክት በግምባራቸው ወይም በቀኝ እጃቸው እንዲቀበሉ ማድረግ ነው:: ሐሳዌ መሲሕን አምላኪየ ፈጣሪየ ብሎ የተቀበለው ሁሉ የስሙን ምልክት በግምባሩ ወይም በቀኝ እጁ እንዲጽፍ ሐሰተኛው ነቢይ በትጋትና በንቃት ያስተምራል::

እንዲህም የሚያደርገው ሐሳዌ መሲሕ በዓይኑ ከሚያየውና በጆሮው ከሚሰማው በቀር የተሰወረውንና የተደበቀውን ነገር የማያውቅ ግብዝ ደንቆሮ ፍጡር ስለሚሆን ነው:: አምላክነቱን የተቀበሉትንና ያልተቀበሉትን ለይቶ ማወቅ ስለማይችል አማኞች የስሙን ምልክት በግምባራቸውና በቀኝ እጃቸው እንዲጽፉ ግዴታዊ ትእዛዝ ስለሚያስተላልፍ ነው:: ዕውቀቱ የተወሰኑ ክልሎችን በማየትና የተወሰኑ ኢንፎርሜሽኖችን በማሰባሰብ የተገታ ዓይኑን ተራራ የሚጋርደው ከተራራ ወዲያ ያለውን የማያይ ጆሮውም ካለበት ግንብ በስተጀርባ የተነገረውን የማይሰማ እንደማናቸውም ሰው በአካባቢው ያለውን ብቻ በማየትና በመስማት የተወሰነ ውሱን ፍጡር በመሆኑ አማኞቹን ለማወቅ የስሙን ምልክት በግምባራቸውና በእጃቸው ከማጻፍ ሌላ አማራጭ የለውም::

ተከታዮቹ በአንደበታቸው እያመሰገኑ በልባቸው ቢነቅፉት፣ በአንደበታቸው ስለአምላክነቱ እያወሩ በውስጣቸው ስለ ፍጡርነቱ ቢወያዩ፣ አንደበታቸው ስለ ኃያልነቱ ሲቀባጥር ልባቸው ስለደካማነቱና አስመሳይነቱ ቢያጉረመርም ምን ታስባላችሁ ብሎ የማይጠይቅ ግብዝ ነው::

«የአውሬውም ስም ወይም የስሙ ቁጥር ያለው ምልክት የሌለበት ማንም ሊገዛ ወይም ሊሸጥ እንደማይችል ያደርጋል» ራእይ 13÷17 ሐሰተኛው ነቢይ ሰዎችን ወደ ሐሰተኛው ክርስቶስ ለማምጣት ምትሐታዊ ምልክት ማድረግ እምቢተኞችን በሰይፍና በጦር ማስገደል ሰፊ መንገድ አይደለም ሊበቃም አይችልም በማለት ሌላ መንገድ ያስጠርጋል:: ሰዎች ያለውድ





በግድ የሐሳዌ መሲሕን አምላክነት እንዲቀበሉ ለማድረግ ውጤታማ የሚሆነው ዘዴ የኑሮአቸውን መንገድ ማጥበብ ብቻ ነው ይላል:: መቼም ሰው በዚህ ዓለም ሲኖር የሥራ ውጤቱን በመሸጥና ለሥጋዊ ሕይወቱ አስፈላጊ የሆነውን ነገር በመግዛት ኑሮውን የሚገፋ መሆኑ ይታወቃል:: ነጋዴም ሆነ የቢሮ ሥራ ያለው ሰው ካልሸጠ ካለወጠ ቤተሰቦቹንና ራሱን በትክክል ሊመራ አይችልም:: ገበያ ያዘመረችውን የማያጭድ የለም:: ስለሆነም ሰዎችን አስጨንቆ፣ አስጠብቦና መፈናፈኛ አሳጥቶ በክሕደት አጥር ውስጥ እንዲቆዩ ለማድረግ የፈለገው ሐሰተኛው ነቢይ የአውሬው ስም ወይም የስሙ ቁጥር ምልክት በግምባሩ ላይ ወይም በቀኝ እጁ የሌለበት ሰው ወደገበያ ወጥቶ መሸጥ መለወጥ እንዳይችል ጽኑ አዋጅ ያውጃል::

ገበያ የሰዎች ጥቅም መግቢያ ዋና በር መሆኗን የተረዳው ይኸው ሐሳዌ ኤልያስ ወደ አምልኮተ ሐሳዌ መሲሕ ያላዘነበሉትን ሰዎች ገበያ ከምታስገኘው በረከት ሁሉ ይለያቸዋል:: የአውሬው ምልክት የሌለበት ሰው ወደገበያ ወጥቶ ከተገኘ የያዘውን ንብረት በሙሉ ተወርሶ ወደ ወህኒ ቤት እንዲወርድ ይደረጋል:: እንደ ሌባ እንደወንበዴ በመቆጠር በሐሳዌ መሲሕ ፖሊሶች ይደበደባል:: የሥቃይና የመከራ ጽዋን ይቀምሳል::

ሐሰተኛው ነቢይ በዚያ ዘመን ተወልደው የተገኙትን የሰው ዘሮች የአእምሮ ደካማዎቹን በምልክቶች በሠራዊተ አጋንንት ኃይል የጉልበት ደካማዎቹን በሰይፍ፣ በጦር በሐሳዌ መሲሕ የጦር ኃይሎች እያስነዳ በሐሳዌ መሲሕ አምልኮት ግቢ ውስጥ ይመላቸዋል:: የሰው ነጻነት እንደጭራ የቀጠነበት እንደድንክ ያጠረበት እንደበጋ የውኃ ምንጭ የነጠፈበት ዘመን ቢኖር የሐሳዌ መሲሕ ዘመን ነው:: የመንግሥቱ ዘመንም በአጭር የሚቀጨው ከተንኮሉ ብዛት የተነሣ ነው «እነዚያ ቀኖችስ ባያጥሩ ሥጋ የለበሰ ሁሉ ባልዳነም ነበር:: ነገር ግን እነዚያ ቀኖች ስለተመረጡት ሰዎች ያጥራሉ» ማቴ. 24÷22 ከሰው ልጅ አእምሮ አውድማ የእውነትና የነፃነት ምርትን ጠራርጎ ካስወጣ በኋላ በምትኩ የሐሰትና የጭንቀት ገለባን የሚቆልልበት የዲያብሎስና የሐሳዌ መሲሕ መልእክተኛ /ሠራተኛ/ የሆነው በኤልያስ ስም የሚነግደው ሐሳዌ ኤልያስ ነው::



www.ethiopianorthodox.org

# የሐሰተኛው ኤልያስ ዋጋ ምን ይሆን?

ሐሰተኛው ኤልያስ የሐሳዌ መሲሕን አምላክነት ለማንጸባረቅ ደፋ ቀና የሚለው በምን ያህል ዋጋ ተገዝቶ ይሆን? መቼም ቢሆን የሰው ልጅ እንደነፋስና እንደውኃ ሌሎችን ለመጥቀም ብቻ እንደማይንቀሳቀስ የታወቀ ነው:: ሰው ሲባል ችሎታው በደረሰበት ልክ እራሱን ለመጥቀም የሚወጣ የሚወርድ ፍጡር ነው:: ለሰዎች ጥቅም ብቻ ሲል እንደሻማ አይቀልጥም እንደፋና አይከስልም::

የሀገር ዳርድንበር የሚጠብቁ ወታደሮች እግራቸውን ለጠጠር ደረታቸውን ለጦር ሰጥተው የሚዋጉት ከባለሥልጣኖች ሹመት ሽልማት ፈልገው ነው:: በፖለቲካዊ መድረክ ተሰልፈው የሚተጋተጉትም እንዲሁ ራሳቸውን ለማብለጥና አንደኛውን ደረጃ ለመያዝ ነው:: ወላጆች ልጆቻቸውን ተንከባክበው የሚያሳድጉ የሚያስተምሩ ኋላ ጉልበታችን ሲደክም ይረዱናል ይንከባከቡናል ብለው ነው:: በተስፋ የሚጠባበቁት ጥቅም አለ ማለት ነው:: አንዳንድ ጊዜ እንኳ ልጆቻቸው የማይረዷቸው ወላጆች የወላድ መካን እንደሆኑና ድካማቸው በከንቱ እንደቀረ ሲገልጹ ይደመጣሉ::

ጻድቃን በገዳም ድምፀ አራዊቱን ግርማ ሌሊቱን ታግሰው ጤዛ ልሰው ድንጋይ ተንተርሰው የሚኖሩት የማታልፈውን መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ ነው:: የሌለውን እንዳለ የምታደርግ ተስፋን ተመልተው ነው:: ሰማዕታት ወደነደደ እሳት የሚገቡት በተሳለ ስለት የሚቀሉት የደማቸውንና የድካማቸውን ዋጋ ከፈጣሪያቸው ዘንድ በመጠባበቅ ነው:: የሚያከብራቸው እግዚአብሔር ክብር የማያልቅበት ባዕለ ጸጋ መሆኑን ስለተረዱና በቸርነቱ ስለሚተማመኑ ነው::

ሐዋርያት ዓለምን ዞረው ያስተማሩ መንግሥተ ሰማያትን በዓይነ ተስፋ እየተመለከቱ ነው:: ዋጋቸው እንደማይቀርባቸው ተነግሮአቸዋል:: በማቴ.19÷27-30 ዋጋቸውን ደሞዛቸውን በተመለከተ «እነሆ እኛ ሁሉን ትተን ተከትለነሃል እንኪያስ ምን እናገኝ ይሆን» በማለት በጴጥሮስ አንደበት ላቀረቡት ጥያቄ በ12ቱ ነገደ እስራኤል ለመፍረድ በ12 ዙፋን





እንደሚቀመጡና ስለስሙ ቤቶቻቸውን ወንድሞቻቸውን እ
ቻቸው ከሚስታቸው ጋር መላውን ቤተሰባቸውን መረባቸው
እርሻቸውን ትተው የተከተሉት መቶ እጥፍ እንደሚቀበሉ
የዘለዓለምን ሕይወት እንደሚወርሱ በመግለጽ ጌታ የመለ
ቸው መልስ አርክቷቸዋል:: ጨክነው መከራውን እንዲቀበ
ያደረጋቸውም ይኸው የተስፋ ቃል ነበር::

የሰው ልጅ ወዶና ፈቅዶ በመከራዎች ውስጥ የሚ
ልፈውና ለሥጋዊም ሆነ ለመንፈሳዊ ተግባር የሚሮጠው ል
ካሰበው ግብ ለመድረስ ነው:: ያለጥቅም ያለተስፋ ወደ አን
አቅጣጫ እግሩን የሚያነሳ ሰብአዊ ፍጡር አይኖርም:: በዚ
ዓለምም ሆነ በወዲያኛው ዓለም የሚያገኘው አንዳች ነገር ሳ
ኖር የደከመ ለሰው ልጅ ቤዛ ራሱን ለሕማም ለሞት አሳል
የሰጠ ክርስቶስ ብቻ ነው:: እንዲህ ከሆነ ሐሰተኛው ኤልያስ
የሰው ዘር ሥጋና ደም ያሉት በመሆኑ በዚህ እሩጫው ሊያ
ኘው ተስፋ ያደረገው ወይም ከመሮጡ በፊት የጨበጠው አንደ
ነገር እንደሚኖር አንጠራጠርም::

ሐሰተኛው ኤልያስ የሐሳዌ መሲሕ አምላክነት ተቀባይ
ነትን እንዲያገኝ የሚጥረው፣ ዮሐንስ አውሬ በማለት የገለፀው
ከሐዲ ክርስቶስ አሰኝቶ ሲሰብክ እራሱንም ኤልያስ አሰኝቷልና
ለኤልያስ ተለክቶ የተሰፋውን የክብር ካባ የራሱ አስመስሎ
ለመጐናፀፍ ፈልጎ ይሆናል:: ወይም በሐሳዌ መሲሕ ቤተ መንግ
ሥት ውስጥ የሚገኘው የወርቁና የብሩ ሽልማት አስጐምጅቶት
ይሆናል:: ወይም ሐሳዌ መሲሕ ከእኔ በታች ያለውን የቤተ
መንግሥት ሥልጣን እሰጥሀለሁ በሕዝብም ላይ እሾምሀለሁ ስለ
ሚለው ይሆናል:: ወይም ባላቅ መተተኛውን በለዓምን «እስራኤ
ልን እረግመህ ብታጠፋልኝ ክብርህን እጅግ ታላቅ አደርገዋለሁ
የተናገርኸውንም ሁሉ አደርግልሀለሁ» ዘኍ. 22÷1-41፤ 23÷1
እንዳለው ይህን የመሰለ ተስፋ በሐሳዊ መሲሕ አንደበት
ይነገረው ይሆናል:: ወይም ምትሐታዊ ምልክትን በማድረግ
የመተተኝነትና የአስማተኝነት ችሎታውን ለማንጸባረቅና ለመ
ደነቅ ፈልጎ ይሆናል:: ወይም በሚያደርጋቸው ምልክቶች
ከተሳቡትና ከሚያደንቁት ሰዎች አንደበት የውዳሴና የክብር
ቃላት እየመነጩ ወደ እርሱ ሲፈሱ አይቶ ሊጨልጣቸውና
ሊረካባቸው ፈልጎ ይሆናል:: ወይም መሐመዳዊ መንፈስ



www.ethiopianorthodox.org

አድሮበት ሰዎችን በማስጨነቁና በማስገደሉ የምጸድቅና የምከብር መስሎት ይሆናል:: የሐሳዌ ኤልያስ ምኞቶችና ተስፋዎች ከተዘረዘሩት የዘለሉና ያለፉ አይሆኑም:: ውኃ የተጠማ እንስሳ ውኃ ወደሚያገኝበት እንደሚገሰግስ የፈለገውን ካላገኘም እንደ ማይመለስ ሐሳዌ ኤልያስም የተዘረዘሩት ነገሮች ሁሉ ጥማተኛ ስለሚሆን እስኪያገኛቸው ድረስ ወደ ምንጩ ያደርሰኛል ብሎ በመረጠውና ባመነበት መንገድ እሩጫውን ይቀጥላል::

## ሐሳዌ ኤልያስ ወደ ተዘረዘሩት ነገሮች የሚሮጥበት ኃይል

ሐሳዌ ኤልያስ እነዚህን የተዘረዘሩ ተስፋዎች ለመጨበጥ የሚሮጥበት ኃይል ዲያብሎሳዊ ኃይል መሆኑ ግልጽ ነው:: ሆኖም ግን ሰው በዲያብሎሳዊ ኃይል ብቻ ተቀስቅሶ ወይንም ተንቀሳቅሶ ስሕተትን ይፈጽማል ማለት አይቻልም:: ሰው ራሱ ለሥጋዊ ነገር በሥጋዊ ፍላጐቱ የሚሸነፍ ፍጡር ነው:: የመጀመሪያውን ኃጢአታዊ እርምጃ የሚራመደው ወደ ኃጢአት የሚያዘነብል ባሕርይ ያለው ሰው እራሱ ነው፡፡በሥጋዊ ፍላጐት ኃይል ላይ ሰይጣናዊ ኃይል ሲጨመር ግን ረጋ ባለ ሁኔታ ከመራመድ ወደ መሮጥ ይሸጋገራል ማለት ነው:: መንፈሳዊ ፍላጐትና ሥጋዊ ፍላጐት በሰው ባሕርይ ከተማ ውስጥ የመኖር ነፃነት አላቸው:: ወደ ኃጢአት ወይም ወደ ጽድቅ የማዘንበል ችሎታ የሰው ተፈጥሮአዊ ሀብቱ ነው:: ያ ዝንባሌ ወደ ኃጢአት ከሆነ ዲያብሎስ ወደዚያ ሰው ይጠጋል:: ዝንባሌውንም ያጠናክራል ያ ዝንባሌ ወደ ጽድቅ ከሆነ ግን የሰይጣን መንገድ ተዘጋ ማለት ነው:: በዚህ መንገድ የሚሄደው መንፈስ ቅዱስ ነው:: መንፈስ ቅዱስና ሰይጣንም በአንድ መንገድ አይሄዱም:: ሰውም የጌታን ጽዋና የአጋንንትን ጽዋ መጠጣት እንደማይችል፣ የጌታን ማዕድ እና የአጋንንትን ማዕድ መካፈል እንደማይችል ተነግሮታል:: 1ቆሮ. 10÷21-22

ውሻ ጌታው ሲጠራው እየበረረ ካለበት እንደሚመጣ ሁሉ የሰው ወደ ኃጢአት ያለው ዝንባሌም የሰይጣን መጥሪያ ቋንቋ ነው:: ቆሻሻ ባለበት ቦታ ዝንቦች እንደሚከማቹ ቦታውም





እንደማይሰወራቸው አሸትተው እንደሚወሩት በኃጢአት የቆሸሸውን ሰውም አጋንንት ይወሩታል ያለበት ቦታም አይሰወራቸውም:: የኃጢአት ማግኔት በእጃቸው አለ ዲያብሎሰ ሰውን ወደመጥፎ አቅጣጫ የሚነዳው የፍላጐቱን ሞተር በማንቀሳቀስ ነው:: ዲያብሎስ ወደሰው ልብ የሚገባው እራሱ ሰውየው በተፈጥሮአዊ ዝንባሌ መንገዱን ጠርጐ ሲቆየው ነው:: ወደ ኃጢአት በመመልከት መጀመሪያ መንገድን የሚያዘጋጀው እራሱ ሰው ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ለገላትያ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ የሚከተለውን ቃል ተናግሯል «ተቆጡ ኃጢአትንም አታድርጉ በቁጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ ለዲያብሎስም ፋንታ አትስጡ» ኤፌ. 4÷26-27

ሐዋርያው ጳውሎስ ሰው ቁጣ የሚስማማውን ባሕርይ የተሸከመ ፍጡር ስለሆነ ከቁጣ መራቅ እንደማይቻለው ከገለጸ በኋላ ፀሐይ ሳይገባ ከተጣላው ሰው ጋር መታረቅ እንደሚገባ ያመለክታል:: ለዲያብሎስ ፋንታ አትስጡት በማለቱም መታረቅ የመንፈስ ቅዱስ ፈንታ ሲሆን አለመታረቅ የዲያብሎስ ፈንታ መሆኑን ያስረዳል:: የተጣሉ ሰዎች ፈጥነው ካልታረቁ ዲያብሎስ መኮራረፋቸውን መንገድ በማድረግ ወደ እነርሱ ገብቶ እስከመጋደል ያደርሳቸዋል ማለት ነው:: ተንኮልን ኃጢአትን መጀመር የሰው የተፈጥሮአዊ ባሕርይ ድርሻ ሲሆን ማጠናከርና ማስፈጸም የዲያብሎስ ድርሻ ነው:: ነገሩ እንዲህ ከሆነ ሐሳዌ ኤልያስ የሐሰተኛውን ክርስቶስን አምላክነት በማስተማር ወደ ስሕተት ወደ ክሕደት የሚገባው በሥጋዊ ፍላጐቱ ኃይል ስለሚሸነፍ ነው:: ለምትብለጨለጨው ዓለም ስለሚንበረከክ ነው:: በእርግጥ ይህን ትልቅ ስሕተት ብቻውን አይፈጽመውም:: ዝንባሌውን ምክንያት በማድረግ በዚያ ወራት ከእስራቱ የሚፈታው ሰይጣን ይጨመርበታል:: በትንኝ መጠን የነበረችውን ኃጢአት በግመል መጠን ያደርጋታል::



www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ አራት
# ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት

## ስድስት መቶ ስድሳ ስድስት ኮምፒዩተር ነውን?

«ጥበብ በዚህ አለ አእምሮ ያለው የአውሬውን ቁጥር ይቁጠረው:: ቁጥሩ የሰው ቁጥር ነውና ቁጥሩም 666 ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት ነው» ራእይ 13÷18 የአውሬውን ቁጥር ሊያውቀው የሚችለው ምን ዓይነት ጥበብ ያለው ሰው ነው? ይህ ጥበብ ሥጋዊ ጥበብ መሆን የለበትም የሥነ ከዋክብት ተመራማሪዎች ወይም የጠፈር ተመራማሪዎች የአውሬውን ቁጥር ሊቆጥሩት አይችሉም:: የተለያዩ ፈላስፋዎችም በፍልስፍናቸውና በምርመራቸው አይደርሱበትም::

ይህ ቁጥር የሒሳብ ስሌቶችን የማስላት ልምድ ባላቸው ሰዎች ሊታወቅ አይችልም:: ወይም ግምታዊ በሆነው በጠንቋዮች ጥበብና በመተተኞች ማስመሰል የሚሰጠው ትርጓሜ ትክክለኛ ትርጓሜው አይሆንም:: በእግዚአብሔር ፊት ሞኝነት በሆነው በዚህ ዓለም ጥበብ ተመርምሮ የአውሬው ቁጥር አይታወቅም:: የዚህ ዓለም ጥበብ ያላቸው አወቅን ተራቀቅን የሚሉ ሰዎች እንተርጉመው ካሉ የተሳሳተ ትርጉም ይለጥፉበታል እንጂ ውስጠ ምሥጢሩን አያገኙትም::

አሁንም በዘመናችን እንተረጉማለን ብለው የሚሳሳቱ ብዙዎች ናቸው:: ስድስት መቶ ስድሳ ስድሰት /666/ የተባለው የአውሬው ቁጥር ኮምፒዩተር ነው የሚሉ ሰዎች እንዳሉ ይነገራል:: እንዲህ ዓይነት ግምት የሚሰጡ ሰዎች ካሉ ፍጹም ስሕተት ተሳስተዋል:: ደምረውም ሆነ ቀንሰው አባዝተውም ሆነ አካፍለው ያገኙትን 666 /ስድስት መቶ ስድሳ ስድስት/ ቁጥር የኮምፒዩተር ቁጥር ነው ካሉት አውሬውን ምን ሊሉት ነው? ይህ ቁጥር የአውሬው ቁጥር እንደሆነ ተገልጿል:: አውሬ የተባለውም ኮምፒዩተር ነው ይሉ ይሆን? ኮምፒዩተር የዘመኑ ጥበበኞች በጥበባቸው የሠሩት መገልገያ ዕቃ አይደለምን?





አውሬው ግን በዮሐንስ ራእይ በምዕራፍ 13 ቁ. 2 ላይ ነብር እንደሚመስል እግሮቹም እንደ ድብ እግሮች እንደሆኑ አፉም እንደአንበሳ አፍ እንደሆነ ተገልጿል:: ተፈጥሮው በሰብአዊ ተፈጥሮ የከፍወነ ሲሆን ስለክፉ ሥራው ስለተንኮሉ በአውሬ መልክ የተገለጸ ፍጡር ነው:: ስለዚህ የሰዎች የእጅ ሥራ የሆነው ኮምፒዩተር ከአውሬው ጋር ምንም ግንኙነት ወይም ተመሳሳይነት አይኖረውም::

ዳግመኛም በዚሁ በራእይ መጽሐፍ ምዕራፍ 19 ቁ. 20 ላይ አውሬው እንደሚያዝ በአውሬው ፊት ምልክትን የሚያደርገው ሐሰተኛው ነቢይም እንደሚያዝና ሁለቱም በዲን ወደሚቃጠል ወደ እሳት ባሕር እንደሚጣሉ በግልጥ ተነግሮአል:: አውሬ የተባለው ኮምፒዩተር ነው ካልን በየመሥሪያ ቤቱ ያሉትኮምፒዩተሮች ሁሉ ተሰብስበው ወደ እሳት ባሕር ይጣላሉ ማለታችን ነው:: ወደፊት ይጣሉ ይሆናል እንዳንል እንኳ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ በሕይወት ሳሉ ተጣሉ ይላል:: ኮምፒዩተሮች ሕይወት አላቸውን? እንዲህ ዓይነት አተረጓጐም ከአስተዋዮች ልቡና አይመነጭም:: የመጻሕፍትን ምሥጢር በሚያውቁ ሰዎች አንደበትም አይነገርም:: የአውሬው ቁጥር የኮምፒዩተር ቁጥር ነው ማለትም ፍየል ባሌ ቁዝምዝም ሰላሌ እንደሚባለው ያህል ነው::

ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት የተባለው የአውሮው ቁጥር የሰዎች መገልገያ በሆኑ እቃዎች ላይ ይጻፋል አልተባለም:: ይህ ቁጥር አውሬው ሐሳዌ መሲሕ በነገሠ ጊዜ ወይም ራሱን በክርስቶስ ስም ሰይሞ በተገለጠ ጊዜ በተከታዮቹና በአማኞቹ በግምባራቸው በቀኝ እጃቸው የሚጻፍ ቁጥር ነው:: ይህ ቁጥር የአውሬው የሐሳዌ መሲሕ የስሙ ቁጥር ሲሆን ትርጉም ያለው ቁጥር ነው:: ባለራእዩ ዮሐንስ ጥበብ ያለው፣ አእምሮ ያለው የአውሬውን ቁጥር መቁጠር እንደሚቻለው ገልጿል:: ጥበብ የተባለው ግን ሥጋዊ ጥበብ፣ ሥጋዊ ፍልስፍና፣ ሥጋዊ እውቀትና ሥጋዊ ምርምር እንዳይደለ ከዚህ በላይ ስለተገለጠ ይህ ጥበብ መንፈሳዊ ጥበብ መሆን አለበት::



www.ethiopianorthodox.org

# መንፈሳዊ ጥበብ ምንድን ነው?

መንፈሳዊ ጥበብ እንደሥጋዊ ጥበብ በምርምር፣ ወይም ከጥበበኞች በመማር፣ ወይም የጥበበኞችን መጻሕፍት በማንበብ የሚገኝ ጥበብ አይደለም:: ጥሩ አድርጎ በማሰብ ከአንጎል የሚመረት የአንጎል ውጤት አይደለም:: መንፈሳዊ ጥበብ፣ በሃይማኖቱ ጠንክሮ ለቆመ እንዲሁም ከቅንነት ጋር ሰፊ ትዕግሥት ላለውና ማራኪ ትሕትናን ለተጐናጸፈ ሰው ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚሰጥ ትልቅ ሀብት ነው::

በዚህ ሀብት የበለጸገ ሰው ሥውር ነገሮችን ሁሉ ያውቃል «መንፈሳዊ ሰው ግን ሁሉን ይመረምራል ራሱ ግን በማንም አይመረመርም» 1ቆሮ. 2÷15:: መንፈሳዊ ጥበብ የነበራቸው አባቶች የረቀቀውን አጉልተው የራቀውን አቅርበው የተሰወረውን ገላልጠው አብራርተው ተናግረዋል::

መንፈሳዊ ጥበብ የተሰጣቸው አባቶች:-

1. ዮሴፍ:-

ዮሴፍ መንፈሳዊ ጥበብን የተመላ እንደመሆኑ በሥጋዊ ጥበብ የበለጸጉ የተደበቀውን እንገልጣለን ለወደፊት የሚሆነውንም እንተነብያለን ንባብ እንተረጉማለን እናመሠጥራለን ከሚሉ ከግብጽ ጥበበኞች የተሰወረውን የፈርዖንን ሕልም መተርጐም ችሏል:: ራሱም ፈርዖን «እንደአንተ ያለ ብልህ አዋቂም ሰው የለም:: እግዚአብሔር ይህን ሁሉ ገልጦልሀልና» በማለት የዮሴፍ ጥበብ ከእግዚአብሔር የተገኘ መሆኑን መስክሮለታል:: በግብፅ ከሚገኙት ጥበበኞች በላይ ስለሆነም አልቆ ሾሞታል:: ዘፍ. 41÷1-40

2. ዳንኤል:-

ዳንኤል ከባቢሎን ጥበበኞች እጅግ የላቀና የበለጠ ጥበበኛ የሆነው ከእግዚአብሔር ባገኘው መንፈሳዊ ጥበብ ነው:: ለአናንያ ለአዛርያና ለሚሳኤል ለዳንኤልም ጥበብንና ማስተዋልን የሰጠ እግዚአብሔር ነው:: ዳን. 1÷17 ከከለዳውያን ጥበበኞች አስማተኞችና መተተኞች ከሕልም ተርጓሚዎች የናቡከደነፆርን ሕልምና ትርጓሜ ሊያገኝ የተቻለው አልነበረም::





የናቡከደነፆር ሕልም ትርጓሜው ብቻ ሳይሆን ራሱ ሕልሙ ንባቡ መጥፋቱ ከለዳውያን ጥበበኞች በተመሳሳይ ትርጓሜ ንጉሡን እንዳያታልሉ መንገድ ዘግቶባቸዋል:: ሌላ ተመሳሳይ ነገር ፈጥረው ሕልምህ ይህ ነው እንዳይሉትም ትዝታው በውስጡ ነበረ:: በልቡናው ይወጣል ይወርዳል አእምሮው መዝግቦታልና አይቀበላቸውም:: ሥጋውያን ጥበበኞች ናቸውና የእግዚአብሔርን ምሥጢር ሊያውቁ አልቻሉም:: ማስተዋልን እግዚአብሔር የለገሠው ዳንኤልም የንጉሡ ሕልም በሥጋዊ ጥበብ ወይም እውቀት እንደማይተረጐም በሚከተለው ንባብ አስረድቷል::

«ዳንኤልም በንጉሡ ፊት መልሶ እንዲህ አለ ንጉሡ የጠየቀውን ምሥጢር ጠቢባንና አስማተኞች የሕልም ተርጓሚዎችና ቃላተኞች ለንጉሡ ያሳዩ ዘንድ አይችሉም:: ነገር ግን ምሥጢር የሚገልጽ አምላክ በሰማይ ውስጥ አለ እርሱም በኋለኛው ዘመን የሚሆነውን ለንጉሡ ለናቡከደነፆር አስታውቋል» ዳን. 2÷27-28 የአምላካዊ ጥበብ ነጸብራቅ የድንቁርና ጨለማን የገፈፈለትና ጸጋ እግዚአብሔር ፀሐይ ሞቅ ያደረገው ዳንኤል የናቡከደነፆርን ሕልም ንባቡን ከነትርጓሜው ትርጓሜውን ከነንባቡ እንደማግኔት ከተሰወረበት ስቦ አወጣው ዳን. 2÷1-49

ዳግመኛም ዳንኤል በብልጣሶር ቤት ተጽፎ የተገኘውን ንባብ ተርጉሟል:: ብልጣሶር በቤተ መንግሥቱ የሚገኙትን መኳንንቱን መሳፍንቱን ከእርሱ በታች የሆኑ ባለሥልጣኖቹንና ቤተሰቦቹን ሰብስቦ የመጠጥ ግብዣ አድርጐ ሳለ በቤቱ ግንብ ላይ ጽሕፈት የምትጽፍ እጅ ታያቸው:: ጽሕፈቱም ማኔ ቴቄል ፋሬስ የሚል ነበር:: በቤቱ ግንብ ላይ ስትጽፍ የታየችው አንዲት እጅ ብቻ ነበረች እንጂ ሌላ የሚታይ ነገር አልነበረም::

ጽሕፈቱም የተሰወረ ነበር:: ንጉሡም የሚተረጉምለት አጥቶ በድንጋጤ ባሕር ውስጥ ብቅ ጥልቅ ሲል አይቶ ዳንኤል እንዲህ ብሎ ተረጐመለት «እግዚአብሔር መንግሥትህን ቆጠረው ፈጸመው በሚዛን ተመዝነህ ቀልለህም ተገኘህ መንግሥትህም ተከፈለ። ለሜዶንና ለፋርስ ሰዎችም ተሰጠ» ዳን. 5÷25-28 ዳንኤል ከባቢሎን ጥበበኞች ከአዋቂዎች በልጦ የተገኘውና የተሰወሩ ነገሮችን ሊገልጥ የቻለው ከእግዚአብሔር በተሰጠው መንፈሳዊ ጥበብ ነው::



www.ethiopianorthodox.org

3ኛ. ኤልሣዕ

የሶርያ ንጉሥ ከእስራኤል ጋር በሚዋጋበት ጊዜ እንዴት ማሸነፍ እንዳለበት ከሠራዊቱ ጋር መከረ:: የሶርያ ንጉሥና ሠራዊቱ የመከሩት ምክር በስውር ቦታ መደበቅ እንዳለባቸውና እስራኤላውያንን አሸንፈው ድሉን ለመጐናጸፍ ነበር:: ነገር ግን የሶርያ ንጉሥና ሠራዊቱ በእልፍኛቸው በጓዳቸው ሆነው የመከሩትን ምክር በመንፈስ ቅዱስ የተረዳው የእግዚአብሔር ሰው ኤልሣዕ «ሶርያውያን በዚያ ተደብቀዋልና በዚያ ሥፍራ እንዳታልፍ ተጠንቀቅ» ብሎ ወደ እሥራኤል ንጉሥ በመላክ የእሥራኤልን ንጉሥ ከሶርያውያን እጅ አድኖታል:: ኤልሣዕ ሶርያውያን የመከሩትንና የተደበቁበትን ቦታ ማንም ሳይነግረው ሊያውቅ የቻለው ከእግዚአብሔር በተሰጠው መንፈሳዊ ጥበብ ነው:: 2ነገ. 6÷8-11

4ኛ. ቅዱስ ጴጥሮስ

ቅዱስ ጴጥሮስም ከእግዚአብሔር በተሰጠው መንፈሳዊ ጥበብ የሐናንያንና የሚስቱን የሰጲራን ተንኮል በውስጣቸው የተደበቀውንም ሐሰት ማንም ሳይነግረው ገልጠባቸዋል:: ቃሉን በማሰማት ብቻ የሞት ቅጣት ቀጥቷቸዋል ሐዋ. 5÷1-11

5ኛ. ዮሐንስ አፈወርቅ

ዮሐንስ አፈወርቅ በሁለቱ አላውያን ነገሥታት ማለትም በዲዮቅልጥያኖስና በመክስምያኖስ ዘመነ መንግሥት አብያተ ክርስቲያናት ሲተኮሱ ምእመናን ሲፈልሱ በመጻሕፍት ላይ በደረሰው የመቃጠልና የመዘረፍ አደጋ ምክንያት የዮሐንስ ራእይ ጠፍቶ ቀርቶ ነበርና በጸሎት ወደ እግዚአብሔር በማመልከት ዮሐንስ ወንጌላዊ ያየው ራእይ ሳይቀነስበት ሳይጨመርበት ለዮሐንስ አፈወርቅ ተገልጾለት ጽፎታል:: ከእግዚአብሔር ዘንድ በተሰጠው ጸጋ የጠፋውን ራእይ በማግኘቱ የጠፋውን የናቡከደነፆርን ሕልም አግኝቶ ከተረጐመው ከዳንኤል ጋር ስለ ተነጻጸረ ሐዲስ ዳንኤል ተብሏል:: የዘመነ ሐዲሱ ዳንኤል ማለት ነው::

ሥጋውያን ጥበበኞች ካልደረሱበት የዕውቀት ደረጃ መንፈሳውያን ጥበበኞች እንደሚደርሱ እስከ አሁን በጠቀስናቸው





አባቶች አረጋግጠናል:: በሰዎች ፍልስፍና ከተገኘ እውቀት ይልቅ በእግዚአብሔር ገላጭነት የታገዘ እውቀት እጅግ አመርቂና አስተማማኝ ውጤት ይገኝበታል::

ሥጋውያን ፈላስፎች ወይም ጥበበኞች እርስ በእርሳቸው ይለያያሉ:: ኋለኞች ፈላስፎች ፊተኞች ፈላስፎችን ይነቅፏቸዋል:: የመጀመሪያዎቹ ያመኑበትን የኋለኞቹ ይክዱታል:: ሐሳባቸውን ፍጹም ስሕተት ያደርጉታል:: የኋለኛው ፍልስፍና የመጀመሪያውን ፍልስፍና ይቃወመዋል:: አንዳንድ ጊዜ ደግሞ አንዱ ፈላስፋ አዲስ ሐሳብ ባገኘ ጊዜ የመጀመሪያውን ፍልስፍናውን ያፈርሰዋል:: ይለውጠዋል:: ተሳስቼ ነበር ይላል፣ እራሱን በእራሱ ይቃወመዋል::

መንፈሳውያን ጥበበኞች ግን በእንዲህ ያለ መንገድ አይሄዱም:: ምሥጢሩን የሚገልጽላቸው መንፈስ ቅዱስ ስለሆነ አይሳሳቱም፣ ቃላቸውን አይለውጡም እርስ በእርሳቸውም አይለያዩም:: ነቢያት አበውን አይነቅፉም፣ ሐዋርያትም ነቢያትን አይነቅፉም ሊቃውንትም ሐዋርያትን አይነቅፉም:: ይልቁንም ለትምህርታቸው ማጠናከሪያ እንዲሆን ኋለኞች የፊተኞችን ቃል ይጠቅሱታል::

መንፈሳዊ ጥበብ ከሥጋዊ ጥበብ እጅግ የራቀ ነው:: ሥጋዊ ጥበብን በሸክላ መደብ ብናስቀምጠው መንፈሳዊ ጥበብን በወርቅና በዕንቊ መደብ እናስቀምጠዋለን:: ሥጋዊ ጥበብ የሸክላውን ምሳሌ ሲይዝ መንፈሳዊ ጥበብ የወርቁንና የዕንቁን ምሳሌ ቢይዝ ለመንፈሳዊ ጥበብ ያንስበታል እንጅ አይበዛበትም::

## የአውሬውን ቁጥር ትርጉም የሚያውቀው ማን ነው?

የአውሬውን ቁጥር ትርጉም ሊያውቀው የሚችለው:-

1. እንደዮሴፍና እንደዳንኤል፣ እንደኤልሣዕና እንደጴጥሮስ እንደዮሐንስ አፈወርቅ እንደሌሎችም የእግዚአብሔር ወዳጆች ምሥጢራትን የማወቅ ጸጋ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተለገሰው ሰው ነው::



www.ethiopianorthodox.org

2. የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው ተብሎ እንደተጻፈ መዝ.110÷10 እግዚአብሔርን የመፍራት ጥበብን በውስጡ ያበቀለ እንደደጋ ዛፍ የለመለመ የጽድቅን ፍሬ ያፈራ እግዚአብሔርን የመደፋፈር እሾህን ከልቡናው ነቅሎ የጣለ እንደአቤል የዋህ የሆነ ሰው ነው::
3. ከሁሉም ነገር አስቀድሞ ጥበብንና ማስተዋልን ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደለመነ እግዚአብሔርም ልመናውን ሰምቶ በምድር ላይ ከሚኖሩ ሰዎች አብልጦና አልቆ ጥበብንና ማስተዋልን እንደሰጠው እንደሰሎሞን 1ነገ. 3÷5-15:: የማስተዋልና የጥበብ ጸጋ የተትረፈረፈለት ሰው ነው::
4. እንደቄርሎስ እንደዮሐንስ አፈወርቅ እንደአትናቴዎስ እንደባስልዮስ ሀብተ-ትርጓሜ የመተርጐምን ሀብት መንፈስ ቅዱስ የሰጠው ሰው ነው::

ቁጥሩ የሰው ቁጥር ነውና፡

ቁጥሩ የሰው ቁጥር ነውና ማለት ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት የአውሬው ቁጥር በሰው ሥሮች ቁጥር ልክ ነው ማለት ነው:: ዋና ዋና የሰው ሥሮች ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት እንደሆኑ መንፈሳውያን አባቶችና የትርጓሜ መጻሕፍት ይናገራሉ:: ወንጌላዊው ዮሐንስ ቁጥሩ የሰው ቁጥር ነው:: ይኸውም ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት /666/ ነው በማለቱ የአውሬውን የሐሳዊ መሲሕን ፍጡርነቱን፣ ውሱንነቱን፣ ምድራዊነቱንና አዳማዊ ባሕርዩን ገልጾበታል::

ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት /666/ አሥራው ወይም ሥሮች ያሉት ሰብአዊ ፍጡር ደካማ አስተሳሰቡ ጠማማ ዓቅመ ቢስ የሚፈርስ የሚበሰብስ፣ ኃላፊ ከነተከታዮቹ ጠፊ መሆኑንም ያመለክታል:: የተገጣጠሙ የአጥንቶችና የስድስት መቶ ስልሳ ስድስት /666/ ሥሮች አንድነት ውጤት እንዲሁም በሥጋዊና በደማዊ ኃይል ጸንቶ ለተወሰነ ጊዜ በዚህ ዓለም የሚቆይ ዘርዓ አዳም የአዳም ዘር /ልጅ/ እንጂ በሰማይና በምድር የመላ የሰማይና የምድር ንጉሥ አሸናፊዎችን የማሸነፍ ችሎታ ያለው የፍጥረታት ባለቤት አምላክ አለመሆኑንም በዚሁ ባስቀመጠው ቁጥር ያስረዳል::





ወንጌላዊው ዮሐንስ ገና ወደፊት ዘመን የሚያበቅለውን ሐሰተኛውን ክርስቶስ ከአውሬ ጋር በማነጻጸር የተንኰሉን መልክ የገለጸ ሲሆን ቁጥሩ በሰው ጅማቶች /ሥሮች/ ቁጥር ልክ ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት /666/ መሆኑን በመግለጹ ከዓቅሙ በላይ የሚከናነበውን የሐሰት አምላክነት ክንንብ ገልጾ ለብዙዎች ድብቅ የሚሆነውን የሰብአዊ ባሕርዩን ገጽታ አጉልቶና አድምቆ ያሳያል:: በአማርኛው ቁጥሩ የሰው ቁጥር ነውና ተብሎ የተገለጸው በግዕዙ እስመአምጣነ እጓለመሕያው ውእቱ ተብሎ ተገልጿል:: መጠኑ ልኩ የሰው መጠን የሰው ልክ ነው ማለት ነው:: ወይም ባሕርዩ መዋቲ የሆነ የሰው ባሕርይ ነው ማለት ነው::

እጓለመሕያው ማለት ሰብአዊ፣ አዳማዊ፣ ምድራዊ፣ መሬታዊ ፍጥረት ማለት ነው:: እጓለመሕያው የሚለው ንባብ /ቃል/ ሰባት ፊደሎች አሉት:: የአውሬው ቁጥር በእጓለመሕያው መጠን ነው ማለት አውሬው ሐሳዊ መሲሕ ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋ ከሦስቱ ባሕርያተ ነፍስ ማለትም ከሰባቱ ባሕርያት የተፈጠረ ሰብአዊ ፍጡር ነው እንጂ አምላክ አይደለም ለማለት ነው:: አስተዋይ ልቡና ላለው ሰው በአማርኛም ይጻፍ በግዕዝ ወይም በሌላ ቋንቋ የአውሬው ቁጥር የያዘው ትርጉም አውሬውን ሐሳዊ መሲሕን ከአምላክነት ደረጃ አውርዶ በሰዎች ደረጃ ከዚያም በታች ለማስቀመጥ ሰብአዊ ፍጡርነቱን የሚገልጽ ቁጥር ነው::

## መርምያዋያስ

አውሬውን ሐሳዊ መሲሕን በአምላክነት ደረጃ በሚቀበሉትና በሚሰግዱለት በተከታዮቹ በአማኞቹ በግምባራቸውና በቀኝ እጃቸው የሚጻፈው የአውሬው የስሙ ቁጥር መርምያዋያስ የሚል ነው:: መርምያዋያስ ከሚለው ንባብ /ቃል/ ሰባት ፊደሎችን እናገኛለን:: የዚህ ንባብ /ቃል/ ፊደሎች እያንዳንዳቸው የራሳቸው የሆነ መለያ ቁጥር አላቸው:: የሚቆጠሩትም ፊደሎች የዕብራይስጥ ፊደሎች ናቸው:: የዕብራይስጥ ፊደሎች እንደሚከተለው ይቀርባሉ::



www.ethiopianorthodox.org

አሌፍ፣ ቤት፣ ጋሜል፣ ዳሌጥ፣ ሄ፣ ዋው፣ ዛይ፣ ሔት፣ ጤት፣ ዮድ፣ ካፍ፣ ላሜድ፣ ሜም፣ ኖን፣ ሳምኬት፣ ዔ፣ ፌ፣ ጻዴ፣ ቆፍ፣ ሬስ፣ ሳን፣ ታው፣ ሃያ ሁለት ናቸው::

የራሳቸው የሆነው የእያንዳንዳቸውም መለያ ቁጥር እን ደሚከተለው ይገለጻል:: አሌፍ 1፣ ቤት 2፣ ጋሜል 3፣ ዳሌጥ 4፣ ሄ 5፣ ዋው 6፣ ዛይ 7፣ ሔት 8፣ ጤት 9፣ ዮድ 10፣ ካፍ 20፣ ላሜድ 30፣ ሜም 40፣ ኖን 50፣ ሳምኬት 60፣ ዔ 70፣ ፌ 80፣ ጻዴ 90፣ ቆፍ 100፣ ሬስ 200፣ ሳን 300፣ ታው 400፣ የዕብራይስጥ ፊደል ቁጥር ይህ ነው:: ኪዳነወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት ይመልከቱ፣ አስረስ የኔ ሰው በ1951 ዓ.ም ባሳተመው የካም መታሰቢያ ገጽ 16ንም ይመልከቱ::

መርምያዋዖስ የሚለው ንባብ /ቃል/ የመጀመሪያው ፊደል መ፣ ሁለተኛው ር፣ ሦስተኛው ም፣ አራተኛው ያ፣ አምስተኛው ዋ፣ ስድስተኛው ዖ፣ ሰባተኛው ስ ናቸው:: እነዚህን ሰባት ፊደሎች በዕብራይስጥ ፊደል ቁጥር ስንቆጥራቸው ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት /666/ ይሆናሉ::

እንደ መ ሆኖ የሚነበበው የዕብራይስጡ ፊደል ሜም ቁጥሩ፣ አርባ ነው፤
እንደ ር ሆኖ የሚነበበው ሬስ፣ ቁጥሩ ሁለት መቶ ነው፤
እንደ ም ሆኖ የሚነበበው ሜም ቁጥሩ አርባ ነው፤
እንደ ያ ሆኖ የሚነበበው ዮድ ቁጥሩ አሥር ነው፤
እንደ ዋ ሆኖ የሚነበበው ዋው ቁጥሩ ስድስት ነው፤
እንደ ዖ ሆኖ የሚነበበው ዔ ቁጥሩ ሰባ ነው፤
እንደ ስ ሆኖ የሚነበበው ሳን ቁጥሩ ሦስት መቶ ነው::
እነዚህን ሰብስበን ብንደምራቸው ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት /666/ ይሆናሉ::

እነዚህ እያንዳንዳቸው ቁጥር ያላቸው የዕብራይስጥ ፊደ ሎች ማለትም ሜም፣ ሬስ፣ ሜም፣ ዮድ፣ ዋው፣ ዔ፣ ሳን፣ በመባል የተዘረዘሩት ፊደሎች መርምያዋዖስ ተብለው እንደሚ ነበቡ አስተውል:: መርምያዋዖስ በሚለው ንባብ የሚገኙ ሰባት ፊደሎች ሲመረመሩ ስድስት መቶ ስድሳ ስድስት /666/ ቁጥርን ይዘው ይገኛሉ:: በንባቡ ውስጥ የተደበቀው ምሥጢር ሲተረጐም የሐሳዊ መሲሕን ውስጣዊ ማንነት የተሸከመ ነው::





ሆኖም በሐሳዊ መሲሕ ጀሌዎች ወይም ተከታዮች በቀ[illegible] እጃቸውና በግምባራቸው የሚጻፈው መርምያዋዖስ በሚል ንባ[illegible] /ቃል/ የሚገለጸው ጽሑፍ የያዘው ትርጓሜ ለሁሉ ግልጸ[illegible] አይሆንም::

ጠንቋዮች የዓስማት ዓይነት በብራና ወይም በወረቀት[illegible] ጽፈው በቆዳ ወይም በልብስ ቁራጭ ጠቅልለው በአንገታቸውና[illegible] በክንዳቸው ያንጠለጠሉላቸው ሰዎች ያንጠለጠሉትን ነገር ገልጠ[illegible] ን እንይ ሳይሉና ምንም እንደሆነ ሳያውቁ ምኞታቸውና ፍላ[illegible] ጐታቸው በዚያ እንደሚፈጸምላቸው አምነው እንደሚኖሩ ሁሉ[illegible] የሐሳዊ መሲሕም ተከታዮች በግምባራቸውና በቀኝ እጃቸው[illegible] የሚጻፈውን የሐሳዊ መሲሕን የስሙን ቁጥር እንዲሁ ይሸከ[illegible] ሙታል ያንጠለጥሉታል እንጂ ትርጉሙ ምን እንደሆነ[illegible] አይረዱትም::

የአውሬው የሐሳዊ መሲሕ ስም በውስጡ ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት /666/ ቁጥርን የያዘ በትርጉሙም የሐሳዊ መሲ ሕን ፍጡርነት ደካማነትና ኃላፊ ጠፊነት የሚገልጽ መሆኑን የሚጠቁማቸው አይኖርም::

በተጨማሪም በሐሳዊ መሲሕ ዘመን የሚፈነዳው እሳተ ገሞራ ዲያብሎስ ማስተዋላቸውንና መንፈሳዊ አመለካከታቸውን ገለባብጦና ናንዶ እንደሚጥልባቸው ከመንፈሳዊ ጥበብ ከተማቸ ውም አስወጥቶ እንደሚያሳድዳቸው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሳያመለክት አላለፈውም:: 2ተሰ. 2÷11-12

ማስተዋላቸውን በዲያብሎስ ተገፈው ራቁታቸውን የሚ ቆሙት የሐሳዊ መሲሕ አማኞች በግምባራቸውና በቀኝ እጃቸው የሚጻፈውና ተሸክመውት የሚዞሩት መርምያዎዖስ በመባል የሚገለጸው ቃል /ንባብ/ ከክፉ ነገሮችና አደጋዎች ከመቅሠፍቶ ችም የሚጠብቃቸው ሳይመስላቸው አይቀርም::

የሕይወታቸው ሕንፃ የቆመበት መሠረት በሰውነታቸው የተቀረጸው የአውሬው የሐሳዊ መሲሕ የስሙ ቁጥር እንደሆነና ያ ጽሑፍ ከሰውነታቸው ከተፋቀ ግን ሕይወታቸው እንደምታ ልፍ አድርገው ከእንስሳዊ አእምሮ ባልተሻለ አእምሮ ያስቡ ይሆናል::

ሕፃናት ከፊታቸው ያገኙትን ሰውነታቸውን የሚጐዳ ስለት ነገር ከያዙ በኋላ ልቀቁ ቢሉአቸው ሞጭጨው ይዘው



www.ethiopianorthodox.org

ከማልቀስ በስተቀር ወደውና ፈቅደው እንደማይለቁት ልቀቁ የሚሏቸውን ሰውም እንደ ክፉ ጠላት እንደሚመለከቱት ሁሉ የሐሳዊ መሲሕም ደጋፊዎች ሕፃናተ አእምሮ እንደመሆናቸው መጠን ስለሐሳዊ መሲሕ ከሀዲነትና አታላይነት የሚነግራቸውን ሰው የቻሉትን ያህል ከመበቀል በስተቀር ትምህርቱንና ምክሩን ሰምተው የሕይወታቸው መቅሠፍት የሆነውን የያዙትን ከንቱ ነገር ለመልቀቅ አይሞክሩም። ሞኝና ወረቀት ያስያዙትን አይለቅም ይባል የለ? አንዳንድ ጊዜ የሰው አእምሮ እንደማስ ቲሽ ያለ ነው። ዛሬ እንኳን በዓለማችን አንዳንድ ቡድኖች ሃይማኖት ብለው የያዙአቸው ነገሮች እንደቀልድ፣ እንደጨዋታ ይመስላሉ። እነርሱ ግን በልምድ ስለያዙአቸው ነገሮች እስከ ሞት ድረስ ይጋደሉላቸዋል።

## ፀራዊ

የአውሬው የሐሳዊ መሲሕ የስሙ ቁጥር በዕብራይስጥ ቋንቋ መርምያዎያስ ተብሎ የተገለጸ ሲሆን በግዕዝ ቋንቋም ፀራዊ ተብሎ እንደሚገለጽ መምህራን ቤተክርስቲያን ያስረዳሉ። ፀራዊ ማለትም ክፉ ጠላት ነው። ይኸውም ፀራዊ የሚለው ንባብ /ቃል/ ሦስት ፊደሎችን የያዘ ሲሆን ሦስቱ ፊደሎችም ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት /666/ ቁጥርን የያዙ ናቸው።

ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት /666/ ቁጥርም ከዚህ በፊት እንደተገለጸው የሐሳዊ መሲሕን ፍጡ ርነት መዋቲነት ያስረዳል። ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት /666/ ሥሮች ወይም ጅማቶች ያሉት የአዳም ዘር ከዘርአ አዳም አባቱና ከዘርአ ሔዋን እናቱ አዳማዊ ባሕርይን ወርሶ የተወለደ ደካማ ፍጡር መሆኑንም ያመለክታል።

መርምያዎያስ በሚለው ንባብ /ቃል/ የተገኙ ሰባት የዕብራይስጥ ፊደሎች እያንዳንዳቸው ተቈጥረው ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት /666/ ቁጥርን ይዘው እንደተገኙ ሁሉ ፀራዊ በሚለው የግዕዝ ንባብ /ቃል/ የሚገኙ ሦስት ፊደሎችም እያን ዳንዳቸው ሲቈጠሩ ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት /666/ ቁጥርን ይዘው ይገኛሉ። የዕብራይስጥ ፊደሎች እያንዳንዳቸው መለያ ቁጥር እንዳላቸው ሁሉ የግዕዝ ፊደሎችም ለእያንዳንዳቸው





መለያ ቁጥር አላቸው። የግዕዝ ፊደሎች ቁጥር እንደሚከተለው ይቀርባል።

ሀ. አንድ፣ ለ. ሁለት፣ ሐ. ሦስት፣ መ. አራት፣ ሠ. አምስት፣ ረ. ስድስት፣ ሰ. ሰባት፣ ቀ. ስምንት፣ በ. ዘጠኝ፣ ተ. አሥር፣ ኀ. ሀያ፣ ነ. ሠላሳ፣ አ. አርባ፣ ከ. ሃምሳ፣ ወ. ስልሳ፣ ዐ. ሰባ፣ ዘ. ሰማኒያ፣ የ. ዘጠና፣ ደ. መቶ፣ ገ. ሁለት መቶ፣ ጠ. ሦስት መቶ፣ ጰ. አራት መቶ፣ ጸ. አምስት መቶ፣ ፀ. ስድስት መቶ፣ ፈ. ሰባት መቶ፣ ፐ. ስምንት መቶ፣ ይሆናል።

የግዕዝ ፊደሎች ቁጥር ስምንት መቶ መሆኑን ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ይገልጻሉ። በዚህ የአቆጣጠር ስልት ፀራዊ በሚል ንባብ /ቃል/ የሚገኙ ሦስት ፊደሎችን እንቆጥራለን። የፊደሎች ቁጥር ከዚህ በፊት እንደተገለጸው ሲቆጠር ፀ. ስድ ስት መቶ፣ ረ. ስድስት፣ ወ. ስልሳ፣ ስንደምራቸው ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት /666/ ይሆናሉ። ፊደሎች እንዴት እንደ ሚቆጠሩ በአስረስ የኔሰው በ1951 ዓ.ም. የታተመው የካም መታሰቢያ ገጽ 17 ተመልከት።

የአውሬው የሐሳዊ መሲሕ ወይም የሐሰተኛው ክርስቶስ የስሙ ቁጥር በዕብራይስጥም ሆነ በግዕዝ ቢጻፍ ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት /666/ ቁጥርን በውስጡ ሰውሮ የያዘ የሰይጣናዊ ምሥጢር ጓዳ መሆኑን መምህራን ቤተክርስቲያን ይገልጻሉ። ሐሳዊ መሲሕ ማንነቱን በሐሰት መቃብር ውስጥ ቀብሮ ሊሆን የሚመኘውን ማንነት መስሎ ብቅ ቢልም ማስተዋል ለተሰጣቸው ሰዎች ማንነቱ ይገለጣል «የማይገለጥ የተከደነ የማይታወቅ የተሰወረ ምንም የለምና» ማቴ. 10÷26።

## የአውሬው ቁጥር ምሥጢር መገለጥ

አውሬው ሐሳዊ መሲሕ በተገለጠ ጊዜ የመገለጡ መታ ወቂያ ልዩ ነገር እንዳለው ዮሐንስ ወንጌላዊ በስፋት ይገልጻል። በዓለም ላይ የአውሬው የሐሳዊ መሲሕ አገላለጥ ዓለም ከተፈጠ ረ ጀምሮ እስኪፈጸም ድረስ ወደዓለም ከመጡና በዓለም ላይ ከተገለጡ ወደፊትም ከሚገለጡ የአዳም ዘሮች አመጣጥና አገላለጥ እጅግ የተለየ ነው። ሰዎች እንዲያመልኩአቸውና



www.ethiopianorthodox.org

እንዲሰግዱላቸው መልእክት በማስተላለፍ ራሳቸውን ወደአምላክነት ደረጃ እያደረሱ የተመኩ አንባገነኖች ነገሥታት እንደነበሩ በታሪክ የተወሱ ሲሆን የስማቸውን ቁጥር በሰዎች ግምባርና ቀኝ እጅ ላይ እየጻፉ የመጡ ነገሥታት ግን አልነበሩም። እንዲህ ያለ ከስድስት መቶ ስልሳ ስድስት /666/ ቁጥር ጋር የተያያዘና የተቆራኘ ታሪክም ተፈጽሞአል ተብሎ በመጽሐፍ ላይ አልተጻፈም።

በሰዎች ግምባርና ቀኝ እጅ ላይ የስሙን ቁጥር ማጻፍ የሐሳዊ መሲሕ ብቻ ልዩ የጣያታዊነቱ መገለጫ ነው። ሐሳዊ መሲሕ የስሙን ቁጥር በሰዎች ግምባርና ቀኝ እጅ ላይ እንደሚያጽፍ ምስሉን እንደሚያስመስል ስዕሉን እንደሚያስል እነዚህ የስሙ ቁጥር ምስሉና ስዕሉ የመምጣቱ ምልክቶች እንደሚሆኑ የገለጸልን ዮሐንስ ወንጌላዊ ነው።

የስሙም ቁጥር ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት /666/ መሆኑንና ይኸውም ቁጥር ሰብአዊ ፍጡርነቱን እንደሚገልጽበት ግልጽ በሆነ ኃይለቃል ነግሮናል። ዮሐንስ ወንጌላዊ ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት /666/ በማለት የገለጸውን የአውሬውን ቁጥር ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን በዕብራይስጥ መርምያዋያስ፣ በግዕዝ ፀራዊ ተብሎ እንደሚነበብና ትርጉሙም ክፉ ጠላት ማለት እንደሆነ ከመግለጻቸውም በላይ የዕብራይስጡን ንባብ ወይም ቃል በዕብራይስጥ ፊደል የግዕዙን ንባብ ወይም ቃል በግዕዝ ፊደል በመቁጠር በንባቡ ውስጥ ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት /666/ ቁጥር እንዳለ ወይም ይህን ቁጥር የያዘ ንባብ እንደሆነ በየጉባኤ ቤቱ ለደቀመዛሙርት በማስተማር ላይ ይገኛሉ።

በመተርጐምና በማመሥጠር ዮሐንስ ወንጌላዊን መሠረት ያደረጉ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን የአውሬውን የሐሳዊ መሲሕን የስሙን ቁጥር ምሥጢር በመተንተንና በማብራራት ጥልቅ ሐሳባቸውን ገልጸዋል። የአውሬው የስሙ ቁጥር ፊደሎችን ተከናንበ እንደማይታይ ከአመለከቱ በኋላ የተከናነባቸውን ፊደሎች በመግለጥ ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት /666/ ጉዱን ብቅ አድርገውበታል።





# የአውሬው ቁጥር ምሥጢር መገለጥ የሚሰጣቸው አገልግሎቶች

1. በሐሳዊ መሲሕ ዘመን የሚኖሩ ምእመናን ሐሳዊ መሲ[illegible] በሚያስቀምጠው የመሰናከያ ደነጊያና በሚተክለው እሾ[illegible] ተመተውና ተወግተው እንዳይቆስሉ የአውሬው ምሥጢ[illegible] መገለጥ ደንጊያውንና እሾሁን ያመለክታቸዋል ወይም ይ[illegible] ቁማቸዋል።
2. አንዳንድ ጭካኔን የተመሉ የሀገር አስተዳዳሪዎች /መሪዎ[illegible] በዓለም ላይ ብቅ ባሉ ጊዜ ያ የጥፋት ልጅ የዓመጽ ሰ[illegible] ሐሳዊ መሲሕ የሚነሳበት ጊዜ ደርሶ ይሆን በማለ[illegible] ከመደንገጥና ከመደናገር ያድናል።
3. አውሬው ሐሳዊ መሲሕ በተገለጠ ጊዜ በዮሐንስ ወንጌላዊ[illegible] በሌሎች ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን የተገለጠው የአውሬ[illegible] ቁጥር ምሥጢር እሱነቱን /አውሬነቱን/ ቁልጭ አድር[illegible] የሚያሳይ መስታወት ይሆናል።



www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ አምስት
# ሁለቱ ወይራዎች

ሁለቱ የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክሮች፣ ሁለቱ ወይራዎችና ሁለቱ መቅረዞች በመባል ተገልጸዋል:: በራእየ ዮሐንስ 11÷3-4 ስናነብ የሚከተለውን ንባብ እናገኛለን:: «ለሁለቱም ምስክሮቼ ማቅ ለብሰው ሺህ ከሁለት መቶ ስልሳ ቀን ትንቢት ሊናገሩ እሰጣለሁ:: እነዚህ በምድር ጌታ ፊት የሚቆሙ ሁለቱ ወይራ ዎችና ሁለቱ መቅረዞች ናቸው» ፍሬ ሐሳቡን በጥሩ ሁኔታ ለመጨበጥ ራእይ 11÷3-12 አንብብ::

ወይራ ዘይት /ቅብዓት/ የሚመረትበት እንጨት ነው:: በእስራኤል አገርና በደቡብ አውሮፓ የሚገኝ ወይራ ቁመቱ ልከኛ ፍሬው ወፍራም ቅብዓት የሞላው ነው:: ከዚህ ወይራ የሚገኝ ዘይት ለምግብ ለመድኃኒትና ለቅብዓት ይጠቅማል:: የመ.ቅ.መዝ. ቃላ. ገጽ 186 ይመልከቱ::

መቅረዝ የመብራት መስቀያ ወይም ማብሪያ ማቴ. 5÷15 መቅረዝ የመብራት ዕቃ የቀንዲል የፋና ማኖሪያ የሚ ቆም የሚተከል ወይም የሚሰቀል የሚንጠለጠል ባለሰባት አጽቅ ሦስቱ በጐን ሦስቱ በጐን አንዱ በመካከል እንዲወጣ ሆኖ የተሠራ ዘጸ. 25÷31-40 ኪዳ. ወል ክፍ. መዝ. ቃላ. ገጽ 786 በብሉይ ኪዳን ከቤተ መቅደስ ዕቃዎች አንዱ እንደነበር በእግ ዚአብሔር ማደሪያ በቅድስቱ በስተግራ በኩል ከወርቅ የተሠራ ሰባት ቅርንጫፍ ያለው መቅረዝ እንደነበርና ካህናት በወይራ ዘይት ከማታ እስከማለዳ ድረስ ያበሩበት እንደነበር በሚከተሉት ጥቀሶች ተገልጿል:: ዘጸ. 25÷31-40፤ 40÷24፣ ዘጸ. 27÷20:21፣ ዘሌ. 24÷2-4፣ 1ሳሙ. 3÷3 ሰሎሞንም ለቤተመቅደስ አሥር መቅረዞችን እንደሠራ በ1ኛነገ. 7÷29 ላይ ተገልጿል::

የወይራና የመቅረዝ ትርጉም በመጠኑ ከተገለጸ ሁለት ወይራዎችና ሁለት መቅረዞች የተባሉ እነማን ናቸው ወደሚለው ጥያቄ መሄድ አስፈላጊ ይሆናል:: ሁለቱ ወይራዎችና ሁለቱ መቅረዞች በመባል የተገለጹት ሁለቱ የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክ ሮች ሔኖክና ኤልያስ ናቸው:: የሔኖክና የኤልያስ መንፈሳዊ ተግባር እንዲንጸባረቅና ማንነታቸው እንዲታወቅ ወይራና





መቅረዝ የሔኖክና የኤልያስ መገለጫዎች ሆነዋል:: ወይራና መቅረዝ የሔኖክና የኤልያስ መገለጫ የሆኑበት ምሥጢር:

1ኛ. በወይራ የተገለጹበት ምሥጢር:- ወይራ ዘይትን ቅብዓትን የተመላ የዘይት ማምረቻ እንጨት መሆኑ ተገልጿል:: የሔኖክና የኤልያስም የስማቸው ትርጉም ከዘይት ጋር ተመሳሳይነት እንዳለው የትርጓሜ መምህራን በማመስጠር ያስረዳሉ::

ሀ. ኤልያስ:- ኤልያስ ማለት ዕፀ ዘይት ፍሬ ዘይት ቅብዓ ዘይት ማለት ነው:: ኪዳነወልድ ክፍሌ መዝ. ቃላ. ገጽ 223 ኤልያስ ከዘይት ጋር በስም ብቻ ሳይሆን በግብርም ይስ ማማል:: ዘይት ቁስል ያለዝባል ሉቃ. 10÷34 ዘይት የበሽተኛ መፈወሻ መድኃኒት ነው:: ያዕ. 5÷14 ዘይት ነገሥታት ተቀብተው የሚነግሡበት የከበረ ቅብዓት ነው:: 1ሳሙ. 10÷1 ሰዎችና ዕቃዎች ለእግዚአብሔር አገልግሎት ሥራ ሲለዩ ዘይት ይቀቡ ነበር:: ዘጸ. 30÷22-29፤ 30÷30፣ 1ኛነገ. 19÷16 ዘይት በብሉይ ኪዳንም ሆነ በሐዲስ ኪዳን መብራት በመሆን የቤተመቅደስ መገልገያ ነበር:: ዛሬም የኤሌትሪክ መብራት በሌለበት በገጠር በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት በመብራትነት ያገለግላል::

- ዘይት ቁስል እንደሚያለዝብና የበሽተኛ መፈወሻ መድኃኒት እንደመሆኑ ኤልያስም በትምህርቱ በትንቢቱ የኃጢአት ቁስል የጸናባቸውንና በአምልኮተ ጣዖት በሽታ ተይዘው የሚማቅቁትን ቁስላቸውን የሚያለዝብ በሽተኞችን የሚፈ ውስ መንፈሳዊ መድኃኒት ነው::
- ዘይት ነገሥታት ተቀብተው የሚነግሡበት ካህናት ተቀብ ተው እግዚአብሔርን የሚያገለግሉበት ዕቃዎችም ተቀብተው የሚከበሩበት የከበረ ቅብዓት እንደመሆኑ ኤልያስም በንጽ ሕና በድንግልና በቅድስና የከበረ ሰማይና ምድር የሚታዘ ዙለት አምላካዊ ኃይልን በጸጋ የተጐናጸፈ ለሰራጵታዊቷ ሴት ሥጋዊ በረከትን ለኤልሣዕ መንፈሳዊ በረከተን የለገሠ በእግዚአብሔር ጸጋ የከበረ ታላቅ ነቢይ ነው::



www.ethiopianorthodox.org

- ዘይት መብራት በመሆን ጨለማን የሚያርቅ ብርሃንን የሚፈነጥቅ እጅግ ተወዳጅ ምርት እንደመሆኑ ኤልያስም በአስተማረው ትምህርትና በአደረጋቸው ተአምራት በአምልኮተ ጣዖት ጨለማ ተውጦ በነበረው ሕዝብ ላይ አምልኮተ እግዚአብሔርን ያንጸባረቀ አክአብንና ኤልዛቤልን ከስምንት መቶ ሃምሳ /ከ850/ የሐሰት ነቢያትና የጣዖት ካህናት ጋር በድቅድቅ የሐፍረት ጨለማ ውስጥ አስገብቶ በአንጻሩ በኃጢአትና በመቅሠፍት ጉድጓዶች ተደፍነው የነበሩ ሕዝበ እስራኤልን እግዚአብሔርን ወደማየት አፋፍ ብቅ ያደረገ ታማኝ የእግዚአብሔር አገልጋይ እውነተኛ ነቢይ ነው:: የቤተክርስቲያን ሊቃውንት የኤልያስን መንፈሳዊ አገልግሎት ከዘይት አገልግሎት ጋር በማነጻጸር በማመሳሰል ኤልያስ ማለት ዘይት ማለት ነው ይላሉ::

ለ. ሄኖክ:- ሄኖክም ማለት ሐዲስ ቅዱስ ማለት ነው:: ኪዳ. ክፍ. መዝ.ቃላ. 452 ይመ. ያረጀውን ጥቅርሻ ያጠቆረውን ያደፈውን ዕቃ በዘይት ወልውለዉ ሰንግለዉ አዲስ ያደርጉታል:: ያረጀ ዕቃ የሚታደሰው በዘይት ነው:: የሰው ልጅም ካረጀ ከፈረሰ ከበሰበሰ በኋላ ታድሶ እንደሚነሣ ለሞት ባልተገኘው በሄኖክ ታውቋል:: ሄኖክ እርጅናን ድል አድርጎ አዲስ በሆነ ሰውነት የኖረ ሰው ነው:: ስለዚህም የወይራ ዘይት ሊባል ችሏል::

አዳም እንዲሸከመው የተነገረው ከባድ የሞት ሸክም በአቤል ራስ ላይ በመታየቱ አቤልን ያየና የአቤልን ታሪክ የሰማ የአዳም ልጅ ሁሉ ሲፈራና ሲደነግጥ ይኖር ነበር:: ኋላ ግን ሄኖክ ለሞት ባለመገኘቱ ከሞት በማምለጡ ሞትን ማሸነፍ እንደሚቻል ታወቀ:: ሕይወትን የማግኘት ተስፋው ጨልሞበት ለነበረ የአዳም ዘርዕ ሁሉ የተስፋው ብርሃን ብልጭ አለለት:: በሕሊናው ተሸክሞት የነበረው የጭንቀት ሸክም ጥቂት ቀለለለት:: ዮሐንስ አፈወርቅም ስለሄኖክ በሕይወት የመኖር ምሥጢር የሚከተለውን ጽፏል:: «በአቤል አፍርሆሙ ወበሄኖክ አንቅሆሙ. ትርጉም: በአቤል አስፈራቸው በሄኖክ ግን አስደሰታቸው» ዮሐ.አፈ.ድር.22÷160 በአቤል ሞት የደነገጡና





ያዘኑ የአዳም ዘሮች ሁሉ በሄኖክ ሕይወት ተረጋግተው ደስተኞች ሆነዋል::

የሞት መኖር የሞትን ጽዋዕ ከሁሉ አስቀድሞ በቀመሰው ወይም የሞት ጀማሪ በሆነው በአቤል የተረጋገጠ ሲሆን የሕይወት ወይም የትንሣኤ መኖር ደግሞ በሄኖክ ተረጋግጦአል:: ስለዚህ ሄኖክ አዲስ የትንሣኤ ነገር የተገለጸበት የታወቀበት የሕይወት ተስፋን አብሣሪ ሰው በመሆኑ መምህራን የስሙን ትርጉም ከግብሩ ጋር በማስተባበር ሄኖክ ማለት ዘይት አዲስ ቅዱስ ማለት ነው ይሉታል::

ወይራ ከዘይትነቱም በተጨማሪ በጥንካሬውና በዕድሜአማነቱ ሄኖክና ኤልያስን ይገልጣል:: ወይራ በምድር ላይ ከሚገኙ ዕፀዋት ወይም እንጨቶች ሁሉ በጥንካሬው የታወቀ ዕፅ /እንጨት/ ነው:: ወይራ ጠንካራ ከመሆኑ የተነሣ የሰዎች ጥንካሬ መገለጫ ሆኖ ይነገራል:: ዕገሌ ወይራ ነው ይባላል:: ጉልበታም ነው ጠንካራ ነው ለማለት::

ወይራ እንደሌሎች እንጨቶች ፈጥኖ አያድግም:: ብዙ ዓመታትን ወስዶ ያድጋል በብዙ ዓመታት ውስጥ ካደገ በኋላ ፈጥኖ አያረጅም ቶሎ አይወድቅም ብዙ ዘመን ይቆያል:: ሄኖክና ኤልያስም በሐሳዌ መሲሕ ሥጋዊ ኃይል የማይንበረከኩ በሚያደርጉት ምልክት ወይም ተአምር የሐሳዌ መሲሕን የምትሐት ምልክት ከንቱ የሚያደርጉ ከቆሙባት የሃይማኖት ሥፍራ የማይነቃነቁ መንፈሳውያን አርበኞች ጠንካሮች በመሆናቸውና ለሞት ሳይገኙ ለብዙ ዘመናት እስከዕለተ ምጽአት ድረስ በሕይወተ ሥጋ በመኖራቸው ጥንካሬያቸውና የዕድሜአቸው ርዝመት ይገለጽ ዘንድ ወይራዎች ተብለዋል:: በንባብ ሁለቱ ወይራዎች የተባሉት በትርጓሜ ሄኖክና ኤልያስ ተብለዋል::

2ኛ. መቅረዝ የተባሉበት ምሥጢር:- መቅረዝ መብራትን በመሸከም የመብራቱን ብርሃን አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ የሚችል ዕቃ ነው:: መብራት ከዝቅተኛ ቦታ ወይም ከጓዳ ወይም በወንጌል እንደተገለጸው ከዕንቅብ በታች ማቴ. 5÷15 ቢቀመጥ ተፈላጊውን አገልግሎት መስጠት አይችልም::

ስለሆነም መብራት በመቅረዝ ላይ ሆኖ በአንድ ቤተ መቅደስ ውስጥ ያለውን ጨለማ በማስወገድ ተገቢ የሆነውን



www.ethiopianorthodox.org

አገልግሎት እንዲሰጥ ይደረጋል:: ሄኖክና ኤልያስም በሐሳዊ መሲሕ ዘመን ለሚኖሩ ምእመናን መብራት የተባለውን የእግዚአብሔርን ቃል በመሸከም የአምልኮተ እግዚአብሔርን ብርሃን ጨረር ይነዛሉ:: ያንጊዜ ትክክለኛዋ የወንጌል ትምህርት መብራት የምትታየው በሄኖክና በኤልያስ አንደበት ላይ ነው:: ሰይጣን ከእስራቱ በሚፈታበት ወራት ፀሐይ ሳትገባ ዓለሙን የሚውጠውን ድቅድቅ ጨለማ ሐሳዊ መሲሕን ድል ለማድረግና እንደሌባ ይህንኑ ጨለማ ተገን በማድረግ ወደ ምእመናን ጓዳ የሚገባውን የሐሰተኛውን ኤልያስን ስሕተታዊ ትምህርት ገላልጠው ለማሳየት እውነተኛውን ብርሃን ዓለም ክርስቶስን ተሸክመው የሚታዩ ኤልያስና ሄኖክ ናቸው:: ስለዚህ ኤልያስና ሄኖክ መቅረዝ ተብለዋል:: መብራትን በሚሸከሙ መቅረዞች ተመስለዋል መቅረዞች ተብለው ተገልጠዋል::

## ሄኖክና ኤልያስ ለምን አልሞቱም?

ሄኖክና ኤልያስ የአዳምን ልጆች እንደዱር እንስሳት በሚያድናቸው ቆላ ቢወርዱ ቆላ ወርዶ ደጋ ቢወጡ ደጋ ወጥቶ ቦታ ቢያቀያይሩ ቢሸሹ ተከትሎ ሄዶ:: ከገቡበት ገብቶ እያነቀ በሚይዛቸው በሞት ወጥመድ አልተያዙም:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደሮሜ ሰዎች በላከው መልእክቱ ሞት ጻድቃንንም ኃጥአንንም አንድ አድርጎ እንደገዛቸው በሚከተሉት ንባባት ግልጽ አድርጎ ያስረዳል:: «ነገር ግን በአዳም መተላለፍ ምሳሌ ኀጢአትን ባልሠሩት ላይ እንኳ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ ሞት ነገሠ» ሮሜ. 5÷14

ሐዋርያው ሞት በአዳም ልጆች ላይ እንደሠለጠነና እንደነገሠ ከመሠልጠኑም የተነሣ ከአዳም ጀምሮ በአዳም ልጆች ላይ ጅምላ ጭፍጨፋ እንዳካሄደና ሁሉንም ቁስለኞች እንዳደረጋቸው ቢገልጽም ሄኖክና ኤልያስ ግን ከሞት ሕግ በታች አልነበሩም:: የሰው ዘሮች በሙሉ አባት እናት ከልጆቻቸው ልጆችም ከወላጆቻቸው ከወንድሞቻቸውና ከእኅቶቻቸው በመለየት የሞት ምርኮኞች ሲሆኑ ሄኖክና ኤልያስ መንፈሳውያን አርበኞች እንደመሆናቸው ለማረኪው ሞት እጃቸውን አልሰጡም::





ሄኖክና ኤልያስ ሥጋና ደምን የተዋሀዱ ምንም ጉድለት የሌለበት ሰብአዊ ባሕርይ ያላቸው የአዳምና የሔዋን ዘሮች መሆናቸው ጥርጣሬ የሌለበት እውን ሆኖ እያለ በሥጋ ላይ ለሠለጠነው ለሞት ያልተገዙበት ምክንያት ምንድን ነው? የሚለው ጥያቄ በውስጣችን መጕነሱ አይቀርም::

ሄኖክና ኤልያስ ለሞት ያልተገኙት በልባቸው ቅንነት በሃይማኖታቸው ጽንዓት ይሆን? ወይስ ጽድቃቸው ከጻድቃን ከነቢያት ስለበለጠ ይሆን? ለጥያቄያችን መልስ የሚሰጡልን ከሆነ እስኪ የሄኖክና የኤልያስን የቀና ሃይማኖታቸውን መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን ከእግዚአብሔር ዘንድ የተለገሡ ጸጋቸውን የሚገልጹ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን እንያቸው እንመርምራቸው::

1ኛ. ስለሄኖክ የተጻፉትን እንይ፤ ሄኖክም የኖረበት ዘመን ሁሉ ሦስት መቶ ስልሳ አምስት /365/ ዓመት ሆነ «ሄኖክም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስለአደረገ አልተገኘም እግዚአብሔር ወስዶታልና» ዘፍ. 5÷23-24 በዚህ ምዕራፍ ከቁጥር አንድ ጀምሮ የአባቶችን ሞት እየተናገረ መጥቶ ከሄኖክ ሲደርስ ሄኖክን ሞተ አለማለቱን ልብ እንበል:: ሄኖክ ያልተገኘው ለሞት ነው:: እግዚአብሔር ወሰደው ማለትም ከዚህ ሞት ከነገሠበት ዓለም አሸሽቶ ወደ ብሔረ ሕያዋን ወሰደው ማለት ነው::

ሄኖክ በጽኑዕ ሃይማኖቱና በመልካም ሥነ ምግባሩ እግዚአብሔርን ደስ አሰኝቶ ሞትን ሳያይ ከዚህ ዓለም ተለይቷል:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም በዕብራውያን መልእክቱ ስለሄኖክ የሚከተለውን ጽፏል:: «ሄኖክ ሞትን እንዳያይ በእምነት ተወሰደ እግዚአብሔርም ስለወሰደው አልተገኘም:: ሳይወሰድ እግዚአብሔርን ደስ እንዳሰኘ ተመስክሮለታልና ያለእምነትም ደስ ማሰኘት አይቻልምና» ዕብ. 11÷5-6 በእነዚህ ጥቅሶች እንደተመለከትነው ሄኖክን የሃይማኖቱና የመልካም ሥነ ምግባሩ ውጤት ያለሞት በሕይወት እንዲኖር አድርጎታል::

2ኛ. ስለኤልያስ የተጻፉትን እናያለን:: ኤልያስ በብሉይ ኪዳን ከነበሩት ከታወቁት ነቢያት አንዱ ነው:: ኤልያስ በጣዖት አምላኪዎች በአክአብና በኤልዛቤል ዘመን ስለነበር ጣዖታውያኑ አክአብና ኤልዛቤል ጣዖታቸውን እንዲለቁ ከኃጢ



www.ethiopianorthodox.org

አታቸው እንዲመለሱ ይመክራቸውና ያስተምራቸው ነበር። በጣዖትና በኃጢአት ፍቅር ባሕር የሰጠሙ አክአብና ኤልዛቤል ከሰጠሙበት ባሕር መውጣት በተሳናቸው ጊዜ ለአምልኮተ እግዚአብሔር ቀናተኛ በመሆኑ ሰማይ ዝናብ ለዘር ጠል ለመከር እንዳይሰጥ ምድርም የዘሩባትን እንዳታበቅል የተከሉባትን እንዳታጸድቅ ሰማይንና ምድርን አወገዘ እንደቃሉም ሆነለት። 1ነገ.17÷1 ሦስት ዓመት ከስድስት ወር አክአብንና ኤልዛቤልን ከነሠራዊታቸው በረሀብ አለንጋ ከገረፋቸው በኋላ እንደገና ጸልዮ ዝናብ እንዲዘንብ ምድርም እንድታበቅል አደረገ 1ነገ. 18÷42-45 ያዕ. 5÷17-18

ዝናብን በተሸከመ ደመናና ደመና በተሸከመው ዝናብ ላይ ሥልጣን የተሰጠው ኤልያስ ደመናው እንዳይዳምንና እንዲዳምን ዝናቡን እንዳይዘንብና እንዲዘንብ ማድረግ ችሎአል። ሆኖም የኤልያስ ጸጋ በዚህ ብቻ የተገታ አይደለም። የጣዖት አምላኪው የአካዝያስ መልእክተኞች በትዕቢትና በቁጣ በሄዱበት ጊዜ በኤልያስ ቃል ከሰማይ እሳት ወርዶ ሁለት የሃምሳ አለቃዎችንና መቶ ሠራዊቶቻቸውን በልታለች። 2ነገ.1÷10-13

ከዚህም ሌላ በመጐናጸፊያው ባሕረ ዮርዳኖስን በመታው ጊዜ የዮርዳኖስ ባሕር ከሁለት ተከፍሎ ከደቀመዝሙሩ ከኤልሳዕ ጋር በደረቅ መሬት ተሻግሮአል። 2ነገ. 2÷8 ኤልያስ የነቢይነቱን አገልግሎት በትጋትና በቅንነት ከፈጸመ በኋላ በሥጋ ሳይሞት ሕያው ሆኖ በእሳት ሠረገላ ወደ ሰማይ ተወስዷል። 2ነገ. 2÷11 ከቁጥር 1-12 አንብቡ። የኤልያስን የሕይወት ታሪክ በእነዚህ ጥቅሶች እንደተመለከትነው ሰማዩም ደመናውም ባሕሩም የብሱም ለኤልያስ የታዘዙለት፡- ኤልያስ በሃይማኖቱ በንጽሕናው በቅድስናው በቅንነቱ በመልካም ሥነ ምግባሩ በድንግልናው እግዚአብሔርን ደስ ስለአሰኘው መሆኑ ግልጽ ነው። በመጨረሻም ሞትን ሳያይ በእሳት ሠረገላ ለመወሰድ በቅቷል።

ሄኖክና ኤልያስ በፅኑዕ ሃይማኖታቸው በመልካም ሥነ ምግባራቸው ሰይጣንን ያሳዘኑ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኙ ታማኞች የእግዚአብሔር አገልጋዮች እግዚአብሔርን የሚወዱ እግዚአብሔር የሚወዳቸው ምርጥ ዘሮች መሆናቸው ከረዥሙ በአጭሩ ከብዙው በጥቂቱ ከምሉው በክፍሉ ተገልጿል።





ሆኖም ሄኖክና ኤልያስ ለምን አልሞቱም የሚለው ጥያቄ አሁንም መልስ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል። ሄኖክና ኤልያስ ለምን አልሞቱም ለሚለው ጥያቄ ሄኖክና ኤልያስ የእግዚአብሔር ባለሟሎች ሕጉን ጠባቂዎች ትእዛዙን አክባሪዎች ስለሆኑ ነው ተብሎ ቢመለስ ጥያቄውን በከፊል ሊመልሰው ይችላል። ምክንያቱም ለብዙ ዘመናት በሕይወተ ሥጋ መኖር የጽድቅ መለኪያ አይደለም እንዳይባል እግዚአብሔር ነፍሰ ገዳዩን ቃኤልን አቤልን በገደለበት ድንጋይ በላሜህ እጅ እንዲሞት አደረገው እንጂ በሕይወተ ሥጋ አላኖረውም። በዘፍ. 4÷19-24 ላሜህ ሰውን እንደገደለ ተጠቅሷል። ላሜህ የገደለው ሰው ቃኤል እንደሆነ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ይናገራሉ። ጨካኙንና ከሃዲውን ፈርዖንንም በባሕረ ኤርትራ አስጠመመው እንጂ በሕይወተ ሥጋ አላኖረውም። ዘጸ.14÷26-31 የእስራኤል ሴቶችን ልጆች አልባ ያስቀረ ጨካኙን አጋግንም በሳሙኤል እጅ መራራ ሞትን አቀመሰው እንጂ በሕይወተ ሥጋ አላኖረውም። 1ሳሙ.15÷32-33 ጣዖት አምላኪዋንና ነፍሰ ገዳይዋን ኤልዛቤልንም ከግምብ ላይ ተወርውራ እንድትወድቅና ሥጋዋን ውሾች እንዲበሉት አደረገ እንጂ በሕይወተ ሥጋ አላኖራትም። 2ነገ. 9÷30-37

በእግዚአብሔር ላይ አፉን የከፈተውንና ትዕቢተኛውን ሰናክሬምንም ከጣዖቱ ፊት በልጆቹ ሰይፍ እንዲሞት አደረገው እንጂ በሕይወተ ሥጋ አላኖረውም። ኢሳ. 37÷36-38 ለምሳሌ ያህል እነዚህ አምስት ሰዎች ተጠቀሱ እንጂ ብዙ ኃጢአተኞች በመቅሠፍት ሞተዋል። ሕገ ወጦች እንደሄኖክና እንደኤልያስ እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ በሕይወተ ሥጋ መኖሩ ይቅርና በሰባና በሰማኒያ የተወሰነች ዕድሜያቸውን እንኳ ሳይጨርሱ ነው የኃጢአታቸው ደመወዝ ሞት የሚከፈላቸው። እግዚአብሔር ለብዙ ዘመናት በሕይወተ ሥጋ የሚያቆያቸውን ሰዎች ከሕግ ጠባቂዎች መካከል እንጂ ከሕገ ወጦች መካከል አልመረጠም።

ነገር ግን ሄኖክና ኤልያስ ለምን አልሞቱም ለሚለው ጥያቄ የሄኖክና የኤልያስ ጽድቅ ሞትን ከእነርሱ ማራቅ ስለቻለ ነው ተብሎ ቢመለስ በቂ መልስ ሊሆን አይችልም። ጥያቄው



www.ethiopianorthodox.org

የማያዳግም መልስ አገኘ አይባልም። ሄኖክና ኤልያስ ከሌሎች የአዳም ዘሮች በተለየ ሁኔታ በሥጋቸው ሞትን ሳያዩ በሕይወተ ሥጋ እንዲኖሩ የሆኑበት ትልቁ ምክንያት ምንድን ነው ለሚለው ጥያቄ የጽኑዕ ሃይማኖታቸው፣ የመልካም ሥነ ምግባራቸው በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ አገልግሎታቸው ውጤት ብቻ ነው ብለን ብንመልስ ዳግመኛ የሚከተሉት ጥያቄዎች ለአንባብያን ብልጭ ማለታቸው አይቀርም።

1ኛ. ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር በራእይ ያነጋገረው ከጣዖት አምላኪዎች ጋር እንዳይኖር ከከላውዴዎን ወደካራን ከካራን ወደ ከነአን የጠራው ዘፍ. 12÷1-9 ልጁን ይስሃቅን እስከመሰዋት ድረስ ታማኝነቱንና ታዛዥነቱን የገለጸ። ዘፍ. 22÷1-18 እምነቱ ጽድቅ ሆኖ እንደተቆጠረለትና የምእመናን ሁሉ አባት እንደ ተባለ ሐዋርያት የመሰከሩለት ያዕ. 2÷23፣ ሮሜ. 4÷1-25፣ ገላ. 3÷6-7 ደጉ ጻድቁ አባት አብርሃም ለምን ሞተ?

2ኛ. ፈጣሪው እግዚአበሔር ባሪያዬ አገልጋዬ በማለት በቅንነት ላይ የተመሠረተ አልግሎቱን ያንጸባረቀለት፣ በምድር ላይ እንደእርሱ ፍጹምና ቅን እግዚአብሔርንም የሚፈራ ከክፋትም የራቀ ሰው የለም። ኢዮ. 1÷8 ብሎ ታማኝነቱንና ጻድቅነቱን የመሰከረለት፣ ሰይጣን ፈጣሪውን ሊያስክደው በፈተናው ጊዜ ሰይጣንን ድል ያደረገ ያሸነፈ፣ ባሪያዬም ኢዮብ ስለእናንተ ይጸልያል። ኢዮ. 42÷8 በማለት ስለኃጢአተኞችም ለመጸለይ የበቃ ጻድቅ መሆኑን የጽድቅ ባለቤት እግዚአብሔር የመሰከረለት ጻድቁ ኢዮብ ለምን ሞተ?

3ኛ. ባሕረ ኤርትራን ከፍሎ እስራኤልን ያሻገረ፣ ዘጸ. 14÷21 በምድር ከሚኖሩት ሰዎች ሁሉ ይልቅ እጅግ ትሑት የነበረ፣ ወንድሙ አሮንና እኅቱ ማርያም በነቀፉት ጊዜ እነሱን እግዚአብሔር የነቀፈለት የገሰጸለት በመካከላችሁ ነቢይ ቢኖር እኔ እግዚአብሔር በራእይ እገለጽለታለሁ ወይም በሕልም እናገረዋለሁ ባሪያዬ ሙሴ ግን እንዲህ አይደለም እርሱ በቤቴ ሁሉ የታመነ ነው። እኔ አፍ ለአፍ በግልጥ እናገረዋለሁ በምሳሌ አይደለም። የእግዚአብሔርንም መልክ ያያል ዘኁ. 12÷1-16 ብሎ ሁሉን የሚመረምር እግዚአብሔር ታማኝነቱንና ቅንነቱን የተናገረለት ሙሴ ለምን ሞተ?





4ኛ. በሆድ ሳልሠራህ አውቄሃለሁ ከማኅፀንም ሳትወጣ ቀድሼሃለሁ ለአሕዛብም ነቢይ አድርጌሃለሁ ኤር. 1÷5 በማለት ንጽሕናውን ቅድስናውን ለአገልግሎት መመረጡን ራሱ እግዚአብሔር የመሰከረለት ኤርምያስ ለምን ሞተ?

5ኛ. እውነት እላችኋለሁ ከሴቶች ከተወለዱት መካከል ከመጥምቁ ዮሐንስ የሚበልጥ አልተነሣም ማቴ. 11÷11 በማለት ከሰው ልጆች የሚበልጠው እንደሌለ የጽድቅ ባለቤት ኢየሱስ ክርስቶስ የነቢያት ሁሉ ራስ መሆኑን በጉባኤ ያሳወቀለት ዮሐንስ መጥምቅ ለምን ሞተ?

ይህን ሐሳብ ለማስረዳት እነዚህ አምስት ቅዱሳን ተጠቀሱ እንጂ በሃይማኖታቸው በጽድቃቸው በአገልግሎታቸው እግዚአብሔርን ደስ ያሰኙ ቅዱሳን ነቢያት አበው ጻድቃን ብዙ ናቸው። ነገሩ እንዲህ ከሆነ የሄኖክና የኤልያስ በሕይወተ ሥጋ መኖር የአገልግሎት ዋጋ ነው ብለን ብንደመድም የሌሎቹ ቅዱሳን አገልግሎት ያለ ዋጋ በከንቱ የቀረ ያስመስልብናል። የሄኖክና የኤልያስ ጽድቅ በሕይወተ ሥጋ ለመኖራቸው መሠረቱ ቢሆን እንጅ ጉልላቱ ወይም ቁንጮው ሊሆን አይችልም። ሄኖክና ኤልያስ በሕይወተ ሥጋ ስለመኖራቸው ለሚነሣው ጥያቄ የሚሰጡ የማያዳግሙ መልሶች ከአሁን በፊት ካየናቸው ሐሳቦች ለየት ያሉ ይሆናሉ። እንደሚከተለውም ይቀርባሉ

## 1. የሕይወትና የትንሣኤ ምልክቶች ሊሆኑ:-

### 1.1 የሞትና የሕይወት ወሬ ለአዳም

እግዚአብሔር አምላክ በምድር ላይ ከሚኖሩ ፍጥረታት ሁሉ አልቆና አብልጦ የፈጠረው አዳም ትእዛዙን በማፍረስ ዕፀ በለስን በመጉረስ በዘማዊት ዓይኑ ወደ አምላክነቱ ወደመንግሥቱ በተመለከተ ጊዜ ከሞተ ሥጋ ጋር ሞተ ነፍስን ከርደተ መቃብር ጋር ርደተ ሲኦልን /ወደመቃብር ከመውረድ ጋር ወደሲኦል መውረድን/ ፈረደበት። ሆኖም ግን አዳም እንደዲያብሎስ በትዕቢት ልቡን ያሳጸና ትሑት ፍጡር በመሆኑ በሕገ ወጥነቱ ተጸጽቶ ቢያለቅስና መሥዋዕት ቢያቀርብ መዓቱ የራቀ ምሕረቱ የበዛ እንደሆነ የተነገረለት ፈጣሪው እግዚአብሔር በሞት ማዶ ሕይወትን አሻግሮ እንዲያይ አደረገው። ለ አዳም



www.ethiopianorthodox.org

መሬት አንተ ወትገብእ ውስተ መሬት፡ አዳም ሆይ መሬት ነህ ወደመጣህበት መሬት ትመለሳለህ ዘፍ. 3፥19 ብሎ በተናገረበት አንደበቱ በሐሙስ ዕለት ወበመንፈቃ ለዕለት እትወለድ እምወለተ ወለትከ ወእድህክ ውስተ መርህብከ ወእትቤዘወከ በሞትየ ወበመስቀልየ፡ ትርጉም በአምስት ቀን ተኩል ማለትም 5500 ዘመን ሲፈጸም ከልጅ ልጅህ እወለዳለሁ በምድርህ እመላለሳለሁ በመስቀልም ተሰቅዬ ሞቼ አድንሃለሁ የሚል የተስፋ መልእክትን አስተላለፈለት።

አዳም የሞት ድምፅን በሰማበት ጆሮው የሕይወትን ድምፅ ሰማ። በኃዘን በመከራ ድርቆ የነበረው የአዳም ልቡና ከእግዚአብሔር አንደበት በመረዳት በዚች የተስፋ ጠብታ ረሰረሰ። ነገር ግን አዳም ይህን የሕይወት ተስፋ ቢጐናጸፍም ስለ ድኅነቱ ከተነገሩ ቃላት የልቅ ስለሞቱ የተነገሩ ቃላት ሲተገበሩ በተግባር ሲገለጡ ይመለከት ነበር። ስለሆነም የተነገሩት የመርገም ቃላት ሳይፈጸሙ እንደማይቀሩ አረጋግጧል። አዳም ብቻ ሳይሆን ልጆቹም በዚህ የጭንቀት ትውፊት ተውጠው ይኖሩ ነበር።

1.2 አዳም የሞትን ተግባራዊነት ያረጋገጠባቸው ነገሮች:-

1.2.1 የጸጋ ልብሱን ተገፎ በበለስ ቅጠል እስከ መጠለልና ከፈጣሪው ከእግዚአብሔር እስከመሠወር እስከ መሸሸግ ደርሶ መራቆቱ።

1.2.2 ለሰባት ዓመት ያህል በውስጡ ላሉት ፍጥረታት ሁሉ ገዥ ሆኖ ያለሀዘን ያለችግር በተድላ በደስታ ከኖረ ባት ገነት መባረሩ።

1.2.3 ከዕፀ በለስ በቀር ለምግብነት ከተሰጡት በገነት ውስጥ ከሚገኙ አትክልት ዕፀዋት ከመዓዛቸው ከጣዕማቸው ተለይቶ እሾህና አሜከላ ታብቅልብህ የተባለችው ምድር በእሾሕና በአሜከላዋ እየደማችውና እያቆሰለችው ሥጋዊ ምግቡን ለማግኘት ወዙን እያበሰ መንከራተቱ።

1.2.4 የአባቱን ትእዛዝ በመፈጸምና እግዚአብሔርን በመፍራት ጽድቅን በውስጡ ያበቀለ የሚወደው ልጁ አቤል ሰይጣን የመጥፎ ምክሩ ተሳታፊ ባደረገው በቃኤል እጅ በተወ ረወረ ድንጋይ ሞቶ ማየቱ።





እነዚህ የሞት ተግባር ውጤቶች በአዳምና በልጆቹ አእምሮ ውስጥ ሰፊውን ስፍራ ይዘው በመገኘታቸው የሕይወትን ገጽታ ማየት አልተቻለም ነበር። የሚያሳዝንና የሚያስጨንቅ ክፉ የሞት ወሬ ከተሰማ በኋላ በሰው አእምሮ ውስጥ የሞላውን ጭንቀት የሚያጐድል በቦታውም የሚተካ ሞትን የማሸነፍና የድኅነት ወሬ ቢሰማም አዳምና ልጆቹ ግን ብዙ ጊዜ ተግባራዊ ሲሆን ያዩት ሞትን ነው። ካለንበት የሞት ጨለማ ተላቀን የሕይወትን ፈገግታ የምናየው መቼ ነው ወይስ እግዚአብሔር የተስፋ ፍትፍትን ብቻ አውጦን ሊቀር ነው? የሚለውም ጥርጣሬ የሰዎችን ሁለንተና ሳይቆጣጠረው አልቀረም።

የተናገረውን የማያስቀር እግዚአብሔር ለተጨነቁት የአዳም ዘሮች የተሰጠው ተስፋ - ሕይወት የውኃ ሽታ የነፋስ መልክ ሆኖ መቅረት እንደሌለበት መግለጡም አስፈላጊ እንደ ሆነና ከባድ የሰዎችም የጭንቀት ሸክም መቃለል እንዳለበት ስለፈለገ አስቀድሞ ሄኖክን ኋላም ኤልያስን በሕይወተ ሥጋ አኖራቸው።

የሄኖክና የኤልያስ በሕይወት መኖር ሰዎች ከሞት ጉያ ወጥተው በሕይወት እቅፍ መያዝ እንደሚችሉ አረጋገጠ። ትሞታለህን ተከትሎ የመጣ አድንሀለሁ ሄኖክና ኤልያስን ምልክት አድርጐ ቆየ። የሄኖክና የኤልያስ በሕይወተ ሥጋ መኖር የሃይማኖታቸው ጽንዓትና የታዛዥነታቸው መለኪያ መስፈረት ብቻ ሳይሆን ወደፊት በሚደረገው ትንሣኤ ሙታን ለሚገኘው ሕይወት እንደናሙና የቀረበ ነው። ስለሄኖክና ስለኤልያሰ አለመሞት ዮሐንስ አፈወርቅ እንደሚከተለው ጽፏል።

«ወብዙኃን እምሰብእ እለ ይትኃሠሡ በእንተ ፍልሰተ ሄኖክ ወኤልያስ ወለምንት ኢሞቱ ወከመ ምንት ውእቱ ሥረዓተ ሕይወቶሙ ወዝንቱ ኅሠሣ ከመ ተረፍ ውእቱ ሄኖክ ፈለሰ ወኤልያስ ዐርገ በከመ ይነግሩ መጻሕፍት» ትርጉም: ሄኖክ ስለወጣ ኤልያስ ስለዐረገ የሚከራከሩ ብዙ ናቸው። ለምን አልሞቱም ካልሞቱስ የሕይወታቸው የአኗኗራቸው ሥርዓት እንደምን ነው ብለው ይከራከራሉ። እንዲህ ያለው ክርክር በመጽሐፍ የሌለ ልብ ወለድ ነው። መጻሕፍት እንደተናገሩ ሄኖክ ከዚህ ዓለም ሞትን ሳያይ ተለየ። ኤልያስም ዐረገ



www.ethiopianorthodox.org

በማለት የሄኖክ ፍልሰት የኤልያስ ዕርገት በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈ እንጂ ልብ ወለድ የሰዎች ፍልስፍና አነጋገር እንዳልሆነ ካስረዳ በኋላ ምክንያቱን እንደሚከተለው ይገልጻል።

ወባሕቱ ኮነ ፍልሰቶሙ ለአዕንዖ ነፍሳተ ሰብእ ከመ ይእመኑ ከመ ሀለዎ ለብሔር ሞት ይትመዘበር ወትንሣኤ ሙታን ይኩን ሀሎ ወይሠዓር ትምይንቱ ለጸላዒ ትርጉም፡ ነገር ግን የሄኖክ ፍልሰት የኤልያስ ዕርገት የምእመናንን ልቡና በሃይማኖት ለማጽናት ተደረገ። የሞት ሀገር መቃብር ይፈረስ ዘንድ እንዳለው የሙታን ትንሣኤም ይደረግ ዘንድ እንዳለው የዲያብሎስም ተንኮል ያልፍ ዘንድ እንዳለው የምእመናንን ልቡና ለማሳመን በሃይማኖት ለማጽናት ተደረገ ዮሐ. አፈ. ድር 22 ቁ. 132-147 እንደዮሐንስ አፈወርቅ አተረጓጐም የሄኖክና የኤልያስ አለመሞት፡- የሚገልጻቸው ነገሮች የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. ሥጋዊ ደማዊ ፍጡር የሆነውን የአዳምን ዘርዕ በቁጥጥሩ ውስጥ በማድረግ ሙሉ ሥልጣን የነበረው የሰውን ልጅ ሕይወት እንደደረቀ ስንዴ ሲያጭድ በመቃበርም ሲከምር ለምግብነት እንደሚዘጋጅ እህል ሲፈጭና ዱቄት ሲያደርግ የነበረው ሞት፡- ሙታን በኢየሱስ በኩርነት በተነሡ ጊዜ የሚይዘውን የሚጨብጠውን አጥቶ ሕልውናውን እንደሚያጣና እንዳልነበር እንደሚሆን ይገልጻል። በዕለተ ምጽአት ሞትና መቃብር የሚጠፉ መሆናቸውንም ያመለክታል።

ለ. ሰው ከሞተ በኋላ ነፍስ ከሥጋ ሥጋም ከነፍስ ከተለያዩና ወደተለያዩ ቦታዎች ከሄዱ በኋላ ሥጋም በመቃብር ከፈረሰ ከበሰበሰ ወደ አፈርነት ከተለወጠ በኋላ ተለያይተው የነበሩ ነፍስና ሥጋ እንደገና በትንሣኤ ተገናኝተው አዲስ ሰው ሕያው ፍጡር ይሆናል የሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ወደ ምእመናን ጆሮ በደረሰ ጊዜ የምእመናንን ልብ አምኖ ወደ መቀበል ያደርሳል። የትንሣኤን መኖር እንደመረጃ ሆኖ ያረጋግጣል።

ሐ. ከእግዚአብሔር ሕግ ክልል ውጭ በኃጢአት ዋሻ ተደብቀው ያገኛቸውን የአዳም ልጆች ማርኮ ወስዶ ለእርሱ እንዲንበረከኩ እርሱንም እንዲያመልኩ ካደረጋቸውና ከሞቱም በኋላ ሥጋቸውን በመቃብር ነፍሳቸውን በሲዖል ተቆራኝቶ





በመኖር የዓለም ገዥ የነበረው ዲያብሎስ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሂድ አንተ ሰይጣን ካለው በኋላና የክርስቶስም መስቀል ከቆመ በኋላ ድል የተነሣ፣ የተሸነፈ፣ የወደቀ ከምእመናን የራቀ መሆኑን ያበሥራል።

ሄኖክና ኤልያስ ያልሞቱበት ትልቁ ምክንያት ምንድን ነው? ለሚለው ጥያቄ በአጭር ቃል የሚሰጠው መልስ፡- እግዚአብሔር በሄኖክና በኤልያስ ሕይወት የዲያብሎስን ተንኮል መክሸፍ የሞትን መሸነፍ የትንሣኤ ሙታንን መኖር ለምእመናን ለመግለጽ ስለፈለገ ነው የሚል ይሆናል።

## 2ኛ.የእግዚአብሔርን ሕያውነት ሊገልጹ

የሐናጺው ጥበብ በሕንፃው ይታወቃል። ደና ሸማኔ ወይም ልብስ ሰፊ በሰፋው ልብስ ይታወቃል የእሳት ልጅ ረመጥ እንዲሉ ማንኛውም ችሎታ ያለው ሰው በችሎታው ተግባር ውጤት ማንነቱን ይገልጣል። የእግዚአብሔርም ሕያውነትና ዘላለማዊነት ይገለጥ ዘንድ ለዘለዓለም ሕያዋን ሆነው የሚኖሩ ሕያዋን ፍጥረታትን ሰውና መላእክትን ፈጥሮአል።

ሆኖም ከተፈጠሩበት ሥርዓት ሳይነቃነቁ በሕይወት ወይም በሕያውነት የኖሩ መላእክት ናቸው እንጂ ሰው ግን በፈጸመው ስሕተት ሞትን ስቦ ጐትቶ በማምጣት ከሕይወት ወደሞት አሽቆልቁሏል። ቢሆንም መታየት ያለበት ሰው ራሱ ሞትን አመጣው እንጂ እግዚአብሔር ሰውን በሕይወት እንዲኖር ሕያው አድርጐ መፍጠሩ ነው። እግዚአብሔር ሞትን በሰው ላይ እንዳላመጣ ሰው ራሱ ሞትን ጠርቶ እንዳመጣው በመጽሐፈ ጥበብ የሚከተለው ንባብ ይገኛል «እግዚአብሔር ሞትን አልፈጠረምና ነዋሪ ይሆን ዘንድ ፍጥረትን ፈጥሯልና የሰዎች ጥፋት ደስ አያሰኘውምና በእጃችሁ ሥራ ሞትን አታምጡ የሰውም መፈጠር ለድኅነት ነውና በእነርሱ ዘንድ ሁሉን የሚያጠፋ የሞት መርዝ ኃጢአት አልነበረምና ሕይወት የማታልፍ ስለሆነች ለመቃብርም በዚህ ዓለም ግዛት አልነበረውምና እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች ግን በቃል ጠሩት ባልንጀራም አደረጉት በዚሁም ጠፉ» ጥበብ 1÷13-17



www.ethiopianorthodox.org

ሞት የኃጢአት ቅጣት ሆኖ በሰብአዊ ፍጡር ላይ ቢመጣም ሰው ግን በሕያው እግዚአብሔር አምሳል ለዘለዓለማዊ ሕይወት የተፈጠረ ሕያው ፍጡር መሆኑን ይህ ንባብ ያስረዳል፡፡ እግዚአብሔር የፈጠራቸው ሕያዋን ፍጥረታት የእርሱን ሕያውነት አጉልተው የሚያሳዩ የሕያውነቱ ምስክሮች ናቸው ሰው በሕይወት እንዲኖር የተፈጠረ መሆኑ አዳምና ሔዋን በዘረጉት የሞት መጋረጃ ተጠልሎ ተሰውሮና ተደብቆ እንዳይቀር የሚገልጡት ሄኖክና ኤልያስ ናቸው፡፡ የእግዚአብሔር ሕያው ተግባር የጋን መብራት እንዳይሆን እግዚአብሔር የሰውን ሕያው ፍጡርነትና የእግዚአብሔርን ሕያው ፈጣሪነት የሚያመለክቱ ሄኖክንና ኤልያስን በሕይወተ ሥጋ አኖራቸው፡፡

የሄኖክና የኤልያስ ሕያውነት የእግዚአብሔርን ሕያው ፈጣሪነትና የሰውን ሕያው ፍጡረነት በደመቀ ሁኔታ ያስረዳል፡፡ ይገልጣል፡፡ ዳግመኛም እግዚአብሔር ሰው ኃጢአት በሰራ ጊዜ ሞትን ጽድቅ በሰራ ጊዜ ሕይወትን በሰው ላይ የማምጣት ችሎታ ያለው አምላክ መሆኑ በዘዳግም 32÷39 «እኔ እግዚአብሔር አድንማለሁ እኔ እመታለሁ እፈውስማለሁ» ተብሎ እንደተነገረ የመግደል ችሎታው በአዳምና በሌሎች ልጆቹ የተገለጠ ሲሆን የማዳን ችሎታው ደግሞ በሄኖክና በኤልያስ ተገልጿል፡፡ ሄኖክና ኤልያስ በሕይወት ባይኖሩ የእግዚአብሔር የማዳን ችሎታው አይገለጥም ነበር እንዲሁ ወሬ ብቻ ይመስል ነበር፡፡

### 3ኛ. የእግዚአብሔርን አምላክነት ሊመሰክሩ

ሐሳዊ መሲሕ ፈጣሪነት ይገባኛል ሲል ጥያቄውን በዲያብሎሳዊ አደባባይ ባቀረበ ጊዜ ምንም ፍርደ ገምድሉ ዲያብሎስ ለሐሳዊ መሲሕ ቢፈርድለት የእግዚአብሔርን ፈጣሪነት የሐሳዊ መሲሕን ፍጡርነት የዲያብሎስን ፍርደ ገምድልነት በመግለጽ የሚመሰክሩ ሄኖክና ኤልያስ ናቸው፡፡ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የእግዚአብሔርን ሕልውና አድምቀው አጉልተው በዓይነ ሕሊና አሳይተው በእደ ልቡና አስጨብጠው የሚመሰክሩ አምላካዊ ጸጋ የጉበኛቸው የሐሰት ዘማች ዲያብሎስ ያልማረካቸው ስለ አምልኮተ እግዚአብሔር ኤልያሳዊ ቅንዓት ያቃጠ



ሺህ ዓመትና ሐሳዊ መሲሕ

ላቸው እውነተኞች የእግዚአብሔር ምስክሮች በዓለም ላይ አልጠፉም፤ አይጠፉምም፡፡

እግዚአብሔር እርሱነቱን በኃያልነቱና በችሎታው የሚያሳውቅ ቢሆንም የእማኞች ልቡና እንዳይነቃነቅ ሆኖ በሃይማኖት መሠረት ላይ ይታነጽ ዘንድ ራሱን ያለምስክር አልተወም፡፡ ሐዋ.14÷17 ሄኖክና ኤልያስም በሐሳዊ መሲሕ ዘመን ለሚኖሩ ምእመናን እውነት አብሣሪዎች የጽድቅ መንገድ አመልካቾች ወይም ጠቋሚዎች በመሆን የምስክርነታቸውን ተግባር ያከናውናሉ፡፡ ምስክርነታቸውንም የሚፈጽሙት እንደሌሎች ሰማዕታት በሥጋቸው መበጣጠስ በደማቸው መፍሰስ በመከራ መንገዶች ላይ በመገሥገሥ ከሥጋዊ ሕይወት በመፍለስ ነው፡፡ ለተራቡት የሐሳዊ መሲሕ ሰይፎች ሥጋቸውን አጉርሰው ደማቸውን አልሰው ከጸጋ እግዚአብሔር ለተራቆቱት ምእመናን የእግዚአብሔርን ጸጋ አልብሰው የስሕተት ምርኮኞችን መልሰው ተልዕኮአቸውን በመፈጸምና በማከናወን ነው፡፡ ሄኖክና ኤልያስ በሕይወተ ሥጋ እስከ ዕለተ ምጽአት የሚቆዩበት አንዱ ምክንያት የምስክርነታቸውን ተግባረ የሚያከናውኑበት ጊዜ የዓለም ፍጻሜ ዋዜማ በመሆኑ ነው፡፡

ስለሄኖክና ኤልያስ በሕይወት መኖር ይህን ያህል ከተመለከትን ንግባዕኬ ኀበ ጥንተ ነገር ወደቀደመው የነገር ጥንት ወደቀደመው ሐሳባችን እንመለስ፡፡ በራእየ ዮሐንስ 11÷3-12 ያለውን የእግዚአብሔርን ቃል ስናነብ ሁለቱ ምስክሮቼ ሁለቱ ወይራዎች ሁለቱ መቅረዞች የሚለውን ንባብ እናገኛለን፡፡ ሁለቱ ወይራዎች ሁለቱ መቅረዞች የተባሉት የወይራንና የመቅረዝን ውስጣዊ ትርጉም ይዘው የተገኙ ሄኖክና ኤልያስ ናቸው በማለት ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን የጉባኤ መምህራን በትርጓሜ መግለጻቸውን ከአሁን በፊት አይተናል፡፡ ሁለቱ ምስክሮቼ ሁለቱ ወይራዎች ሁለቱ መቅረዞች በማለት በዮሐንስ አንደበት ሄኖክና ኤልያስን የገለጸ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን የሄኖክና የኤልያስም ምስክርነት ለኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡



www.ethiopianorthodox.org

# ምስክር ወይም ሰማዕት

ምስክር ማለት አንዱ የሌላውን ሰው ነገር የሚያስረግጥ እውነተኛነቱን የሚገልጽ ማለት ነው። በግዕዙም ሰማዕት ይባላል። ሰምዐ መሰከረ ከሚለው የግዕዝ ቃል የተገኘ ነው። ምስክር በሁለት ይከፈላል። እውነተኛ ምስክር ሐሰተኛ ምስክር ተብሎ ወይም ሰማዕተ ጽድቅ ሰማዕተ ሐሰት ተብሎ ይከፈላል።

1ኛ. እውነተኛ ምስክር፡- እውነተኛ ምስክር ያየውን አይቻለው የሰማውን ሰምቻለው የሚያውቀውን አውቃለሁ የሚል የታዩትንና የተሰሙትን ነገሮች ድርጊቶችንና ክንውኖችን አእምሮ የመዘገባቸውን ሁሉ በአንደበቱ የሚገልጽ የሚናገር ማለት ነው። «የምናውቀውን እንናገራለን ያየነውንም እንመሰክራለን» ዮሐ. 3÷11 «እኔም አይቻለሁ እርሱም የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ መስክሬአለሁ» ዮሐ. 1÷34 የእውነት ምስክር የሆነውን ሆነ የተደረገውን ተደረገ በማለት ድርጊቶችን እንደታላቅ ተራራ /ጋራ/ አጉልቶ የሚያሳይ ሲሆን በአንጻሩ ደግሞ ያላየውን አላየሁም ያል ሰማውን አልሰማሁም የማያውቀውን አላውቅም ያልሆነውን አልሆነም ያልተደረገውን አልተደረገም ብሎ እውነትን ከተቀበረበት ጉድጓድ ቆፍሮ የሚያወጣ በዚያው ጉድጓድ ሐሰትን የሚቀብር የሚያጠፋ ማለት ነው። የእውነት ምስክር ከእምነት ጋር የተቆራኘ የተሳሰረ ነው።

2ኛ. ሐሰተኛ ምስክር፡- ሐሰተኛ ምስክር ያየውን አላየሁም የሰማውን አልሰማሁም የሚያውቀውን አላውቅም የሆነውን አልሆነም የተደረገውን አልተደረገም የሚል እውነትን በሐሰት የሚያፍን የሚደፍን ሁነቶችንና ድርጊቶችን የጊዜ ክስተቶችን ደመና እንደተጨመረበት ጨለማ ማለትም እንደሐምሌና እንደሐነሴ ጨለማ ሆኖ የሚጋርድ ሲሆን በአንጻሩ ደግሞ ያላየውን አይቻለሁ ያልሰማውን ሰምቻለሁ የማያውቀውን አውቃለሁ ያልሆነውን ሆነ ያልተደረገውን ተደረገ የሚል ነው። ያልተፈጨውን የሚያቦካ ያልተቦካ





ውን የሚጋግር የድርጊቶች ፈጣሪ ለመሆን የሚፍጨረጨር ነው።

ሁለቱ ረበናት /መምህራን/ ሶስናን ስትዘሙት አገኘናት ብለው የሐሰታቸው ፍላፃ ተመልሶ ራሳቸውን እስኪወጋቸው ድረስ በሶስና ላይ በሐሰት እንደመሰከሩ። መጽ.ቅዱ.ገጽ 900። የጌታን መቃብር ሲጠብቁ የነበሩ ጭፍሮች ከሊቃነ ካህናት ብዙ ገንዘብ ተቀብለው ሞትን ድል አድርጐ የተነሣክርስቶስን ሳያዩ ሳይሰሙ ደቀመዛሙርቱ በሌሊት ሠርቀው ወሰዱት ማቴ. 28÷12-15 በማለት ሐሰትን እንደወለዱ ሐሰተኛ ምስክር የሐሰትና የክህደት ዲቃላዎችን ከዲያብሎስ በመደቀል በልቡ ጸንሶ በአንደበቱ የሚወልድ ማለት ነው። ሐሰተኛ ምስክር ከክህደት ጋር የተቆራኘ የተሳሰረ ነው።

# የሄኖክና የኤልያስ ምስክርነት

ሄኖክና ኤልያስ የእውነት ምስክሮች ናቸው። ምስክርነታቸውን ተግባራዊ የሚያደርጉት ሐሳዌ መሲሕ አምላክ ነኝ ብሎ በተነሣ ጊዜ ነው። ምስክርነታቸውም እንደሚከተለው ነው።

1ኛ. የሐሳዌ መሲሕ የሐሰት ጥላ ባጨለመው ዓለም ሰማይንና ምድርን የፈጠረ መላእክትን ፀሐይ ጨረቃን ከዋክብትን ደቂቀ አዳምን እንስሳትን አራዊትን ዕፀው አዕባን ውቅያኖሶችን በውስጣቸውም የሚኖሩ አሣ አንበሪን አዞ ጉማሬን በሰማይም በምድርም ያሉ ፍጥረታትን ሁሉ ያስገኘ ዓለምን ከፈጠረ በኋላም 5500 ዘመን ሲፈጸም ወደዚህ ዓለም መጥቶ ዲያብሎስን ድል ነስቶ በመስቀል ተሰቅሎ ደሙን አፍሶ የአዳምን ልጆች ከሲዖል መንጥቆ ያወጣ ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር ውሎ አድሮ በሦስተኛው ቀን ሞትን ድል አድርጐ የተነሣ በአርባኛው ቀን ተመልሶ ያረገ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው በማለት እውነትን ፈገግ ያደርጓታል።

2ኛ. ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ የሚመጣ መሆኑ ቢነገርም እንደመብረቅ እንደሌባ አመጣጥ ድንገት ሳይታሰብ ይመ



www.ethiopianorthodox.org

ጣል እንጂ እንደከዚህ በፊቱ ድውያንን እየፈወሰ አጋንን
ትን እያወጣ ሕብስት እያበረከተ ውኃውን የወይን ጠጅ
እያደረገ ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ በመዘዋወር ወደተራራ
በመውጣት ከአይሁድ ምኩራብ በመግባት ወንጌልን እየሰ
በከ እኔ ክርስቶስ ነኝ ተቀበሉኝ እመኑብኝ እያለ የማይ
መጣ መሆኑን ይገልጻሉ:: በክርስቶስ ስም ክርስቶስን በመ
ምሰል ከሚመጣው ከሐሰተኛው ክርስቶስ ተጠንቀቁ ተብሎ
በወንጌል የተነገረ እንደሆነና በዚያ ወራት ክርስቶስን
መስሎ የተገለጠውም ሐሰተኛው ክርስቶስ ሐሳዊ መሲሕ
እንደሆነ ያስረዳሉ::

## ሄኖክና ኤልያስ የሚያደርጉት ተአምር

ሄኖክና ኤልያስ የእግዚአብሔር መልእክተኞች መሆናቸ
ውን ይገልጡ ዘንድ ተአምራት ያደርጋሉ:: የሚያደርጉት ተአ
ምር ሐሰተኛው ክርስቶስና ሐሰተኛው ኤልያስ የሚያደርጉአቸ
ውን የምትሐት ምልክቶች በመስበር ስመጥርነታቸውንም በማ
ደብዘዝ የእግዚአብሔርን ኃያልነት አድምቆና አጉልቶ የሚያሳይ
ይሆናል::

በሁለት ወይራዎችና መቅረዞች የተመሰሉ ሄኖክና ኤል
ያስ በመቅረዝ ላይ ያለሙብራት የደመቀ ብርሃን እንደሚሰጥና
ጨለማን እንደሚገፍ ሁሉ በሐሳዊ መሲሕ ትምህርት የጨለመ
ውን የሰዎችን ልቡና ለመግለጥ የእውነተኛ ትምህርታቸውን
ነጸብራቅ በአንጸባረቁ ጊዜ የነጸብራቁ ጨረር የከሀዲዎችን
ዓይን ሳያስለቅሰው አይቀርም:: ሐሳዊ መሲሕ በሰዎች ልቡና
ላይ የገነባውን የሐሰት ትምህርት ግንብ የጽድቅ መሐንዲሶች
ሄኖክና ኤልያስ ይንዱታል:: ያፈርሱታል:: የግንቡ ባለቤት ግን
ያለውን ኃይል ተጠቅሞ ይታገላቸዋል::

ሆኖም በትግሉ የማሸነፍ ውጤት አይታይበትም:: ከእግ
ዚአብሔር መልእክተኞች ጋር የሚታገል ከእግዚአብሔር ጋር
እንደሚታገል ይቆጠራልና ከእግዚአብሔር ጋርም የሚታገል
ከራሱ ጋር እንደሚታገል ይቆጠራል:: ከራሱ ጋር የሚታገልም
ራሱን ይጥላል ከሄኖክና ከኤልያስ ጋር የሐሳዊ መሲሕ ትግል





ደንጋይ ቢያጐኑት ተመልሶ ካናት እንደሚባለው ይሆናል:
«ማንም ሊጐዳቸው ቢወድ እሳት ከአፋቸው ይወጣል:: ጠላቶቻ
ቸውንም ይበላል ማንም ሊጐዳቸው ቢወድም እንዲሁ ሊገደል
ይገባዋል» ራእይ 11÷5

ንባቡ የሚጠቁማቸው ሰዎች ሄኖክና ኤልያስ ናቸው:
የኃይለኞችን ኃይል የሚያቀልጥ እሳታዊ ኃይል እንደሚኖራቸ
ውና አሸናፊዎች እንደሚሆኑ ንባቡ ያመለክታል:: እሳት ከአፋ
ቸው ይወጣል ማለት በቁሙ እሳት በአፋቸው ውስጥ ሲነድ
ሲንቦገቦግ ቆይቶ ሰዎችን ይበላል ማለት ሳይሆን በአንደበታቸው
የተናገሩት ኃይለ ቃል እንደእሳት ያቃጥላል ማለት ነው:: የተ
ናገሩት ሁሉ ይሆንላቸዋል ይደረግላቸዋል እንደቃላቸው ይፈጸ
ማል ማለት ነው::

ለምሳሌ ኤልያስ የአካዝያስን ሠራዊትና የሃምሳ አለቃ
ከሰማይ እሳት ወርዳ አንተንና ከአንተ ጋር ያሉትን ትብላ
ብሎ በተናገረ ጊዜ ከሰማይ እሳት ወርዳ እንደበላቻቸው 2ነገ.
1÷10 ኤልሣዕም የሦርያን ንጉሥ ሠራዊት እንዲታወሩ ጸልዮ
እንደተናገረው ቃል ዕውራን እንደሆኑ 2ነገ.6÷18-19 ሐናንያና
ሚስቱ ሰጲራም ጴጥሮስ በተናገረው የተግሣጽ ቃል እንደሞቱ
ሐዋ. 5÷1-10 ቅዱስ ጳውሎስም በሪያሱስ የተባለው ጠንቋይ
የወንጌልን ትምህርት ሲቃወም አሁን ዕውር ትሆናለህ ፀሐይንም
ማየት አትችልም ብሎ በተናገረ ጊዜ በሪያሱስ ወዲያውኑ
ዕውር እንደሆነ ሐዋ. 13÷6-12

ሄኖክና ኤልያስም ትምህርታቸውን በሚቃወማቸውና
ለማቁሰልም ሆነ ለመግደል በሚነሣሡባቸው ሰዎች ላይ በቃላ
ቸው ተናግረው የፈለጉትን የመቅሠፍት ዓይነት ያመጡባቸዋል
ማለት ነው:: ቃላቸው በጠላቶቻቸው ላይ የሚነድ የሚንበለበል
እሳት ይሆናል:: እሳት የበላው አመድ ከመሆኑም ባሻገር
ነበልባሉ የገረፈው ሁሉ እንደሚደርቅና ሕይወት አልባ እንደ
ሚሆን በሄኖክና በኤልያስ አንደበት ተጠርቶ በሚመጣው
መቅሠፍትም የወንጌል ተቃዋሚዎች ሁሉ ሕይወት አልባ
ይሆናሉ:: በእሳት ኃይል ወደ አመድነት የተለወጡ የደረቁ
ቅጠሎችን ይመስላሉ:: የሄኖክና የኤልያስ የጠላት መምቻ



www.ethiopianorthodox.org

መሣሪያ ቃላቸው ነው:: የእውነተኛው አምላክ አገልጋዮች መሆናቸውም በዚህ ይታወቃል::

በዚሁ ምዕራፍ ማለትም የሄኖክና የኤልያስ ነገር በተጻፈበት ራእይ11÷6 ላይ የሚከተለውን ንባብ እናገኛለን «እነዚህ ትንቢት በሚናገሩበት ወራት ዝናብ እንዳይዘንብ ሰማይን ሊዘጉ ሥልጣን አላቸው ውኃዎችንም ወደደም ሊለውጡ በሚፈልጉበት ጊዜ ሁሉ በመቅሠፍት ሁሉ ምድርን ሊመቱ ሥልጣን አላቸው» በንባቡ የተጠቆሙት ትንቢት ተናጋሪዎች ሄኖክና ኤልየስ መሆናቸውን መዘንጋት የለብንም:: ሰማይን እስከ መዝጋትና ውኃውን ለውጦ ደም እስከማድረግ ድረስ ከፍታ ያለው ሥል ጣን የተሰጣቸው፣ ሌሎችንም በአምላካዊ ኃይል በአምላካዊ ሥልጣን የሚደረጉ የተለያዩ መቀሠፍቶች እግዚአብሔርን በዘነጉ ዐመፀኞች ላይ የሚያዘንቡ ሄኖክና ኤልያስ ናቸው::

ሄኖክና ኤልያስ ከእግዚአብሔር ዘንድ በተሰጣቸው ሥልጣን ምልክቶችን /ተአምራትን/ የሚያደርጉ፣ እሾህን በእሾህ እንዲሉ የሐሳዊ መሲሕን ምልክቶች በምልክቶች ለመሻር ነው:: አውሬ የተባለው የክርስቶስ ተቃዋሚ ሐሳዊ መሲሕ ከዘንዶው ከዲያብሎስ በተሰጠው ሥልጣን የማስመሰልና የማጭበርበር ምልክቶችን እያደረገ አምላክ ለመምሰል ቢከጅልም በወርቅ መሰል ቀለሞች ወርቅ የመሰለ መዳብ ቀለሞቹ ሲለቁ የመዳብነቱ ገጽታ እንደሚገለጽ ሁሉ ሄኖክና ኤልያስ በሚያደርጉት ምልክት የማስመሰያ ልብሶቹን ተገፎ የፍጡርነቱ ዕርቃን ተጋልጦ በሀፍረት ይዋጣል::

በሐሳዊ መሲሕ ገላጭነት በዲያብሎሳዊ ሥልጣን የሚገለጥ ዲያብሎሳዊ ተግባር በሄኖክና በኤልያስ ገላጭነት በእግዚአብሔራዊ ሥልጣን በሚገለጥ እግዚአብሔራዊ ተግባር ይወድማል:: የገለባ አጥቂ እሳት ሲሆን የእሳት አጥቂ ደግሞ ውኃ ነው:: በአጥቂ ላይ አጥቂ በኃይለኛ ላይ ኃይለኛ ያለ ነው:: የሰዎችን ልቡና ለማቅለጥ ሐሳዊ መሲሕ ያነደደውን ዲያብሎሳዊ እሳት በሄኖክና በኤልያስ ሥልጣን የሚገለጥ አምላካዊ ኃይል ውኃ ሆኖ ያጠፋዋል ማለት ነው::

ሄኖክና ኤልያስ የሚያደርጉት ምልክት /ተአምር/ ደምቆና ጐልቶ ይታይ የነበረውን የሐሳዊ መሲሕን የምትሐት /የማስመሰል/ ምልክት ያፈዘዋል ያደበዝዘዋል:: የአድናቂዎችንም





ስሜት ያቀዘቅዘዋል:: ሄኖክና ኤልያስ ዝናብ እንዳይዘንብ ሰማ ይን የሚዘጉት እንዳይጠጣ ውኃን ደም የሚያደርጉት የእግዚአ ብሔርን ፈጣሪነት ኃያልነትና ችሎታ የሐሳዊ መሲሕን ፍጡር ነትና ደካማነት የሐሰተኞች ነቢያቶቹንም ስሕተት ለመግለጽ ነው:: ከጥንት ጀምሮ የእግዚአብሔር መልእክተኞች ቅዱሳን በዐመፀኞችና በከሃዲዎች ሰዎች ላይ የእግዚአብሔርን ኃይልና ችሎታ ይገልጣሉ::

ዐመፀኛውና ከሃዲው ፈርዖን እስራኤልን አልለቅም እግ ዚአብሔርንም አላውቀውም ብሎ በዐመፀ ጊዜ እስራኤልን እን ዲለቅ እግዚአብሔርንም እንዲአውቅ ለማድረግ ሙሴና አሮን በፈርዖንና በጠንቋዮቹ ፊት የግብፅን ውኃ ከውኃነት ወደደምነት ለውጠውት ነበር ዘጸ.7÷19-22 አክአብና ኤልዛቤልም ከተምበረ ከክንለት ጣዖት ፊት አንነሣም ለእግዚአብሔርም አንሠዋም ብለው በዐመፁ ጊዜ የተምበረከኩለት ጣዖት ዝናም አዝንሞ እነሱን መመገብ የማይቻለው መሆኑን ለማሳወቅ የእግዚአብ ሔርን ኃያልነት ከሃሊነት ለመግለጽ ኤልያስ በአክአብና በኤል ዛቤል ፊት በካህናተ ጣዖቱና በነቢያተ ሐሰቱም ፊት ዝናብ እንዳይዘንብ ሰማይን ዘግቶ ነበር:: 1ነገ. 17÷1

ሙሴና አሮን በፈርዖንና በጠንቋዮቹ ላይ ኤልያስም በአክአብና በኤልዛቤል በነቢያተ ሐሰትና በካህናተ ጣዖቱም ላይ መቅሠፍተ እግዚአብሔርን ሲአፈሱና የኃይለ እግዚአብሔር መተላለፊያ ቧንቧዎች ሆነው እናገኛቸዋለን:: ሄኖክና ኤልያስም በሥልጣኑ የእግዚአብሔርን ስፍራ ለመያዝ እግዚአብሔር ነኝ የሚል የሐሳዊ መሲሕን ስሀተትና ሐሳዊ መሲሕ እግዚአብሔር እንደሆነ በሐሰት የሚመሰክሩ የሐሰተኞች ነቢያቱን ሐሰት ለመግለጽ የእግዚአብሔርን አምላክነት ሁሉን ቻይነትና አዳኝነት ለመመስከር በውኃው ላይና በሰማይ ላይ ኃይላቸውን ይገልጣሉ:: ውኃው በጡንቻማ ጐረምሳ በተወረወረ ደንጊያ ግምባሩን የተገመሰ ሰው መስሎ ደም በደም ይሆናል:: ሰማይም ወንበዴ ልብሱን እንደገፈፈው መንገደኛ ያለደመና ራቁቱን ይቆማል::

ሄኖክና ኤልያስ ደም ያደረጉትን ውኃ ወደቀደመ ሕይወቱ መለወጥ የዘጉትንም ሰማይ ከፍቶ ዝናብ ማዝነብ በመተተኛው ሐሳዊ መሲሕና በመተተኞች ነቢያቶቹ ዘንድ የማይቻል ጉዳይ ነው:: የፈርዖን ጠንቋዮች ምንም በምትሐት



www.ethiopianorthodox.org

ደም ማስመሰል ቢችሉ ሙሴና አሮን ደም ያደረጉትን ውኃ ጤናማ ውኃ አድርጐ መጠጣት ተስኖአቸው በአሮንና በሙሴ ፊት እንደተዋረዱ:: በቁጥር 850 የሚሆኑ የአክአብና የኤልዛቤል መምህራን የጣዖት ካህናቱ የሐሰት ነቢያቱ ኤልያስ የዘጋውን ሰማይ ከፍቶ ዝናብ ጠብ ማድረጉ ይቅርና የደመና መልክ እንኳ ማሳየት አቅቶአቸው በኤልያስ ፊት እንደአፈሩ:: መተተኛው ሐሳዊ መሲሕና መተተኞች ነቢያቱም የምትሐት የውሸት ተአምራትን ሲያሳዩና የማስመሰል ዘዴያቸውን ሲጠቀሙ ከቆዩ በኋላ ሄኖክና ኤልያስ ደም ያደረጉትን ውኃ ወደ ጤናማ ውኀነት ለመለወጥ ከበሽታውም ለመፈወስ የዘጉትንም ሰማይ ከፍቶ ዝናብ ጠብ ለማድረግ ባለመቻላቸው አንዱን ሠርቶ ሌላውን መሥራት የማይችል ቀለል ያለውን ነገር ማድረግ ሲችል ከበድ ካለው ነገር ሲደርስ ወገቤን የሚል ፍጡር ነውና የሐሳዌ መሲሕ ፍጡርነት ተገልጦ የነቢያቱም ምስክርነት ስሕተት ሆኖ በሔኖክና በኤልያስ ፊት በተከታዮቻቸውም ዘንድ ይዋረዳሉ ያፍራሉ::

የሐሳዌ መሲሕና የሐሰት ነቢያቱ ሐሰት ሄኖክና ኤልያስ በሚያስቀምጡት የእውነት ሚዛን ሲመዘን ቀሎ ይገኛል «ሐሰትና ስንቅ እየቆየ ይቀላል» ይባላል:: አቁማዳውም እንጂ ባዶ ይሆናል:: ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስኪያልፍ ድረስ በእግዚአብሔር እውነት የማይዋጥ የማይሰምጥ ውሸት የለም:: ንስሐ ካልገቡና ካልተመለሱ በቀር የዐመፀኞችም ሰውነት በእግዚአብሔር ጣት ያልተዳበሰበት ጊዜ የለም:: የእግዚአብሔር ኃይል ያልተገለጸበት ዐመፀኛ ማን ነው:: ሳጥናኤል ነውን? ፈርዖን ነውን? ናቡከደነጾር ነውን? ሰናክሬም ነውን? ሄሮድስ ነውን? ዲዮቅልጥያኖስ ነውን? እነዚህ ሁሉ በእግዚአብሔር ኃይል የተፈጩ፣ የተደቆሱ፣ የደቀቁ፣ የላሙና ዱቄት የሆኑ ናቸው:: ሐሳዊ መሲሕም ለመፈጨት የወፍጮውን ወረፋ ጠብቆ ያገኛል::





# የሄኖክና የኤልያስ ተአምራት ማድረግ አስፈላጊነት

1ኛ. ከእግዚአብሔር የተላኩ የእግዚአብሔር መልእክተኞች መሆናቸውንና የምስክርነታቸውን እውነተኛነት ለመግለጽ ለማሳወቅ::

2ኛ. የምእመናን ልቡና የሐሳዌ መሲሕ የሐሰት ትምህርትና ክህደት ነፋሳትና ማዕበላት በመቱት ጊዜ እንዳይነቃነቅ እንዳይገለባበጥና ቦታውን እንዳይለቅ በሃይማኖት አለት ላይ ለማነጽ እንዳይወድቅ ለማድረግ::

3ኛ. ሐሳዌ መሲሕና ሐሰተኞች ነቢያቶቹ ተከታዮቻቸውም በኃጢአታቸውና በክህደታቸው ምክንያት በወልደ እግዚአብሔር አንደበት ሑሩ እምኔየ ርጉማን ውስተ እሳት ዘለዓለም እናንተ ርጉማን ከእኔ ተለይታችሁ ወደገሃነመ እሳት ሂዱ በተባሉ ጊዜ የእውነተኛውን አምላክ ነገር አልሰማንም አላወቅንም ምልክትም አላየንም ብለው እንዳያመካኙ ምስክር ሊሆንባቸው::

4ኛ. ውኃውን ደም በማድረግ ሰማዩንም በመዝጋት ከዚህ በፊት በሙሴና በኤልያስ አማካይነት ኃይለ እግዚአብሔር የተገለጠበትን ተአምር ሳይለወጥ በመድገም የሙሴና የኤልያስ አምላክ የማይለወጥ መሆኑን ለማመልከት::

5ኛ. ሥጋዊ ደማዊ ሰው ከተፈጠረባቸው ከአራቱ ባሕርያት አንዱ ውኃ ነው:: ሐሳዌ መሲሕም ሥጋዊ ደማዊ ፍጡር እንደመሆኑ ከውኃ የተፈጠረ የውኃ ልጅ የደመና የልጅ ልጅ ሲሆን የውኃና የደመና ፈጣሪ እኔ ነኝ ባለ ጊዜ አንተ ያልፈጠርከው ውኃ ደም ሆኖአል አንተ ያልፈጠርከው ደመናም መካን ሆኖአል እስኪ ንጹሕ ውኃ ፈጥረህ ያንተንና የተከታዮችህን ጥማት ማርካት ቻል ደመናንም ፈጥረህ ዝናብ አዝንበህ እህልን አብቅለህ ያንተንና የተከታዮችህን ረሀብ አስወግድ ችሎታህ ይገለጥ ለማለት::

5ኛ. እግዚአብሔርን ለመሳደብ አፉን የከፈተ አውሬውን ሐሳዌ መሲሕንና አውሬውን አድናቂዎችን ደጋፊዎችን የአውሬው ስም ምልክት የተጻፈባቸውን የሚያመልኩትና የሚንበረከኩለትን በተለያዩ መቅሠፍቶች ለመምታት::



www.ethiopianorthodox.org

# የሄኖክና የኤልያስ ሞት

ሄኖክና ኤልያስ የእግዚአብሔርን አምላክነት የሁሉ አስገኝ የሥነ ፍጥረት ባለቤት መሆኑንና ከእርሱ ሌላ አምላክ የሌለ መሆኑን የሐሳዌ መሲሕንም ፍጡርነት ስሑትነትና የሰይ ጣን መልእክት ተሸካሚ መሆኑን ከመሰከሩ በኋላ የምስክርነታ ቸውንም ተግባር በትጋትና በድፍረት ካከናወኑ በኋላ በሰማዕት ነት ይሞታሉ:: ተልዕኮአቸውን እስኪፈጽሙ ድረስ ነው እንጂ «ከማያድሩበት ቤት አያመሻሹበትም» እንዲሉ ለኀልፈት ለጥፋት በቀረበችው ዓለም ብዙ ማምሸትም ማደርም አይፈልጉም:: ለሞታቸው ምክንያት የሚሆነው ከጥልቁ የሚወጣው አውሬ /ሐሳዊ መሲሕ/ ነው:: ሦስት ዓመት ከመንፈቅ በተለያዩ መቅሠፍቶች ሲመቱት ሐሰቱን ሲገልጡበት ትምህርቱን ሲገለ ባብጡበት ሲያሳፍሩት ሲያዋርዱት ከቆዩ በኋላ ተበሳጭቶ ያስገድላቸዋል::

ነገር ግን ሄኖክና ኤልያስ የሚሞቱት መንፈሳዊ ተልዕኮ አቸውን የስብከተ ወንጌል ተግባራቸውን አምላካዊ ኃይልን ከማንጸባረቅ ጋር ሲያጠናቅቁ በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው እንጂ በሐሳዌ መሲሕ ፈቃድ አይደለም:: በሐሳዌ መሲሕ ምኞትና ፈቃድ ቢሆንማ ገና በመጀመሪያው ዓመት እንዲገደሉ ያደርግ ነበር እንጂ መጥፎና አሳፋሪ ታሪኩን የተደበቀ የተሰወረ በሐሰ ታዊ ስብከት የተሸፈነ ጉዱን በሕዝብ ፊት ሲያነቡበት የዝምዝ ምታ የተባለ ይመስል አፉን ገጥሞ ዝም ባላለም ነበር::

ሰይጣናዊ ሥራውን በሰይጣን ኃይል ስለሚሠራ የሰይ ጣን ኃይልም በእግዚአብሔር ኃይል አንጻር ሲቆም በእሳት ነበልባል ፊት እንደቀረበ ሻማ ይላላልና የእግዚአብሔርን ጸጋ የተላበሱ የተጐናጸፉ ሄኖክና ኤልያስን መቃወም ሰማይን እንደ መንካት የሚቆጠር በመሆኑ ኃይሉም ከውኃ እንደተጨመረ ጨውና ለፀሐይ ሙቀት እንደተገለጠ ቅቤ እያነሰና ሕልውናውን እያጣ በመሔዱ ግን ሄኖክና ኤልያስ ንጹሕ ስንዴ ትምህርታቸ ውን እርሱ ባለበት ከተማ መዝራት ይችላሉ::

መዝራት የሚገባቸውን ዘር ዘርተው ከፈጸሙ በኋላ ቀኑ ሲመሽ ከሥጋዊ ድካም ለማረፍ የሐሳዌ መሲሕን ሰይፍ ለብሰው መተኛት ይፈልጋሉ:: እስከ ሦስት ቀን ተኩል ሞት በሚባል





ከባድ እንቅልፍ ተይዘው ይቆያሉ:: የመኝታቸውም ቦታ በም ሌያዊ አነጋገር ሰዶምና ግብፅ የተበላች ጌታቸው የተሰቀለባት የታላቂቱ ከተማ አደባባይ ነው:: ጌታቸው የተሰቀለባት የሚለው ንባብ ታላቂቱ ከተማ ማን እንደሆነች ወደማወቅ ይመራናል::

የሄኖክና የኤልያስ ጌታ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑ ግልጽ ነው:: የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል የቆመባት ከተማም ዓለም ያወቃት ፀሐይ የሞቃት ኢየሩሳሌም ናት:: የሄኖክና የኤልያስም ደም በኢየሩሳሌም ይፈስሳል ማለት ነው:: በምሳሌያዊ አነጋገር ሰዶምና ግብፅ ተብላለች ለምን ኢየ ሩሳሌም ሰዶምና ግብፅ ተባለች? ለዚህ ጥያቄ መልስ የሚሆነን በትንቢተ ኢሳይያስ ምዕራፍ 1÷10 ላይ ያለው ንባብ ነው:: እንደሚከተለው ይነበባል «ስምዑ ቃለ እግዚአብሔር መላእክተ ሰዶም ወአጽምኡ ሕገ እግዚአብሔር ሕዝበ ገሞራ» ትርጉም: «እናንተ የሰዶም አለቆች ሆይ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ እናንተ የገሞራ ሕዝብ ሆይ የአምላካችንን ሕግ አድምጡ»

እነዚህ የሰዶም አለቆችና የገሞራ ሕዝቦች የተባሉት የኢየሩሳሌም አለቆችና ሕዝቦች ናቸው:: የሰውን ደም በማፍሰስ ሰውነታቸውን በኃጢአት በማርከስ የገሞራን ሰዎች ስለመሰሉ ሀገራቸው ኢየሩሳሌምን ሰዶም ገሞራ ሲያስብሉ እነርሱም የሰዶም አለቆች የገሞራ ሕዝቦች ተብለዋል::

ሰዶምና ገሞራ በሰዎች ኃጢአት ምክንያት የተደመሰሱ የወደሙ አገሮች በመሆናቸው ኃጢአት ለሚሠራበትና በኃጢ አት ለሚጠፋ አገር ሁሉ ምሳሌ ሆነው ይቀርባሉ:: ግብፅም ከጥንት ጀምሮ በጣዖት አምላኪዎችና በጠንቋዮች የተወረረች ይልቁንም እግዚአብሔረን የሚሳደብ ፈርዖን የነገሠባት ሀገር መሆንዋ ይታወቃል:: በኢየሩሳሌምም እግዚአብሔርን የሚሳደብ ከዚህም አልፎ ራሱን በእግዚአብሔር ስም ሰይሞ የእግዚአብሔ ርን አምልኮት ለመንጠቅ የሚከጅል ርጉም ፍጡር ሐሳዌ መሲሕ ስለሚነግሥባትና ኢየሱስ ክርስቶስ ንስሀ የማይገቡ ከመሆናቸው የተነሣ በጢሮስና በሲዶና በሰዶም ከነበሩ ሰዎች የባሱ ልበ ደንዳናዎች እንደሆኑ የመሰከረባቸው ማቴ. 11÷20-24 ክፉዎች ኃጢአተኞች ስለ ሚኖሩባት በምሳሌያዊ አነጋገር ግብፅና ሰዶም የተባለች ኢየሩሳሌም ናት::



www.ethiopianorthodox.org

አውሬው ሐሳዊ መሲሕ ሄኖክና ኤልያስን ካስገደላቸው በኋላ የበቀል አጻፋ ለመመለስ የጐዳኋቸው መስሎት እንዳ ይቀበሩ ቀባሪ ይከለክልባቸዋል:: እስከ ሦስት ቀን ተኩል ጌታቸው በተቀበረባት በኢየሩሳሌም አደባባይ በድናቸውን ሕዘብም አሕዛበም ይመለከቱታል:: ሄኖክና ኤልያስ በተለያዩ መቅሠፍቶች የመቱአቸው ያስቃዩአቸው የሐሳዊ መሲሕ ቤተሰቦች በሄኖክና በኤልያስ ሞት ደስ ይሰኛሉ:: ከልክ ያለፈ እንደበታቸው ሊናገረው የማይችለው ደስታ በውስጣቸው እንደሞላ ለመግለጽ የደስታ መግለጫ የሚሆን ስጦታ ይሰጣጣሉ::

በቤት ውስጥም ሆነ በውጭ ሰዎች ሲገናኙ የሚነጋገሩበት ጉዳይ የሄኖክና የኤልያስ ጉዳይ ይሆናል:: ሰማይን በመዝጋት ውኃውን ደም በማድረግ እሳት በማዝነብ ሌሎችንም የተለያዩ መቅሠፍቶች በማምጣት ያደረሱባቸውን ሥቃይ በማውሳት አሁን የእጃቸውን አገኙ ይባባላሉ:: በጨለማ ቆይተው ልክ ፀሐይ እንደወጣላቸው አድርገው ይቆጥራሉ:: በክርስቶስ ዘመን የነበሩ አይሁድ ክርስቶስን ሰቅለው ገድለው የተደሰቱትን ያህል ይደሰታሉ:: እንኳን በዚህ ዓለም በወዲያኛውም ዐለም እረፍት ያገኘን ይመስላቸዋል::

ከሦስት ቀን ተኩልም በኋላ ነፍሳቸው ከእግዚአብሔር ዘንድ ተአዝዛ መጥታ ከሥጋቸው ጋር ተዋህዳ ሄኖክና ኤልያስ ሕያዋን ሆነው ይነሣሉ:: በሄኖክና በኤልያስ ሞት ተደስተው የነበሩ ሐሳዊ መሲሕና መሰሎቹ ወደሀዘን ይመለሳሉ:: በፍርሃት ተውጠው ይርበደበዳሉ ልቡናቸው ይፈራል ጉልበታቸው ይርዷል አእምሮአቸው ይጨነቃል:: በድናቸውን እየተመለከቱ በሞታቸው ደስ የተሰኙ የደስታቸው መግለጫ ስጦታ ሲሰጣጡ የነበሩ ሁሉ የደስታቸው ቀኖች ሦስት ቀን ተኩል ብቻ ሆነውባቸው ደስታቸው በኃዘን ተውጦ ሰጥሞ /ሰምጦ/ በፍርሃት በድንጋጤ ጥቁር ልብሶች ፊታቸውን ይሸፍናሉ:: ሄኖክና ኤልያስ በዚያ መቅሠፍት መልሰው የሚገርፏቸው ይመስላቸዋል:: ወደእውነተኛው አምላክ በመመለስ ፈንታ በዚያው በክህደታቸው ጸንተው ይርበተበታሉ::

በሰማይም ወደዚህ ውጡ የሚላቸውን ታላቅ ድምፅ ሰሙ:: ጠላቶቻቸውም እየተመለከቱአቸው ወደሰማይ በደመና ወጡ:: ራእይ 11÷12 ሄኖክና ኤልያስ ከሙታን ተለይተው





ከተነሡ በኋላ ወደሰማይ ውጡ የሚል አምላካዊ ድምፅ እንደሚሰሙና በክብር እንደሚያርጉ ነው ንባቡ የሚያስረዳን:: በሰብአዊ አስተሳሰባቸው ሙተው የሚቀሩ መስሎአቸው የገደሉአቸው ጠላቶቻቸው እየተመለከቱአቸው በጠላቶቻቸው ፊት ያርጋሉ::

ሐሳዊ መሲሕና መሰሎቹ ተከታዮቹ አይጥ ይዛ ያመለጠቻት ድመት እስኪመስሉ ድረስ የብስጭት ድምፅ ያሰማሉ:: ሐሳዊ መሲሕ አምላክ አለመሆኑ ሄኖክንና ኤልያስን የጠራ እውነተኛ አምላክ መኖሩ በችሎታም ከሐሳዊ መሲሕ ችሎታ በላይ የሆነ ችሎታ ያለው መሆኑ ዓይነ ልቡና ላለው ሰው ደምቆ የሚታይ ይሆናል::

አንባብያን ሆይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ያልተሰጠ ደስታ ዕድሜው አጭር እንደሚሆን ልብ በሉ:: የእግዚአብሔርን አገልጋዮች ቅዱሳን ሄኖክና ኤልያስን ገድለው በሞታቸው ደስ የተሰኙ ሰዎች የደስታቸው ቀኖች ሦስት ቀን ተኩል ብቻ ነበሩ:: ከዚህ በኋላ ወደ ሀዘን ነው ያመሩት:: የሀዘናቸው ቀኖች እንደደስታቸው ቀኖች አጭር አይደሉም:: ድርጊቱ ገና ወደኋላ የሚፈጸም ቢሆንም የማይቀር ስለሆነ እንደተፈጸመ አድርገን እንየው::

እነዚህ የዐመፅ ሰዎች የተንኮል ሰዎች የሕሊና ዕረፍት አላገኙም:: ሄኖክና ኤልያስን ገለን እናርፋለን መስሎአቸው ነበረ:: ወደባሰ የመታወክ አዘቅት ውስጥ ነው የገቡት:: እሳት ያዘንቡብን ይሆን በረዶ ያዘንቡብን ይሆን ፀሐይን ያጨልሙብን ይሆን ወዘተ... የሚለው ሥጋትም ሳያጥለቀልቃቸው አልቀረም:: ዛሬስ በከተማችን ሰዎችን ገድለው ድርጅታቸውን የሚወርሱ ቤታቸውን የሚወርሱ ጋንጃ መትተው ዘርፈው ቀምተው ቢራ ውስኪ የሚጠጡ ጮማ የሚቆርጡ በዐመፅ ገንዘብ የሚፍነሽነሹ ሰዎች ስንት ቀን የሚደሰቱ ይመስላችኋል::

አነሣሥቶ ላስጀመረን አስጀምሮ ላስፈጸመን ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው::



www.ethiopianorthodox.org

## ዋቢ መጻሕፍት /የተጠቀሱ ምንጮች/


1. ዮሐንስ አፈወርቅ ድርሳን በተስፋ ገ/ሥላሴ 1987 ዓ.ም.
2. መዝሙረ ዳዊት ትርጓሜ በተስፋ ገ/ሥላሴ 1982 ዓ.ም.
3. ትንቢተ ሕዝቅኤል ትርጓሜ አ.አ. ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት 1990 ዓ.ም.
4. መጻሕፍተ ሰሎሞን ወሢራክ ትርጓሜ አ.አ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት 1988 ዓ.ም.
5. ሃይማኖተ አበው አ.አ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት 1996 ዓ.ም.
6. ተግሣፅ ዘዮሐንስ አፈወርቅ ተርጓሚ ተስፋ ገ/ሥላሴ 1987 ዓ.ም.
7. ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት 1948 ዓ.ም.
8. የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት አ.አ ንግድ ማተሚያ ድርጅት 1989 ዓ.ም.
9. ጳውሎስ ትርጓሜ ትርሣኤ ዘጉባዔ ማተሚያ ድርጅት 1948 ዓ.ም.
10. መጻሕፍተ ሐዲሳት ሠለስቱ ትርጓሜ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት 1989 ዓ.ም.
11. መጽሐፈ ቅዳሴ ትርጓሜ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት 1988 ዓ.ም.
12. አርባዕቱ ወንጌል ትርጓሜ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት 1988 ዓ.ም.
13. አስረስ የኢኔሰው የካም መታሰቢያ ኮከበ ጽባሕ ማተሚያ ቤት 1951 ዓ.ም.
14. ደቂቅ ነቢያት ትርጓሜ
15. ስምንቱ ብሔረ ኦሪት ትርጓሜ
16. እዝራ ሱቱኤል ትርጓሜ
17. መጽሐፈ ሄኖክ ትርጓሜ


www.ethiopianorthodox.org